# ዓምደ ሃይማኖት

ከ

ብርሃኑ ጉበና

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

አዲስ አበባ

የመጀመሪያ እትም የካቲት 1985 ዓ. ም

ሁለተኛ እትም መጋቢት 1986 ዓ. ም

ሦስተኛ እትም ጥር 1987 ዓ. ም

አራተኛ እትም መጋቢት 1988 ዓ. ም

አምስተኛ እትም ሐምሌ 1990 ዓ.ም

ስድስተኛ እትም የካቲት 1992 ዓ.ም.

መታሰቢያነቷ በሃይማኖት ትምህርት ኮትኩታ ላሳደገችኝ
በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ቤተ
ክርስቲያን ለምትገኘው ለዓምደ ሃይማኖት
ሰንበት ትምህርት ቤቱ ትሁንልኝ ።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።

## ምስጋና

ረቂቁን በማረምና ታይፕ በማድረግ ለዚች መጽሐፍ ህትመት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገችልኝን ወ/ት ወሰኔ በየነን በእግዚአብሔር ስም ሳላመሰግን አላልፍም ። እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ መጽሐፉን በማረምና በማስተካከል ከፍተኛ ትብብር ስለአደረገልኝ መምሪያውን በተጨማሪም በሞራልና በማቴሪያል በኩል ትብብሩን ያልነፈገኝን አቶ አበበ ዳኜን በአንባብያን ስም አመሰግናለሁ ።

From the Library of

ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ

FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

## የሽፋን ሥዕል መግለጫ

## የኢየሱስ እውነተኛ መልክ ሥዕል

ይህ ሥዕል የተሣለው ጢባርዮስ ንጉሠ ነገሥት በከበረ ድንጋይ ላይ «ኤሚራልድ» ካስቀረጸው ምስል ላይ ነው ። ይህም ቅርጽ የቍስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ሀብት ሆኖ ከቆየ በኋላ እ. ኤ. አ. ፲፬፻፺፪ ዓ. ም. በቱርኮች እጅ ወድቆ ስለነበረ ዳግማዊ ባዛዜድ የተባለው ሡልጣን በክርስቲያን ጦርነት ጊዜ ሮዲ ላይ ወንድሙ ተማርኮ ታስሮ ስለነበረ እሱን ለማስለቀቅ ለፓፓ ኢኖቼንሶ ስምንተኛው ይህንን ቅርጽና እንዲሁም የክርስቶስ ጐን የተወጋበትን ቅዱስ ጦር ጋር አብሮ የተሰጠ ነው ። በኢኮኖግራፍ ለተነሣው ለዚህ እጅግ ጣዕም ላለው ሥዕል በአይሁድ አገር ተጠባባቂ ገዥ የነበረው ፒ. ሌንቱሎ ለዚሁ ለጢባርዮስ ንጉሠ ነገሥት በጻፈው የታወቀው ታሪካዊ መልዕክቱ የሰጠው ጽሑፋዊ አገላለጽ ዓይነተኛ ምስክር ነው ።

ይህ ቃል ከሥዕሉ ግርጌ ተጽፎ የሚገኘው የጣልያንኛው ትርጉም ነው ።

# ማ ው ጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 9 |
| ልዩ መግለጫ | 10 |
| ምዕራፍ 1 ከእንዲት ሃይማኖት ብዙዎች ወጥተው እንዴት ሊሄዱ ቻሉ ? | 15 |
| ምዕራፍ 2 መጽሐፍ ቅዱስ | 29 |
| 2.1 ብሉይ ኪዳን | 29 |
| 2.2 ሐዲስ ኪዳን | 30 |
| 2.3 አራቱ ወንጌላውያን | 30 |
| 2.4 የወንጌል ጸሕፍት አራት ብቻ የመሆናቸው ምስጢር | 31 |
| 2.5 ስለ ሌሎች የሐዲስ ኪዳን ጸሐፍት | 34 |
| 2.6 የመጽሐፍ ቅዱስ ብዛት | 35 |
| ምዕራፍ 3 ምሥጢረ ሥላሴ | 39 |
| ምዕራፍ 4 ምሥጢረ ሥጋዌ | 45 |
| 4.1 የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ? | 46 |
| 4.2 ወልድ ሥጋን በመንሣቱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ስለ አለማነሱ | 46 |
| 4.3 የንስጥሮስ ትምህርት ስለኢየሱስ ክርስቶስ | 47 |
| 4.4 የፓፓ ሊዮን ትምህርት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ | 48 |
| 4.5 የኢየሱስ ክርስቶስ ተዋህዶ በቅዱሳን አባቶች ሲተነተን | 48 |

4.6 ሥጋ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ መሆኑን የሚ ያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ..................... 49
4.7 የኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ..................... 51
4.8 ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ..................... 54
4.9 ተጠራጣሪዎች የሚያቀርቡአቸው ጥቅሶችና መልሶቻቸው ..................... 57
4.10 ማጠቃለያ ..................... 64

ምዕራፍ 5 ምሥጢረ ጥምቀት ..................... 67
5.1 ጌታ በ30 ዘመኑ የተጠመቀበት ምሥጢር ..................... 68
5.2 ክርስቲያኖች በ40 ቀንና በ80 ቀን የመጠመቃ ችን ምሥጢር ..................... 69
5.3 ጌታ በዮርዳኖስ የተጠመቀበት ምክንያት ..................... 73
5.4 ጌታ ወደ ዮሐንስ ሄዶ የተጠመቀበት ምክንያት ... 74
5.5 ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው እጆቹን ያልጫነ በት ምክንያት ..................... 74
5.6 መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል የወረደበት ምክንያት ..................... 75
5.7 ሰዎች በማን ስም ሊጠመቁ እንደሚገባቸው ..... 75
5.8 የጌታ በውሃ መጠመቅ ምሥጢሩ ..................... 76
5.9 ማጠቃለያ ..................... 76

ምዕራፍ 6 ፡ ምሥጢረ ቁርባን ..................... 79
6.1 ሥጋ ወደሙ በስንዴና በወይን የሆነበት ምክንያት ..................... 80

ምዕራፍ 7 ፡ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ..................... 83
7.1 የትንሣኤ ሙታን ትርጉም ..................... 83
7.2 ትንሣኤ ሙታን የሚሆንበት ጊዜ ..................... 84
7.3 የሰው እንሣስ ..................... 84
7.4 በበግና በፍየል የተመሰሉት እነማን እንደሆኑና ትርጉም ..................... 85





7.5 በግራና በቀኝ የተመሰሉት እነማን እንደሆኑ ... 87
7.6 ሕያዋንና ሙታን የተባሉት ማንነት ..................... 88
7.7 አንዳንድ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው በትንሣኤ ሙታን ላይ ..................... 88

ምዕራፍ 8 ፡ ክብረ ድንግል ..................... 91
8.1 የማርያም የስምዋ ትርጓሜ ..................... 91
8.2 ዘለዓለማዊ ድንግል ስለመሆንዋ ..................... 92
8.3 የእመቤታችን ለዮሴፍ መታጨት ምክንያት ..... 92
8.4 የበኩር ልጅዋን . . . የሚለው ትርጉም ..................... 95
8.5 እስከትወልድ ድረስ ሀላወቃትም የሚለው ትርጉም ..................... 97
8.6 ክብርዋና አማላጅነትዋ በመጽሐፍ ቅዱስ..................... 99
8.7 በመጽሐፍ ቅዱስ የእመቤታችን ምሳሌዎች..... 103
8.8 ማጠቃለያ ..................... 106

ምዕራፍ 9 ፡ የቅዱሳን አማላጅነት ..................... 109
9.1 በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ያማልዱ እንደነበር ..... 109
9.2 ቅዱሳን የጸጋ አማልክት ይባላሉ ..................... 113
9.3 ከሞቱ በኋላ ማማለዳቸው ..................... 117

ምዕራፍ 10 ፡ ታቦት ፡ ጽላት ..................... 121
10.1 ጽላት ከእግዚአብሔር መሰጠቱን ..................... 121
10.2 ታቦት የጽላት ማደሪያ ስለ መሆኑ ..................... 123
10.3 ቤተ መቅደስ ..................... 123
10.4 ለታቦት ሊደረግ የሚገባው ክብር ..................... 124
10.5 በሐዲስ ኪዳን ክርስቶስ ቤተ መቅደስን ባርኮ ስለመስጠቱ ..................... 126

**ምዕራፍ 11 ፥ መስቀል** ........................................ 129

11.1 ጌታ የተሰቀለው በተመሳቀለ እንጨት ላይ ስለ መሆኑ ........................................ 129

11.2 የመስቀል ጠላቶች ........................................ 131

**ምዕራፍ 12 ፥ ስግደት** ........................................ 133

12.1 የስግደት ዓይነት ........................................ 133

12.2 ለመላእክት የጸጋ ስግደት እንደሚገባ ........................................ 133

12.3 ለቅዱሳን ሰዎች መስገድ ተገቢ መሆኑ ........................................ 135

12.4 ለቤተ ክርስቲያንና ለታቦት መስገድ ተገቢ ስለመሆኑ ........................................ 137

**ምዕራፍ 13 ፥ ቅዱሳን ስዕላት** ........................................ 141

**ምዕራፍ 14 ፥ ጾም** ........................................ 153

14.1 የጾም ትርጉም ........................................ 153

14.2 የጾም ጥቅሙ ........................................ 153

14.3 ጾም በብሉይ ኪዳን ........................................ 154

14.4 ጾም በሐዲስ ኪዳን ........................................ 157

14.5 የአዋጅ አጽዋማት ........................................ 158

**ምዕራፍ 15 ፥ ስለሰው ነፍስ ሕያውነት** ........................................ 161

15.1 የሰው ተፈጥሮ ........................................ 162

15.2 የሰውና የእንስሳት ሞት አንድ ስለ አለመሆን ........................................ 162

15.3 የነፍስ ሕያውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማስረጃ ........................................ 164

15.4 ስለ ገነት ........................................ 167

15.5 ስለ ሲኦል........................................ 168




# መ ግ ቢ ያ

“ ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም ” ይላሉ አበው ሲናገሩ ። እኔም ይኸን የቆየ የአበው ብሂል ባለመዘንጋት ። ምንም እንኳን ጠለቅ ያለ የነገረ መለኮት (ቲዎሎጂ) ዕውቀት ባይኖረኝም የቤተ ክርስቲያንን ጡት እየጠባሁ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ያደግኹት በቅጥረ ቤተ ክርስቲያን ከሊቃውንት አበው እግር ሥር ቁጭ ብዬ ነውና እንደ አቅሜ እናቴ ቤተ ክርስቲያንን ሊያደሙ የተነሱትን መናፍቃንን ለመዋጋት የሃይማኖት ( የተዋሕዶ) ሠይፌን እንስቻለሁ ።

ይህችን “ <u>ዓምደ ሃይማኖት</u> ” ብዬ የሠየምኳትን መጽሐፍ እን ድጽፍ የገፋፉኝ በየቤተ ክርስቲያኑ ርትዕት ለሆነችው ተዋሕዶ ሃይ ማኖቴ ለመመስከር በምሔድበት ወቅት ከስብከተ ወንጌሉ ተሳታፊ ዎች በየጊዜው የሚቀርበው ጥያቄ ነበር ። በአብዛኛው ከምእመኑ የሚ ቀርቡት ጥያቄ መናፍቃን ቤተክርስቲያናችንን በመንቀፍ በሚያስተ ምሩት የኑፋቄ ትምህርት ላይ ነው። ስለሆነም በየጊዜው መናፍቃን እንዲህ ይላሉ ለዚህ መልስ ስጡን የሚለውን ሁኔታለመቀነስ ለምእ መናን ጥያቄ መጠነኛ መልስ ሊሰጥ የሚችል አንድ የመናፍቃን ጥያቄ ምላሽ መጽሐፍ ማዘጋጀት እንዳለብኝ አሰብኩ ። ሀሳቤንም እግዚ አብሔር ከግቡ አደረሰልኝ ።

“ <u>ዓምደ ሃይማኖት</u> ” ተብሎ መሠየሙ ስለ ሁለት ነገር ነው ፤ አንደኛው ይኸን መሠረቱ ከሐዋርያት ከሠለስቱ ምዕት ሲወርድ የመ ጣ እውነተኛ የተዋሕዶ ሃይማኖት ከሕፃንነቴ ጀምሬ ላስተማረችኝ ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ ት/ ቤት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ፤ ሁለተኛው ደግሞ በውስጡ ያለው ልዩ ልዩ መልእክት መሠረታዊ የሆነ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና እምነት ስለሆነ ነው ። ዓምደ ሃይማኖት ማለት የሃይማኖት ምሰሶ ማለት ነው ።

በቤተ ክርስቲያናችን ብሉይን ከሐዲስ እያቀናጁ ምሥጢርን ከምሥጢር እያመሳጠሩ ታሪክን ከመጻሕፍት እያዋደዱ ማስተማርና መጻፍ የሚችሉ እያሌ ሊቃውንት ቢኖሩም ነገር ግን ከብዛታቸውና ከዕውቀታቸው አንጻር የጻፏቸው መጻሕፍት ቁጥር ሲነጻጸር በጣም ኢምንት ሆነው እናገኛለን ። ይህ ደግሞ መክሊቱን ተቀብሎ እንደቀ

በረው ሰው በፍጻሜ ዘመን የሚያስፈርድ ስለ ሆነ ሊቃውንት አባቶች በመናፍቃን የስሕተት ትምህርት የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ ለሚባዝነው የሃይማኖት ወገኔ ባለበት ጸንቶ እንዲኖር የሚያስችለውን መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት እየጸፋችሁ በእጁ እንዲገባና አንብቦ ስለሃይማኖቱ እንዲረዳ እንደ ባህር አሸዋ በብዛት የተባተነውን የኑፋቄ ትምህርት የሰፈረበትን መጽሐፍ ከማንበብ ተቆጥቦ የሕይወት ቃል የሰፈረበትን የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ሃይማኖት የሚገልጽ መጽሐፍ በተባ ብዕራችሁ ትጽፉ ዘንድ ማንቃቂያ ይሆን ዘንድ ባለኝ መጠነኛ እውቀት ይህችን ጽፌያለሁ ።

ይህን ስል ግን በተለያዩ ወቅቶች ለተነሱት መናፍቃን መልስና ለምእመናን እምነት መጠንከር ምርጥና አስደሳች ጠለቅ ያለ የሃይማኖት መሠረት ያለባቸው መጻሕፍት የጻፉትን፦— መልእከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ (ኰኵሐ ሃይማኖት) ብጽዕ አቡነ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳስ (ሥርወ ሃይማኖት) ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣የዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ) ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ( መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት) አለቃ አያሌው ታምሩ (ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ ) ባለመዘንጋት ከልብ የመነጨ አድናቆቴንና አክብሮቴን በመለገስ ነው ። ዳሩ ግን እነኚህ አባቶች በሕይወት ያሉትም ሆኑ በሞት የተለዩት እነዚህን መሠረታዊ የሃይማኖት መመሪያ ጽፈው ቢያሳትሙም በአሁኑ ጊዜ ግን አስፈላጊነታቸው እጅግ ጉልቶ በታየበት ወቅት በድጋሚ አለመታተማቸው ያሳዝናል ።

እግረ መንገዴን እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ሊቃውንት አባቶች የጻፏቸውን መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን አሳትማ ለምእመናን እንዲደርስ ማድረግ ግዴታዋ ስለሆነ የሚመለከተው ክፍል ያስብበት ስል በትህትና ነው ።

## ልዩ መግለጫ ።

መንፈሳዊ መጽሐፍ መጻፍ እጅግ አስቸጋሪ ነው ። ይኸውም የሆነበት ምክንያት የዘላለማዊውን አምላክ ህልውና ማስረዳት ነውና ። የመጻሕፍት ምሥጢር እንዳይዛባ ጠንቅቆ መጻፍ ተገቢ ነው እንዲሁም የተለያዩ የመናፍቃንን አባባል ለማፍረስ ብሉይን ከሐዲስ ማስማማት ያስፈልጋል ። ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ብዙ ደክሜያለሁ ። በተለይ በቤተ ክርስቲያናችን በአማርኛ የተጻፉ የእምነታችን መግለጫዎች የሆኑ መጻሕፍት በብዛት አለመኖር ያሉትም በተወሰኑ ሰዎች እጅና



በቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት ብቻ መሆኑ ዝግጅቱን እጅግ አድካሚና ውስብስብ ሊያደርገው ችሎአል ።

አንዳንድ ለጽሑፌ ረዳት ያደረግኋቸው መጻሕፍት ርእሳቸውን ብቻ ለማመሳከር ያህል ጽፌ ማለፍ ስችል በውስጣቸው ከያዙት አስፈላጊ ታሪኮች ውስጥ አንዳንዶቹን ያለምንም ለውጥ ቃል በቃል በመጽሐፌ ውስጥ ልጽፍ ተገደጃለሁ ። ይኸም ሊሆን የቻለው መጻሕፍቱ ከመጥፋታቸውና ካለመገኘታቸው የተነሣ አንባቢው እነሱን ለማግኘት ብዙ እንዳይደክም እንዲሁም መጻሕፍቱን ፈልጐ በማጣት የተፈለገውን ሀሳብ ለመረዳት እንዳይቸገር በቅን ልቡና በማሰብ መሆኑን አንባቢያን እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ ።

ብርሃኑ ጉበና

# ምዕራፍ ፩

## ማስገንዘቢያ ፤

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !

በአብ ስም አምኜ አብን ወላዲ ብዬ ፣ በወልድ ስም አምኜ ወልድን ተወላዲ ብዬ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ ፣ ምንም እንኳን በአካል በግብር በስም ሶስት ብዬ ባምንም ፣ በመለኮት ፣ በህልውና ፣ በባሕርይ ፣ ይህን ዓለም በመፍጠርና በማሳለፍ አንድ አምላክ ብዬ በማመን በሁለት ወገን ድንግል ንጽሕት በምትሆን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ፣ በጻድቃን ፣ በሰማዕታትና በቅዱሳን መላእክት አማላጅነት በመተማመን ሕይወት የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ማስተላለፍ እጀምራለሁ ። ሁሉን የሚችለው እግዚአብሔር ምሥጢሩን ይግለጽልን ።

— " እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፣ በመንገድ ላይ ቁሙ ፣ ተመልከቱም ፤ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ ፣ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች ዕወቁ ፡ በእርስዋም ላይ ሂዱ ፣ ለነፍሣችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ " ኤርምያስ 6 ፥ 16 ።

— " አንድ ጌታ ፣ አንድ ሃይማኖት ፣ አንዲት ጥምቀት " ኤፌሶን 4 ፥ 4—5 ።

ይህች አንዲቱ ሃይማኖት በጌታ ደም የተመሰረተች እንጂ በፍጡር ፍልስፍና የተመሠረተች አይደለችም ። ይህቺ ሃይማኖት የመላእክት ሃይማኖት ነች ፤ ይህቺ ሃይማኖት የነቢያት ሃይማኖት ነች ፣ ይህቺ ሃይማኖት የሐዋርያት ሃይማኖት ነች ፣ ይህቺ ሃይማኖት የሠልስቱ ምዕት ሃይማኖት ነች ፣ ይህቺ ሃይማኖት ቅዱስ ጴጥሮስ በቂሣርያ ላይ የተመሰገነባት ሃይማኖት ነች " አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነህ ማቴዎስ 17 ፥ 16 ።

— “ መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ” 1ኛ ጢሞቴዎስ 4 ፥ 1—2 ።

— እናንተ ግን (አንተ ግን) በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር ፤ ከማን እንደተማርኸው ታውቃለህና ። ከሕፃንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን እውነተኛ የባሕርይ አምላክ መሆኑን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት አውቀሃል ” 2ኛ ጢሞቴዎስ 3 ፥ 14—17 ። ስለዚህ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በላከው መልእክቱ በምዕራፍ 3 በቁጥር 14 ላይ “ የመጀመሪያ እምነታችንን እስከመጨረሻው ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና ” በማለት በአንዲቷ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ጸንተን እንድንኖር ይመክረናል ።

— “ አማላጆች ከግብጽ ይመጣሉ ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ” መዝሙር 67(68) ፥31 በተባለው አምላካዊ ቃል መሠረት አገራችን ኢትዮጵያ ከ328 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ጸንታ ትገኛለች ። ቢሆንም ግን ዘመን የወለዳቸው የክፍለ ጊዜው ቢፅ ሐሳውያን (መናፍቃን) እንግዳ የሆነ የኑፋቄ ትምህርት ትንቢት በተነገረላትና በአንዲቷ ሃይማኖት ጸንታ በምትገኘው ሀገራችን ላይ እየነዙ ስለሆነ ልንጠነቀቅና ልንጠበቅ ይገባናል ። ይህ ይሆን ዘንድ አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረ ስለሆነ ይህን ያህል አያስደንቀንም ።

— “ የበግ ለምድ ለብሰው (መጽሐፍ ቅዱስን ይዘው የክርስቶስን ስም እየጠሩ ) ከሚመጡባችሁ ነጣቂ ተኩላዎች ተጠበቁ ” ማቴዎስ 7 ፥ 15—23 ።

— “ ወዳጆች ሆይ ፤ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ ። ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና” 1ኛ የዮሐንስ መል. 4 ፥1 ።

— ‘ የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው ። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለም ያው ነው ። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ ። ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም ። በዚህ የሚሠሩቧት አልተጠቀሙምና ” ዕብራውያን 13 ፥ 7—9።



— “ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንዳትመለከቱ እለምናችኋለሁ ። ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ ፤ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና ፤በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ ” ሮሜ 16 ፥ 15—23 ።

— “ እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሣቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና ። ይህም ድንቅ አይደለም ፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና ። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሣቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም ። ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል ” ቆሮንቶስ 11 ፥ 13 ።

— እንግዲህ “ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ” ማቴ. 7 ፥ 16 እንደ ተባለው ሁሉ የኑፋቄ ትምህርታቸው ተበባሪ እንዳንሆን መጠንቀቅ ይሊብን ።

## የሃይማኖት ክፍፍል እንዴት ሊጀመር ቻለ ?

በዘመናችን ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ውጥረት ያለባት መካከለኛው ምሥራቅ ስትሆን ፤ ቀደም ብሎም የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትም መዲና ነበረች ። የተለያዩ እምነቶች ምንጫቸው ከዚህ ክልል መሆኑ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም ። ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀደምትነት ያላቸው እሥራኤላውያንም በዚሁ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ናቸው ። ክርስቶስ የተወለደው በቤተልሔም እንደመሆኑና ሐዋርያትም የዚሁ ክልል ተወላጆች እንደመሆናቸው መጠን ፤ የክርስትና እምነት ምንጩም ይኸው መካከለኛው ምሥራቅ ነው ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ትተን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለውን ክስተት ለመቃኘት እንሞክራለን ።

የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምክረ ሰይጣን ተታሎ በኃጢአት ተሎሳቁሎ ሃይሉ ደክሞ ፤ ጸሎቱ የማይሰማ ሆኖ ተፈርዶበት በመንፀፈ ደይን ወድቆ የነበረ አዳምንና ልጆቹን ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ ለማውጣት ሲል እሱ ራሱ ሰው ሆኖ ተሰቅሎ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጐ ከተነሣ በኋላ ፤ በሃምሣኛው ቀን ለደቀ መዛሙርቶቹ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ አደላ

ቸው ። ከዚያ በኋላ ፍሩሃን የነበሩ ሐዋርያት ደፋር ሆኑ ፤ ሥጋቸውን
ለእሳት ፥ አንገታቸውን ለሰይፍ አሳልፈው መስጠት ጀመሩ ። ወንጌ
ልንም በስፋት ማስተማር ቀጠሉ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሐዋርያት በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ ። የአ
ንጾኪያ ከተማ የተመሠረተችው ከጌታ ልደት በፊት በሶስተኛው መቶ
ክፍለ ዘመን መሆኑ ቢታሪክ ተዘግቧል ። አንጾኪያ በዚያን ዘመን ዝነ
ኛ የክርስቲያኖች መናኸሪያ ነበረች ። ሐዋርያት በአንጾኪያም ሆነ
በሮም ፥ እንዲሁም ዕጣ ክፍላቸው ወደሆኑት ሃገሮች ሁሉ በመበታተን
አልሜ የሆነውን ዓለም በወንጌል ጨውነት ያጣፍጡት ጀመር ፤ ጨለ
ማ የወረሰውንም ዓለም በወንጌል ብርሃንነት አበሩት ።

ክርስትና እየተስፋፋች ስትሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ ክፍል
በምትሆን በግብጽ ከተማ በእስክንድርያ የመጀመሪያው የክርስቲያ
ኖች ትምህርት ቤት በ60 ዓ. ም. በቅዱስ ማርቆስ ተመሠረተ ። ይህም
ት/ቤት የትርጓሜ ት/ቤት ነበር ።

ቀጥሎም በሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በሶርያ
ዋና ከተማ በአንጾኪያ ሁለተኛው የክርስቲያኖች ት/ቤት ተቋቋመ ።
በሁለቱም ት/ቤቶች ውስጥ የተለያዩ የፍልስፍና ሰዎች እየገቡ ብዙ
ዎች የሙት ፍልስፍናቸውን እርግፍ አርገው በመተው የወንጌል ሰባኪ
ሆኑ ። አንዳንዶቹ ግን ያ ቀድሞ የሚያውቁትን የፍልስፍና ትምህርት
እንዳይተው በማለት የክርስትናውን ትምህርት ከፍልስፍና ጋር እያ
ጣመሩ በጠባብዋ የወንጌል ጐዳና ሊጓዙ ሞከሩ ። ዳሩ ግን ጠባብዋ
የወንጌል መንገድ ደባል እምነት የያዘ ሰው የማያልፍባት ስለሆነች
ፍልስፍናችሁን አራግፉ ብትላቸውም እነሱ ግን አልተስማሙም ።
በዚህም ምክንያት የሰይጣን ማህደሮች ሆነው በክርስቶስ ደም የተገ
ነባቸውን ቤተ ክርስቲያንን ሊያናጉ ተነሱ ።

በሃይማኖት መድረክ ላይ ግንባር ቀደም የቤተ ክርስቲያን ተቃ
ዋሚ ሆኖ የቀረበው አውራ ተዋናይ አርዮስ ነበር ። በሦስተኛው መቶ
ክፍለ ዘመን አጋማሽ በ257 ዓ. ም. ገደማ በአፍሪካ ሰሜን ክፍል በም
ትገኘው ሊቢያ የተወለደው አርዮስ የተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ
ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይተርካል ።

ለተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ አኪላስ ፥ እለ እስክንድሮስ
እና አርዮስ የተባሉ ደቀ መዛሙርት ነበሩት ። አርዮስ የተባለው ደቀ
መዝሙር አይኑ ከማንበብ የማይቦዝን ግጥም ገጣሚ ፥ ድምፀ መል
ካም ፥ ንግግር አሳማሪ ነበር ። " እጅግ ጥበብ ያደርሳል ከሞት " እን
ዳለ ጠቢቡ ፥ አርዮስም ከመጠን ማለፉ ይመስላል ወደ ሙት ፍልስ



ፍና ማምራት ጀመረ ። የተጻፈውን ትቶ ያልተጻፈውን ማንበብ ጀመረ።
በቅዱስ መንፈስ የተተረጐመውን ትቶ የራሱን ትርጉም ይሰጥ ጀመረ።
በመጨረሻም በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 8 ላይ ያለውን ቃል ወስዶ
" ወልድ ፍጡር ነው " ብሎ አረፈው ። ይህም የክህደት ትምህርቱ
አንድ ጊዜ ተናኘ ።

በዚህ ጊዜ ጌታ በራእይ ቀሚሱ ለሁለት የተቀደደ ሕጻን መስሎ
ለቅዱስ ጴጥሮስ ታየው ። እሱም ደንግጦ " አንተ ጌታዬ ኢየሱስ ክር
ስቶስ አይደለህምን ? " ቢለው " አዎን ነኝ " ሲል መለሰለት ፥ " ታዲ
ያ ልብስህን ማን ቀደደብህ " ቢለው " አርዮስ ልብሴን ቀደደብኝ ፥
ከባሕርይ አባቴ ከአብ ፥ ከባሕርይ ሕይወቴ ከመንፈስ ቅዱስ ለይቶ
ፍጡር አለኝ ፤ እነሆ ከእንግዲህ የማይመለስ ስለሆነ አውግዘህ ከቤተ
ክርስቲያን አንድነት ለየው " ብሎ ነገረው ። ጴጥሮስም ከዚህ ቀደም
ብዙ መከሮት ስለነበር የጌታን የመጨረሻ ቃል ሰምቶ አርዮስን
አወገዘው ። ለአኪላስና ለእለ እስክንድሮስም ከግዝቱ እንዳይፈቱት
አስጠንቀቃቸው ። አኪላስ ግን ማስጠንቀቂያውን ጥሶ አርዮስን ከግ
ዝቱ ፈትቶ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ጨመረው ። አኪላስም የመ
ምህሩን ማስጠንቀቂያ ባለመፈጸሙ በእግዚአብሔር ተቀሰፈ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የአርዮስ ክህደት አደባባይ የወጣው በ325 ዓ.
ም. ነበር ። የክህደት ትምህርቱ የክርስትናውን ዓለም ስለአናጋው ቤተ
ክርስቲያን የተቃውሞ ደወልዋን አሰማች ። በመላው ዓለም ያሉ የቤተ
ክርስቲያን መሪዎች ለጉባኤ ተጠሩ ። በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ
መንግሥት ኒቂያ በተባለችው ቦታ ላይ ትልቅ ጉባኤ ተደረገ ። በጉባ
ኤውም ላይ 318 ሊቃውንት ተሰበሰቡ ። አርዮስም በጉባኤው ላይ የኑ
ፋቄ ትምህርቱን አሰማ ፥ የትምህርቱ ይዘት በአጭሩ እንዲህ የሚል
ነበር ። " ወልድ ፍጡር ነው ፥ ነገር ግን ከሌሎች ፍጡራን ይበልጣል ።
ለአብ ፍጡሩም ልጁም ነው ፥ ኋላም በመዋዕለ ሥጋዌ ባሳየው ታዛ
ዥነትና የተጋድሎ ጽናት ከእግዚአብሔር ቡራኬንና ጸጋን ተቀብሎ
እንደ ጻድቃን እንደ ሰማዕታት ሱታፌ አምላክነት አገኘ " ።

ይህን የክህደት ትምህርቱን ያለምንም ማፈር በጉባኤው አሰማ ።
ቀጥሎም ቅዱስ አትናቴዎስ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ፥

1ኛ/ ወልድ የአብ ፍጡር ሳይሆን ራሱ የፍጥረታት ባለቤት
መሆኑን ፥

2ኛ/ እንደ አባቱ የስግደትና የአምልኮት ባለቤት መሆኑን ፥

3ኛ/ ሰውም ቢሆን ከአምላክነቱ የጐደለበት እንደሌለ ፥ በስ
ፋትና በጥልቀት ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሰ አፉን አስያዘው ። ጉባ

ኤውም እንደ አንድ ልብ መካሪ ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ የአ
ትናቴዎስን ትምህርት ተቀበለ ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው
ና ። አርዮስን ግን ከክህደት ትምህርቱ ይመለስ ዘንድ ጠየቁት ፣ እምቢ
ስለአለ አውግዘው ለዩት ። ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንም አርዮስን
አውግዛ ሳትከፋፈል ሐዋርያዊ ጉዞዋን በአንድነት ቀጠለች ።

ከአርዮስ ቀጥሎ በሰይጣናዊ ትምህርቱ ቤተ ክርስቲያንን ሊያ
ውክ የሞከረው መቅዶንዮስ የተባለ መናፍቅ ነው ። ይህ መናፍቅ ከቅ
ድስት ሥላሴ ሦስተኛው አካል መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ (ፍጡር) ነው ፣
አካል የለውም ብሎ በቁስጥንጥንያና በአካባቢው የክህደት መርዙን
ባገሳ ጊዜ በግሳቱ የተመረዙ ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ያውኳት
ጀመር ። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞ ድምጽዋን አሰማች ።
በዚህም ምክንያት በ381 ዓ. ም. በቁስጥንጥንያ 150 የሚያህሉ ከዓ
ለም አብያተ ክርስቲያን የመጡ ሊቃውንት በጉባኤው ላይ ታደሙ ።
መቅዶንዮስም የክህደት ትምህርቱን አቀረበ ። ጉባኤውም የመንፈስ
ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ከአብ ከወልድ ጋር በአንድነት የሚመ
ለስ የሚቀደስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ አስረዳ ። መቅዶ
ንዮስም ከዚህ ሰይጣናዊ ትምህርቱ እንዲታቀብ ተጠየቀ ፣ እሱ ግን
ወይ ፍንክች ስላለ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን ማኅበር ተለየ ።

ከመቅዶንዮስ ቀጥሎ “ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት
ባሕርይ ነው ፣ ከማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ነው ፣ ቃል በጥም
ቀት በዮርዳኖስ እስኪያድርበት ድረስ ወልደ ማርያም የቃል ማደሪያ
ለመሆን ተወለደ። ስለዚህ ማርያም ወላዲተ ሰብእ ናት እንጂ ወላዲተ
አምላክ አትባልም ” የሚል አይን ያወጣ የኑፋቄ ትምህርት ይዞ የቁ
ስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ንስጥሮስ ወደ ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ
ወጣ ። የመንበረ ማርቆስ 24ኛ ፓትሪያርክ የነበረው ቅዱስ ቄርሎስ
የሐዋርያትን የሰልስቱ ምዕትን የተዋህዶ መዶሻ ይዞ ወደ መድረኩ
ወጣ ። በ431 ዓ. ም. ኤፌሶን በተባለችው ከተማ 200 የሚሆኑ ሊቃነ
ጳጳሳት ከተለያዩ ዓለማት ተጠርተው ጉባኤ ተደረገ ።

ንስጥሮስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተከለውን የኑፋቄ ሚስማር
የታወቀው የተዋህዶ አናጺ ቄርሎስ በተዋህዶ ፋስ ፈንቅሎ አወጣ
ው ። ጉባኤውም ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ፣ እመ
ቤታችንም ወላዲተ አምላክ መሆንዋን መስክሮ ንስጥሮስንና ትምህ
ርቱን አውግዞ ተበተነ ። የሮም ፣ የአንጾኪያ ፣ የእስክንድርያና ሌላው
የተቀረው የክርስትናው ዓለም እስከዚህ ቀን ድረስ አንዲት ቤተ ክር
ቲያን በሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ይጓዝ ነበር ።



ይሁን እንጂ ይህችን አንዲቷን ቤተ ክርስቲያን የሚከፍል ሃሣብ
በ451 ዓ. ም. ብቅ አለ ። ቤተ ክርስቲያን እስከ መቼውም የማትረሳው
የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ክፋፋይ ፓፓ ሊዮን በነገሥታቱ በነመርቅ
ያንና በነብርክልያ ታጅቦ ቀረበ ። በቅዱስ ቄርሎስ ተዋህዶአዊ ትም
ህርት ግብዓተ መሬቱ የተፈጸመለትን የንጥሮስን ክህደት የተቀበረበ
ትን አፈር ምሶ በማውጣት ሕይወት ዘርቶበት በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ
አቆመው ። የተዋህዶ'አርበኞች አንገታችንን ለሰይፍ ፣ በአባታችን
በቄርሎስ የተወገዘው ትምህርት ዛሬ ከየት መጣ ? መጽሐፍ ቅዱስ
ያወገዘው ይህን ትምህርት በፍጹም አንቀበልም ብለው ከጉባኤው
ወጥተው ሄዱ ። የተዋህዶ አርበኛ በመባል የሚታወቀው ታላቁ
ዲዮስቆሮስም “ አንድ አካል አንድ ባህርይ ” የሚለውን መጽሐፍ
ቅዱሳዊ ትምህርት በገሃድ መሰከረ ።

በጉባኤው ውስጥ የታደሙ የመለካውያን ፈቃድ ፈጻሚዎች የነ
በሩ ጳጳሳት የክርስቶስን መንግሥት በምድራዊ መንግሥት ለውጠው
ከዓላማቸው አዘንብለው የነገሥታቱ ፈቃድ ፈጻሚዎች ሆኑ ። ልባ
ቸው እያወቀ የክርስቶስን የባሕርይ አንድነት አበሉ ። በዚህም የተነሣ
የእስክንድርያውን አንበሳ ዲዮስቆሮስን የሐዋርያትን እምነት በመ
መስከሩ አውግዘንሃል አሉት ። እርሱ ግን ትምህርታችን በንስጥሮ
ስና እሱን በመሰሉት ዘንድ እንጂ በክርስቲያኖች ዘንድ ግን ተቀባይ
ነት አለው ብሎ ከጉባኤው ወጥቶ ሄደ ። ከሕንድ ፣ ከአርመንያ ፣ ከሶ
ሪያ ፣ ከእስክንድርያና ከሌሎችም የምሥራቅ ክፍሎች ተወክለው የመ
ጡ ጳጳሳት የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ፈለግ ተከትለው ከጉባኤው ወጥተው
ሄዱ ። በዚህም የተነሣ የሮም ንግሥት የነበረችው ብርክልያ እኛ የጠ
ራነውን ስብሰባ ንቀህ እኛ ባልነው ሁሉ ያልተስማማኸው ለምንድር
ነው ? ብላ ጽሕሙን አስነጨችው ፣ ጥርሱም እስኪረግፍ ድረስ አስደ
በደበችው ። እርሱ ግን የተነጨው ጽሕሙንና የረገፈው ጥርሱን በአ
ንድነት አድርጐ ለእስክንድርያ ክርስቲያኖች “ ንሱ የኃይማኖት ፍሬ ”
ብሎ ላከላቸው ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባ
ሎች ከሮም ቤተ ክርስቲያንና ከመሰሎችዋ ጋር ተቆራርጠው ቀሩ ።
የክርስትናውም ዓለም ምሥራቅና ምዕራብ ተብሎ በሁለት ጐራ ተከ
ፈለ ። ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ምንጊዜም ብትሆን ልትጠፋ አት
ችልም ። ምክንያቱም በፍጡር ደም ሳይሆን በፈጣሪ ደም የተመሠረ
ተች ናትና ። የፓፓሊዮን ልጆች ግን ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንን
በሰይፍም በገንዘብም በድለላም ሊያጠፉ ብዙ ጥረዋል ። ግን አልሆነ
ላቸውም ። “ በዓለት ላይ የተመሠረተ ቤት ዝናብም ቢመጣ ጐርፍም

ቢዘንብ አይወድቅም ፤ በአሸዋ ላይ የተመሠረተ ቤት ግን ጐርፍ በጐረፈበት ጊዜ ይወድቃል ” ።

ከዚህ ዘመን በኋላ ማለትም ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ (በነገራችን ላይ ይህ የኬልቄዶን ጉባኤ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ “ ጉባኤ ከለባት ” ወይም “ ጉባኤ አብዳን ” ተብሎ ይታወቃል ፤ የውሾች ጉባኤ እንደማለት ነው ። ምክንያቱም የነገሥታትን ፍላጐት ለማሟላት ብቻ የተደረገ ጉባኤ ነበርና) ፤ ሮም በሥርዋ ያሉትን ጠቅልላ ካቶሊካዊት በሚል ስም ተጠራች ። ትርጉሙም “ የሁሉም ” ማለት ነው ። ከኦርቶዶክሳዊት እምነት አፈንገጠች ። ቀደም ብለን ያየናቸው የሃይማኖት አባቶች አትናቴዎስ ፤ ቄርሎስ ፤ ጢሞቴዎስ ሁሉም ኦርቶዶክሳውያን ናቸው ። ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ፤ ትርጉሙም እውነተኛ ወይም ቀጥተኛ ሃይማኖት ማለት ነው ።

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመሐመድ እንቅስቃሴ ተጀመረ ። መሐመድ በ570 ዓ. ም. ልዩ ስሙ መካ ተብሎ በሚጠራው ከተማ ተወለደ ። አባቱ መጠነኛ ገቢ የነበረው ነጋዴ ነበር ። ገና በልጅነቱ አባቱ ከእጠገቡ በሞት ስለተነጠቀ ለአጐቱ የበግ እረኛ ሆኖ ማገልገል ጀመረ ። ዳሩ ግን እስከ መጨረሻው የበግ እረኛ ሆኖ አልዘለቀም ነበር ። በዕድሜ ከእሱ ብዙ ለምትርቀው ለሐብታምዋ ነጋዴ ለከድጃ ባል ሆነ ። መሐመድ እንቅስቃሴውን እንዲጀምር ያነሳሳውን ሁኔታ ራሱ ሲገልጽ ፤ አንድ ቀን ከከተማ ውጭ በኮረብታ ላይ ለብቻው ተቀምጦ ታላቁ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ነብይ እንዲሆን እንደተመረጠ መንገሩን ይናገራል ። ከዚያ ወዲያ በመካ አዲሱን እምነት መስበክ ጀመረ ። ዳሩ ግን በዚያ ቅጽበት መካ እሺ በጂ ብላ በአዲሱ እምነት ውስጥ ልትገባ አልቻለችም ፤ እንዲያውም ብዙ ተቃዋሚዎች ተነሱበት ። በተለይ ካህናተ ጣኦታት ሕዝቡን ያሳድሙበት ጀመር ። በመካ ካባ የተባለ ቤተ ጣኦት ነበር ። በዚህ ምክንያት የተነሣ የመሐመድን እንቅስቃሴ የሚደግፉ ወገኖቹ በግመል አስርቀው መዲና ወደተባለች ከተማ ወሰዱት ። ይህም የሆነበት ጊዜ 622 ዓ. ም. ነበር ። እስላሞችም ዘመናቸውን ከዚህ ጊዜ ጀምረው ነው የሚቆጥሩት ይባላል ።

መሃመድ መዲና እንደገባ ብዙ ተከታዮችን ያሰባስብ ጀመር ። በ630 ዓ. ም. እምነቱን የተቀበሉትን ሰዎች እሰልፎ የመካን ከተማ ወረረና በቁጥጥሩ ሥር አደረገ ። ካባ በተባለው መቅደስ ውስጥ የነበሩትን 308 የጣኦት ምስሎችም አፈራረሰ ።



የእስልምና እምነት ሊስፋፋ የቻለው ከመሃመድ ሞት በኋላ ነበረ ። መሃመድ በ632 ዓ. ም. ከሞተ በኋላ ተከታዮቹ “ በጀሐድ መንፈስ ” ትጥቃቸውን አጠናክረው ፤ ወገባቸውን አጥብቀው ብዙ ሃገሮችን በጦር አንበረከኩ ። በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ያሉት አገሮች የመጀመሪያዎቹ ኢላማዎች ነበሩ ። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

1ኛ/ እስልምና የተጀመረበት አካባቢ በዚሁ ክልል መሆኑ ፤

2ኛ/ ሮማውያን የኦርቶዶክስን እምነት ትታችሁ ካቶሊካዊ ሁኑ እያሉ ያስጨንቁአቸው ስለነበር ፤ በዚሁ እልህ ተነሳስተው ከመሐመድ ሠራዊቶች ጋር ተባብረው ሮማውያንን ለማጥቃት ሲሉ እንደሰለሙ ይነገራል ።

3ኛ/ አዲሱን እምነት የተቀበሉ ሁሉ ከሌሎቹ ለየት ያለ መብትና ጥቅም ስለነበራቸው ከጥቅም አንፃር የሰለሙም ጥቂቶች አልነበሩም ።

የመሃመድ ሠራዊቶች ወደብዙ የአፍሪካ ክልሎችም በመዝለቅ በዛ ያሉ አገሮችን በመዳፋቸው ውስጥ ከተቱ ።

የምዕራቡን የክርስትና እምነት ተከታይ የሚከፋፍል ሃሣብ ደግሞ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቅ አለ ። የዚህ እንቅስቃሴ ፊትአውራሪ የነበረው ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ነበር ። ማርቲን ሉተር በጀርመን አገር አይስሌበን በተባለች ከተማ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1483 ዓ. ም. ተወለደ ። ማርቲን ሉተር የካቶሊክ እምነት ተከታይ ነበር ። ራሱንም ለካቶሊክ እምነት ሙሉ ለሙሉ አሳልፎ የሰጠ ገዳማዊ ሰው እንደነበረ ፤ ተከታዮቹ ይናገሩለታል ። የኋላ ኋላ ግን ከምንኩስና ዓለም ወጥቶ ገዳማዊ ኑሮን በመንቀፍ ብዙ ገዳማትን እንዲዘጉ አድርጓል ። ይህ ከክርስትና መመሪያና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ ድርጊት መሆኑ ግልጽ ነው ። ምክንያቱም እግዚአብሔር የምንኩስናን ሕይወት የነቀፈበት ጊዜ የለምና ። ራሱ ጌታ መንፈሣዊ ሥራ ለመሥራት ገዳማት የተመረጡ ቦታዎች መሆናቸውን ሲያስረዳና ለመነኰሣትም አብነት ሲሆን ለመጾም ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ነበር የሄደው ። በዚያም ከአራዊት ጋር እንደነበር ይገልጽልናል ፤ ማቴዎስ 4 ፥ 1 ማርቆስ 1 ፥ 13 ። ሉተር ግን በኋለኛው ዘመን ተነስቶ ይህን ሁሉ በመብቱ ሽሯል ፤ ዛሬም ተከታዮቹ አርአያውን በመከተል ምንኩስናን ሲቃወሙ ይሰማሉ ።

ማርቲን ሉተር የሉተራንን እንቅስቃሴ እንዲጀምር ያነሳሳው እውነተኛ ምክንያት ቢኖረውም ፤ የኋላ ኋላ ግን ወደ ፍፁም ስሕተት አምርቷል ። ምክንያቱም እንደሚከተለው ተጠቅሷል ፤

እሱ በሚያገለግልበት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ዮሐንስ የተባለ መነኩሴ ድንኳን ተክሎ ለከተማው ሕዝብ በገንዘብ የኃጢአትን ሥርየት ይሸጥ ነበር ። ይህም ገንዘብ ለመሰብሰብ ካለው ጠንካራ ምኞት የተነሣ የፈጸመው ድርጊት እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኃጢአት ሥርየት በንስሃ እንጂ በገንዘብ ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው ። ይህ ገንዘብ የመሰብሰቢያ ስልት አጥጋቢ መሆኑ ስለ ታመነበት የሮም ሊቀ ጳጳስ ሌዎ አሥረኛ በሮም ከተማ ታላቁን የጴጥሮስ ቤተክርስቲያን ለማሳነጽ የገንዘብ እጥረት ገጥሞት ስለ ነበረ ፥ ዮሐንስ የተባለው መነኩሴ የጀመረውን የስርየት ንግድ እሱም አጧጧፈው ። ሰውም መንግሥተ ሰማያት በካርዲ ካልሆነ በፍጹም መግባት እንደማይችል በማመን የመንግሥተ ሰማያትን መግቢያ ደረሰኝ ይገዛ ጀመር ።

ሉተርም ይህን ዓይን ያወጣ የሌብነት ሥራ በግልጽ ማውገዝ ጀመረ ። ብዙዎችም የሃሣቡ ደጋፊ ሆኑ ። የኋላ ኋላ መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር አለብኝ ብሎ ተነሣ ። አብዛኛዎቹ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትመራበት የነበረው ሥርዓትና እምነት ትክክል አለመሆኑን ገለጸ ።

በእሱ መሪነት የተመሠረተው የፕሮቴስታንት እምነት ስሙ እንደሚጠቁመን ተቃውሞ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ጥገናዊ ለውጥ ያስፈልጋታል በማለት ከሐዋርያት ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ወጥቶ ብዙ ነገሮችን ነቀፈ ።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1517 ዘጠና አምስቱ ዓረፍተ ነገሮች የተባለውን በዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ በወረቀት አድርጐ ለጠፈ ። በዚህም ምክንያት ከሮም ቤተ ክርስቲያን ማፈንገጡን ይፋ አደረገ ። ከማርቲን ሉተር ስሕተታዊ ትምህርቶች ውስጥ አንዳንዶቹን ብንጠቅስ

ሀ. ምንኩስና አላስፈላጊ እንደሆነና ገዳማትም መዘጋት እንዳለባቸው

ለ. በጸሎት ጊዜ የቅዱሳንን ስም መጥራት እነርሱንም እንደ አማላጆች አድርጐ መቁጠር ስሕተት መሆኑን ፥

ሐ. ማንኛውም ሰው በራሱ አተረጓጐም መጽሐፍ ቅዱስን መተርጐም እንደሚችል ሲሆን ፥ በተለይ ይህ ሰፊ መንገድ ለብዙ እምነቶች መፈጠር ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ ነው ። በአሁን ጊዜ እንደ ሰማይ ከዋክብት ለብዙ ለተለያዩ የእምነት ድርጅቶች መፈጠር ዋና መንስኤ የሆነው ይኸው አባባል እንደሆነ በብዙዎች ይታመናል ።



ሉተር በ1546 ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይም እሱ የቀደደው መንገድ ግን ለብዙ የእምነት ድርጅት ፈጣሪዎች ጥሩ አስተዋጽኦ አበርክቶላቸዋል ። ፈረንሣዊው ጆን ኬልቪን በስዊዝ እና በተለያዩ የአውሮፓ ክፍሎች የሉተርን አርማ ይዘው የምዕራቡን ክፍል በሉተራን እምነት ከፋፈሉት ። የምዕራቡ የክርስትናው ክፍል በተለያዩ ዶክትሪን ተከፋፈለች ፥ ቀድሞም ቢሆን ፥ በልዩን ስሕተት ላይ የተመሠረተ ስለነበረ ትንሽ ነፋስ ነበር የሚጠብቀው ፥ አሁን ደግሞ የሉተር እንቅስቃሴ አናጋው ። ከሉተር በኋላ የተለያዩ ሰዎች አሁንም ከሐዋርያዊ ጉዞ የተለየ ሃሣብ በመያዝ ክርስቲያኑን መሠረታዊ ባልሆነ የፍልስፍና ትምህርት ይበጠብጡት ጀመር ።

በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሔንሪ ስምንተኛ የተባለው የእንግሊዝ ንጉሥ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ የሚወጣበትን ምክንያት አበጀ ። በሕይወት ያለችውን ሚስቱን ምንም ሳትበድለው እስዋን ፈትቶ ሌላ ሴት ለማግባት ፍላጐት ስላደረበት ለሮማው ፓፓ ይህን ፍላጐቱን እንዲያጸድቁለት መልዕክት ይልካል ። ጳጳሱ ግን ሥርዓት አለመሆኑን ገልጸውለት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን አሳወቁት ። ይህን ምክንያት በማድረግ እንግሊዝ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ተለይታ “ የእንግሊካን ቸርች ” በሚል ስያሜ የራስዋን ቤተክርስቲያን መሠረተች ።

የሮም ቤተክርስቲያን ብዙ ሃገሮችን እንዳጣች በተገነዘበችበት ወቅት (ካውንተር ሪፎርሜሽን) ጀመረች ። በዚህ ጥገናዊ ለውጥ ላይ ጀስዊት (ኢየሱሳውያን) የሚባሉ በጀነራል የሚመሩ የሃይማኖት ወታደሮች አሰለጠነች ። እነዚህም ካህናት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ማለትም በሕክምና ፥ በምህንድስናና በመምህርነት የሰለጠኑ ነበሩ ። በዚህ ስልት ሮም ያጣቻቸውን አገሮች ባትመልስም ፥ ተጨማሪ መለየት እንዳይፈጠር ልታግድ ችላለች ። እንዲሁም ወደ አፍሪካ ጐራ በማለት አንዳንድ አገሮችን ማርካለች ።

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሌላ የእምነት ድርጅት ብቅ አለ ። ይኸውም የአድቬንቲስት እምነት ነው ። ስሙ እንደሚጠቁመን ‘አድቬንት ’ ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የወጣ ነው ። አድቬንት ማለት የክርስቶስ እንደገና ለፍርድ መምጣት ማለት ነው ። አድቬንቲስት ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሌት ተቀን የሚያወሩ ፥ ክርስቶስ ነገ ይመጣል ፥ ከነገ ወዲያ ይመጣል እያሉ በትንቢት ላይ ተመስርተው የሚኖሩ ናቸው ።

የአድቬንቲስትን እምነት በዘመናዊ መልኩ ያደራጀው ዊሊያም ሚለር የተባለው አሜሪካዊ ነው ። ዊሊያም ሚለር እምነቱ በብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ከተጠቀመባቸው ዘዴዎች መካከል

የክርስቶስ ምጽአት መቃረቡን መስበክ ነበር ። ይህ ሰው በአሜሪካ ቀጥሩ በርከት ላለ ሕዝብ ክርስቶስ ለፍርድ በ1843 እና በ1844 ዓ. ም. አካባቢ ይመጣል ብሎ ትንቢት ተናግሮ ነበር ። ይህ ትንቢቱ ለወቅቱ ብዙ ሰዎችን በፍርሃት የእምነቱ ተካፋይ ቢያደርጋቸውም ኋላ ግን ውሸቱን መሆኑ ሲታወቅ ሲበታተኑ ችለዋል ።

የአድቬንቲስት እምነት ተከታዮች በብዙ ክፍል ይከፈላሉ ። አንዳንዶቹ “ ኮንሰርቫቲቭ ” ሲባሉ ሌሎቹ ደግሞ “ ኢቫንጀሊካል ” በመባል ይታወቃሉ ። እንዲሁም ደግሞ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ ።

የመጀመሪያዎቹ “ ዘሰቨንዝ ዴይ አድቬንቲስት ” በሚል ስም ሲጠሩ ፣ ሰንበት ቀዳሚት እንጂ እሁድ አይደለችም ይላሉ ። እንዲሁም የሰው ሁሉ ነፍስ እስከ ዕለተ ምጽአት በመቃብር እንደምትኖር አድርገው ያስተምራሉ ።

ሁለተኛዎቹ “ ዘ አድቬንት ክርስቲያን ቸርች ” በመባል ሲታወቁ እነዚህኛዎቹ ደግሞ ከላይኛዎቹ ለየት ብለው ሰንበት እሁድ መሆንዋን ያስተምራሉ ።

ሶስተኛዎቹ “ ዘ ቸርች ኦፍ ጎድ ኦፍ ዘ አብርሃሚክ ፌዝ ” የሚባሉት ሲሆኑ ፣ በሰንበት አከባበር በኩል ከሁለተኛዎቹ ጋር አንድ ናቸው ።

በ1870 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የተነሣው ቻርልስ ራስል የተባለው ሰው በአሜሪካን ዩናይትድ ስቴትስ ፣ “ ጂሖቫ ዊትነስ ” የተባለውን የእምነት ድርጅት ፈለሰፈ ። ቻርልስ ራስል ለየት ያለ ትምህርት ይዞ ቢነሳም ፣ ይህ የሙት ትምህርቱ ግን በ325 ዓ. ም. በኒቂያ ላይ የተወገዘ የአርዮስ ትምህርትና በ381 ዓ. ም. በቁስጥንጥንያ “ መንፈስ ቅዱስን ጉደሎ ” ብሎ የተወገዘው የመቅዶንዮስንና የሌሎችንም መናፍቃን ትምህርት አካቶ የያዘ ነው ።

የእምነቱ ተከታዮች እንደሚሉት መጠሪያ ስማቸውን “ የይሖዋ ምስክር ” የሚለውን ያገኙት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢሳያስ 43 ፥ 10 እንደ አሜሪካኑ ስታንዳርድ ቨርሽን አተረጓጎም ነው ብለው ነው ። በዚህ ቦታ ላይ “ እናንተ የይሖዋ ምስክሮች ናችሁ ” ይላል ። እና በኢሳያስ የተነገረልን እኛ ነን ሲሉ ይሰማሉ ። በመሠረቱ ይሆዋ የእግዚአብሔር ክቡር ስሙ መሆኑ ቢታወቅም ፣ እነሱ ግን የታላቁ አምላክ ምስክሮች እንዳልሆኑ ሥራቸውና እምነታቸው ይገልጻቸዋል ።

እንደ “ ይሖዋ ምስክሮች ” ወይም አርዮሳውያን አባባል ይሖዋ ሁሉን የሚችል አምላክ ሲሆን ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ወደፊት



ለምትፈጠረው አዲሲቱ ዓለም ንጉሥ ይሆን ዘንድ የታጨ ነው ይሉታል ። ትምህርታቸውንም በማርዘም ክርስቶስ ማለት የመጀመሪያው መልአክ ሚካኤል የተባለው ነው ብለው ክርስቶስን ሚካኤል ነው ብለው ያምናሉ ፣ ያስተምራሉም ።

እንደ ኢንሳይክሎፒዲያ አሜሪካና አገላለጽ ፣ ከ25,206 በላይ ኮንግሪጌሽንስ በመላው ዓለም ላይ ሲኖራቸው ከእነዚህም ኮንግሪጌሽንስ 5141 በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ውስጥ ይገኛሉ ። በ1967 ዓ. ም. ብቻ 17 ሚሊዮን የሚያህሉ የተለያዩ ትናንሽ መጻሕፍቶች በዓለም ላይ በትነዋል ። ዋችታወር ብለው የሰየሙት መጋዚን በ72 የተለያዩ ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ሲሆን ፣ በ1968 ዓ. ም. እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ5 ሚሊዮን 3 መቶ ሺህ በላይ ተሰራጭቷል ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ይህ በክርስትና ስም የሚንቀሳቀስ ድርጅት ትምህርቱ ከክርስትና እምነት ፍጹም የራቀ ሆኖ ሳለ፣ዳሩ ግን ምዕመናንን በክርስትና ስም በማሳሳትና የአርዮስን እምነት እንዲከተሉ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ነው ።

አንዳንዶቹ ቻርልስ ራስል ከአድቬንቲስት እምነት የወጣ እንደ ሆነና በስምንት ቀን ስብከት ብዙዎችን የእምነቱ ተከታዮች እንዳደረገና አሚሚቱም እንደ ግብር አባቱ እንደ አርዮስ በመቅሰፍት መሆኑን ይናገራሉ ። በ1916 ዓ.ም. ከካሊፎርኒያ ወደ ቤቱ ሲመለስ እንደ ሞተ ይነገራል ። ምናልባት ብዙ ጊዜ አርዮሳውያን ስለሁለተኛው አባታቸው ስለ ራስል የማያወሩት ሕይወቱ ሙሉ በውሸት የተሞላ ስለ ሆነ ይሆናል ።

ይህ ሰው ክርስቶስ በዚህ ዘመን ይመጣል ብሎ ጊዜውን ወስኖና ቦታ ከልሎ ተናግሮ ነበር ። ትንቢቱ ሳይዝለት የቀረ ደህና የሐሰት ነቢይ ነው።

* ይህንንም የውሸት ትንቢቱን ለማስተባበል ተከታዮቹ የማይሆን ምክንያት ሲሰጡ ይሰማሉ ። የይሖዋ ምስክሮች በዘመናችን ብዙዎችን በገንዘብም ሆነ በሐሰተኛ ትምህርታቸው እያታለሉ በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፉ ስለሆነ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልክ ወገኔ ሁሉ ከእነዚህ በኋለኞቹ ዘመናት በስሜ ይመጣሉ ከተባሉት ሐሰተኞች ክርስቶሳውያን እንድትጠበቅ ምክሬን እየለገስኩ የእነዚህን መሳቲዎች ትምህርትና ለመሳቲ ትምህርታቸው የተሰጠውን መልስም በቦታው ስለጻፍኩልህ ተመልከት ።

---

* በ1874 ዓ. ም.

** ስለተለያዩ የእምነት ክፍሎች ካነሳን ዘንድ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እጋማሽ ላይ ስለተከሰተው ስለ ‘ በሐ ሁላ ’ እምነት ትንሽ ልበላችሁ ። ለእዚህ እምነት ጥርጊያ መንገድ ያደረገው ኦሊ መሃመድ የተባለው ሰው ሲሆን ፣ በ1819 ዓ. ም. ሺራዝ በተባለችው ቦታ የተወለደ ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ እምነቱን ሲጀምር ፣ “ ባብ ” የሚል ስያሜ ሰይሞት ነበር ። ትርጉሙ በእንግሊዝኛ ‘ ጌት ’ ማለት ሲሆን በአማርኛችን ‘ በር ’ እንደማለት ነው ።

ከዚያ በኋላ የተወጠነውን ጅምር ይዞ የተነሣውና በመጨረሻ ላይ የአሊ መሃመድን ሃሣብ ከግብ ያደረሰው መርዛ ሁሴን አሊ የተባለው የፐርሻ ሰው ነው ። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1863 ዓ. ም. ሁሴን አሊ የእምነቱን መጠሪያ ‘ በሐሁላ ’ ብሎ ሰየመው ። “ስብሐተ እግዚአብሔር ” ወይም “ የእግዚአብሔር ክብር ” እንደማለት ነው ። ከእሱ ሞት በኋላ ማለትም ከ1892 ዓ. ም. በኋላ የእምነቱ መሪነት ለታላቅ ልጁ ለአብደላ በሐ ተዘዋውሯል ።

የባሀይ እምነት ተከታዮች የተለየ አቋም የላቸውም ። የትኛውም እምነት በውስጡ ትክክለኛ ዓላማ ስላለው እኛም ከሁሉም መልካም መልካሙን እንወስዳለን ሲሉ ፣ የዘመናችን ታላቁ ጌታ ሰው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብበት የሚችልበት “ በሀሁላ ” ነው ብለው ያምናሉ ። በእነርሱ እምነት መሠረት ክርስቶስም ሆነ መሐመድ ለአሁኑ ትውልድ አስፈላጊ እንዳልሆኑ ይናገራሉ ።

በዚህ ባለንበት ዘመን በክርስትና ስም እንኳን ከ22 ሺህ በላይ የእምነት ድርጅቶች እንዳሉ ይነገራል ። እንግዲህ ጳውሎስ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው “ አንዲት ሃይማኖት ፣ አንዲት ጥምቀት ” ብሎ ስለአንዲት ሃይማኖት ሰብኮ እያለ ይህ ሁሉ እምነት ታዲያ ሊኖር ይገባል ?

ተገቢ አለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ ስለሆነ እንዷን ሃይማኖት ፈልገን ማግኘትና በእሷ ውስጥ መጓዝ አለብን ። ይህቺን ሃይማኖት ፈልገን የምናገኝበትን መንገድ እግዚአብሔር ራሱ ሲጠቁመን “ የቀደመችይቱን መንገድ (ሃይማኖት ) ጠይቁ ፣ መልካሚቱ መንገድ (ሃይማኖት) ወዴት እንደሆነች እወቁ ፣ በእርስዋም ላይ ሂዱ ፣ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ ” ሲል አሳስቦናል ። ኤርሚያስ 6 ፥ 16 ፥

---

** Encyclopaedia Britannica, Page 928 ( Vclume 2 )



እንግዲህ ታሪክ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነታችን ከሁሉ በፊት የነበረች መሆንዋን ያስረዳናል። ለኢትዮጵያውያንም የመጀመሪያዋ ሃይማኖታችን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መሆንዋ አሌ የማይባል ሐቅ ነው ። ኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበለችው በ34 ዓ. ም. ነው ። ይህንንም በሐዋርያት ሥራ 8 ፥26—40 የምናገኘው ነው ።

እምልኮተ እግዚአብሔርም ለእኛ አዲስ አይደለም ፣ የዛሬ ሦስት ሺህ ዓመታት ነው እግዚአብሔርን ያወቅነው ። ታዲያ የዛሬዎቹ ክርስቶስን እናስተዋውቃችሁ ባዮች ትንሽ አያፍሩም ? ሌላ ክርስቶስን እንዳንቀበል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላስጠነቀቀን አንፈልግም ። እኛ ስለኃጢአታችን ሲል በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ክርስቶስን ከማንም ቀድመን አውቀነዋል ፣ አምነንበታል ፣ በስሙም ተጠምቀናል ፣ የባሕርይ ስግደትም እናቀርብለታለን ፣ ሌት ተቀን እናመሰግነዋለን ። አሁንም ለወደፊትም የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይከበር ይመስገን አሜን ! ! !

# ምዕራፍ ፪

## መ ጽ ሐ ፍ ቅ ዱ ስ

መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ ካሉት የተለያዩ ዓለማዊ መጻሕፍት
ማለትም የፍልስፍና ፥ የልብወለድ መጻሕፍት በጣም የተለየና በፍጡር
አእምሮ የተደረሰ ሳይሆን ፥ በመንፈስ ቅዱስ ያራሲነት በቅዱሳን አባ
ቶች ፀሐፊነት የተጻፈ ነው ። በውስጡ ያሉትም መንፈሣዊ ትምህር
ቶች ጊዜ የማይሽራቸው ምን ጊዜም የማያረጁ ዘለዓለማውያን ናቸው።
ትውልድ ያልፋል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ግን ከጊዜ ወደጊዜ በተለያዩ
ሰዎች አንደበት አዲስ ሆኖ ይነገራል ። ሌሎች መጻሕፍት በተደጋጋሚ
ሲነበቡ ይሰለቻሉ ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ግን ምንጊዜም አዲስ ነው ፥
ምሥጢሩም እንደ ባሕር እሸዋ የበዛ ነው ። ምክንያቱም የዘለዓለማ
ዊው የእግዚአብሔር ቃል ነውና ፤ " ትውልድ ያልፋል አንተ ግን ከዘለ
ዓለም እስከ ዘለዓለም ያው ነህ ፥ ዘመኖችህም አይወሰኑም " የዚህ
ታላቅ ጌታ ሕያው ቃል ነው ። ስለሆነም ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ በእ
ሱም የሚመሠረቱትን ሕያው ሊያደርግ ይችላል ። ታላቁ መጽሐፍ ፥
መጽሐፍ ቅዱስ ።

### ብሉይ ኪዳን ፤

በመጀመሪያ በእብራይስጥ ቋንቋ ተጻፈ ፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት
ያለውን የአንድ አምላክ አማኞች የሆኑትን የእብራውያንን ታሪክ ይተ
ርካል ። በውስጡም ብዙ የተስፋ ቃሎችን የያዘ ነው ። ስለመሲሁ ክር
ስቶስ መምጣትም የተነገሩ ትንቢቶች በብዛት አሉበት ። በ1400
ዓመተ ዓለም አካባቢ ፥ ይህም ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑ ነው
በዚያን ጊዜ እንደተጻፈም ይገመታል ።

የብሉይ ኪዳን ጻሕፍት በብዛት አርባ ሲሆኑ ከእነሱም ውስጥ
አምስቱን አሪት የጻፈው ታላቁ ነቢይ ሙሴ ነው ። በ284 ዓ. ዓ. ከክ
ርስቶስ ልደት በፊት ፥ በጥሊሞስ በተባለው ንጉሥ የንግሥና ዘመን
ብሉይ ኪዳን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ ቋንቋ ተተረጐመ ። ከዚያም
በሄሮዲሞስ ዘመነ መንግሥት ጀሮም የተባለው የላቲን ቤተ ክርስቲ
ያን አባት ወደ ላቲን ቋንቋ ተረጐመው ። ዘመኑም 366 ዓ. ም. ነው ።

ብሉይ ኪዳን በሐገራችን ቋንቋ በግዕዝ የተተረጐመው ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሉ ሲሆን ፥ ይኸውም በንግሥተ ሳባ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው ።

## ሐዲስ ኪዳን ፥

ስለመሲሁ ክርስቶስ መወለድ ፥ በዚህች ምድር ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር መመላለስ ፥ መሞት ፥ እንዲሁም ሞትን ድል አድርጎ መነሣት ፥ ማረግ ፥ የመሳሰሉትን የሚያስረዳ ሲሆን የተጻፈው ከ48—98 ዓ. ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ይገመታል ።

የሐዲስ ኪዳን ጻሕፍት ብዛታቸው ስምንት ሲሆን ከእነሱም ውስጥ ብዙዎቹ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ የተማሩ ፥ በጥለበት የዋሉ ፥ ባደረበት ያደሩ ነበሩ ። ስለዚህም ጌታ ራሱን በዓይናቸው አይተው ፥ በጆሮአቸው ሰምተው ፥ በእጃቸው ዳስሰው የጻፉ ናቸው ። ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ጻሕፍት ለየት ያሉ ናቸው ።

## አራቱ ወንጌላውያን ፤

ማቴዎስ ፥ ማርቆስ ፥ ሉቃስ ፥ ዮሐንስ በመባል ይጠራሉ ። ማቴዎስና ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ውስጥ ሲሆኑ ፥ ማርቆስና ሉቃስ ደግሞ ከሰባ አርድእት ውስጥ ናቸው ። ሁለቱ ከሐዋርያት ፥ ሁለቱ ከአርድእት የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው ? ቢባል ጌታ ወንጌሉን ሐዋርያት ጨርሰው እንዲጽፉት ቢያደርግ ኖሮ አርድእት ለማስተማር ሲወጡ እናንተንማ ማን ይሰማችኋል ፥ የውጭ ሰው ናችሁ ፥ የውስጥማ ሰዎች ብትሆኑ ወንጌልን በጻፋችሁ ነበር ብለው አይሁድ ትምህርታቸውን ከመቀበል ወደ ኋላ ባሉ ነበር። ስለዚህ ጌታ ይህን አስቀድሞ ስለሚያውቅ ከአርድእትም ወንጌልን እንዲጽፉ አደረገ ። እንዲሁም ደግሞ ሐዋርያት ብቻ ጨርሰው ቢጽፉት ኖሮ የአርድእት ክብር በአይሁድም ዘንድ ሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ ባልታወቀ ነበር ። አሁን ግን አርድእትም በጌታ ዘንድ የከበሩ መሆናቸውን ወንጌልን በማጻፉ ታወቀ ።

አርድእት ብቻስ ለምን አልጻፉትም ፥ ሁለቱን ከሐዋርያት ስለምን አደረገ ? የሚል ጥያቄ በአያንዳንዳችን ሕሊና ሊቀረጽ ይችላል ። ለዚህም ምክንያት አለ ፥ ይህ የሆነበት ምክንያት ስለወንጌል ክብር ነው ። በአጠቃላይ ወንጌል በአርድእት ብቻ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ይህችማ ተርታ ሕግ ናት ፥ ደጊቱማ ሕግ ምሥጢረ ታምራትን በቤተ ኢያኢሮስ ፥ ምሥጢር መንግሥትን በደብረ ታቦር ፥ ምሥጢረ ምጽአትን በደብረ ዘይት ፥ ምሥጢረ ጸሎትን በጌቴሴማኒ ባዩ አዕማደ ምድር



በተባሉ በልበ ሐዋርያት ቀርታለች በማለት አይሁድ ደገኛይቱን ሕገ ወንጌል ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ።

## የጻሕፍቱ አራት መሆን ምሥጢሩ ፤

ወንጌልን የጻፉት አራቱ ወንጌላውያን ብቻ ናቸው ፥ ከፍ ብለው አምስት ፥ ዝቅ ብለው ሦስት አልሆኑም ፥ አላደረጋቸውም ። ስለምንድነው ቢባል ስለብዙ ምክንያቶች ነው ።

1ኛ/ የምድር ሥርዓት በሰማይ ሥርዓት አንጻር የተሰራ ነውና በሰማይ አራት ጸወርተ መንበር ኪሩቤል አሉ ፥ በዘፈቀደ የሚገለጽባቸው መንበሩን ተሸክመው የሚታዩ የሚቀድሱት ። በፀጋ የሚያድርባቸው ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ የሚሸከማቸውስ እሱ ነው ፤ እነዚህም የሰው ፥ የአንበሳ ፥ የላምና የንስር መልክ አላቸው ። የዮሐ. ራዕይ 4 ፥ 6—8 ተመልከት ።

አራቱ ወንጌላውያንም በእነዚህ በአራቱ ኪሩቤል ይመስላሉ ፥ አራቱ ኪሩቤል በእነዚህ አራቱ እንስሳት መመሰላቸው ፥ የሰው ምስል ያለው ለአዳም ፍጥረት ሁሉ የሚጸልይ ፥ የንስር መልክ ያለው ለአእዋፋት የሚጸልይ ፥ የአንበሳ መልክ ያለው ለአራዊት የሚጸልይ ፥ የላም መልክ ያለው ለጋማና ለቀንድ ከብቶች የሚጸልይ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው ።

— <u>በሰው መልክ</u> ማቴዎስ ይመስላል ። ምክንያቱም የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ እያለ ምድራዊ ልደቱን በመጻፍ ይጀምራልና ።

— <u>በአንበሳ መልክ</u> ማርቆስ ይመስላል ። ምክንያቱም አንበሳ ኑሮው ከሰው ርቆ በምድረ በዳ ነው ፥ ከዚያ ሆኖ የሕሩን ባሰማ ጊዜ እንስሳት ይገሠጻሉ አራዊት ይደነግጣሉ ። ማርቆስም ከአምልኮተ እግዚአብሔር ትምህርት ተራቁታ ምድረ በዳ በምትሆን በምድረ ግብጽ " የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ " ብሎ ባስተማረ ጊዜ ምዕመናን ተገሥጸዋል ፤ አጋንንትና መናፍቃን ደንግጠዋልና ። ዳግመኛም አንበሳ ለላም ጌታው ነው ይሰብረዋል ፤ ማርቆስም ከግብጽ ምድር በትምህርተ ወንጌል አምልኮተ ላህምን (የላም ጣኦት ሠርተው ያመልኩ ነበር) አጥፍቷልና ። ግብጽ ቀደሞ ሙሴ ፥ ኋላም ኤርምያስ በየተራ ቢያስተምሯት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር አልገባችም ነበር ። በማርቆስ ስብከት ግን ክርስቶስን ፍጹም አምና ተቀብላለች ።

- <u>በላም መልክ</u> ሉቃስ ይመሰላል ። ከሌሎቹ ለየት ባለ ሁኔታ ክርስቶስ በከብቶች በረት እንደተወለደና እንስሶች ትንፋሻቸውን እንደገበሩለት ጽፏልና ።
- <u>በንስር መልክ</u> ዮሐንስ ይመሰላል ። ምክንያቱም ንስር በእግር ይሽከረከራል ፣ በክንፍ መጥቆ ይበራል ። በእግር እንዲሽከረከር ዮሐንስም እንደሌሎቹ ወንጌላውያን የአብን ልጅ ከሰማየ ሰማያት መውረድ ከድንግል ማርያም መወለድ ይጽፋልና ። ንስር በክንፍ መጥቆ እንዲበር ዮሐንስ ከሌሎቹ ወንጌላውያን ለየት ብሎ አካል ከሕልውና ተገልጾለት የቃልን በቅድምና መኖር ፣ እንዲሁም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ጽፏል። የንስር ዓይኑ ጽሩይ ነው ። ሽቅብ ወጥቶ ረቦ ፣ ቁልቁል በተመለከተ ጊዜ የስናፍጭ ቅንጣት ታህል ሥጋ ብትሆን አትሰወረውም ፣ የማየት ሃይሉ ከፍተኛ ነው ። ዮሐንስም ከሌሎቹ ወንጌላውያን ለየት ብሎ ወንጌሉን ሲጀምር እጅግ ርቆና መጥቆ ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የአካላዊ ቃልን በቅድምና መኖር ተናግሯል ።

የአራቱ እንስሳ ኪሩቤል አቋቋም የሰው ገጽ ያለው አቋቋሙ በምሥራቅ ሆኖ ፊቱ ወደ ምዕራብ ነው ። የአንበሳ ገጽ ያለው አቋቋሙ በምዕራብ ሆኖ ፊቱ ወደ ምሥራቅ ነው ። የላም ገጽ ያለው አቋቋሙ በሰሜን ሆኖ ፊቱ ወደ ደቡብ ነው ። የንስር ገጽ ያለው አቋቋሙ በደቡብ ሆኖ ፊቱ ወደ ሰሜን ነው። እንደዚሁም ማቴዎስ ጽፎ ለማርቆስ ደቀ መዛሙርት ማርቆስ ጽፎ ለማቴዎስ ደቀ መዛሙርት ፣ ሉቃስ ጽፎ ለዮሐንስ ደቀመዛሙርት ፣ ዮሐንስ ጽፎ ለሉቃስ ደቀ መዛሙርት መስጠታቸውን መናገሩ ሲሆን ፣ ይህም ወንጌል በጥንተ ስብከት የደረሰችበትን ማሳየቱ ነው ። ከእዚያ በኋላማ በመላው ዓለም ተሰብካለች ።

2ኛ/ በአራቱ አፍላጋት (ወንዞች) ይመሰላሉ ፣ እነዚህም ከገነት ከአንድ ከእጸ ሕይወት ሥር መንጭተው ይህን ዓለም ዞረው አጠጥተው ዕጽዋትን ከመድረቅ ወደ ልምላሜ ፣ ከልምላሜ ወደ ጽጌ (አበባ) ፣ ከጽጌ ወደፍሬ ያደርሳሉ ። ልክ እንደዚሁ አራቱ ወንጌላውያንም ወንጌልን ከአንድ ጌታ ተምረው ይህን ዓለም ዞረው አስተምረው ምዕመናንን በኃጢአት ከመድረቅ ወደ ልምላሜ ንስሐ ፣ ከልምላሜ ንስሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ከጽጌ ትሩፋት ወደ ፍሬ ክብር ያደርሳሉና ።



3ኛ/ በአራቱ ከዋክብት ይመሰላሉ ፤ እነዚህ አራቱ ከዋክብት ሀልመልሚሌክ ፣ ምልክኤል ፣ ምልኬል ፣ ናርኤል በመባል ይጠራሉ ። እነዚህም ዓመቱን ከአራት ይካፈሉታል ። ዘጠና አንድ ቀን ከአሥራ አምስት ኬክሮስ ይደርሳቸዋል ። ጸሐይን ተከትለው ሥጋዊ ምግብን ይመግባሉ ። እንዲሁም አራቱ ወንጌላውያንም ዘመኑን ከአራት ተካፍለው ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለው መንፈሳዊ ምግብን ይመግባሉና ።

4ኛ/ በአራቱ ወቅቶች ይመሰላሉ ፤ እነዚህም ጸደይ ፣ ክረምት ፣ መጸው ፣ ሐጋይ (በጋ) ተብለው ይጠራሉ ።

- <u>ጸደይ</u> ፣ የዘር ወቅት ነው ። ማቴዎስ በዚህ ይመሰላል ። ምክንያቱም የዘርን ምሣሌ ከሁሉ ይልቅ አምልቶ አስፍቶ አብዝቶ ጽፏልና ።
- <u>ክረምት</u> ፣ የውሃ ወር ነው ። ማርቆስ በዚህ በወርሃ ክረምት ይመሰላል ። ምክንያቱም ወንጌሉን በጌታችን በኢየሱስ ጥምቀት ይጀምራል ።
- <u>መጸው</u> ፣ የነፋስ ወር ነው ። ወንጌላዊው ሉቃስ በዚህ ወቅት ይመሰላል ። ምክንያቱም በነፋስ አምሳል መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ተናግሯልና ። እንዲሁም እመቤታችንን "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል " እያለ ጽፏልና ።
- <u>ሐጋይ (በጋ)</u> ፣ ይህ ወቅት መሬትዋ እሳት ላይ እንደተጣደ ብረት ምጣድ የምታቃጥልበት ወቅት ነው ። እንዲሁም ርጥበት የሌለበት ደረቅ ወር ነው ። በአጭሩ ወርሃ እሳት ነው ማለት እንችላለን ። በዚህ ወር ዮሐንስ ወንጌላዊ ይመሰላል ። ምክንያቱም መስተጻርር መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል በመጀመሪያ ቃል ነበር ፣ . . . እያለ ጽፏልና ።

አራቱ ወንጌላውያን ተመሳሳይና መንፈሱ የማይቃረን ቃል ጽፈዋል ። የመጀመሪያው ወንጌል የማቴዎስ ወንጌል ሲሆን አንዳንድ የታሪክ ምሁራን (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ማለቴ ነው ) ፣ ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው በኢትዮጵያ ውስጥ ነው ይላሉ ። ምን ያህል እውነት እንደሆነ ግን አላውቅም ። የማቴዎስ ወንጌል 28 ምዕራፎች አሉት ። ከሌሎቹ ወንጌላውያን አስፍቶ አምልቶ ነው የጻፈው ።

ሁለተኛው ሉቃስ ነው ፣ እርሱም የጻፈው ሃያ አራት ምዕራፎችን ነው። ሶስተኛው ዮሐንስ ነው ፣ የዮሐንስ ወንጌል ከሌሎቹ ለየት የሚልበት እንደሌሎቹ በሥነ ፍጥረት ፣ በትውልድ ሐረግ ፣ በጥምቀት ሳይሆን የሚጀምረው ፣ እጅግ ለሰው አዕምሮ በሚከብደው በረቀቀው በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ነው ። እንዲሁም ከሌሎቹ ለየት ባለ ሁኔታ የአካላዊ ቃልን በቅድምና መኖር የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በደንብ አብራርቶ ይገልጻል ። በዚህም ምክንያት ዮሐንስ ታዖጎሎስ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶታል ። ይህም ነባቢ መለኮት ፣ የመለኮትን ነገር የሚናገር ማለት ነው ። ዮሐንስ ወንጌላዊ እንዳልሞተና በብሔረ ሕያዋን ከነሄኖክና ከነኤልያስ ጋር እንዳለ ይነገራል ። አራተኛውና ከሌሎቹ ወንጌላውያን አነስ ያለ ምዕራፍ የጻፈው ማርቆስ ነው ፣ አሥራ ስድስት ምዕራፎችን ነው የጻፈው ።

<u>ስለሌሎች የሐዲስ ኪዳን ጸሕፍት ፤</u>

<u>ጳውሎስ</u> ፣ የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ቅዱስ ጳውሎስ ከብንያም ነገድ እንደሆነና ዳሩ ግን ዜግነቱ ሮማዊ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው እውነታ ነው ፤ ጳውሎስ ለአይሁዳውያን ወገኖቹ ትውልዱ አይሁዳዊ መሆኑን ሲገልጽ (እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ በዚህች ከተማ በገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ ፣ የአባቶችንም ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ ፣ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ) የሐዋ. ሥራ 22፥3—5 ። እንዲሁም ደግሞ በዜግነት ሮማዊ መሆኑን ሲገልጽ “ . . . የሮሜን ሰው ያለፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን ? ” የመቶ አለቃውም በሰማ ጊዜ ወደሻለቃው ቀርቦ ፣ ይህ ሰው ሮማዊ ነውና ታደርገው ዘንድ ካለህ ተጠበቅ ብሎ ነገረው ፣ ሻለቃውም ቀርቦ “ አንተ ሮማዊ ነህን ? ንገረኝ አለው ፣ እርሱም አዎን አለው ” የሻለቃውም መልስ ፣ እኔ ይህን ዜግነት በብዙ ገንዘብ አገኘሁት አለ ። ጳውሎስም እኔ ግን በእርስዋ ተወለድሁ አለ ። ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ ። ሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ ፣ አሳስሮት ነበርና ።

ጳውሎስ የመጀመሪያ ስሙ ሳውል ነበር ፤ በመጀመሪያ ለኦሪት እምነት ቀናኢ የነበረ ሰው ስለነበረ ከአይሁዶች ጋር ሆኖ ክርስቶስን ያሰቃየ ፣ እንዲያውም ጌታን በእርግጫ ሲመታው ጌታም ወደኋላው ዘወር ብሎ “ ሳውል መመለስህ ሳይቀር ለምን ትረግጠኛለህ ? ” ቢለው ፣ ለኦሪት እምነት ቀናኢ ነበረና እንዴት ደፍረህ እኔን እንደዚህ ትለኛለህ ? ብሎ ተጨማሪ ጅራፍ አስገርፎታል ። እንዲሁም ከጌታ



ሞትና እርገት በኋላ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ለስብከት በተሰማሩበት ወቅት የክርስቶስ ወገኖች የሆኑትን ሁሉ በዋሉበት አላስውል ፣ ባደሩበት አላሳድር አለ ። ክርስቲያኖችንም ከገጸ ምድር ለማጥፋት ከሊቃነ ካህናቱ ዘንድ የፈቃድ ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ኢየሩሣሌም ሲሄድ ሳለ ፣ ደማስቆ በተባለችው ቦታ ላይ ድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በዙሪያው አንጸባረቀ ፣ የብርሃን ጐርፍ በዙሪያው ጐረፈ ። ጳውሎስም ደንግጦ ወደቀ ። “ ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ ፣ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ላንተ ይብስብሃል ” አለው ጌታ ፣ ጳውሎስም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አመነ ፤ ከዚያ በኋላ ምርጥ ዕቃነቱን በተግባር አስመሰከረ ።

ቅዱስ ጳውሎስ የጻፋቸው መንፈሣዊ መልዕክቶች አሥራ አራት ናቸው ። በመጨረሻ በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት የሰይፍ ክረባት በአንገቱ ላይ ያሰረ ታላቅ የሃይማኖት አባት ነው ።

<u>ቅዱስ ጴጥሮስ ፤</u>

የዮና ልጅ ስምኦን ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር አሣ ከሚያጠምድበት ከባሕር ዳር እንደተጠራና “ በወንጌል መረብነት ሰውን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ ” ብሎ ጌታ እንዳስከተላቸው ማቴዎስ ጽፎታል ። ማቴ. 4 ፥ 18—21 ። ቅዱስ ጴጥሮስ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በቂሣርያ የመሰከረና በጌታም ዘንድ ብፁዕ ነህ ተብሎ የተመሰገነ ነው ። እርሱም እንደ ጳውሎስ በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት ነበር በሮም አደባባይ የቁልቁሊት የተሰቀለው ። ቅዱስ ጴጥሮስ ሁለት መልዕክታትን ጽፏል ።

<u>ያዕቆብና ይሁድ ፤</u>

ወንድማማቾች ሲሆኑ ፣ የእመቤታችን አገልጋይ የነበረው ዮሴፍ ከሟች ሚስቱ የወለዳቸው ልጆቹ ሲሆኑ ፣ ሁለቱም አንዳንድ መልዕክታት ጽፈዋል ።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ብዛት ፤</u>

ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት ሰማንያ አንድ መሆኑን ትናገራለች ። ዳሩ ግን በዓለም ላይ በብዛት ተሰራጭቶ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ስልሣ ስድስት ነው ። በስልሣ ስድስቱ ውስጥ የሌሉት መጻሕፍት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

<u>ክ ብ ሉ ይ ፤</u>

1. መጽሐፈ ሄኖክ
2. መጽሐፈ ኩፋሌ
3. መጽሐፈ ሲራክ
4. መጽሐፈ ዕዝራ ቀዳማዊ
5. መጽሐፈ ዮዲት
6. መጽሐፈ ጦቢት
7. ጥበበ ሰሎሞን ።

## ከሐዲስ ኪዳን

1. ትዕዛዝ ሲኖዶስ
2. ግጽው ሲኖዶስ
3. አብጥሊስ ሲኖዶስ
4. ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ
5. መጽ. ኪዳን ቀዳማዊ
6. መጽ. ኪዳን ካልዕ
7. ቀለሜንጦስ
8. ዲዲስቅሊያ

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ሳታጓድል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትቀበላለች ። አንዳንዶች ዘመን አመጣሽ እምነቶች ግን ከስልሳ ስድስቱ ውጭ ሌላ የለም ሲሉ ይሰማሉ ፣ ለዚህም የሚጠቅሱት የዮሐንስ ራዕይ መጨረሻው ላይ ያለውን ቃል ነው " ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል ፣ ማንም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጐድል በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጐድልበታል " ። ራእይ 22 ፥ 18

ይህን አባባል በጥሞና ስናጤነው የዮሐንስ ራዕይን ብቻ የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን ። በዚህ በትንቢት መጽሐፍ አለ እንጂ ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውጭ አላለም ። ይግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ከመነሻው እንደዚሁ አንድ ላይ እንደተጠረዘ ሆኖ የተገኘ አይደለም ። ጸሕፍቱ በተለያየ ዘመን የነበሩ እንደሆኑ ሁሉ መጻሕፍቱም በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ ናቸው ። በተለያዩ ቦታዎችም ነበሩ ። እንግዲህ በአንድ ሰው እንደተጻፉና በአንድ ወቅት ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተጽፈው አልቀው በጥራዝ መልክ እንደወጡ አድርጎ በመውሰድ የዮሐንስ ራዕይን ማጠቃለያ ለሁሉም መጻሕፍት አድርጎ መውሰድ አለማወቅ ወይንም ተንኮል ነው ።

ይህ ቃል የተጠቀሰበት የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ። ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ያስፋፉት በቀላል እንዳልነበር ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም ። በተለይ የሮም ነገሥታት በቤተ ክርስቲያን ላይ ያልመዘዙት ሰይፍ ፣ ያላሳረፉት የመከራ ዱላ አልነበረም ። በዘመነ ሰማዕታት ክርስቲያኖች እንደ ሽንኩርት ሲቀረደዱ ቅዱሳን መጻሕፍትም የእሳት እዳኝ ተደርገው ነበር ። በዚህ ወቅት ክርስቲያን ሲሞት ክርስቲያን ይተካል ፣ መመሪያቸው የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ከጠፋ ግን የኋለኞቹ ክርስቲያኖች መመሪያ ያጣሉ በማለት በዋሻ በፍርኩታ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን መደበቅ ጀመሩ ። ክርስቲያኖች መከራውን አሳልፈው በእግዚአብሔር ኃይል ሰላም በሰፈነበት ወቅት የተቀበሩ መጻሕፍትን ከየቦታው ማውጣት ጀመሩ ። ዳሩ ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሁሉም ሲገኙ የዮሐንስ ራዕይ ግን ይጠፋል ። በዚህ አዝነው ሳለ ዮሐንስ አፈወርቅ በግዞት ባለ ጊዜ ስለዚህ መጽሐፍ መቃ



ጠል ያዝን ነበርና መንፈስ ቅዱስ ዮሐንስ ሐዋርያ ፍጥሞ በተባለችው ደሴት ያየውን ራዕይ አንድም ሳያስቀር ይገልጽለትና ይጽፋል ። በመዝጊያውም ላይ ዮሐንስ ማስጠንቀቂያ አስፈረበት ። ይኸውም ማስጠንቀቂያ " ዮሐንስ ወንጌላዊ የጻፈው ላይ እንደዚህ የሚል ነበረበት ዮሐንስ አፈወርቅ በጻፈው ላይ ግን ይሄ የለበትም ፣ ወይም ደግሞ ዮሐንስ ወንጌላዊው ባየው ራዕይ ላይ ይሄ አልተጻፈም ፣ በማለት ሌሎች ሰዎች በዚህ የራዕይ መጽሐፍ ላይ የራሣቸውን ሐሣብ እንዳይጨምሩና እንደዚሁም እንዳይቀንሱ ተብሎ የተጻፈ የማስጠንቀቂያ ቃል ነው ። ምክንያቱም ለዮሐንስ ወንጌላዊ ያሳየው መንፈስ ቅዱስ ለዮሐንስ አፈወርቅም ምንም ሳያስቀር ሳይጨምር ሳይቀንስ ዳግመኛ እንዳሳየው ገልጾለታልና ።

እውነታው ይሄ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ወገኖች ግን ከላይ በዮሐንስ ራዕይ ላይ የሰፈረውን ተገን በማድረግ ድርሣናትና ታምራትን ፣ ገድላትን ሲነቅፉ ይታያሉ ። እነዚህ መጻሕፍት ሃሣባቸውና እምነታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልወጣ አንድ አይነት ሃሣብና እምነትን የሚገልጹ እንጂ ባእድ አምልኮትን የሚሰብኩ አይደለም ። ወንጌል የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖራችሁ የሚሳናችሁ ነገር የለም ብላ የተናገረችውን ቃል እነዚህ መጻሕፍት ተግባራዊነቱን በታሪክ አስደግፈው የሚያቀርቡ ናቸው ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት " የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል " 2ኛ ጢሞቴዎስ 3 ፥ 16—17 ።

እንግዲህ ድርሣናትም ሆኑ ገድላት ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት፣ ታላቅነት የሚገልጹ ስለሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው መሆናቸው የተረጋገጠ ነው ። ጳውሎስ ስልሣ ስድስቱን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ተጠቀም አላለም ። ገደብ ሳያደርግ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው በቅዱሳን አባቶችም ሆነ በሌሎቹ ክርስቲያኖች የተጻፉትንም መንፈሳዊ መጻሕፍት አለ እንጂ ።

ወንጌላዊው ዮሐንስም በምዕ. 20 ፥ 30 ላይ " ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ በሌላ መጻሕፍት የተጻፉ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት ማድረጉን ገልጾአል ። " ጌታ ያደረገው ሥራ ተጽፎ እንደማያልቅ አሁንም ይኸው የጌታ ሐዋርያ የሆነው ዮሐንስ ሲገልጽ " ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ ፣ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል " ዮሐ. 21 ፥ 25 ።

ደርሶ አዋቂ ነን ባዮች ታዲያ የጌታን የታምራቱን ሥራ ገድበው ከዚህ ውጭ ያደረገው የለም ሲሉ ትንሽ አያፍሩም ? የጌታ የ33 ዓመት ከ3 ወር መዋዕለ ዜና በአራቱ ወንጌላውያን ብቻ ተጽፎ የተካተተው ነው ቢሉን ማንም አያምናቸውም ። እንኳን የታላቁ አምላክ የክርስቶስ ታሪክ ቀርቶ የአንድ ተራ ንጉሥ ታሪክ እንኳን ብዙ ሸልፍም መጻሕፍት ይወጣዋል ።

ከስልሣ ስድስቱ ውጭ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ የለም እንዳይሉ አሁንም ሌላ ማስረጃ እነሱ አምነው የተቀበሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርባቸዋል ። በይሁዳ መልዕክት 1 ፥ 14—15 " የሄኖክን ትንቢት ይሁዳ ከመጽሐፈ ሄኖክ ጠቅሶ " ጽፎታል መጽሐፈ ሄኖክ ደግሞ በስልሣ ስድስቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። እንግዲህ ያልተጻፈውን ከልቡናው አንቅቶ ሄኖክ እንዲህ ብሎ ተናገረ ብሎ ዋሸ ? አይደለም ፤ በእውነት መሠከረ እንጂ ። ይህንንም በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ የምናገኘው ነው ። መጽሐፈ ሄኖክ 1 ፥ 9 ።

ለዚያውስ እነሱ የተለያዩ የሞት ፍልስፍና የያዙ መጻሕፍትን እየጻፉ አንብቡ እያሉ ይበትኑስ የለ ? ታዲያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ መጽሐፍ አታንብቡ ካሉ እነሱ ለምን ሌላ መጽሐፍ እየጻፉ ያሰራጫሉ ? ወይስ ትንቢቱ ለኦርቶዶክሳውያን ብቻ ነው የተነገረው ? ይሄ ለማጭበርበር ነውና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸውን መጻሕፍት መርምረን እውነተኛ ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትን የያዙ ከሆነ አንብበን ልንረዳና ልንመራባቸው ተፈቅዶልናል ። ሌላም ማስረጃ መጥቀስ እንችላለን ። በማቴዎስ ወንጌል 27 ፥ 9 ያን ጊዜ የነቢዩ የኤርሚያስ ቃል ተፈጸመ እንዲህ ያለው " የእስራኤል ልጆች የተስማሙበትን የከበርን ዋጋ ሠላሳውን ብር ወሰዱ " ይህን ቃል የምናገኘው በስድሳ ስድስቱ ውስጥ ሳይሆን በተረፈ ኤርሚያስ 7 ፥ 2—4 ባለው ላይ ነው ።

እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ሐዋርያት ያስተምሩ የነበሩት ከ46ቱ የብሉያት መጽሐፍ እየጠቀሱ እንደነበር ነው ።



# ምዕራፍ ፫

## ምሥጢረ ሥላሴ 1

የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚክዱ ጥቂቶች ሣይሆኑ ብዙዎች ናቸው ። እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ፤ ሦስት ሲሆን አንድ ነው ። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያስረዳናል ።

— ዘፍ. 1 ፥ 26 " እግዚአብሔርም አለ ፤ ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌያችን እንፍጠር " እግዚአብሔርም አለ ብሎ አንድነቱን ፤ ሰውን በመልካችን ብሎ ብዛትን ይገልጻል ። አንዳንዶች ይህን አባባል በሌላ ሲተረጉሙት ይስተዋላሉ ። አባባሉ ብዛትን የሚያመለክት ሳይሆን እንደ ነገሥታት ልማድ እግዚአብሔር ራሱን ለማክበር ብሎ በብዙ ቁጥር ተጠቀመ ይላሉ ። ይህ ግን ውሸት መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ይረጋገጣል ። ባመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሥታት ራሣቸውን እኛ ብለው ወይም በብዛት ጠርተው አይናገሩም ።

ፈርዖን ዮሴፍን " በግብጽ ምድር ኹሉ ላይ ሾምኩህ " አለው እንጂ ሾምነህ አላለውም ዘፍ. 41 ፥ 41 ።

ናቡከደነፆር " የሕልሙን ፍቺ እንዲያስታውቁኝ የባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ወደ እኔ ይገቡ ዘንድ አዘዝሁ" አለ እንጂ ወደ እኛ ይገቡ ዘንድ አዘዝን አላለም ፤ ዳን. 4 ፥ 6 ።

— ዘፍ. 3 ፥ 22 " እነሆ አዳም መልካምና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ " ከእኛ የሚለውና እንደ አንዱ የሚለው እግዚአብሔር ከአንድ በላይ እንደሆነ የሚጠቁሙን አባባሎች ናቸው ።

— ዘፍ. 11 ፥ 6—7 " ኑ አንዱ የአንዱን ቋንቋ እንዳይሰማ ቋንቋቸውን እንደባልቀው " ኑ የሚለው ቃል የሚያስረዳን አንዱ አካል ሌሎችን ሁለትና ከዚያም በላይ ሲሆን ይችላል መጥራቱን ነው ።

ይህንንም አባባል ጸረ ሥላሴ የሆኑ ክፍሎች በሌላ አይነት አባባል ይለውጡታል ። ተጣሪው እግዚአብሔር ሲሆን የተጠሩት ደግሞ መላእክት ናቸው ይላሉ። አሁንም ይሄ አባባላቸው ስሕተት መሆኑን እናረጋግጣለን ። እግዚአብሔር በባሕርይው ደካማ ሆኖ የመላእክትን እገዛ ፈልጐ ጥቅመ ስናእርን ለማፍረስ ኑ እርዱኝ ብሎ መላእክትን አይጠራም ። አጋዥ የሚፈልግ ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አይደለም ። እርሱ በራሱ ከሃሊነት ሁሉንም ማድረግ የሚችል ነው ። ስለሆነም መላእክቱን አለመሆኑ ግልጽ ነው ። ለመላእክቱ ሄዱ ይህን አድርጉ ይላል እንጂ ኑ ሄደን እንዲህ እናድርግ አይልም ፣ በባሕርይው ደካማ አይደለምና ።

— ዘፍ. 18 ፣ 1—15 በዚህ ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔር በመምሬ

የአድባር ዛፍ ሥር ለአብርሃም እንደተገለጠለት ፣ ወዲያውም ሦስት ሰዎች እንዳየ ፣ አብርሃምም ሊቀበላቸው እንደ ሄደ እንደ ደረሰም እንደ ሰገደ ቀጥሎም " በፊትህስ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆነ " ብሎ አንድነቱን መግለጹን ፣ እያይዞም ደግሞ " ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁ " ብሎ በአካል ሦስት መሆኑን ተናገረ ። እስከ መጨረሻው ድረስ ስንመለከተው አብርሃም እግዚአብሔርን በአንድነቱና በሦስትነቱ እየጠራው እናያለን ። ቀደም ባሉት ምዕራፎች ላይ ግልጽ ሆኖ ያልተጠቀሰው የእግዚአብሔር ሦስትነት በእዚህ ምዕራፍ ላይ ገሃድ ሆኗል ።

አሁንም ይህን ምዕራፍ እነዚሁ ጸረ ሥላሴ የሆኑ ክፍሎች ከምዕ. 19 ጋር በማቀራኘት ለአብርሃም የተገለጡት መላእክት ናቸው ይላሉ ። ምዕ. 18 ግን የሚለው እግዚአብሔር ተገለጠለት እንጂ መላእክት አይልም ። በእግዚአብሔር ስም ደግሞ መላእክት ሊጠሩ አይገባቸውም ። ሙሴም መላእክትና እግዚአብሔርን መለየት አቅቶት ጻፈ የሚሉ ከሆነ እርሱ ሌላ ነው ። እኛ ግን የተጻፈውን እንጂ ያልተጻፈውን ማንበብ ስላልለመደብን እግዚአብሔር ብሎ የጻፈውን ስለእግዚአብሔር እንደተነገረ ፣ መላእክት ብሎ የጻፈውን ስለ መላእክት እንደ ተጻፈ እንረዳለን ።

— ትንቢተ ኢሳይያስ 6 ፣ 1-3 " ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፣

አንዱ ቅዱስ ለአብ ፣ ሁለተኛው ቅዱስ ለወልድ ፣ ሦስተኛው ቅዱስ ለመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ልብ እንበል ። እዚ ይሄ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ለመግለጽ ሳይሆን ድግግሞሽ ነው እንዳይባል ሁለት ወይም አራት ጊዜ አላለም ፤ ወስኖ ሦስት ጊዜ እንጂ ። ይህንኑ ቃል በሌላም ቦታ እናገኘዋለን ። የዮሐንስ ራእይ 4 ፣ 8 ።



## የእግዚአብሔር አንድነት ፤

በአገዛዝ ፣ በሥልጣን ፣ ይህን ዓለም በመፍጠርና በማሳለፍ ፣ በሕልውና ፣ በመለኮት ፣ በልብ ፣ በቃል ፣ በእስትንፋስና ይህን በመሳሰሉት ሁሉ አንድ ነው ።

### ማስረጃ ፣

**በመፍጠር ፣**

መዝ. 101 ፣ 25 " አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራዎች ናቸው ።
ዘፍ. 1 ፣ 1 " እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ " እዚህ ላይ ፈጠሩ አላለም ፣ ፈጠረ እንጂ ። ኢሳይያስ 66 ፣ 1—2 ።

በልብ ፣ በቃል ፣ በእስትንፋስ ፣ መዝሙር 32 ፣ 1—6 " የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች ፣ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ።

በሥልጣን ፣ " እኔና አብ አንድ ነን " ዮሐንስ ወንጌል 10 ፣ 30

በሕልውና ፣ " እኔ በአብ እንዳለሁ ፣ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ " የዮሐ. ወንጌል 14 ፣ 10

" ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር " ዮሐንስ ወንጌል 1 ፣ 1—2 ። አብ ልባቸው ስለሆነ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ አለ፣ ከቃሉ ከወልድ ፣ ከሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አይለይም ። ወልድም ቃላቸው ስለሆነ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ አለ ፣ መንፈስ ቅዱስም ሕይወታቸው ስለሆነ በአብ በወልድ ውስጥ አለ ።

**ሦስትነት ፤**

— የስም ሦስትነት ፣ አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ማቴዎስ 28 ፣ 19።

" ሂዱና አሕዛብን በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጉአቸው "

— የግብር ሦስትነት ፣ አብ አባት ፣ ወልድ ልጅ ፣ መንፈስ ቅዱስ

ሰራጺ ። አብ ወልድን ወለደ ፣ ማለትም ከአካሉ ከባሕርይው ተገኘ ማለት ነው ። ለምሳሌ የሰው ነፍስ ልብነቷ ቃልነቷን እንደ

ሚያስገኝ ነው ። ወልድ ከአብ ተወለደ ማለት አብን አህሉ መስሎ ከአብ ተገኘ ማለት ነው ። ለምሣሌ የነፍስ ቃልነቷ ከል ብነቷ እንደተገኘ ነው ።

አብ መንፈስ ቅዱስን አሰረጸው ማለት ከአካሉ ከባሕርይው ተገኘ ማለት ነው ። ለምሣሌ የነፍስ ልብነቷ ሕይወቷን እንዳስገኘው ነው ። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሰረጸ ሲባል አብን አህሎ መስሎ ከአብ ተገኘ ማለት ነው ። ዮሐ. ወንጌል 15 ፥ 26 " እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል ። "

<u>የአካል ሦስትነት</u> ፥ አብ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፥ ፍጹም መልክ አለው ፥ ወልድም የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው ፥ መንፈስ ቅዱስም የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፥ ፍጹም መልክ አለው። ይሄም የአካል ሦስትነት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ነው ፥ ማቴ. 3 ፥ 16—17 ።

" ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃ ወጣ ፥ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ ታየ ፥ እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ " ሥላሴ በአካል ሦስት መሆናቸው በዮርዳኖስ በጥምቀት ጊዜ ታይቷል ። ወልድ በተለየ አካሉ ተጠማቂ ሆኖ ፥ መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ በእርግብ አም ሳል ፥ አብ በደመና ውስጥ ሆኖ የምወደው ልጄ በማለቱ ሦስቱ አካላት በአንድ ጊዜ ታዩ ። በዚህም የተነሣ ሰባልዮሳውያን እንደሚሉት አንዱ እግዚአብሔር በተለያየ ዘመናት ራሱን እየቀያየረ ማለትም በዘመነ ብሉይ አብ ተባለ ፥ ከድንግል ማርያም ሲወለድ ወልድ ተባለ ፥ በጰራቅሊጦስ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ተባለ የሚለው አባባላቸው ትክክል አለ መሆኑን ያስገነዝበናል ።

<u>የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በሰው ምሳሌነት ፤</u>

ለሰው በነፍሱ ሦስትነት አለው ። ይኸውም ልብነት ፥ ቃልነት ፥ ሕይወትነት ነው ። የሰው ነፍስ በልብነቷ የአብ ምሣሌ ናት ፥ በቃል ነቷ የወልድ ፥ በሕይወትነቷ የመንፈስ ቅዱስ ። የነፍስ ልብነቷ ቃልነቷንና ሕይወትነቷን ከራሷ ታስገኛለች ፥ ቃልና ሕይወት (እስትንፋስ) ከአንዲት ከልብ ስለተገኙ ግን በከዊን ልዩ እንደሆኑ በመነገርም ይለያሉ ። ቃል ተወለደ ይባላል ፥ እስትንፋስ ሠረጸ (ወጣ) ይባላል ። እንደዚሁ አብ ወልድን በቃል አምሣል ወለደ ፥ መንፈስ ቅዱስን በእስት



ንፋስ አምሣል አሰረጸው ፤ ነፍስ ስትገኝ በሦስትነቷ በአንድ ጊዜ ተገኘች እንጂ ልብነቷ ቀድሞ ቃልነቷና እስትንፋስነቷ በኋላ አልተገኙም።

እንደዚሁም አብ ወልድን ሲወልደው መንፈስ ቅዱስን ሲያሠርጸው አይቀድማቸውም ። ሰው በነፍስ በእዚህ አኳኋን የሚመስለው ስለሆነ እግዚአብሔር " ሰውን እንፍጠር በመልካችን እንደምሣሌያችን " ብሎ ተናገረ ። ነገር ግን ነፍስ ልብ ቃል እስትንፋስ በመሆን የከዊን ሦስትነት ቢኖራት ነፍስ በአካል አንድ ናት እንጂ ሦስት አካል የላትም ። ሥላሴ ግን እንዲህ ሳይሆኑ አብ አካላዊ ልብ ነው በአካሉ ይታያል ፥ ወልድ አካላዊ ቃል ነው በአካሉ ይታያል ፥ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕይወት ነው በአካሉ ይታያል ። ሦስት አካል በመሆናቸው ከነፍስ ይለያሉ ።

የእግዚአብሔርን ሦስትነት የሚያሳዩ ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን መጥቀስ ይቻላል ።

— <u>ትን. ኢሳይያስ 48 ፥ 12-16</u> " . . . አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል " ተላኪ ወልድ እግዚአብሔር ብሎ አብን መንፈሱ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ፤ ማመልከቱ ነው ።

— <u>መዝሙር 117 (118) ፥ 16—17</u> " የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች ፥ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ ፥ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች " ሦስቴ ጊዜ የእግዚአብሔር ቀኝ ማለቱ አብ ወልድ ፥ መንፈስ ቅዱስን መጥራቱ ነው ።

— <u>ዘኍልቅ 6 ፥ 24—26</u> " እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም ፥ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም ፥ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ " እዚህ ላይ ሦስቴ ጊዜ የእግዚአብሔር ስሙ መጠራቱ ሦስትነቱን ለመግለጽ ነው ።

— <u>2ኛ ቆሮ. 13 ፥ 14</u> " የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር ፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችንም ጋር ይሁን " ብሎ ጳውሎስ የሥላሴን ስም ጠርቷል ።

— ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ በምዕ. 5 በቁ. 7 ላይ " በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስቱ ናቸው ፥ እነርሱም አብ ፥ ወልድ ፥ መንፈስ ቅድስ ናቸው " ብሏል ። ይህ ቃል በአሁኖቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ላይ ያልሠፈረ ቢሆንም ፥ በቀደሙት

የመጽሐፍ ቅዱስ አትሞች ላይ ግን የሠፈረ ነው ። የኪንግ ጀምስ ቨርዥን (የእንግሊዝኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይመልከቱ) ።

__ማጠቃለያ ፡__

1/ አብ ወልድን ስለወለደ መንፈስ ቅዱስን ስላሰረጸ አይበልጣቸውም አይቀድማቸውምም ።

2/ ሥላሴ በአካል በስም በግብር ሦስት ናቸው ።

3/ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረጸ እንጂ ከወልድ አይደለም ፡ ወልድ ቢወለድ እንጂ አይወልድም አያሠርጽም አይሰርጽምም ።

4/ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይባላል እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም ።

5. የአካላትና የኩነታት (የሁኔታዎች) ሦስትነት አንድ አይደለም ። አካላት መጠቅለልና መቀላቀል ሳይኖርባቸው በተከፍሎ በተፈልጦ በፍጹም ገጽ በፍጹም መልክ በየራሳቸው የቆሙ ሲሆኑ ኩነታት ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው በተዋሕዶ የነበሩ ያሉ የሚኖሩ ናቸው ። እነዚህም ከዊነ ልብ ከዊነ ቃል ከዊነ እስትንፋስ ናቸው ። ከዊን ሁኔታ ማለት ነው ።



# ምዕራፍ ፬

## ምሥጢረ ሥጋዌ

የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር ማለት ነው ። ብዙዎች እግዚአብሔር አዳምንና ልጆቹን ለማዳን ሰው መሆን ለምን አተጋው ? የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ ይሰማሉ ። እግዚአብሔር ሥጋን ይዋሐድ ዘንድና ሰይጣንን ድል ነስቶ ሰዎችን ነጻ ያወጣ ዘንድ ያስፈለገው ምሥጢር ፡ አዳምና ሔዋን በገነት በተድላ ደስታ ሲኖሩ ባለ ጠላት ዲያቢሎስ ቀንቶ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ ወደ እነሱ ዘንድ ቀረበ ። አዳምና ሔዋንም ሰይጣን መሆኑን ሳያውቁ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ በመጣው በምክረ ሰይጣን ተታለው ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ጣሱ ፡ ከእግዚአብሔር ልጅነትም ወጡ ፡ እግዚአብሔርም ከኤደን ገነት አስወጣቸው ። የገነትንም ዙሪያ በምትገለባበጥ በሱራፌል ሰይፍ አስጠበቃት ፤ ዘፍጥረት 3 ፥ 24 ።

አዳምና ሔዋንም ገነትን የመሰለች ቦታ ፡ እግዚአብሔርን የመሰለ ጌታ በማጣታቸውና በምንጸፈ ደይን በመውደቃቸው የተነግ ሌትተቀን በእንባ ወደ እግዚአብሔር ይምራቸው ዘንድ ይጸልዩ ይጮሁ ጀመር ። እግዚአብሔርም አዳም በበደለ እርሱ ሁለተኛው አዳም ሆኖ ስለአዳም ክሶ ከሰይጣን ባርነት ነጻ እንደሚያወጣው ቃል ገባለት ። ይህንንም የተስፋ ሥንቅ ይዞ አዳም ወደ መቃብር ወረደ ነፍሱም በሲኦል ።

የሰይጣንን ጥበብ ተወዳዳሪ በማይገኝለት ጥበቡ እግዚአብሔር ሊያፈርስ ፡ ሰይጣን አዳምና ሔዋንን እባብን መስሎ ራሱን ሰውሮ መጥቶ እንደ አሳታቸው ሁሉ እርሱም የሥጋዌን ምሥጢር ከሰይጣን ሰውሮ የወደቀውንና የተጐሳቆለውን የአዳምን ሥጋ ከሰይጣን ባርነት ነጻ ለማውጣት ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም አምላክ ፡ ፍጹም ሰው ሆነ ። ዲያቢሎስም አምላክ መሆኑን እስኪዘንጋና እስኪጠራጠር ደካማ ሆኖ ቀረበ ። ዲያቢሎስም ፍጡር መስሎት ነፍሱን በሲኦል ፡ ሥጋውን በመቃብር ሊቆራኝ በቀረበ ጊዜ አምላክ በነፋስ አውታር በእሳት ዛንጀር ወጥሮ ያዘው ። ዲያ

ቢሎስም መሸነፉን አመነ ፣ ከእሱ በላቀ ጥበብ ክርስቶስ እንዳሸነፈው ተረዳ ፣ ምርኮኞቹንም ለዳግማዊው አዳም ለኢየሱስ ክርስቶስ አስረ ከበ ።

<u>የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ፤</u>

ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው ። በኋለኛው ዘመን ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን ከድንግል ማርያም ተወለደ ። ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ ነው ፣ አማላጅ ሳይሆን ተማላጅ ነው ። የእግዚአብሔር ቃል ወልድ እኛን ለመፍጠር የተፈጠረ አይደለም ፣ እኛ በእሱ ተፈጠርን እንጂ ፣ “ በእሱ ኹሉ ተፈጠረ ” ዮሐንስ ወን. 1 ፥ 3 ።

ለእኛ መፈጠሪያ እንዲሆን ልዑሉና ኃያሉ እንደ አገልግሎት መሣሪያ ተፈጠረ ብሎ ማውራት ከደካማ አስተሳሰብ የተገኘ ነው ። ዓለምን እንደፈጠረ የታወቀ ቢሆንም ፣ ወልድ ምንጊዜም ነበረ ፣ ያል ነበረበት ጊዜ የለም ። በእርግጥ ያለ እሱ ምንም አልተፈጠረም ፣ ሁሉም በእሱ የተፈጠሩ ናቸው ። ያለ እጅ ምንም መሥራት እንደማይቻል ፣ ወልድም የአብ እጁ (ክንዱ) ነውና ። አብ በወልድ ዓለማትን ፈጠረ ሲባል በእጅ ጥልፍ እንደ መጥለፍ ፣ ስዕል እንደመሳል ማለት ነው ።

አብ የወልድ አባት ነው እንጂ ፈጣሪ አይደለም ። አባት ከሆነ ፈጣሪውም መሆን አለበት የሚሉ አሉ ፣ ተሳስተዋል ። አባትና እናታችን የእኛ ወላጆች እንጂ ፈጣሪዎች አለመሆናቸው የታወቀ ነው ።

አብን ከወልድ ፣ ወልድን ከአብ ለያይተን መናገር አይቻለንም ። የቅዱስ አቅናቴዎስን አባባል እዚህ ላይ እንጠቅሰዋለን ። የፀሐይ መኖር በጸዳሉ ፣ የእሳት መኖር በነበልባሉ እንዲታወቅ አብን ያወቅነው በወልድ ነው ። ጸዳል ከብርሃኑ እንደማይለይ ፣ ወልድ ከአብ ፣ አብ ከወልድ አይለይም ። ፀሐይና ጸዳል ሁለት ፀሐዮች እንደማይባሉ አብና ወልድም ሁለት አማልክት አይባሉም ። ለዚህም ማስረጃ “ እኔ በአብ ፣ አብም በእኔ ነው ” ብሏል ። ዮሐ. ወንጌል 14 ፥ 10 ።

ከዚህ ተላልፈን እንደ አርዮስ ወይም እንደ አሁኖቹ የይሖዋ ምስክሮች አብ ወልድን አጸናው ወይም ፈጠረው ማለት ሕይወት ሕይወትን አጸናው እንደማለቅ ነውና ወልድ ሕይወት ሊሆን አይችልም ። ዮሐንስ ወንጌል 14 ፥ 6 “ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ”

<u>ወልድ ሥጋን በመዋሃዱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አንሷልን ?</u>

በፍጹም ! ሰውን ለማዳን ሲል ሰው የሆነው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ወልድ ሰውም ቢሆን ከአምላክነቱ የጐደለበት የለም ።



ተለውጦም ሌላ አልሆነም ፣ ያው እሱው ነው እንጂ ። “ ቃል ሥጋ ሆነ ” የሚለውን በመጥቀስ ብዙዎች ራሱ ያ ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ እንጂ ከማርያም ሥጋ አልወሰደም የሚሉ መናፍቃን አሉ ። እግዚአብሔር ግን በባሕርይው ሕልፈት ውላጤ የሌለበት ስለሆነ “ እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም ” ሚልክ. 3 ፥ 6 በማለት በመለወጥ ሳይሆን በተዋሕዶ ሰው ማሆኑን ያስረዳናል ።

ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ሲሆን ፣ የነበረ ፣ ያለና የሚኖር እንጂ ሰው ሆኖ በምድር ሳለ ከአብ ዕሪና አልተለየም ፣ ተለውጦም ፍጡር ወይም አማላጅ አልሆነም ። “ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ዘለዓለም ያው ነው ” ዕብራውያን 13 ፥ 8 ።

በወንጌል የተመዘገበው ድካሙንም ኃይሉንም የገለጠበት ማንኛውም ድርጊት የራሱ <u>የሥግው ቃል</u> ነው ። ከኃጢአት በቀር የሰው የሆነውን ሁሉ የራሱ አድርጓልና ። ብዙ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያደረገው እርሱ ተራበ ተጠማ ፣ አዘነ ፣ አለቀሰ ። በጌቴሴማኒ የጸለየው በጐልጐታ መራራ ጩኸት ያሰማው ፣ እሱ የዕለት ሬሣ ወልደ መበለትን ወለተ ኢያኤሮስን የአራት ቀን ሬሳ አልዛርን ያስነሳው ራሱ ሥግው ቃል ነው ። ማቴዎስ 9 ፥ 25 ሉቃስ 7 ፥ 11—16 ፥ ዮሐ. 11 ፥ 34 ።

ይሁን እንጂ ወልድ በባሕሪው መዋቲነት (ሞት) የሚስማማው ነበር ማለት አይደለም ፤ የክርስቶስ ሞት በሥጋ መሆኑን ሐዋርያው ጴጥሮስ ተናግሮታል ። “ ክርስቶስ በሥጋ ስለእኛ መከራን ስለተቀበለ . . . ” 1ኛ ጴጥ. 4 ፥ 1 ። ስለዚህ የክርስቶስ መከራ መቀበል በመዋዕለ ሥጋዌ በተደረገው መግቦት ከሆነ እግዚአብሔር ሞተልን ብሎ መናገር አያስቸግርም ፤ መለኮት በሥጋው ሞተ ይባላል እንጂ ። የሥጋዌን ሥርዓት ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ካለው ሁኔታ ጋር ቀላቅሎ እግዚአብሔር በባሕርይው ሞተ ብሎ መናገር አይገባም ፣ ክህደትም ነው ። ሦስቱ አካላት ሞቱ እንደማለት ነውና ፣ እግዚአብሔርነት የሦስቱም አካላት ማለትም የአብ ፣ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ገንዘብ ነው ።

<u>የንስጥሮስ ትምህርት ስለኢየሱስ ክርስቶስ ፤</u>

ንስጥሮስ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በ431 ዓ. ም. የተወገዘ መናፍቅ ነው ። የንስጥሮስ ትምህርት በአጭር ሲገለጽ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ነው ፣ የማርያም ልጅ ሌላ ፣ የአብ ልጅ ሌላ ነው ይላል ። የማርያም ልጅ ለአብ ልጅ ማኅደሩ ሆነ ፣ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ አካላዊ ነው ይላል ። ይህም ማለት ሥጋ ለቃል ማኅደሩ ፣ ተሸካሚው ፣ ልብሱ ፣ መቅደሱ ነው ማለት ነው ። እንደ ንስጥሮስ አባባል ሥጋና ቃል ዳዊትና ማኅደር ፣ ሰይፍና ሰገባ መሆና

ቸው ነው ። ይህም ማለት ማኅደር ከመጽሐፍ መለየያየት እንደ ሚችል ቃልና ሥጋም የተለያዩ ማለት ነው ። ይህ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱሳን አባቶች የተወገዘ ነው ። የክርስቶስ አንድ አካል መሆንን በኋላ እናያለን ።

## የፓፓ ሊዮን ትምህርት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ

ፓፓ ሊዮንም ሆነ ተከታዮቹ ከንስጥሮሳዊ አስተሳሰብ ያልራቁ ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ የሚሉ ናቸው ። በሎጂክ (በመሠረተ እውነት) የንስጥሮስ አስተሳሰብ ከእነሱ ይልቅ እውነታነት አለው ፤ ምክንያቱም አካል ያለባሕርይ ፣ ባሕርይ ያለአካል አይገለጥምና ። ሁለት ባሕርይ ካሉ የግዴታ ሁለት አካል ማለት ነበረባቸው ። እነሱ ግን አካልን አዋሕደው አንድ ካሉ በኋላ ባሕርዩን ከፋፈሉ ። መለኮት የመለኮትነትን ሥራ ይሰራል ፣ ሥጋ የሥጋን ሥራ ይሠራል ብለው ያምናሉ ። ይሄም ከሐዋርያት ትምህርትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ መሆኑን ቀጥለን እናየዋለን ።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ተዋሕዶ በቅዱሳን አባቶች ሲተነተን ፤

ቅዱስ ቄርሎስ ስለቃልና ሥጋ ተዋሕዶ እንዲህ ይላል ። “ ቃል ሥጋ ሆነ ሲባል ቃል ተለውጦ ሥጋ ሆነ ማለት አይደለም ፤ ሥጋም ወደ አምላክነት ተለወጠ ማለት አይደለም። ” በማይመረመር የተዋሕዶ ምሥጢር የቃል ሀብት ለሥጋ ፣ የሥጋ ሀብት ለቃል ሆነ እንጂ ። ይህም ማለት የመለኮት ገንዘብ በተዋሕዶ የሥጋ ገንዘብ ፣ የሥጋ ገንዘብ በተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ሆነ ማለት ነው ። ፊተኛና መጨረሻ መባል የሚገባው ቃል ሲሆን ፣ ሥጋ ግን በተዋሕዶ የቃልን ገንዘብ የራሱ አድርጓልና ፊተኛም መጨረሻም እኔ ነኝ ሊል በቃ ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ነው ። ሁለት አካል·ሁለት ባሕርይ እንዴት እንደሆነ እንመልከት ።

<u>መለኮታዊ አካል</u> ፣ ረቂቅ ፣ የማይጨበጥ ፣ የማይዳሰስ ፣ እሳታዊ ፣ ምሉዕ የሆነ ።

<u>ሥጋዊ አካል</u> ፣ ግዙፍ ፣ ውሱን ፣ የሚዳሰስ ፣ የሚጨበጥ ።

<u>መለኮታዊ ባሕርይ</u> ፣ ፊተኛና ኋለኛ ፣ መጀመሪያና መጨረሻ ፣ ፈጣሪነት ፣ ሁሉን ነገር ማድረግ መቻል ፣ ዘለዓለማዊነት ፣ የማይሞት ፣ የማይለወጥ ፣ የማይታመም የማይራብ ፣ የማይጠማ ፣ የማይደክም ።



<u>ሥጋዊ ባሕርይ</u> ፣ መራብ ፣ መጠማት ፣ መድከም ፣ መሞት የሚስማማው ።

እንግዲህ ወልድ የአዳምን ልጅ ከሰይጣን ባርነት ሊያድን ሲመጣ ቃል ከሥጋ ጋር ተዋሐደ ማለት መለኮታዊ አካልና ሥጋዊ አካል ተዋሐዱ ፤ መለኮታዊ ባሕርይና ሥጋዊ ባሕርይ ተዋሐዱ። ከእመቤታችን የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ፣ ባለመለወጥ በተዋሕዶ ማለት ነው መለኮት መለኮትነቱን ሳይለቅ ፣ ሥጋ ሥጋነቱን ሳይለቅ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ ። ለዚህም ነው ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሚባለው ።

የሥጋና የመለኮትን ተዋሕዶ ቅዱስ ቄርሎስ በብረትና በእሳት መስሎ ይናገራል ። ብረት ከእሳት ሲገባ ከእሳት ሲዋሐድ መጠኑን ቅርጹን ወርዱን ቁመቱን ሳይለቅ የእሳቱን ሀብት ወርሶ ሙሉ ሁለንተናው ፍጹም እሳት እንደሚሆን ፣ እሳቱም የእሳትነት ባሕርዩን ጠባዩን ሳይተው በብረቱ መጠን የብረቱን ቅርጽ እንደሚይዝ ኋላም አንጥረኛ በመዶሻ ሲያለዝበው በመጋዝ ሲተረትረው ፣ በብረትና በእሳት መካከል ምንም ልዩነት እንደማይታይ መለወጥ ኅድረት የሌለበት የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶም እንደዚህ ነው ። ስለዚህ አንዱን ክርስቶስን ከፍሎ ሥጋ የሥጋን ሥራ ይሠራል ፣ መለኮት የመለኮትን ሥራ ይሠራል ማለት የተሳሳተ ትምህርት ነው ።

## ሥጋ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ መሆኑን የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ፤

— <u>ትንቢተ ዳንኤል 7 ፥ 13</u> “ በሌሊት ራእይ አየሁ ፣ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ ፣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ፣ ወደ ፊቱም አቀረቡት ። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ። ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው ፣ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው ” ። ሥልጣን ያለው ፣ የአምላክነት ሥልጣን ማለት ነው ። ይሄ የተነገረው ለመለኮት ብቻ ነው እንዳንል የሰው ልጅ ብሎ ገልጾልናል ፤ እንግዲህ ትስብእት (ሰውነት) በተዋሕዶ አምላክ አይሆንም ከተባለ ፣ ሕዝብና ነገድ ልሳናት ያመልኩታል ተብሎ እንዴት ተጻፈለት ?

— <u>መዝሙር 2 ፥ 7</u> “ እግዚአብሔርም አለኝ ፣ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ” እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ አንድ ልጁን ከእመቤታችን የሚዋሐደውን ሥጋ በአካል ፣ በባሕርይ ፣ በፈቃድ

አንድ እንደሆነ አስቀድሞ ያውቃልና እኛን ለማስረዳት ዛሬ
ወለድኩህ ብሎ መሰከረለት ።

— መዝሙር 47 ፥ 5 " እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ አረገ ፥ ዘምሩ
ለአምላካችን ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ " ሐዋርያት ሲያ
ርግ ያዩት አምላክ የሆነ ሰውን መሆኑን ዳዊት ገለጸልን ። ያለበ
ለዚያማ እግዚአብሔር ብሎ ባልጠራው ነበረ ።

— ዮሐንስ ወንጌል 9 ፥ 35 " . . . አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታም
ናለህን ? አለው እርሱም መልሶ ጌታ ሆይ በእርሱ አምን ዘንድ
ማን ነው ? አለ ። ኢየሱስም አይተኸዋልም ፥ ከአንተ ጋርም የሚ
ናገረው እርሱ ነው አለው " ባለቤቱ ራሱ በተዋሕዶ የለበሰው
ሥጋ አምላክ እንደሆነ ያውቃልና በደረቅ ግንባር ዓይን ለፈጠ
ረለት ዕውር የእግዚአብሔር ልጅ ማነው አምንበት ዘንድ ቢለው
ያየኸው ካንተ ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው ብሎ መሰከረ እንጂ
በእርሱ ውስጥ ያለው አላለም ። የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ነውና።

— ዮሐንስ ወንጌል 1 ፥ 14 አንድ ልጅ አንድ ክብር አንድ ገጽ አንድ
ሥራ አየን ብሎ እያስተማረ ፤ በተዋሕዶ አንድ ለሆነ ትስብእት
አንድ ልጅ ፥ አንድ ገጽ ፥ አንድ ክብር አየሁ ብሎ መሰከረ ።
ጴጥሮስም " አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ "
ብሎ መለሰ ። አንተ ያለው በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕ
ርይ ሆኖ በፊቱ ተቀምጦ የነበረ ጌታችን ኢየሱስን አይደለም ?
ማቴ. 16 ፥ 16 ።

— ኢሳይያስ 9 ፥ 6 "ሕጻን ተወልዶልናል ፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶና
ልና ፥ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ፥ ስሙም ድንቅ መካር
ኃያል አምላክ ፥ የዘለዓለም አባት ፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠ
ራል " ሕፃኑን ጌታን የዘለዓለም አባት ፥ ብርቱ አምላክ ፥ የሰላም
አለቃ ነው ያለው ሥጋ በተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ ሆኗልና መለ
ኮትና ትስብእት በባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ከሆኑ በኋላ እንኳን
በግብር በሐሳብ መለየት አይገባም ።

— ዕብራውያን 5፥7 ቅዱስ ጳውሎስ ቃል ሥጋ በተዋሐደ ጊዜ አለቀሰ
ጸለየ አለው ። ማልቀስ መጸለይ መፍራት ለሥጋ ነው እንጂ ለመ
ለኮት አይደለም ። ዳሩ ግን መለኮትና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ባሕ
ርይ ስለሆኑ ሥጋ የሚሠራውን መለኮት ፥ መለኮት የሚሠራውን
ሥጋ ይሠራል ።



— ዮሐንስ ራዕይ 1 ፥ 17 " . . . አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው
ሕያውም እኔ ነኝ ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም
ድረስ ሕያው ነኝ ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ " ሥጋ
በፊትና በኋላም መሆን አይሆንለትም ። ቅድመ ዓለም ድኅረ
ዓለም የሚኖር አምላክ ብቻ ነው ። ሞትም የሥጋ ነው እንጂ የአ
ምላክ አይደለም ። ባለቤቱ ግን ከሥጋ ጋር አንድ ባሕርይ መሆ
ኑን ያውቃልና የፊተኛውም የኋለኛውም የሞትኩትም እኔ ነኝ
ብሎ ተናገረ ።

— ዮሐንስ ወንጌል 6 ፥ 51 " ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ"
ከሰማይ የወረደ እንጀራ ማለቱ ከእመቤታችን የነሣውን ሥጋ
አይደለምን ? ወይስ ከሰማይ ሥጋውን ይዞት ወረደ ሊባል ነው ?
ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም ። ከሰማይ የወረደው
ቃል ብቻውን ነው፥ ግና በባሕርይ ተዋሕዶ ሳይቀላቀል ሳይደባለቅ
አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ እንላለን ። ያለዚያማ ከሰማይ
የወረድኩ እንጀራ እኔ ነኝ አይልም ነበር ።

## የኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆን በመጽሐፍ ቅዱስ

— 1ኛ ዮሐ. መልዕክት 1 ፥ 1 " ከመጀመሪያ ጀምሮ ነበር ያለው
ማንን ነው ? ቀዳማዊ ቃል መለኮትን አይደል? በሥጋ ዓይን እን
ዴት ይታያል ? እጅስ እንዴት ትዳስሰዋለች ? ቃል ከሥጋ ጋር
በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር ቅድመ ዓለም የነበረውን
መለኮት እንዴት አየነው ዳሰስነው አለ ? የሚታይ የሚዳሰስ
ግዙፍ የሆነ ነው እንጂ ረቂቅ የሆነ እንዴት ይታያል ? እንዴትስ
ይዳሰሳል? ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ
ካልሆነ ? ።

— የሐዋ. ሥራ 20፥28 "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ
ክርስቲያን " እግዚ አብሔር ረቂቅ መንፈስ ነው ፥ ደምም የለውም
ደም የሥጋ ነው ፥ ዳሩ ግን መለኮትና ትስብእት በማይለይ ተዋ
ሕዶ አንድ ባሕርይ ፥ አንድ አካል ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቤተ
ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን አለ ። ኢየ
ሱስ በደሙ የዋጃትን ቢል እንኳን ሁለት ባሕርይ ባዮች መግቢያ
ባገኙ ነበር ። የትስብእት ስም ነውና ብለው ፤ አሁን ግን ለይቶ
እግዚአብሔር ብሎ ነው የጠራው ። እንግዲህ ምን ይበሉ ?

— ማርቆስ 14 ፥ 61 " የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን ? አለው ።
ኢየሱስም እኔ ነኝ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማ

ይም ጳመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ ” ቀያፋ በጉባኤ መካከል የጠየቀው የተያዘውን ኢየሱስን አይደለምን ? ሁለት ባሕርይ ነው ካሉ በማናቸው ባሕርይ ነኝ አለ ? በመለኮት ባሕርይ ነው እንዳይሉ መለኮት ግዙፍ አይደለ አይያዝ ፣ አይታሰር ። ያልተያዘ ያልተጠየቀ እንዴት እኔ ነኝ ብሎ መሰከረ ? ተይዞ የተጠየቀ የሥጋ ባሕርይ ብቻ ነው ቢሉ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጁ እኔ ነኝ ብሎ እንዴት ፀሐሰት ይመሰክራል ? እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር የዚህን ምሥጢር ማንም በትክክሉ ሊመልስ አይችልም ።

— ማርቆስ 15 ፣ 37 “ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮሆ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ ፣ ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር አለ። እየው ! ተገርፎ ከመስቀል ላይ የተቸነከረውን የማርያም ልጅ መድኃኔዓለም ክርስቶስን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እንደሆነ ሲያስረዳ ? ።

— መዝሙር 21 (22) ፣ 12 - 18 “ልቤ እንደ ሰም ሆነ . . . እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ ” እየኸው ? ቃል በተዋሕዶ ለሥጋ የሆነውን ሁሉ ለራሱ ሲያደርግ? ከመስቀል ላይ የተቸነከረው ሥጋ ሲሆን ከሺህ ዘመን አስቀድሞ ቀዳማዊ ቃል በዳዊት አድሮ አንድ ባሕርይ መሆኑን ሲያስረዳን ? ።

— ዮሐንስ ራዕይ 2 ፣ 8 “ ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል . . . ” ቅድመ ዓለም የነበረ ድኅረ ዓለም የሚኖር እግዚአብሔር ብቻ ነው እንጂ ለሰው አይቻለውም ። እግዚአብሔር እንዳይሞት እናውቃለን ፣ ባለቤቱ ግን ሙቼ ነበርኩ እነሆም ሕያው ነኝ አለ ። በሰውነቴ ባሕርይ ሙቼ ነበርኩ አላለም ። መለኮት በሥጋው ሞተ እንጂ ። እንግዲህ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር ቅድመ ዓለም የነበረና ሞቶ የተነሣ መሆኑን ባልገለጸ ነበረ ። ቅድመ ዓለም የነበረው እንዱ እሱ ነው ፣ ሙቼም ነበር ያለው ቅድመ ዓለም የነበረው ድኅረ ዓለም ዓለምን አሳልፎ የሚኖር የሞተው ሌላ አይደለም ፣ ሥጋ የሆነ ቃል እንጂ ።

— ፊልጵስዩስ 2 ፣ 6 “ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ እግዚአብሔርነትን እንደመቀማት አልቆጠረውም ፣ የባሪያን መልክ ይዞ መጣ” እያሉ ቅዱስ ጳውሎስ አዋሕዶ አምላክ ስለሆነ በእግዚአብሔር መልክ ነበር አለ ።



— ሮሜ 5 ፣ 10 “ ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን . . . ” በመስቀል ላይ የተሰቀለው ኢየሱስ የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው ብሎ መሰከረ ። የማርያም ልጅ ሌላ ፣ የአብ ልጅ ሌላ ቢሆን ኖሮ ወይም የተሰቀለው ሥጋዊ ባሕርይ ብቻ ቢሆን ኖሮ በልጁ ሞት . . . ብሎ ባልተናገረ ነበር ። ቅዱስ ጳውሎስ ግን መከፈል በሌለበትና አንድ በሆነው በእሱ ላይ የማይገባ ፀያፍ ነገር መናገር እንደማይገባ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን መሰከረ ።

— ማቴዎስ 3 ፣ 17 “ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ ” እንግዲህ ራሱ አብ ከእመቤታችን የተወለደውን መድኃኒታችን ኢየሱስን ልጄ ነው ሲል ። በኢየሱስ ውስጥ አድሮ ያለው ቢል ኖሮ ንስጥሮሳውያን መግቢያ ባገኙ ነበር ።አብ ግን ሥጋና መለኮትን አንድ አድርጐ አዋሕዶ ነው የምወደው ልጄ ብሎ የመሰከረው ። ታዲያ የማርያም ልጅ ሌላ ፣ የአብ ልጅ ሌላ ነው የሚል ትምህርት ከየት መጣ ? ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ነው ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ልደት ከበረ ፣ ከሁለት አካል አንድ አካል ፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ የምትለው ።

— ዮሐንስ ወንጌል 15፣ 24 “ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል ” አይሁድ ያዩት ሥጋን ነው ፣ ረቂቁን መለኮት አላዩም ። ባለቤቱ ግን ስንኳን እኔን አባቴን አይተውጠሉ አለ ። ሥጋ ከቃል ጋር በባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ስለሆነ እኔን ያየ አብን ፈጽሞ አየ ፣ እኔን የጠላ አብን ፈጽሞ ጠላ አለ ። አለዚያ አንድ ባሕርይ አንልም ካሉ አይሁድ ያዩት ሥጋን ነው እንጂ ቀዳማዊ ቃልን አላዩም ። እንግዲህ ለምን ተኰነኑ ይሏቸዋል ? ባላዩ እንዴት ይኮነናሉ ? ጌታስ ሳያዩት አይተው ጠሉኝ እንዴት አለ ? በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር ? ።

— ዮሐንስ ወንጌል 17 ፣ 24 “ አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ . . . ” የተናገረው ኢየሱስ ነው ። ስለራሱ ተናገረ እንጂ ስለ ሌላ አልተናገረም ። ከቀዳማዊ ቃል ጋር በባሕርይ በፈቃድ አንድ ካልሆነ በቀር እንዴት አብን ደፈረና ዓለም ሳይፈጠር ወደኸኛል አለው ? ሳይኖርስ ወደደውና ነው ? ያልኖረስ እንዴት ይወደዳል ? ወይስ ሳይኖር ኖርኩ አለ ?

— ዮሐንስ ወንጌል 3 ፥ 14 “ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ

እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል ” በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ኢየሱስን የሥጋ ባሕርይ ነው የሚሉት ከእግዚአብሔር ከባሕርይ ልጁ ጋር በባሕርይ በፈቃድ አንድ ካልሆነ እንዴት በርሱ የሚያምን ሁሉ አይጠፋም የዘለዓለም ሕይወት ትሆንለታለች ይላል ? የሰው ደም ከኃጢአት ያነጻልን ? በፍጹም ! ልዑል እግዚአብሔር በትንቢተ ኤርምያስ ምዕ. 17 ፥ 15 ላይ “በሰው የሚታመን ሰው ርጉም ነው” ይላል ።

— ዮሐንስ ወንጌል 3 ፥ 16 “ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም

ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና ” በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ የሰውን ልጅ በደሙ የዋጀው የማርያም ልጅ ኢየሱስ አይደለምን ? ከቃል ጋር በተዋሕዶ አንድ ልጅ አንድ ባሕርይ ካልሆነ አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ለምን አለ ?

— ዮሐንስ ራዕይ 5 ፥ 12 “ የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ፥

ጥበብም ፥ ብርታትም ፥ ክብርም ፥ ምሥጋናም ፥ በረከትም ሊቀበል ይገባዋል ” የታረደው በግ የተባለ ከእኛ ሥጋና ደም የሆነ ሰው ነው ፤ ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም በሕቱም ድንግልና ተፀንሶ በሕቱም ድንግልና የተወለደው ነው ፤ ቅድመ ዓለም ካለውና ከነበረው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ካልሆነ ይህ ሁሉ ክብርና ልዕልና እንዴት ተሰጠው ? ትስብእት በተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ ባሕርይ ካልሆነ እንዴት ይሀ ሁሉ ልዕልና ( ለመለኮት ብቻ የሚቀርብ ) ምሥጋና ቀረበለት ?

እስከ አሁን የዘረዘርናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆን የሚያረጋግጡ ናቸው

— ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው

የይሖዋ ምስክሮች ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ስም ሊጠራ አይገባውም ፥ እርሱ ሁሉን የሚችል አምላክ አይደለም፥ እንዲያውም ኢየሱስ ክርስቶስ ሚካኤል የሚባለው የመጀመሪያ መልአክ ነው ይላሉ ። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የመላእክት ፈጣሪ



“ መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ” ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ነው። ዕብ.1፥ 7 ፥ መልአክ አለመሆኑንም ጳውሎስ ሲናገር “ ከመላእክትስ አንተ ልጄ ነህ ዛሬ ወልጄሃለሁ ” ያለው ከቶ ለማን ነው ? በማለት ክርስቶስ መልአክ አለመሆኑን ያስረዳናል ። የክርስቶስን እግዚአብሔርነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያቀርበዋል ።

— ኢሳይያስ 45 ፥20—24 “. . . ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፥

እኔ ድንቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ ከእኔም በቀር ማንም የለም፥ እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ እኔ አምላክ ነኝና ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ ” በዚህ ቦታ ላይ እግዚአብሔር ከእርሱ ሌላ አምላክ እንደ ሌለ መድሃኒትም እሱ መሆኑን ገልጾአል። ይህን የመሰለ ሌላም ጥቅስ እንጨምር።

— ትን. ሆሴዕ 13 ፥ 4 “እኔ ግን ከግብጽ ምድር ጀምሬ አምላክህ

እግዚአብሔር ነኝ ፥ ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም ፥ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም ” አሁንም ከእሱ ከእግዚአብሔር በስተቀር አምላክና መድኃኒት እንደሌለ በማይታበል ቃሉ ነግሮናል ። አሁንም ሌላ ይህን የመሰለ እንጥቀስ ።

— ቲቶ 1 ፥ 3 “ መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ ” እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው ለሰው ሁሉ መድኃኒት ሊሆን የሚችል እግዚአብሕሔር ብቻ መሆኑ ተገልጿል፤የሚከተሉትን ጥቅሶች ከላይኛዎቹ ጋር እናነጻጽራቸው ።

— ቲቶ 2 ፥ 12 — 13 “ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁንና የአምላካችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ”ለጌታችን ክብር ምሥጋና ይግባውና ፥ ጳውሎስ ለቲቶ የክርስቶስን አምላክነትና መድኃኒትነት ገለጸለት ። እንግዲህ ክርስቶስ ፍጡር ከሆነና እግዚአብሔር ካልሆነ እንዴት አምላክ መድኃኒት ሊባል ቻለ ? እግዚአብሔር በሆሴዕ “እኔ ብቻ አምላክና መድኃኒት ነኝ” ብሏል ፥ የባሕርይ አምላክ እርሱ ብቻ ነውና ። ጻድቃን አማልክት ቢባሉም በፀጋ ነው ፥ የክርስቶስ አምላክነት ግን የባሕርይ ነው ።

— የሐዋ.ሥራ 4 ፥12 “መዳን በሌላ በማንም የለም፥እንድንበት ዘንድ

የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ”

— <u>ሉቃስ 2 ፥ 11</u> “ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስ ቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል ።

— <u>ዮሐንስ ወን. 4 ፥ 42</u> “ . . . እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን ” የኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነቱ ከታመነ እግዚአብሔር መሆኑ መታመኑ ግዴታ ነው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ሌላ መድኃኒት የለምና ያ በዘመን ብሉይ ከእኔ በቀር አምላክ መድኃኒት የለም ያለው እግዚአብሔር በኋለኛው ዘመን ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወለደ ፥ አምላክ ሰው ሆነ ። ሌሎች ማስረጃዎችም እና ቅርብ ፥

— <u>ኢሳ. 9 ፥ 6</u> “ ሕጻን ተወልዶልናል ፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ፥ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ” ኃያል አምላክ ፥ የዘለዓለም አባት ፥ የሰላም አለቃ ፥ እነኚህ ኃይለ ቃላት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚነገሩ ናቸው ። ጌታም እግዚአ ብሔር ስለሆነ ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተባለ ። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማስረዳት ይቻላል ። “ ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን ፥ አንድ አምላክስ የፈ ጠረን አይደለምን ? ” ሚልክያስ 2 ፥ 10 አምን ሥላሴ በባሕርይ በአገዛዝ ፥ በመፍጠር አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ ፈጠረን ይባ ላል ። ጌታ የዘለዓለም አባት ከሆነ ሚልክያስ የመሰከረለት አንዱ አባታችን እርሱ ነው ።

— <u>ዮሐንስ ራዕይ 1 ፥ 8</u> “ ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል ” ፥ “ እግ ዚአብሔር ሙሴን ያለና የሚኖር እኔ ነኝ አለው ” ዘፀአት 3 ፥ 14 ፥ በዮሐንስ ራዕይ ላይ የተጠቀሰው ለጌታ ነው ፤ ያለውና የነ በረው እግዚአብሔር መሆኑ በዘፀ. 3 ፥ 14 ላይ ደግሞ የተጠ ቀሰ ነው። እንግዲህ ይሖዋ ማለት ክርስቶስ ነው ። ምክንያቱም ይሖዋ ማለት ያለ የነበረ የሚኖር ማለት ነውና ።

— <u>የዮሐ. ራዕይ 22 ፥ 12</u> “ እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ ። አል ፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ ” ይህን ያለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይህን



ከኢሳይያስ የምስክርነት ቃል ጋር እናዛምደው “እነሆ ጌታ እግዚ ዚአብሔር እንደ ኃይል ይመጣል ፥ ክንዱም ስለእርሱ ይገዛል ፥ እነሆ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙ በፊቱ ነው ” ኢሳ. 40 ፥ 10 ለፍርድ የሚመጣው ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረ ነው ። ኢሳይያስ ጌታን እግዚአብሔር ብሎ እንደጠራው ልብ አልክ ? ጌታም ዋጋ ሰጪ መሆኑን ተናግሯል ። ኢሳይያስም ዋጋው ከእርሱ ጋር ነው ብሎ ተናገረ ።

— <u>የሐዋ. ሥራ 1፥9</u> “ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ፥ ደመናም ከአይናቸው ሰውራ ተቀበለችው ” ሐዋርያት እያዩት በመርቀቅ ሳይሆን በመራቅ ያረገው ጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስ ነው ። ዳዊት እንዲህ ብሏል “ አምላክ በእልልታ እግዚአብ ሔር በመለከት ድምጽ አረገ ” መዝ. 46 (47) ፥ 5 ። እንግዲህ ያረገው አብ አይደለም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ፥ ታዲያ እግዚአብሔር ካልሆነ ዳዊት እግዚአብሔር ብሎ ለምን ጠራው ?

— <u>የሐዋ. ሥራ 1 ፥ 11</u> “የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታ ችሁ ስለምን ቆማችሁ ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየ ሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁም ይመጣል ” መ ጪው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን መላእክትም መስክረዋል ። ዳዊት ደግሞ “ ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል” መዝ. 49 (50) ፥ 2 ብሎ የሚመጣው ኢየሱስ ክር ስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠራው ። መቼ በዳዊት ብቻ ይቆ ማል ፥ ዘካርያስም “ አምላኬ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል ” ትን. ዘካ. 14 ፥ 5 ብሎ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል ። ጳውሎስ ደግሞ የዘካርያስን ምሥክርነት ይዞ “ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ሲመጣ ” 1ኛ ተሰሎንቄ 3 ፥ 12 ብሎ መስክሯል ።

የአምላክን ሰው መሆን በሚገባ ያልተረዱ ብዙዎች ጌታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስን በፍጡር ደረጃና በትንሽ አምላክነት ፥ ሲላቸው ከአብ አሳንሰው በአማላጅነት ሲጠሩት ይሰማሉ ። ለዚሁም ሰይጣናዊ ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድ ርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን ጥቅ ሶቻቸውን አውጥተናቸው ለስሕተታዊ ትርጉማቸውም እርቶ ዶክሳዊ የሆነ ምላሽ ተሰጥቶአቸዋል ።

1/ <u>ማቴ. 12፥32</u> “ በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል ፥ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚና

ገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባ ልለትም ”

መልስ መናፍቃን እንደሚሉት ጌታን የበደለ በደሉ ይቅር ይባ ልለታል ፣ አብና መንፈስ ቅዱስን ግን የበደለ ለዘለዓለም እዳ ኛዳ ይሆንበታል ለማለትና ጌታን ዝቅ ለማድረግ አይደለም ። በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባል ለታል ማለቱ ተሳስቦ ሰው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢ የሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ሳይረዳ ባለማወቅ ሩቅ ብእሲ ( ፍጡር ) ተራ ሰው ብሎ ቢናገርና ኋላ የጌታን የባሕርይ አምላክነት ተረድቶ ቢጸጸት ለኃጢአቱ ሥርየት ይኖረዋል። ም ክንያቱም ጌታ ሰውን ለማዳን ሲል ባሕርዩን ዝቅ አድርጐ በትሕ ትና ሰው የሚሠራውን ሥራ ከኃጢአት በስተቀር ሠርቷልና ለተ ሳሳቢው ምክንያት ይኖረዋል ። ነገር ግን በሥጋ እግዚአብሔር እንደመጣ መምህራን ነግረውት ፣ ወንጌልን አንብቦ እየተረዳ ጌታን ፍጡር ወይም አማላጅ ቢል ፣ ኃጢአቱ በዚህች ምድርም ሆነ በላይኛው አይሠረይለትም ለማለት ነው ። ምክንያቱም በባ ሕርይ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው ።

2/ ማቴ. 27 ፥ 46 “ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ”

መልስ ፣ ጥሬ ቃሉን ብቻ በመመልከት ብዙዎች በዚህ ቃል ሊሰ ናከሉ ይችላሉ ። ዳሩ ግን ቃሉ ለተዋሕዶ ልጆች የሚያሰናክል አይደለም ። “ ከኃይለኛ ሰው ቤት ገብቶ ገንዘቡን የሚዘርፍ ሰው አስቀድሞ እጁን ይዞ ካሠረው በኋላ ከቤት ገብቶ ገንዘቡን ይዘርፋል እንጂ አስቀድሞ እጁን ካልያዘውና ካላሠረው ከቤቱ ሊገባና ሊዘርፍ አይችልም ” ብሎ ጌታ በማቴዎስ 12 ፥ 29 በተ ናገረው መሠረት ዲያብሎስን አሥሮ ሲኦልን ሊበረብር ባለ ጊዜ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ “ አምላኬ አምላኬ ለምን ተው ኸኝ ” የሚል ቃል አሰማው ። ዲያብሎስም ይህን ሲናገር በሰማ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ ( ፍጡር ) መስሎት በሌሎች እንደለመደው ( ከዚህ በፊት ሰይጣን ነፍስን ከሥጋ ይለይ ነበር ) ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ሥጋውን በመቃብር ፣ ነፍሱን በሲኦል ሊቆራኝ ቀረበ ። በዚህ ጊዜ ጌታ ምሥጢረ መለኮቱን ብልጭ ቢያደርግ ለት መላእክት በመስቀል ዙሪያ ወድቀው “ ለከ ኃይል ለከ ጽንዕ ” ትርጓሜው ኃይል ይገባሃል ፣ ጽንዕ ይገባሃል ፣ እያሉ ሲያመሰግኑት አይቶ ፈራ ደነገጠ ። ከዚያም ሾልኬ አመልጣ ለሁ ብሎ ቢቃጣ በነፋስ አውታር በእሳት ዛንጅር አሠረው ።



በዚህ ጊዜ እንዲህ ሲል ተባጠረ ። “ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ድል የነሳኝ ምእመናንን የነጠቀኝ ይህ ማነው ? እንደ ኃጢአ ተኛ በመስቀል ተሰቅሎ ያለ ኃጢአት ሞቶ የወደድኩትን እን ዳላደርግ የከለከለኝ ፣ ልቀርበው የማይቻለኝ ይህ ማነው ? የተሰ ጠኝን ነፍሳት ሁሉ ወደ ክብር ወደ ልዕልና ይወስዳል እንጂ በአ ገሬ እርግጥ በእጄ ጭብጥ አድርጌ ይዣቸው በነበረ በነፍሳት ላይ እንዳልሰለጥን ያደረገኝ ይህ ማነው ? ለካስ እኔ ሳላውቀው ነው እንጂ ኢየሱስ ሰማያዊ ኖሯልና ። ወይኔ ጠፋሁ በለልኩ ከአ ንግዲህ ወዲህ በእርሱ ካመኑ ሰዎች በማንም ላይ ክፉ ማድረግ አይቻለኝም ፣ ማንንም ለመንካት ሥልጣን የለኝም “ ብሎ ፈጽ ሞ ድል መሆኑን መሰከረ ። ከዚህ በኋላ ጌታ ነቢያት የተናገሩት ነገር እኔም ሰው የሆንኩባት ምሥጢር እንዲህ ዲያብሎስን ለማሠር ነው ሲል እነሆ ሁሉ ተፈጸመ ብሎ ክብርት ነፍሱን ከክብርት ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለየ ( ዮሐ. 19 ፥ 30 — 31 ) በአካለ ነፍስም ከአዳም እስከ እርሱ ድረስ ያሉ ነፍሳት ታስረው ተግዘው ወደነበሩበት ወደ ሲኦል ወረደ ፣ ጭንዛንን (ነጻነትን) ሰበከላቸው ፣ ከቁራኝነት አስለቀቃቸው ፣ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ወደ ገነት መለሳቸው ፣ 1ኛ ጴጥሮስ 3 ፥ 20 ። ይህንን ያደረገበት ምክንያት ሰይጣን አዳምና ሔዋንን ያሳሳታቸው በእባብ ሥጋ ተሰውሮ ( እባብን መስሎ ) ነበር ። ጌታ ደግሞ የሰይጣንን ብልሃት በብልሃቱ ሲሽር የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ጭዱም ደካማ መስሎ ነው ።

3/ ዕብ. 5 ፥ 7 “ እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደ ሚችል ከብርቱ ጩኸት ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ”

መልስ እግዚአብሔር ሰው የሆነበት ጠቅላላ አስተያየት በምክረ ሰይጣን ተታሎ በኃጢአት ተጐሳቁሎ ኃይሉ ደክሞ ጸሎቱ የማ ይሰማ ሆኖ ተፈርዶበት በመንፀፈ ደይን ወድቆ በአገረ አጋንንት ተጠቅጥቆ የነበረ የአዳምን ሥጋ ለብሶ በበደለው በደል ሁሉ እሱ ካሣ ሆኖ የረከሰውን ቀድሶ ያረጀውን አድሶ የቀደመ ልጅ ነቱንና ሃይሉን መልሶ ፀሎቱን ተሰሚ መስዋዕቱን ጉዳይ ፈጻሚ አድርጐ ተዋግቶ ድል እንዲነሳና እንዲፈረድበት አደረገው ፤ ከማኅበረ መላዕክት ጨመረው ማለት እንጂ መናፍቃን እንደ ሚሉት ሰው ከመሆኑም አስቀድሞ ከትንሣኤውም በኋላ እንደ ቅዱሳን ማማለድ የለበትም ። ተሰሚነት ያጣውን የአዳምን ፀሎት ተሰሚነት እንዲኖረው ለማድረግ ብቻ ነው ። በክርስቶስ ካሣ ይህን ሁሉ ሥልጣን ካገኘ በኋላ ያ ተዋርዶ በመንፀፈ ደይን

ወድቆ ጽድቃችን እንደመርገም ጨርቅ ሆኖ ይል የነበረው ሰው ጸሎቱ ተሰሚ መሥዋእቱ ጉዳይ ፈጻሚ ስለሆነለት " እኛ በክርስቶስ ፋንታ ክርስቶስን መስለን እንደ ክርስቶስ እንለምናለን፣ እግዚአብሔርም በእኛ ስብከት ልጅነትን በእኛ ፀሎት ተድላ መንግሥተ ሰማይን ይሰጣችኋል" ለማለት ቢቃ 2ኛ ቆር. 5፥20 በክርስቶስ አምሳል እንፀልያለን ብሎ በቃል የተናገረውንም በገቢር ሲገልጸው ጌታ የ38 ዘመን በሽተኛ የነበረውን መጻጉዕ "ተነሳ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ " ብሎ እንደፈወሰው ዮሐ. 5፥8 ጴጥሮስንና ዮሐንስም ከእናቱ ማኅፀን ልምሾ ሆኖ ተወልዶ በመከራ ሥጋ ወድቆ ምጽዋት ሲለምን ይኖር የነበረውን ሰው " ወርቅና ብር የለኝም ያለኝንስ ልስጥህ እነሆ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ ሂድ " ብሎ አሥነሥቶታል የሐዋ. ሥራ 3፥1-12 ጌታ አልዓዛርን እንደ አስነሳ ዮሐ. 11፥41-45 ጴጥሮስም ጸሎቱን ለእግዚአብሔር አቅርቦ " ጣቢታ ተነሽ " ብሎ የሞተችቱን አስነሳ የሐዋ. ሥራ 9፥36-41 ክርስቶስ በመስቀል ለሰቀሉት ለአይሁድ " አባቴ ባለማወቅ ይሠሩታልና ይቅር በላቸው " ብሎ እንደጸለየላቸው ሉቃስ 23፥34 ከሐዋርያትም አንዱ እስጢፋኖስ በደንጊያ ለሚወግሩት ሰዎች " አቤቱ ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ዕዳ በደል አትበልባቸው ብሎ ጸለየላቸው " የሐዋ. ሥራ 7፥60 ።

4/ ማቴ. 24፥36 "ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም " ይህን በመጥቀስ ጌታ የሚመጣበትን ቀን አያውቅም ስለዚህ ሁሉን የሚያውቅ ሁሉን የሚችል አምላክ አይደለም የሚሉ መናፍቃን አሉ ። ነገር ግን ዮሐንስ በራእይ 1፥8 " ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ በማለት ሁሉን የሚችል ከእሱ በላይ ማንም የሌለ መሆኑን ይናገራል ። በተጨማሪም ጌታ በማቴዎስ 24፥1 — 55 ባለው ላይ የምጽአቱን ዋዜማ እንዴት እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ተናግሯል ። ከእዚህ የምንረዳው ቢኖር የሚመጣበትን ቀን ማወቁን ነው ። ታዲያ ስለምን ልጅም ቢሆን አያውቅም አለ ?

ሀ. ቀኒቱን ከአዳም ልጆችና ከመላእክት ሲለያት ነው እንጂ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ሲለይ አይደለም ፣ የሰው ልጅ ብሎ የአዳምን ልጆች ይጠራልና ።

ለ. እንዲሁም ወልድ ቅድመ ተዋሕዶ አላዋቂ የነበረ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ለማስረዳት በእውነት ጌታ የሰውን ባሕርይ ባሕርይው



ማድረጉን ሊያስረዳን ፈልጐ ነው ። እንዲህ ሲባል ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ አላአዋቂ ነው ማለት አይደለም ። ከመለኮት ጋር አንድ አካል ፣ አንድ ባሕርይ ከመሆኑ በፊት ያለውን ሲናገር ነው እንጂ ።

ሐ. አንድም አብ ለልጁ በመስጠት አውቋታል ወልድ ግን በሥራ አላወቃትም ፣ ይህም ማለት ጊዜው እስኪደርስ በልቤ አኖራታለሁ ፣ በኋላ ግን በቃልነቴ እናገራታለሁ ሲል ነው ። አብ ልብ ፣ ወልድ ቃል ፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነውና ፣ በቃልነቱ በሥራ የሚገልጽበትን ሲናገር ነው ።

መ. አንድም ወልድ ብቻ ያለ አብ አያውቃትም ሲል ነው ። ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ አያውቃትም በባሕርይ በማወቅ አንድ ናቸውና ። ንባቡ " ወልድም ቢሆን ያለ አብ ብቻውን " ስለሚል ነው ።

5/ ዮሐንስ ወንጌል 14፥28 " ከእኔ አብ ይበልጣል " ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ አብ ከወልድ ይበልጣል የሚሉ አሉ ። ምሥጢሩ ግን የሚከተለው ነው ፣ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን በመዋሃዱ መከራን የሚቀበል መሆኑን ሲገልጽ ነው ። በዚህም ወልድ ( ኢየሱስ ክርስቶስ ) መከራውን ሁሉ ስለሰው ልጅ ፍቅር ሲል ተቀበለ ። የማይሞተው ሞተ ፣ ሰውን ከወደቀበት ለማንሳት ከጉስቁልናው ለማውጣት ወደ ቀድሞ ክብሩ ለመመለስ ልዑል ባህርይ አምላክ ራሱን አዋርዶ ሥጋን ተዋህዶ መከራን ተቀበለ ። ይህንንም ሲያደርግ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ይኸውም የእግዚአብሔር መልኩ ነው ፣ ቀምቶ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ እንጂ ሰውንም መሰለ ። ፊልጵስዮስ 2፥6—7 ። እንግዲህ ጌታ ስለሰው ፍቅር ባደረገው የትሕትና ሥራ እንኳን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ፣ ከመላእክትም አንሶ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ። " ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነሰው . . . " ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን . . . ዕብራ. 2፥7 — 9 እንግዲህ ጥሬ ቃሉን ይዘን ጌታ ከመላእክት ያንሳል ብለን ልንናገር እንደፍራለን ? ሐዋርያው ግን ስለ እኛ ያደረገውን ዕፁብ ድንቅ ሥራውን ፣ ፍቅሩንና ትህትናውን ሲገልጽ ፣ መላእክትን እንዳይሞቱ አድርጎ የፈጠረ አምላክ እሱ ግን ሞተ ብሎ ታላቅ ፍቅሩንና ሰው መውደዱን ገለጸ ፤ ወዶ ፈቅዶ በአትሕቶ ርእስ መገለጹን ሲያስረዳን ነውና ። ስለዚህ አብና መንፈስ ቅዱስ በተለየ

አካላቸው ሥጋን ተዋሕዶው መከራን ባለመቀበላቸው ስለሰው ልጆች ፍቅር ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በሕልውና ሳይለይ መከራንና ውርደትን በመቀበል በትሕትና በገዛ ፈቃዱ ዝቅ ማለቱን ቢገልጽልን ጊዜ መናፍቃን ልዑሉን ኃያሉን ደካማ አደረጉት ፤ እንደ አርዮስም ከባሕርይ አባቱ ለይተው ፍጡር አሉት ፤ እሱስ ክብር ምስጋና የሚገባው የባሕርይ አምላክ ነው ።

6/ <u>ዮሐንስ ወንጌል 17 ፥ 3</u> " . . . እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነህ አንተን የላከኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁት ዘንድ ይህች የዘለዓለም ሕይወት ናት " የሚለውን በመጥቀስ ጌታ እውነተኛ አምላክ እንዳልሆነ አብ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ የሚያስተምሩ መናፍቃን አሉ ፤ አባባሉ ግን እነሱ እንደሚሉት ሳይሆን " የዘለዓለም ሕይወት የሚገኝበት ሃይማኖት ይህች ናት ። አንተ የባሕርይ አምላክ እንደሆንክ ፤ እኔም የባሕርይ አምላክ እንደሆንኩ ያውቁ ዘንድ ቢያውቁ እውነተኛ ሃይማኖት ይህች ናት " ጌታ በአንዳንድ ቦታ ላይ አምላክ ወይም እግዚአብሔር ብሎ እንደ ሰው መፀለዩ በእውነት የሰውን ባሕርይ ባሕርዩው ማድረጉን ሊያስረዳን ፈልጐ ነው እንጂ በባሕርዩ ከአብ የሚያንስ ሆኖ አይደለም ። እንደ ሰው አምላኬ ወይም እግዚአብሔር ብሎ ባይፀልይ ኖሮ በእርሱ ዘንድ ትስብእት ( ሰውነት ) የለም ወይም መለኮት ትስብእትን ውጦ አጥፍቶታል በተባለ ነበር ።

ይኸውም በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ " ለአጽድቆተ ትስብእት " ተብሎ ይተረጐማል ። ይህም ማለት በእውነት አምላክ ሰው እንደሆነ ያስረዳልና ።

በዮሐንስ ወንጌል 17፥3 አብ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ተገልጿል ። በይሁዳ መልዕክት 1፥25 ላይ ወልድ ብቸኛ አምላክ ነው ተብሏል። በማቴ. 12 ፥32 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ስድብ ብቻ ምሕረት እንደማይደረግለት ተገልጿል ። የዚህም ምክንያት ሦስት አማልክት አሉ ለማለት ሳይሆን በመለኮታዊ ሥልጣን ሥላሴ አንድ ስለሆኑ ነው ። የጌታን እውነተኛ አምላክነትም ዮሐንስ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ገልጿል ። " እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው " 1ኛ ዮሐ. መል. 5፥20 ።

7/ <u>ዮሐንስ ወንጌል 20፥17</u> " ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ፤ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ " ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን በተረጐመበት ሃይማኖተ አበው ገጽ 248 ተመልከት ።



" ነገር ግን እርሱ በዚህ ክርስቶስ በእውነት ሰው እንደሆነ አስረዳ ፤ ዳግመኛም በተነሣ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መሆኑን አስረዳ ፤ ፈጽሞ ከእርሱ ወደ አልተለየው ወደ አብም ከማረጉ አስቀድሞ ለደቀመዛሙርቱ አምላኬ አምላካችሁ አለ ፤ ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላቸው ሰው የሆነ እርሱ እግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ አባቴ ብሎ ከዚህ በኋላ አምላኬ አለ እንጂ ፤ እኔ ሰው የሆንኩ አምላክ ነኝና እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል " ። እንግዲህ ሊቁ እንደ ገለጸው ጌታ ከትንሣኤው በኋላ አምላኬ ማለቱ ቅድመ ተዋሕዶ አምላኬ ይል የነበረን ሥጋ አሁንም እንደተዋሐደ ለማስረዳት ብሎ ነው ፤ ሥጋ ከመቃብር ቀረ የሚሉ በኋላ ዘመን እንደሚነሱ ያውቃልና እነርሱን መልስ ለማሳጣትና ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት አለመኖሩን ራሱ ጌታ በዚህ ቃል አስረዳን ።

በሌላ በኩልም " አባቴ " ያለው ለእርሱ የባሕርይ አባቱ ስለሆነ ነው ። " ወደ አባታችሁ ሲል ለእኛ የፀጋ አባታችን እንደሆነ ለማስረዳት ነው ። " አምላኬ " አለ በሥጋ ይፈጥረዋልና ። ጌታ የፈጠረውን ሥጋ ነውና የተዋሐደው " አምላካችሁ " አለ በጥንተ ተፈጥሮ በሃዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረናልና ።

8/ <u>1ኛ ቆሮ. 15፥24 — 28</u> " በኋላም መንግሥትን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነቱንም ሁሉን ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል ። ሁሉ ነገር ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ወልድ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ተገዥ ይሆናል " ፤ " ሁሉን ላስገዛለት ተገዥ ይሆናል" የሚለውን በመጥቀስ ወልድ የአብ ተገዥ ነው ይላሉ። ነገር ግን ምሥጢሩን ከተመለከትን ከላይ ስለሞት እየተናገረ መምጣቱን እንረዳለን ። የኋላ ጠላት የተባለው ሞት ነው ። ሞት ሁሉንም ገዝቷልና ፤ ነገር ግን ሁሉን ካስገዛለት ከወልድ ሞት እንዲያንስ ይታወቃል ፤ በሁሉ ላይ እንዲሰለጥን ያደረገው ባለቤቱ ነውና ፤ ይህስ ቁም ነገር አይደለም ብሎ ካስገዛለት ከሰው ሁሉ ሞት እንዲያንስ ይታወቃል በዕለተ ምጽአት ። ሁሉ በተገዛለት ጊዜ ያን ጊዜ ወልድም ሁሉን ላስገዛለት ለሞት ተገዝቷል የዕለተ ዓርብን መናገር ነው ። በዕለት ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለይቶአልና ፤ ሞት ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት ጌታን በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ነበርና ይህም የጌታ ፈቃድ ስለሆነ ነው እንጂ እንደ ሌሎች ሳይወድ በግድ አይደለም ።

9. <u>ቆላ. 1 ፥ 15</u> "... እሱም የማይታይ እምላክ ምሳሌ ነው"

የዚህም አባባል እግዚአብሔርን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው ለማለት ነው እንጂ እያ ላከ ያልሆነ አምላክ መሰል ለማለት አይደለም ።

10/ <u>የሐዋ. ሥራ 2፥32</u> "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው..."

እግዚአብሔር ብሎ መለኮትን ለመግለጽ ተጠቀመበት እንጂ አብ ብቻውን ያለወልድና ያለመንፈስ ቅዱስ አስነሺ፥ወልድ በባሕርይ ሥልጣን ከአብ የተለየ ወይም አብ ብቻ ብርቱ ወልድ ግን ለመነሣት ሥልጣን የሌለው ደካማ ነው ለማለት አይደለም ። ጌታ ኢየሱስ በገዛ ፈቃዱ ለመሞቱና በገዛ ሥልጣኑ ለመነሣቱ በዮሐ. ወን. 10 ፥ 17—18 ይገልጸል ። "ነፍሴንም ስለበጐች እኖራለሁ እኔ በፈቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም ፥ ላኖራት ሥልጣን አለኝ ፥ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ" ቅዱስ ሉቃስ ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው ማለቱ መለኮት የተዋሐደውን ሥጋ አስነሳው ለማለት ፈልጐ መሆኑን ሲያስገነዝበን ነውና በሃሳውያን ስሕተታዊ ትርጉም ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ ብሎ ከመካድ እንጠበቅ ፥ እንጠንቀቅ ፥

ከላይ የተጠቀሰው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት እምነን ከሐሰተኞች ትምህርት እንጠበቅ ዘንድ ያስገነዝበናል ። "ክርስቶስ በሥጋ መጣ ፥ እርሱም ከሁሉም በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን" ሮሜ 9 ፥ 5 ።

<u>ማጠቃለያ</u>

1/ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ። በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ ፥ በሥጋ የአዳም ልጅ እንደሆነ እናምናለን ። ሰው ባልሆነ አካል የሰውነት ሥራ አይሠራም ሥጋን ከርሷ የነሣ ቅድስት ድንግል ማርያም ሞት የሚስማማት ስለሆነች ሞት የሚስማማውን ሥጋ ተዋሕዶአልና ። ስለዚህም የተቀበለው ልቅሶ ፥ ሕማም ፥ ሞት ከድንግል የነሣው የሥጋ ገንዘብ ነው ። አዘነ አለቀሰ ሲል ብቅሰማ ያዘነ ያለቀሰ አምላክ ቃል እንደሆነ አታስብ ይህ ሁሉ ሥጋ በመሆኑ ነው እንጂ ።

2/ ይህ ወልድ ለአንዱ የምንሰግድለት ለአንዱ የማንሰግድለት ሁለት ባሕርይ ነው የምንል አይደለም ። ሰው የሆነ የእግዚአብሔር



ቃል ባሕርይ አንድ ስለሆነ ከሥጋው ጋር አዋሕደን አንዲት ስግደት እንሰግድለታለን እንጂ ።

3/ ከእኛ በነሣው ሥጋ ሞተ በማለት ፋንታ እግዚአብሔር አምላካችን ሥጋ በሌለው ባሕርይ ታመመ ሞተ ይሉት ዘንድ አይገባም ።

4/ ክርስቶስ ፈጣሪ ፥ እግዚአብሔር መሆኑን እናምናለን ፥ ስለሆነም ፍጡር ነው የሚሉትንና ዛሬም በአብ ቀኝ ተቀምጦ ለእኛ ያማልዳል የሚሉትን እንቃወማለን ።

5/ ወልድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ሳይለይ በምልአት ሳለ ሥጋ መሆን እንደምን ነው ? ቢሉ የዓይን ብርሃን ከዓይን ብሌን ሳይለይ ከብርሃን ፀሐይ ጋር ተዋሕዶ ምሉእ እንደሆነ ጌታም በምልአተ ባሕርዩ ሳለ በማኅፀነ ድንግል አድሮ ከመቅጽበተ ዓይን ሰው ሆነ ። የማይለይ የማይነገር የማይመረመር ተዋሕዶ ሆነ ።

# ምዕራፍ ፳

## ምሥጢረ ጥምቀት

<u>የጥምቀት ትርጉም</u> – መነከር ፣ መዘፈቅ ፣ ውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ፣ መቀበር ማለት ነው

<u>ምሥጢር መባሉ</u> — ከሥላሴ ልጅነትን የምናገኝበት ስለሆነ ነው ፤ ይኸውም በአይን የማይታይ ስውር ሃብት ነው ፤ ስለዚህ ምሥጢር ተባለ ።

<u>ጥምቀት ለምን አስፈለገ ?</u> የመጀመሪያው ሰው አዳም ከትዕዛዘ እግዚአብሔር አፈንግጦ በምክረ ዲያብሎስ ተታሉዕፀ በለስን ከመብላቱ የተነሣ ሰው ሁሉ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ከፍዳና ከመርገም በታች ሆኖ ይኖር ነበር ። ስለዚህ ሰው ሁሉ ሁለተኛ ከውሃና ከመንፈስ መወለድ አስፈለገው ።

ሰው ሁሉ ሁለተኛ ከውሃና ከመንፈስ በጥምቀት ካልተወለደ በቀረ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይችልም ። ዮሐ. ወንጌል 3 ፥ 3 — 6 ።

— በክርስቶስ ክርስቲያን ፣ በወልድ ውሉድ ፣ የሚያሰኝ ጥምቀት ነው ። ይህችም ጥምቀት አንድ ክርስቶስ የሚመለከባት በአንዲት ሃይማኖት ( በአንዲት ቤተክርስቲያን ) የምትፈፀም ነች እንጂ በተለያዩ እምነቶች ውስጥ የምትገኝ አይደለችም ። ስለሆነም ጥምቀት አንዲት ስለሆነች አትደገምም ፣ አትከለስም ። ኤፌሶን 4 ፥ 5

— ክርስቲያን ለመሰኘት በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከቀኝ ጐኑ በፈሰሰው ማየ ሕይወት (የሕይወት ውሃ) ወይም (ማየ ገቦ ) ( የጐን ውሃ ) ተጠምቀን የእግዚአብሔር ልጆች መባል አለብን ። ይህን ውሃ ከዬት ታገኛላችሁ ? ቢባል ፣ ካህኑ ውሃውን በጸሎት ( በሳህን ) አድርጐ መጽሐፈ ክርስትና ይደግምበታል ፣

ሥርዓተ ቅዳሴ ያደርስበታል ። በፍጻሜው አንዱ አብ ቅዱስ ነው፤ አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው፤አንዱ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው ብሎ ይባርከዋል። ያን ጊዜ ውሃው ተለውጦ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከቀኝ ጐኑ የፈሰሰውን የገግን ውሃ ይሆናል። በዚያም ተጠምቀን ከፍዳ እንነፃለን ፤ ከዲያብሎስ ቁራኝነትም እንላቀቃለን ። ለዚህም ማስረጃ " ሰው በክርስትናው ጥምቀት ከዲያብሎስ ቁራኝነት ለርኩሳን አጋንንት ከመገዛት ፈጽሞ አርነት የወጣ ይሆናል " ብሏል ሳዊሮስ ዘእስሙናይን ።

— ጥምቀት በአሪት ጊዜም ነበር ፤ ለምሣሌ እነ ኢዮብ እነ ንዕማን በዮርዳኖስ ባህር ተጠምቀው ከደዌ ሥጋ ተፈውሰዋል ። ይሁን እንጂ ከሀዲስ ኪዳን ጥምቀት ጋር በምሥጢርም ሆነ በአፈጻጸሙ የተለየ ነው ። የብሉይ ኪዳን ጥምቀት ከሥጋ ደዌ ለመፈወስ ብቻ የሚጠቅም ነበር እንጂ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ለእርኩሣን አጋንንት ከመገዛት ፈጽሞ ሐርነት አያወጣም ነበር ። እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ጥምቀት ከሥላሴ ልጅነትን ማግኘት አይቻልም ነበር ።

## የጥምቀት መስራቹ ማን ነው ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላሣ ዘመኑ በባሕረ ዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ ዳግመኛ ይወለድ ዘንድ መጠመቅ እንዳለበት ተናገረ ። በዚህም የተነሣ የጥምቀትን ትምህርት ያስተማረው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

## ጌታ በ30 ዘመኑ ለምን ተጠመቀ ?

ጌታ ከፍ ብሎ በ40 ዓመቱ ፤ ዝቅ ብሎ በ28 ዓመቱ ያልተጠመቀበትና 30 ዓመትን ጠብቆ የተጠመቀበት ምክንያት አለው ። እንዲያው ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ነው እንጂ በ20 ሊጠመቅ ይችል ነበር የሚሉ ካሉ ፤ እንኳን በፈጣሪ ዘንድ በእኛ ዘንድ እንኳን አጋጣሚ የለም ። ሁሉም በፈቃደ እግዚአብሔር ጊዜውንና ቦታውን ጠብቆ የሚከናወን ነው ። ስለዚህ ጌታ በ30 ዘመኑ የተጠመቀበት ልዩ ምክንያት አለው ።

አዳም የ30 ዓመት ጐልማሣ ሆኖ ተፈጥሮ በ40 ቀኑ ያገኛትን የልጅነት ፀጋ በሰይጣን አሳሳችነት አስወስዶ ስለነበር ፤ ሁለተኛው አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ቀዳማዊ አዳምንና ልጆቹን ወደ ቀደመ ክብራቸው ለመመለስ ነውና አመጣጡ ፤ አዳም በ30 ዘመኑ ያስወሰዳትን ልጅነት ሊያስመልስ መምጣቱን ለማሳወቅና ልጅነትም የምትሰጠው በጥምቀት መሆኑን ለማረጋገጥ በ30 ዘመኑ በባሕር ዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ።



እዚህ ላይ ብዙዎች እሱ በ30 ዘመኑ ከተጠመቀ እኛም በ30 ዘመናችን መጠመቅ አለብን የሚል አመለካከት ያላቸው ክፍሎች አሉ ። ይኼ ደግሞ ከጌታ ጋር መፎካከራቸው መሆኑን ይመሰክርባቸዋል ። ጌታ ያደረገውን ሁሉ በትክክል መፈፀም አለብን ካሉ ጌታ 40 ቀንና 40 ሌሊት ከዘረጋ ሳያጥፍ ፤ ከቆመ ሳያርፉ በገዳም ቆሮንቶስ ያለምግብና ውሃ ጾሟዋል ። ታዲያ እነሱ ይህን ለምን አያደርጉም ? ሁለተኛ ጌታ ለሰማይ ወፎች እንኳን ማደሪያ አላቸው ለሰው ልጅ ግን ማደሪያ የለውም ብሎ ቀን ቀን ሲያስተምር ሌሊት ሌሊት በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሲፀልይ ማደሩ ለእኛ አብነት ለመሆን አይደለምን ? ለምን ይህን ተግባራዊ አያደርጉም ? ደርሶ የወንጌል አርበኛ መምሰል ፤ ቀላጆች ናቸው ። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ እንጂ ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተቆርቁረው አይደለም ። ሐዋርያት በ30 ዓመት መጠመቅ እንዳለብን ተዘንግተዋቸው ይሆን በ30 ዓመታችሁ ተጠመቁ የሚል ትምህርት ሳያስተላልፉ የቀሩት ?

ጌታ እከብር አይል ክቡር ፤ እቀደስ አይል ቅዱስ ሆኖ ሣለ ፤ ስለ ምን ተጠመቀ ? ቢሉ ፤

— አንደኛ ፤ ሦስትነቱን ለማስረዳት ነው ። ከዚያ በፊት የሥላሴ ሦስትነት ግልጽ ሆኖ አይታወቅም ነበር ። ጌታ በዮርዳኖስ በሚጠመቅበት ጊዜ ግን ምሥጢረ ሥላሴ ግልጽ ሆኖ ፤ አብ በደመና ውስጥ ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው በማለቱ የወልድ አባት መሆኑ ታወቀ ፤ መንፈስ ቅዱስም የባሕርይ ሕይወቱ መሆኑን በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ተቀምጦ ሲታይ ፤ ወልድም በተለየ አካሉ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ታየ ። እንግዲህ ሦስት አካላት አንድ መለኮት መሆኑን ሲገልጽ ሲሆን ፤

— ሁለተኛ ደግሞ ትንቢቱን ሊፈጽም ነው ፤ " አቤቱ ውሆች አይሁ ፤ ውሆችም አይተውህ ፈሩ ። ጥልቆች ተነዋወጡ ፤ ውሆችም ጮኹ ፤ ደመናዎች ድምጽን ሰጡ . . . " መዝ. 76 (77) ፥ 16 የሚል ትንቢት ነበርና ይህ እንዲፈጸም ። በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ. 36 ፥ 35 ላይም እንዲሁ ትንቢትዊ ቃል ነበር ፤ ያንንም ተግባራዊ ለማድረግ ነው ።

— ሦስተኛ ለእኛ አርአያ ሊሆነን ብሎ ነው ። እርሱ ተጠምቆ ተጠመቁ ባይለን ኖሮ ብዙዎች ጥምቀት አያስፈልግም አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ጌታ ራሱ ተጠምቆ አብነት በሆነን ነበር እንዳይሉ ነው።

## ክርስቲያኖች በ40 ቀንና በ80 ቀን የመጠመቃችን ምሥጢር ፤

ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን፤ሴቶች በተወለዱ በሰማንያ ቀን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማህፀነ ዮርዳኖስ

ይወለዱ ዘንድ ሕግ መሥርታለች ። ይህንንም ሐዋርያዊ ሕግ አንዳ
ንድ ዘመን ያፈራቸው ሐሰተኞች ክርስቶሳውያን ሲያስተባብሉ ይታ
ያሉ ። እነዚህ ክፍሎች ለሰይጣናዊ ትምህርታቸው ዋቢ አድርገው
የሚያቀርቡት “ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፥ ያላመነ ግን ይፈረድበ
ታል ” ማር. 16 ፥ 16 የሚለውን ሲሆን ፥ ይህንንም ሲተረጉሙ መጀ
መሪያ አንድ ሰው ማመን አለበት ፥ ከዚያ በኋላ እምነቱ ተቀብሎ እጠ
መቃለሁ ሲል መጠመቅ አለበት እንጂ ባላመነበት ምንም በማያ
ውቅበት በሕጻንነቱ ወራት ማጥመቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ ውጭ
ነው ይላሉ ። አቀራረባቸው የዋሃንን ቢያሳስትም መጽሐፍ ቅዱስንና
ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንን ከነሥርዓትዋ የሚያውቋትን ሰዎች ሊያ
ታልሉ አይችሉም ። እንዲት ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ ክፍሎች መጽ
ሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ትሰጣቸ
ዋለች ።

በመጀመሪያ ሕጻናት ሳያምኑ ለሚሉት አባባላቸው መጽሐፍ ቅዱ
ስን በግርድፉ አንብበውት ዐወቅን ፥ ተራቀቅን ብለው ሐዋሪያዊት
ቤተ ክርስቲያንን እናሻሽል ፥ እናርም ብለው ተነሱ እንጂ ፥ ውስጠ
ምሥጢሩን ቢያውቁ ኖሮ እንዲህ ባላሉ ነበር ። መንፈስ ቅዱስ የሚያ
ድረው በንጹህ ሰውነት በአማኝ ሰው ላይ መሆኑን እነሱም ሳያውቁት
አይቀሩም አሁን ካልካዱ በስተቀር ። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ መን
ፈስ ለሕጻናት እንደሚሰጥ ይነግረናል ። “ በሆድ ሳልሰራህ አውቄ
ሃለሁ ፥ ከማህጸንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ” ትንቢተ ኤርምያስ 1፥5።
እንግዲህ ኤርሚያስን ከእናቱ ማህጸን እግዚአብሔር የቀደሰው መሆ
ኑን አላነበቡ ይሆን ? “ በእናቱ ማህጸን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላ
በታል ” ሉቃስ 1 ፥ 15 ። መጥምቁ ዮሐንስ ገና በእናቱ ማህጸን ሳለ
በመንፈስ ቅዱስ መቃኘቱን ሉቃስ ወንጌላዊ ይነግራቸዋል ፥ ያንብ
ቡት ።

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስን ሳያምኑ ሳይማሩ ለምን አደርከባቸው
ብለው ሲከሱት ይችሉ ይሆን ? እስቲ ይሞክሩት መቼም አያፍሩ ።
ደግሞስ ይግረማቸውና እያንዳንዱ ሰው በእምነትም ሆነ በምግባሩ
ሕጻናትን መምሰል ካልቻለ መንግሥተ ሰማያትን እንደማይወርስ አያ
ውቁም? እነሱም እንኳን ቢሆኑ ተመልሰው ሕጻናትን ካልሆኑ የእግዚአ
ብሔርን መንግሥት አያዩአትም። ተንኮላቸውን፣በገንዘብ መደለላቸውን
ትተው በንጹህ ልቡና ፥ በፍጹም እምነት ወደ እግዚአብሔር ካልተ
መለሱ ወዮታ እንዳለባቸው ወንጌል ይነግራቸዋል ። ጌታ “ ሕጻናትም
ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ ፥ እንደ ህጻናት ካልሆናችሁ መንግሥተ
ሰማያት አትገቡም ” ማቴዎስ 19፥15 ማርቆስ 10፥13 ሉቃስ 18፥15 ።



ስለዚህ እንደ ሕጻናት ከሃጢ ካልሆናችሁ ማለቱ ይሆን ? ወይስ
እንደ ሕጻናት ሃይማኖት የለሾች ካልሆናችሁ ማለቱ ነው ? አይደለም፤
ሕጻናት በሁሉም ነገር ፍጹማን ናቸውና እንደ ሕጻናት ቂም በቀል አት
ያዙ ፥ ፍጹም እምነት ይኑራችሁ ማለቱ እንደሆነ አሌ የማይባል ሐቅ
ነው ።

ታዲያ እነዚህ የዘመኑ ጉዶች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንን ሳያ
ምኑ ወይም ከሆዲዎችን ነው የምታጠምቀው የሚሉት ከየት አምጥ
ተው ነው ? ሁለተኛስ የወላጆች እምነት የእነሱ አይደለምን ? ይህ
ንንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊረዱ ቢፈልጉ ወላጆች ልጆቻቸውን ይባር
ክላቸው ዘንድ ሕጻናትን ወደ ጌታ አቀረቡለት ። ጌታ ግን እናንተ አመ
ጣችኋቸው እንጂ እነሱ አምነው አልመጡምና አልባርክም አላላቸ
ውም ፥ የወላጆቻቸውን እምነት አይቶ ባረካቸው እንጂ ። ታዲያ ቅድስት
ቤተ ክርስቲያን የመሪዋን መርህ ተከትላ ወላጆች ልጆቻችንን አጥም
ቁልን ብለው በሚመጡበት ወቅት ከጌታ የተማረችውን ቅታ የእነር
ሱን የሐሰተኞች ክርስቶሳውያን ቃል ሰምታ እይ ፥ ገና አልተማሩም
አላወቁም ፥ አላመኑምና አላጠምቅም ትበል ? በፍጹም ! ቤተክርስቲ
ያን ራስዋ የሆነው ክርስቶስን ትከተላለች እንጂ እነርሱን አትከተልም
እንላቸዋለን ።

በተጨማሪም ደግሞ ሕጻናት ንጽሐ ጠባይ ሳያድፍባቸው ንጹሕ
አስተሳሰብ ፥ ንጹሕ የሆነ አእምሮ በያዙበት ወቅት ልክ እንደ አዳምና
እንደ ሔዋን ከሥላሴ ይወለዳሉ እንጂ ኃጢአት በሚሰሩበት ለኃ
ጢአት በሚገዙበት በጉርምስናቸው ወቅት ከሥላሴ በጥምቀት ይወ
ለዱ ቢባል ማን ይሆን ወደ ጥምቀት የሚቀርበው ? ዛሬ ራሱን ለክር
ስቶስ ሥጋና ደም አዘጋጅቶ ያለ ጕረምሳ ወይም ኮረዳ ስንቱ ይሆን ?
ቤተ ክርስቲያን ግን ንጽሐ ጠባይ ሳያድፍባቸው ወንዶችን በ40 ቀን
ሴቶችን በ80 ቀን በማጥመቅ ከሥላሴ እንዲወለዱ ታደርጋለች ።

ይህ ሥርዓት ቀድሞ በኦሪት ጊዜ የነበረ ነው ፥ ለዚህም ኦሪት ዘሌ
ዋውያን 12 ፥ 1 - 8 ማንበብ እችንላለን ። ሴት ብታረግዝና ወንድ ልጅ
ብትወልድ በአርባ ቀንዋ ፥ ሴት ልጅ ብታረግዝና ብትወልድ በሰማ
ንያ ቀንዋ የመንጻትዋ ወራት ሲፈጸም የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃ
ጠል መሥዋዕት የርግብም ግልገል ወይም ዋኖስ ለኃጢአት መስዋ
ዕት ወደ መገናኛ ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ትወስድ ነበር ።

ይህ ሥርዓት ወደ ሀዲስ ኪዳን ሥርዓት ተለውጦ በበግ ጠቦት
በርግብ ዋኖስ ፋንታ ልጁን ወይም ልጅቱን በመያዝና ሥርዓተ ጥም
ቀትን በመፈጸም ከሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኝ ወይም እንድታገኝ ይደ
ረጋል ። ( ከመስዋዕቱ ጋር )

ሌላው ወንዶች በ40 ቀን ሴቶች በ80 ቀን የሚጠመቁበት ምሥጢር የአዳምና የሔዋን የልደት ምሳሌ ነው ። “ በተፈጠረበት ምድር ለአዳም 40 ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባነው ፣ ሚስቱንም በሰማንያ ቀን አስገባናት ” መጽሐፈ ኩፋሌ 4 ፥ 9 — 12 ።

መላእክት አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ የባሕሪ ንጽሕና ሳያድፍበት ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዶ ወደ ገነት እንዳስገቡት ፣ እኛም ይህን ምሳሌ በማድረግ እንደ መላእክት ወላጆቻችን ፣ እንደ ገነት ቤተ ክርስቲያን ፣ እንደ አዳም ከተወለዱ አርባ ቀን የሆናቸው ወንዶች ወይም እንደ ሔዋን ከተወለዱ ሰማንያ ቀን የሆናቸው ሴቶች ይመስላሉ ። አዳምና ሔዋን በተፈጠሩ በ40 እና በ80 ቀን አግኝተዋት የነበሩአትን ልጅነት አስወስደው ስለነበር እኛም ያን ልጅነት ለማስመለስ በአርባና በሰማኒያ ቀን እንጠመቃለን ።

የዘመናችን ሐሰተኞች “ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም ” ዮሐንስ ወንጌል 3፥5 በግልጽ ራሱ ጌታ የጥምቀትን አስፈላጊነት እየገለጸ እነሱ ግን ጥምቀት ግዴታ አይደለም ፣ አንድ ሰው ባይጠመቅ ከክርስቶስ መንግሥት ውጭ ሊሆን አይችልም ይሉናል።

እኛስ የምናመልከው ክርስቶስን ስለሆነ እነሱን ለሚያመልኩ ሞኞች ይንገሩአቸው እንጂ እኛ ግን ክርስቶስ የተናገረውን በመያዝ ያለጥምቀት መዳን የለም እንላለን ። እነርሱማ ለስሕተታዊ ትምህርታቸው ድጋፍ የሆናቸው መስሎአቸው “ ያላመነ ይፈረድበታል” አለ እንጂ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል አላለም ሲሉ ይሰማሉ ። አሁንም የዋሃንን በዚህ ቃል ያታሉ እንጂ የተዋሕዶ ልጆችን ሊያታልሉ አይችሉም የተጠመቀ ከዳነ ያልተጠመቀስ ምን ይሆናል ? የሚል ጥያቄ እናቀርብላቸዋለን ። ምንም አይሆንም የሚሉ ከሆነ እንግዲያውስ የተጠመቀውም ዋጋ ቢስ ነው ማለት ነው ። የተጠመቀውም ያልተጠመቀውም የሚድን ከሆነ “ ጌታ የተጠመቀ ይድናል ” ብሎ ባልተናገረ ነበረ ። ጌታ ግን የተጠመቀ ይድናል ብሎ አላቆመም ፣ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል ብሏል ። ይህም የሚታወቀው ለኒቆዲሞስ በነገረው “ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው በጥምቀት ልጅነትን ካላገኘ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያያትም ” ያላመነኮ ነው የሚለው ፣ መች ያልተጠመቀ ይላል ? ሊሉን ይችሉ ይሆናል ። ሰው በክርስቶስ ካላመነ በክርስቶስ ስም እንዴት ሊጠመቅ ይችላል ? አንድ ሰው ካላመነ አልተጠመቀም ማለት ነው ። ስለዚህ አለማመኑ አለመጠመቁንም ይገልጽልናል ።



ሐዋርያት በመጀመሪያ የክርስቶስን ወንጌል ሲሰብኩ ብዙዎችን ያጠምቁ ነበር ። ይህን በመጥቀስ ሐዋርያት ያጠመቁት ትልልቅ ሰዎችንኮ ነው ፣ ሕጻናትን አይደለም ይላሉም ። ሕጻናትን ማጥመቅ የተጀመረው ቤተ ክርስቲያን ራሱዋን ችላ ከቆመችና ሥርዓትና ደንብ ካወጣች በኋላ ነው ። መጀመሪያማ ብዙዎች አማኞች ስላልነበሩ ሐዋርያት ባመኑ ጊዜ ያጠምቁአቸው ነበር ፣ አርጊቱንም ጐልማሳውንም ፣ ሕጻኑንም ። በኋላ ግን እነዚያ ያመኑ ሰዎች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከተደነገገ በኋላ ያንን ሥርዓት በመከተል ልጆቻቸውን በ40 ቀንና በ80 ቀን ያስጠምቁ ጀመር ።

## ጌታ በዮርዳኖስ ለምን ተጠመቀ ?

— ጌታ በዮርዳኖስ የተጠመቀው ትንቢቱንና ምሳሌውን ለመፈጸም ነው ።

ትንቢት ፡ “ ባሕር አይታ ሸሸች ፣ ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ ፣ ባሕር የሸሸሽ ምን ሆነሽ ነው ? አንተስ ዮርዳኖስ ወደ ኋላህ የተመለስሽው ምን ሆነህ ነው ? መዝሙር 113 ፥ 3-5 ይህ ትንቢት ስለነበር ጌታ ከሌሎቹ ወንዞች ሁሉ መርጦ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ።

ምሳሌው ፡ አብርሃም ከገንዘቡ ከዓሥር አንድ አውጥቶ ዓሥራቱን ይዞ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ መልከ ጼዴቅ ሲሄድ የአብርሃምን መምጣት አውቆ ኅብስተ አኰቴት ጽዋዓ በረከት አዘጋጅቶ ቆይቷል ፣ ይህም መልከ ጼዴቅ የካህናት ፣ አብርሃም የምእመናን ምሳሌ ነው ። ዮርዳኖስ የጥምቀት ፣ ኅብስተ አኰቴት የሥጋው ፣ ጽዋዓ በረከት የደሙ ምሳሌ ነው ። እንዲሁም ኢዮብና ንእማን በዮርዳኖስ ተጠምቀው ከደዌያቸው ተፈውሰዋል ፣ እናንተም ብትጠመቁ ከፍዳ ሥጋ ከፍዳ ነፍስ ትድናላችሁ ሲለን ነው ። ዮርዳኖስ አንድ ወንዝ ሲሆን ፣ ዝቅ ብሎ በዮር እና በዳኖስ ተለይተዋል ፣ ዮር በእሥራኤል በኩል ያለው ሲሆን ፣ ዳኖስ በአህዛብ ፣ ዝቅ ብሎ ደግሞ ሁለቱም ተገናኝተዋል ፤ በመገናኛው ቦታ ጌታ ተጠምቋል ።

ይህም ምሳሌ አለው ፣ ዮርዳኖስ ነቁ ( ምንጩ ) ከላይ አንድ እንደ መሆኑ የሰው ዘር ሁሉ የአንድ አዳም ልጅ እንደሆነ ሲያስረዳ ነው ። ዝቅ ብሎ መለየቱም እሥራኤል በኦሪት አህዛብ በጣኦት ወይም እሥራኤል በግዝረት አህዛብ በቁልፈት ተለያይተዋል ። ዝቅ ብሎ መገ

ናኘቱ ሁሉም በአንድ ወንጌል የምናመናቸው ምሥሌ ነው ። ጌታ በመገናኛው ቦታ መጠመቁ ሁላችሁን አንድ ላደርግ መጥቻለሁ ሲል ነው ።

ምሥጢሩ ፤ አዳምና ሔዋን ፈጣሪያቸውን አሳዝነው ከገነት ከወጡ በኋላ ዲያብሎስ በጨለማ ጋርዶ ፍዳ አጽንቶ “ አዳም የዲያብሎስ ወንድ አገልጋዩ ነው ፤ ሔዋን ደግሞ የዲያብሎስ ሴት አገልጋዩ ናት ” ብላችሁ ስመ ግብርናችሁን ጽፋችሁ ስጡኝ አላቸው ፤ እነርሱም ፍዳ የሚያቀልላቸው መስሏቸው እንዳላቸው አደረጉ ። እርሱም ( ዲያብሎስ ) ያንን የዕዳ ደብዳቤ አንዱን በሲኦል ፤ ሌላውን በዮርዳኖስ አኖረው ። ዲያብሎስ በዮርዳኖስ ያኖረውን የዕዳ ደብዳቤ ጌታ በጥምቀቱ ጊዜ ተረግጦት ስለነበር በተጠመቀበት ወቅት በጥምቀቱ አጥፍቶልናል እንዲሁም በሲኦል ያለውንም በዕለተ ዓርብ ሲኦልን አመዝብሮ ነፍሳትን ነፃ ሲያወጣ አጥፍቶታል ። ቈላስይስ 2 ፤ 13 — 5

## ጌታ ወደ ዮሐንስ ሄዶ የተጠመቀበት ምክንያት ፤

ጌታ ዮሐንስን ወደ እኔ ዘንድ መጥተህ አጥምቀኝ ሳይል እራሱ ወደ ዮሐንስ ዘንድ ሄዶ መጠመቁ ፤ አንድም ለትሕትና ሲሆን ፤ ሌላው ደግሞ ሥርዓትን ሲደነግግልን ነው ። ጌታ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ቢለው ኖሮ የዛሬ ነገሥታት ፤ መኳንንትና ታላላቅ ሰዎች ካህናትን ቤተ መንግሥታችን ወይም ቤታችን ድረስ መጥታችሁ ልጆቻችንን አጥምቁ ባሉ ነበር ። ይህን እንዳይሉ ጌታ ራሱ አርአያ ስለሆነ እነሱም አይሉም ፣ ቢሉም ቤተክርስቲያን አትቀበለውም ።

## ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው እጆቹን ሳይጭንበት ነበር ፤

የዚህ ምክንያት ፤

1ኛ/ መስዋዕተ ኦሪት አለፈ ፤ መስዋዕታችን አንተ ነህ ሲል ነው ። በኦሪት ጊዜ የላም ፤ የርግብ ፤ . . . የመሳሰሉ መስዋዕቶች ይቀርቡ ነበር ። አሁን ግን ክርስቲያኖች ለምግብ ሥጋ ብለው እንስሳትን ያርዳሉ እንጂ ለኃጢአታችን ማስተስረያ ብለው አይደለም ። የክርስቲያኖች መስዋዕት በቀራንዮ አደባባይ የተሰዋው አማናዊ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ። “ እነሆ የብዙዎችን ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ ”

2ኛ/ እጁን ቢጭንበት ኖሮ ዮሐንስ ጌታን አከበረው ብለው በኋላ ዘመን የሚነሱ ሐሰተኞች በተናገሩ ነበር ።

3ኛ/ የመለኮትን አካል መንካት አይቻለንም ሲል ነው ።



## መንፈስ ቅዱስ በአርግብ አምሳል የወረደበት ፤

— በኖህ ጊዜ ርግብ “ የጥፋት ውሃ ጎደለ ” ስትል ቆጽላ ዘይት (የወይራ ቅጠል) ይዛ መጥታለች ። አሁን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ “ የኃጢአት ባሕር ጎደለ ” ሲል በርግብ አምሳል ታየ ።

— ርግብ ቢመቷት ፤ እንቁላሏን ቢያፈርጡባት ፤ ቤቷን ካላፈረሱባት በስተቀር ቦታዋን አትለቅም ፤ መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሰሩ ፤ ጨርሰው ካልካዱት ፤ ማለትም ሰው ሕንጸ እግዚአብሔር መሆኑን ዘንግቶ በራሴ ሃግብና ምኞት የምንቀሳቀስ ፤ ፈጣሪ የሌለኝ ነኝ ብሎ ካልካደ በስተቀር ከፍጥረቱ አይለይም ።

— ርግብ የዋህ ናት ፤ ቂም በቀል አትይዝም ፤ መንፈስ ቅዱስም ሐዳጊ በቀል ( በቀልን ይቅር ባይ ) የዋህ ፤ በኃጢአት በደል ቂም የማይዝ ፤ ተጸጽተን ይቅር በለን ካልነው ይቅር የሚል ነውና ።

## ሰዎች በማን ስም ሊጠመቁ ይገባቸዋል ?

“ ሂዱና አሕዛብን በአብ ፤ በወልድ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ” ማቴ. 28 ፤ 19 የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝ መሠረት በማድረግ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ታጠምቃለች ። በክርስቶስ ስም ብቻ ማጥመቅ አለብን የሚሉ ክፍሎች አሉ ፤ እነዚህ ክፍሎች የሐዋ. ሥራ 2 ፤ 38 “ ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ በክርስቶስ ስም ተጠመቁ ” የሚለውን በመጥቀስ በክርስቶስ ስም ብቻ ልንጠመቅ ይገባል ይላሉ ። ይህ ግን ስሕተታዊ አባባል ነው ። ጴጥሮስ በክርስቶስም ስም መጠመቅ እንደሚገባቸው ጠቀሰ እንጂ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ ተጠመቁ ማለቱ አይደለም ። የኢየሱስን ስም መጥራቱ ለምስክርነቱ ነው የሐዋርያት ዓላማቸው አይሁድም ሆኑ ሌላው ሕዝብ በክርስቶስ እንዲያምን ማድረግ ስለሆነ ፤ ብዙውን ጊዜ የክርስቶስን ስም እየጠሩ ነበር ማንኛውንም ነገር የሚፈጽሙት ። ምክንያቱም አይሁድም ሆኑ መናፍቃን በክርስቶስ ላይ እንደሚነሱ በመንፈስ ቅዱስ ያውቃሉና ።

ጥምቀት ማለት ከሥላሴ መወለድ ማለት ሲሆን ከሥላሴ መወለዳችን እንዴት ይታወቃል ? ቢባል ሕጻናት ከእናት ከአባት ሲወለዱ እንደማያውቁና ወላጆች ግን እንደሚያውቁ ከሥላሴ መወለዳችንንም ሥላሴ ያውቁታል እንጂ እኛ አናውቀውም ። በመጠመቃችን ምክንያት ከምናገኘው በረከት በስተቀር ፤ ጌታ እንደ ጌትነቱ በማር በወተት ለምን አልተጠመቀም የሚል ሊኖር ይችላል ይሆናል ። ለዚህም ውሃን የመረጠበት ምክንያት ምሥጢሩን እንገልጻለን ።

1. በኖኅ ዘመን መላው ዓለም ከታች ከምድር ፥ ከላይ ከሰማይ በመፈደ ውኃ ጠፍቶ ነበር ። በዚህ የተነሣ በእያንዳንዱ ሰው ሃሣብ ውኃ ለሞት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም የሚል አመለካከት ስለነበር ለምሕረትና ለድህነትም የተፈጠረ መሆኑን ሊያረጋግጥ ጌታ በውኃ ተጠምቋል ።

2. ጌታ አምላክነቱን ጌትነቱን ለመግለጽ ብሎ በወተት በማር ጥምቀቱን ቢያደርግ ኖሮ ማርና ወተት በማንኛውም ሰው ቤት ስለማይገኝ ድህነት ለሀብታሞች ብቻ በሆነ ነበር ። ዳሩ ግን ውኃ በሁሉም ቤት ይገኛል ። ጥምቀትም ለሃብታምም ለድሃም እኩል እንዲዳረስ ብሎ ሁሉም ሰው ሊያገኘው በሚችል በውኃ አደረገው።

3. ማርና ወተት ምንም እንኳን በቀላሉ የማይገኙ ለሰው ተፈላጊ ፈሳሾች ቢሆኑም በአትክልት ላይ ቢያፈሱአቸው አትክልት ያደርቃሉ እንጂ አያለመልሙም። ውኃ ግን ያለመልማል ፥ እናንተም በውኃ ብትጠመቁ ልምላሜ ሥጋ ፥ ልምላሜ ነፍስ ታገኛላችሁ ሲል ነው ።

4. ማርና ወተት ልብስ ቢያጥቡበት እድፍ አያጠሩም ፥ ውኃ ግን ያጠራል ፥ ከኃጢአት እድፍ ከጉስቁልና ሥጋና ነፍስ በውኃ ተጠምቃችሁ ትጠራላችሁ ሲል በውኃ ተጠመቀ ፥

5. ከማርና ከወተት ይልቅ ፥ ውኃ መልክን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል እናንተም በውኃ ብትጠመቁ መልክአ ሥላሴን በመንፈስ ታያላችሁ ሲል ነው ።

6. ውኃ እሳትን ያጠፋል ፥ እናንተም በማየ ገቦ ብትጠመቁ ከገሃነመ እሳት ትድናላችሁ ሲለን ነው ።

7. ውኃ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሣል ፤ ጥምቀትም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳልና ።

<u>ማጠቃለያ ፤</u>

— በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 3 ፥ 5 እንደተጠቀሰው ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያገባል ፤ ያልተጠመቀ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ።

— በሮሜ 6 ፥ 3 ጳውሎስ እንደገለጠው ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ ያስፈልጋል ።

— ጴጥሮስም ጥምቀት እንደሚቀድስና እንደሚያነጻ ጠቅሷል ፥ 1ኛ ጴጥሮስ 3 ፥ 21 ።



— መጠመቅ ያለብን በአብ ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው ፥ ማቴዎስ ምዕ. 28 ፥ 19 ።

— ጥምቀት አትደገምም አትከለስም ፥ ኤፌሶን ምዕ. 4 ፥ 5 ።

— ሊያጠምቅ የሚገባው ስልጣነ ክህነት ያለው ሰው ብቻ እንጂ ማንኛውም ተራ ሰው በክርስቶስ አምኛለሁና ብሎ ሊያጠምቅ አይገባም ። ከቤተ ክርስቲያን ስርዓት ወጥቶ በትዕቢት ተነሳስቶ ቢያደርግ ግን እዳ ፍዳ ይሆንበታል “ ሒዱና አሕዛብን አጥምቁ ” ማቴ. ምዕ. 28 ፤ 19 የተባለው ለሐዋርያት በኋላም ጊዜ ሐዋርያትን መስለው ለሚነሱ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች እንጂ ለተራው ምእመን አይደለም ።

# ምዕራፍ ፮

## ምሥጢረ ቁርባን

ቁርባን የተለያየ ትርጉም ቢኖረውም ፣ በዚህ ክፍል የምናየው ስለ ጌታ ሥጋና ደም ነው ። ይኸውም ቀሳውስት በቅዳሴ ጊዜ የሚያቀርቡት ኅብስት የክርስቶስ ሥጋ ሲሆን ፣ ወይኑም የክርስቶስ ደም ነው ።

"ጌታ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ" ዮሐ. ወን. 6 ፥35 ባለው መሠረት ሰው ሁሉ የጌታን ሥጋና ደም ካልበላና ካልጠጣ በስተቀር ከክርስቶስ ጋር አንድነት አይኖረውም ። የዘለዓለም ሕይወትም አያገኝም። ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነው የጌታ የራሱ ቃል ነው ። "ሥጋዬን ያልበላ ፣ ደሜን ያልጠጣ የዘለዓለም ሕይወት የለውም " ዮሐ. ወን. 6 ፥ 53 — 54 ።

ይህን የሚጠራጠሩ አንዳንድ ተረፈ አይሁድ አይጠፉም ፣ ጌታ " ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ፣ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል ፣ እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው " አይሁድ እንጉራጉሩ ፣ ጌታ ግን ቃሉን ጠበቅ አድርጐ " እውነት እውነት እላችኋለሁ ፣ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ፣ ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ፣ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው " ዮሐ. ወን. 6 ፥51 - 59

እያችሁ ጌታ ራሱ እውነተኛ መብልና እውነተኛ መጠጥ ብሎ ሥጋ ወደሙ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም እንጂ ምሣሌ አለመሆኑን ሲያስረዳን ፣ አንዳንድ አሳሳቾች ግን እውነተኛ የጌታ ሥጋና የጌታ ደም ሣይሆን መታሰቢያው ነው ሲሉ ይሰማሉ ። ይህ ግን የሰይጣን ትምህርት መሆኑን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን " እውነት እላችኋለሁ ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ " ነው ያለው እንጂ ምሣሌውን አላለም ።

ለደቀ መዛሙርቱም ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ መስጠቱን ሲያስረዳ "ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ቆርሶም እንካችሁ ይህ (ኅብስቱን መሆኑን ልብ በሉ) ሥጋዬ ነው፣ (ምሳሌው ነው አላለም) በጽዋ ያለውን ደሙንም አንስቶ (ወይኑን) ስለብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው" ብሎ ሰጣቸው እንጂ (ምሳሌ ነው) አላለም። ማቴ 26፣ 26 — 29 ።

ስለዚህ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን ለሥጋ ወደሙ የሚሰጠው ክብር ከዚህ እንጻር መሆኑን ልብ እንበል ። ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት እንዴት ይሆናል ቢሉ? ቄሱ ኅብስቱን በጻሕል (በትሪ) ወይኑን በጽዋዕ አድርጐ በጸሎተ ቅዳሴ በባረከው ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል ። ይህም በእግዚአብሔር ኃይል የሚሆን ነው ።

ለመለኮት ሥጋና አጥንት የለውም ይል የለምን? ለመለኮት ምን ሥጋ አለው? ቢሉ ከንጽሕት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሥዋ ነፍስ ነሥቶ የተዋሐደው ነው ። የምንበላው ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው ሲሆን መለኮት ግን የተዋሐደው ነው ። መለኮት ከነፍስም ከሥጋም አልተለየም ። ከነፍስ ጋር ወደ ሲኦል ወርዶ ለነፍሳት ነጻነትን ነገረ ። ከሥጋ ጋር አብሮ ወደ መቃብር ወርዷል ። "በሥጋ ሞተ በመለኮት ተነሣ" 1ኛ ጴጥሮስ 3፣ 18 ማለቱ ይህን መንገሩ ነው ።

ሥጋ ወደሙ በእድሜ፣ በጾታ ሳይወሰን ለማንኛውም ክርስቲያን የተፈቀደ ነው ። ዳሩ ግን "ሽማ ሲያድፍ በውሃ፣ ሰውነት ሲያድፍ በንስሐ" እንዲሉ በንስሐ ሳሙና ታጥበን ራሳችንን ጠብቀን በመንቀጥቀጥ በመራድ የአንተን ሥጋ መቀበል የማይገባን ቢሆንም፣ ሥጋህን ካልበላንና ደምህን ካልጠጣን በስተቀር ካንተ ጋር አንድነት የለንምና በፍርሃት ቸርነትህን ተገን በማድረግ ቀርበናል ብለን በቅሕትና መሆን አለበት ። ልቦናችንን ከቂም ከበቀል ሳናነጻ ከኃጢአት ሥራ ሳንጠራ በድፍረት ብንቀበል ግን እዳ ፍዳ ይሆንብናል ። 1ኛ ቆሮ. 11፣ 28 ።

ሥጋውን ሰጥተው ደሙን የሚከለክሉ አሉ ። እነዚህ ክፍሎች ከሃይማኖት ወጥተው በምድራዊ ሥርዓት የሚጓዙ ናቸውና ትክክል አለመሆናቸውን ማወቅ ይገባናል ።

<u>ሥጋ ወደሙ በስንዴና በወይን የሆነበት ምክንያት</u>

ከእዝርእት ሁሉ ለጌታ ሥጋ ይሆን ዘንድ ስንዴ፣ ከፍራፍሬ ደግሞ ለደሙ ወይን መሆኑ ምን ምሳሌና ምሥጢር አለው ቢሉ፣



<u>ምሳሌ</u>፣ መልከ ጼዴቅ በወይን በስንዴ ይሠዋ ነበር ። ዘፍ. 14፣ 18 ዕብ. 7፣ 1 -3 ይህም የሥጋ ወደሙ ምሳሌ ነው ።

<u>ትንቢት</u>፣ "በልቤ ደስታ ጨመርኩ ከስንዴ ፍሬ ከወይን ከዘይትም በዛ" መዝ. 4፣ 6 ።

<u>ምሥጢሩ</u>፣ ስንዴ ስብ ሥጋን ይመስላል፣ ወይን ደግሞ ቅኩስ ደምን ይመስላል ። ስለዚህ በሚመስል ነገር መስጠቱ ነው

እንዲሁም ጌታና እመቤታችን በዚህች ምድር ላይ በኖሩበት ጊዜ ይመገቡ የነበሩት ስንዴ፣ ይጠጡ የነበሩት ወይን ነበር እና ጌታም እውነተኛ ሥጋውን እውነተኛ ደሙን መስጠቱን ሲገልጽልን ሥጋውና ደሙን በሥንዴና በወይን አደረገው ።

ሥጋ ወደሙን እንደ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ተቀብለን የምናቆም ሳይሆን በተደጋጋሚ የምንቀበለው ምሥጢር ነው ። ሰው ከስቻለው በየወቅቱ ቢቀበል በፀጋ ላይ ፀጋ ያስጨምር ለታል እንጂ የሚያስነቅፈው አይደለም ።

— ጥምቀት . . . . . የአባትነትና የእናትነት፣

— ሥጋ ወደሙ . . . የምግብነቱ ሲሆን ጥምቀት የማይደገምበት ምክንያት ከእናትና ከአባታችን የምንወለደው አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነው ሁሉ፣ ከሥላሴም የምንወለደው እንደዚሁ አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ ነው ። ምግብ ግን በየጊዜው በፈለግን ወቅት እንመገባለን፤ ሥጋ ወደሙንም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ልንቀበል ይገባናል ።

# ምዕራፍ ፯

## ምሥጢረ - ትንሣኤ ሙታን

<u>የትንሣኤ ሙታን ትርጉም</u> ፣ ትንሣኤ ሙታን ማለት ተለያይተው በተለያየ ሥፍራ ይኖሩ የነበሩ ነፍስና ሥጋ እንደገና ተዋሕዶ መነሣትና ከሞት በኋላ በነፍስና በሥጋ ሕይወት ማግኘት ማለት ነው ።

<u>ትንሣኤ ያለው ፍጡር ማን ነው ?</u>

ከሀያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ውስጥ መላእክት የማይሞቱ ሲሆኑ ትንሣኤ አይመለከታቸውም ፣ ከሌሎቹ ደግሞ ሰው ለየት ብሎ ከሞተ በኋላ ይነሣል ። ለሰው ትንሣኤ ያስፈለገበት ምክንያት ሰው የተፈጠረው ጥንቱንም ነፍሱና ሥጋው ሳይለያዩ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ለሞት አልነበረም " እግዚአብሔር ለሞት አላደረገንምና ለሕይወት እንጂ " 1ኛ ተሰ. 13 ፣ 16 ። ዳሩ ግን ሰው እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥፍራ ጸንቶ በላልተገኘ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ። ኋላም ንስሐ ስለ ገባ ትንሣኤ ሙታን ታወጀለት ። ስለዚህ ክፉም ሠራ ደግ ሁሉም ከሞት ይነሣሉ ። ዳንኤል እንዳለ " በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ ፣ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ፣ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና " ትን. ዳን. 12 ፣ 2 ። እንዲሁም ኢሳይያስ ጳውሎስ ሌሎቹም የትንሣኤ ሙታንን መኖር እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል ።

- <u>ትን. ኢሳ. 26 ፣ 19</u> " ሙታንም ሕያዋን ይሆናሉ ፣ ሬሣዎችም ይነሳሉ ፣ በምድር የምትኖር ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ፣ ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ "
- <u>1ኛ ተሰሎንቄ 4 ፣ 14</u> " ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና "
- <u>ዮሐ. ወን. 5 ፣ 28</u> " በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል ፣ መልካምም ያደረገ ለሕይወት ትንሣኤ ፣ ክፉም ያደረገ ለክፋ ትንሣኤ ይወጣሉና "

## ትንሣኤ ሙታን የሚሆነው መቼ ነው ?

በኋለኛው ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ሊፍርድ በሚመጣበት ወቅት ነው ። በዚያም ጊዜ የሞቱት ሰዎች ሁሉ ይነሣሉ "እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ፥ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል ፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ" ራዕይ 1 ፥ 7 እምነ ጌታ በእልፍ አእላፋት መላእክት ታጅቦ ሰማይና ምድር በመብረቅ እየታረሱ ፥ እሳት በፊቱ እየነደደ በታላቅ ግርማ ይመጣል ። የተሰቀለበትን መስቀል ይዞ ፥ የተወጋ ጎኑን እያሣየ ደሙን እያንጠፈጠፈ በዕለተ ዓርብ ስለ እኛ ሲል የተቀበለውን መከራ እያስታወሰን ይመጣል ።

ይህንንም አስፈሪና ታላቅ ቀን ልበ አምላክ ዳዊት ሲገልጽ "ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል ። ዝምም አይልም ፥ እሳት በፊቱ ይነዳል ፥ በዙሪያውም ብዙ አውሎ አለ" መዝ 49 (50) ፥ 2 - 3 ።

አወይ ስለዚያች ቀን ማሰብ ምንኛ ያስጨንቃል ፥ የሰማይ ኃይላት ሁሉ ሲንዋወጡ ሰማይና ምድር እንደብራና ተጠቅልለው ሲያልፉ፥ አበት የዚያን ቀን ! ሁላችንም በክብር ባለቤት በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንቆማለን ። ኃጥአን ያለቅሳሉ ፥ እንባቸው እንደ ክረምት ውሃ በጉንጫቸው እስኪሽቀለቀል ። ዳሩ ግን የዚያን ጊዜ ለቅሶና እንባ ከንቱ ነው ። እነሆ የማልቀሻ ፥ ወደ እግዚአብሔር የመመለሻ ወቅት ዛሬ ነው ። ኃጥአን የጌታ ቀን ሲዘገይ የማይመጣ መስሎአቸው በኃጢአት ባሕር ውስጥ ገብተው ሲዋኙ ፥ ሲሰቁ ፥ ሲቦርቁ ይኖራሉ ። ጻድቃን ደግሞ የጌታ ምጽአት ባልታሰበ ወቅት እንደሚመጣ ስለተረዱ ራሣቸውን ተቆጣጥረው ሰውነታቸውን ከኃጢአት ገትተው ተጠብቀዋልና ያን ጊዜ ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው መሪያቸው ክርስቶስን መስለው ወደተዘጋጀላቸው መንግሥት ይገባሉ ። የትንሣኤያችን በኩር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ይህ ይሆናል አይቀርም ፥ ጌታም ይመጣል ፥ የቅዱሳን ዋጋም እንዲሁ በከንቱ አይቀርም ። የኃጥአንም የሥራቸው ደመወዝ አይነፈጋቸውም ፥ ለሁሉም እንደ ሥራው ይከፍላል ። "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" ራዕይ 22 ፥ 12 ።

## የሰው እንሣስ

የሞትህ ተነሣ የሚል አዋጅ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ይታወጃል ። ሶስት ረቂቃን ነጋሪቶች አሉ ፥ ነጋሪት ሲባል ነጋሪት እንዳይመስለን የጌታ ትዕዛዝ ነው ። "ጌታ እራሱ በትእዛዝ በመላእክ



ትም አለቃ ድምጽ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና" 1ኛ ተሰሎንቄ 4 ፥ 16 ።

— የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ፥ ነፋስ የበተነው ያለቀው ፥ የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል ( ያዕቆብ ዘሥሩግ ቁ. 91 )

— ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋሕደው ሳይንቀሳቀስ ቅኩስ ሬሣ ይሆናል ፥ አጥንቶችና ጅማቶች ከሥጋና ከደም ጋራ ይያያዛሉ ። እስኪነሱ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናሉ ፥

— ሶስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቀዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጎድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈሉ ወንድ በጸቅመ አዳም የሠላሣ ዓመት ጐልማሳ ፥ ሴት በአቅመ ሔዋን የአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው በአርባ ቀን በእናቱ ማኅጸን ደም ሆኖ የወረደ ጽንስ ሳይቀር በጐም ይሁን ክፉ ሥራቸውን ይዘው ይነሣሉ ። ጌታ ራሱ በማቴዎስ ወንጌል 25 ፥ 31 — 46 ባለው ላይ እንዳጠቀሰው በጐቹን በቀኝ ፥ ፍየሎቹን በግራ ያቆማቸዋል ።

## በበግና በፍየል የተመሰሉት እነማን ናቸው ?

ጻድቃንን በበግ፥ኃጥአንን በፍየል መስሎአቸዋል። ለምን ተመሰሉ ቢባል የበጐች ተፈጥሮ ከጻድቃን ሥራ ጋራ ሲመሳሰል የፍየሎች ተፈጥሮ ደግሞ ከኃጥአን ጋር ስለሚመሳሰል ነው ። ምክንያቱም

ሀ. በጐች በደጋ እንጂ በቆላ አይኖሩም ፥ ተስማሚያቸው ደጋ ነው ። ጻድቃንም በመከራ ሥጋ እንጂ በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ከደው በምግባረ ብልሹነት አይገኙም ። ፍየሎች በቆላ እንጂ በደጋ አይኖሩም ፥ ኃጥአንም በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለወርቅ ፥ ለብር ብለው ይለውጣሉ ።

ለ. በጐች እረኛቸው ባስማራቸው ሥፍራ ጸንተው ይኖራሉ ፥ ጻድቃንም እረኛቸው ክርስቶስ ባስማራቸው በአንዲት ሃይማኖት ጸንተው ይኖራሉ ፍየሎች እረኛቸው ባስማራቸው ሥፍራ ጸንተው አይቆዩም ፥ እንዲሁ ሲባዝኑ እረኛቸውንም ያደክሙታል ። ኃጥአንም እንዲሁ በአንዲት ሃይማኖት ጸንተው አይቆዩም ። አሥሩን ሃይማኖት መስል ሁሉ እንደ ሸሚዝ ሲለዋወጡ ይታያሉ ። እንዲሁም ፈጣሪያቸው ክርስቶስ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ያለውን ትምህርት ተላልፈው በዝሙት ሕይወት ይኖራሉ ።

ሐ. በጐች ጥቂት ሣር ካገኙ ተፋቅረው አብረው ይበላሉ ፣ እርስ በእርሣቸው አይጣሉም ፣ ጻድቃንም ያለቻቸውን ያገኟዋትን ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ጋር ሆነው ተፋቅረው ይበላሉ እንጂ ምቀኝነትና ስስትም የለባቸውም ። ፍየሎች ግን እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ ሳሩ ፣ ቅጠሉ ሞልቶ ለሁላቸውም ሲበቃ ሳለ ፣ ከስስታቸው የተነሣ ሲዋጉ ሲጣሉ ይታያሉ ። ኃጥአንም የሚበላ የሚጠጣ ሞልቶ ሀብት ተትረፍርፏቸው ሳለ እነሱ ግን ከስስታቸው የተነሣ ወገኖቻቸው የሚልሱት የሚቀምሱት አጥተው እያዩ እነሱን ካላቸው ከፍለው ማብላትና ማጠጣት ሲገባቸው እነርሱ ግን ያላቸው አልበቃ ብሎአቸው ሲጣሉ ለገንዘብ ብለው የማይገባቸውን ሲያደርጉ የሌላ ሰው ሀብት ዘለው ሲመኙ ይገኛሉ ።

መ. የበጐች ላታቸው የወደቀ ሐፍረተ ሥጋቸው የተሸፈነ ነው ። የጻድቃንም ኃጢአታቸው በሰው ዘንድ የተጋለጠ አይደለም ። ኃጢአት ቢሠሩም በንስሐ ሌላ ሰው ሳይሰናከልባቸው በስውር ለንስሐ አባታቸው ነግረው ቶሎ ያጠፉአታል ። የፍየሎች ግን ላታቸው የተሰቀለ ፣ ሐፍረተ ሥጋቸው የተጋለጠ ነው። የኃጥአንም የኃጢአት ሥራቸው በሰው ዘንድ የተገለጠ ለሚሠሩት እኩይ ምግባር ቅንጣት ታክል የማያፍሩ በየአደባባዩ ኃጢአትን የሚፈጽሙ ምን ይሉኛልን ከሰብዓዊ ጠባያቸው ፍቀው የጣሉ ናቸው ።

ሠ በጐች አቀልቅለው እንጂ አሻቅበው አያዩም ። ጻድቃንም ሁል ጊዜ በትሕትና ሕይወታቸውን ይመራሉ ፣ ደካማነታቸውንና ኃይል የእግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ። ስለዚህ አይታበዩም አዋቂ ሆነው ሳለ አላዋቂ ነን ይላሉ ፣ ባለጸጋ ሆነው ሳለ ድሆች ነን ፣ ሀብት የእግዚአብሔር ነው ይላሉ ፣ ምግባር ፣ ትሩፋት እያላቸው ምንም የሌለን ኃጢአተኞች ነን ፣ አንተ ፈጣሪያችን በቸርነትህ ማረን ይላሉ ። ፍየሎች ግን አሻቅበው ነው የሚያዩት ፣ ሁልጊዜ አንገታቸውን እንዳንጠራሩ ፣ በዚህ ላይ ትዕቢታቸው ፤ ልክ እንደ ፍየሎች ኃጥአንም ደካማ ሆነው ሳለ ብርቱዎች ነን ይላሉ ። ሀብት የእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ እነሱ ግን ለጊዜው ባገኙት ሀብት በመመካት ድሀ ወገናቸውን ይንቃሉ፣ያንቋሽሻሉ ። አዋቂ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ እነሱ ግን ትንሽ ፊደል ቆጥረው ከኛ በላይ አዋቂ ለአሳር ነው ይላሉ። ሁልጊዜ ስለ ታላቅነታቸው፣ ስለ ኃያልነታቸው ሲያወሩ ነው የሚውሉት ። ትሕትና በእነሱ ዘንድ የበታችነት ምልክት ነው ።



ረ. ከበጐች ውስጥ አንዷቱን ተኩላ ቢነጥቅ “ በግ ከበረረ የሰው ልጅ ካመረረ ” እንዲባል እነርሱም ሁለተኛ ወደዚያች ቦታ ፊታቸውን አይመልሱም ፣ በዚያው ጠፍተው ይቀራሉ ። ጻድቃንም እኩይ ሞት ከእነሱ አንዱን ነጥቆ በወሰደው ጊዜ ነገም የእነሱ ተራ እንደሚሆን ተረድተው ከኃጢአት ሥራቸው በንስሐ ተመልሰው እግዚአብሔርን በንጽሕና በቅድስና ሕይወት ያገለግሉታል እንጂ ወደዚያ የኃጢአት ሥራቸው ዳግም አይመለሱም ። ፍየሎች ግን ከመሃከላቸው ነብር አንድዋን ቢወስድ ለጊዜው ደንብረው ይሄዳሉ የኋላ ኋላ ግን ተመልሰው በጉረኖአቸው ውስጥ ይገኛሉ ። ኃጥአንም ከመካከላቸው አንዱ ሳያስቡት በሞት ተነጥቆ ሲወሰድ ሲያዩ ለጊዜው ደንግጠው ከኃጢአት ሥራቸው ታቅበው በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ ፣ የኋላ ኋላ ግን ያ የሞተው ሰው ከሕሊናቸው ሲጠፋና የዓለምም ሁኔታ ሲማርካቸው ይረሱትና እንደገና ወደ ቀድሞ የኃጢአት ሥራቸው ይመለሳሉ ። በዚህ ጸባያቸው በጐች የጻድቃን ፣ ፍየሎች የኃጥአን ምሣሌ ሆነዋል ። ዳሩ ግን በግ ጻድቅ ፣ ፍየል ኃጥእ ማለት አለመሆኑ በእያንዳንዳችን ሕሊና ሊታወቅ ይገባል።

## የግራና የቀኝ ምሣሌ

ጻድቃን በቀኝ የሚቆሙት ምሣሌያቸው ስለሆነ ነው ፣

— ቀኝ ቅን ነው፣ ጻድቃንም ሃይማኖት ምግባር ለመሥራት ቅን ናቸው

— ቀኝ ፈጣን ነው፣ ” ” ” ” ፈጣን ”

— ቀኝ ብርቱ ነው፣ ” ” ” ” ብርቱ ”

ኃጥአን በግራ የሚቆሙት ምሣሌአቸው ስለሆነ ነው ፣

— ግራ ጠማማ ነው ፣ ኃጥአንም ሃይማኖት ምግባር ለመሥራት የተጣመሙ ናቸው ፣ በዚህ ሲሉአቸው በዚያ ይላሉ ፣ ምክንያት ያበዛሉ ።

— ግራ ዳተኛ ነው ፣ ኃጥአንም ሃይማኖት ምግባር ለመሥራት ዳተኞች ናቸው ። ቤተ ክርስቲያን ለምን አትሄዱም ሲሉአቸው ፣ እዚህ ቦታ ደርሼ መጥቼ ደከመኝ ፣ ጸልዩ ሲባሉ መጮሁ ምን ዋጋ አለው ! እራሱ እግዚአብሔር ፍላጐቴን ያውቀው የለ ? ስገዱ ጹሙ ሲባሉ ይለግማሉ ።

— ግራ ሰነፍ ነው ፣ ጠንከር ያለ ሥራ መሥራት አይችልም ። ኃጥእንም በሃይማኖት በምግባር በኩል ጠንከር ያለ ነገር ሲገጥ

ማቸው ደክመን ስለቻን ብለው ይተውታል ። ለኃጢአት ሥራ ግን አይደክሙም ፣ ሌሊት ጨለማን ተገን አድርገው ሲዘርፉ ሲዘሙቱ ይውላሉ ።

## ሕያዋንና ምውታን የተባሉትስ እነማን ናቸው ?

ሕያዋን — ጻድቃንን ሕያዋን ይላቸዋል ፣ ምክንያቱም በዚህች ምድር ላይ በወዲያኛው ዓለም ላይ ሕያው የሚያሰኛቸውን ሃይማኖትና ምግባር ጠብቀው ተገኝተዋልና ።

ምውታን — ኃጥአንን ምውታን ይላቸዋል ፣ ምክንያቱም በዚህ ምድር ላይ በወዲያኛው ዓለም ምውት የሚሆኑበትን ሥራ ሠርተዋልና ።

## አንዳንድ ጥያቄዎች በትንሣኤ ሙታን ላይ

— ሰው ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ እንዴት ይነሣል ?
የቅዱስ ጳውሎስ መልስ “ አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራውን ስንዴ ሳይሞት ሳይፈርስ ሳይበሰብስ ፍሬ እንደማያፈራ አታይምን ? ሰውም እንደዚሁ ” 1ኛ ቆሮ. 15 ፥36

— ጻድቃንና ኃጥአን በስሕተት ተቀላቅለው አይነሱም ?
አይነሱም ፣ ኃጥአን ኃጢአታቸውን ይዘው ሲነሱ ፣ ጻድቃን ደግሞ የጽድቅ ሥራቸውን ይዘው ነው የሚነሱት ። ምሣሌ ኑግና ስንዴ በአንድነት ተቀላቅለው በአንድ መሬት ላይ ቢዘሩ ኑግ ኑግ ሆኖ ይበቅላል እንጂ ስንዴ ሆኖ አይበቅልም ፣ ስንዴውም ስንዴ ሆኖ ይበቅላል እንጂ ኑግ ሆኖ አይበቅልም ኃጥአንና ጻድቃንም እንደዚሁ ።

— አውሬ የበላቸው ሰዎች ወደ አውሬው ሥጋነት የተለወጡ ስለሆነ በትንሣኤ ወቅት ሥጋቸው ከአውሬው ሥጋ ተለይቶ እንዴት ይነሳል ?
አሁንም ይህንን በምሣሌ መልሱን እንሰጣለን ። አፈርና እህል በአንድነት ተቀላቅሎ ቢዘራ አፈሩ እዚያው አፈር ሆኖ ሲቀር እህሉ ግን ይበቅላል ። አውሬ የበላቸው የሰዎች ሥጋም በትንሣኤ ወቅት በእግዚአብሔር ሥልጣን የእነሱ ሥጋ ከአውሬው ሥጋ ተለይቶ ሲነሳ የአውሬው ሥጋ ግን ትንሣኤ ስለሌለው እዚያው ፈርሶ በስብሶ ይቀራል ።

— የክርስቶስ መምጫው ቀን ይታወቃል ወይ ?
“ ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከእግዚአብሔር በቀር መላእክትም የሰው ልጅም ቢሆን አያውቁትም ” ማቴዎስ 24 36 እንግዲህ ከባለቤቱ ከክርስቶስ በቀር ማንም ፍጡር አያውቃትም ።



— ክርስቶስ ሶስት መአልት ፣ ሶስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አደረ የሚባለው እንዴት ሆኖ ነው ?

ለዚህ ምላሽ የዕብራውያንን አቆጣጠር ማወቅ ያስፈልጋል ። የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት የዕብራውያንን ሥርዓት ወግና ጂኦግራፊያዊ (መልክአ ምድራዊ) አቀማመጥ ማወቅ ያስፈልጋል ። ምክንያቱም ጸሐፊዎቹ ባህላቸውንና ሥርዓታቸውን ጠብቀው የጻፉት ስለሆነ ። ጌታ ዓርብ ተሰቅሎ ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ ከተነሣ እንዴት ብሎ ሶስት መአልት ሶስት ሌሊት ይሞላል ሊያሰኝ ይችላል ። በዕብራውያን አቆጣጠር ሌሊት የሚቆጠረው በዋዜማው ካለው አሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ ነው ። ከአሥራ አንዱ ሰዓት በፊት ያሉት ሰዓቶች ግን አንድ ሰዓትም ቢሆን እንደ አንድ መዓልትና ሌሊት ይቆጠራል ። ጌታ የተቀበረው ዓርብ ከአሥራ አንድ ሰዓት በፊት ስለሆነ የተቀበረበት ሰዓት የዓርብን መአልትና ሌሊት ያጠቃልላል ። ዓርብ ከሠርክ አሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ቅዳሜ አሥራ አንድ ሰዓት ከሰዓት በኋላ ድረስ ያለው የቅዳሜ መአልትና ሌሊት ነው ። ቅዳሜ ከአሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ ያለው እሑድ ነው ። አንዱም ሰዓት ቢሆን ከላይ እንደተገለጠው የዕለቱን ሰዓቶች ያሟላል ። ጌታም የተነሣው እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ስለሆነ ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት ይሆናል ። ሁለተኛው ደግሞ የተሰቀለው በዕለተ ዓርብ ስለሆነና የሞተውም በዕለተ አርብ በመሆኑ አቆጣጠሩ ከአርብ ጠዋት ይጀምራል ። አርብ ጠዋት ከ12 ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ በምድር ላይ ብርሃን ነበር ፣ አንድ ቀን ። ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ላይ ጨለማ ሆነ ይላል መጽሐፍ ቅዱስ ፣ ያም ጨለማ እውነተኛ ጨለማ እንጂ በምትሐት የሆነ ባላልሆነ እንደ ሌሊት ይቆጠራል ። አንድ ቀን አንድ ሌሊት ይኖረናል። ዓርብ ከዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እንደገና ቀን ሆኖአል ፣ አርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥቢያ ያለውን ጨለማ ወይም ሌሊት ስንቆጥር ሁለት ቀን ሁለት ሌሊት ይሆናል። ቅዳሜ ሙሉ ቀንና ሌሊት ለእሁድ አጥቢያ ጌታ እሁድ ሌሊት ተነስቷል፣ አንድ ላይ ሲደመር ሶስት መዓልት ፣ ሶስት ሌሊት ይሆናል ። እንግዲህ በሁለቱም ዓይነት የሚቆጥሩ ስላሉ ሁለቱም ዓይነቶች ቀርበዋል ፣ እኛም የገባንና የተረዳነን አቆጣጠር መርጠን ማስረዳትም መረዳትም እንችላለን።

— አንዳንድ የእምነት ክፍሎች ክርስቶስ ነገ ይመጣል ፣ ከነገ ወዲያ እያሉ የክርስቶን ምጽአት ቅርብ አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ ፣ ይህ እንዴት ነው ?

ለዚህ ጥያቄ ቅዱስ ጳውሎስ መልስ አለው ። " ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ስለጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለመሰብሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ ፥ እንዳት ደንግጡም እንለምናችኋለን ። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመጽ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለው ሁሉ ሰዎች ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው " 2ኛ ተሰሎንቄ 2 ፥ 1 — 4 ።

እንግዲህ አስቀድሞ ስለተነገረን ዛሬም ማንም ክርስቶስ ሊመጣ ነው እያለ ያሻውን ቢለፈልፍ ጆሮአችንን እንዳንለግሰው ተመክረናል ፤ የክርስቶስን መምጫ ጊዜ ማንም ሰው አያውቅም ። እርሱ ባለቤቱ ግን አስቀድሞ የሚሆነውን ሁሉ ገልጦልናል ጊዜውና ደርጊቱ ራሱ ወቅቱ መድረሱን ይገልጽልናል ።

ሞንታንየስ የተባለ ሐሰተኛ ሰው ክርስቶስ ሊመጣ ነው በማለት ብዙውን ሕዝብ በቀቢጸ ተስፋ ውስጥ ከቶ ሰው ሁሉ ሥራ ፈትቶ ቁጭ ብሎ ሰማይ ሰማዩን ሲያይ ይውል ነበር ። ከአሁን አሁን ሰማይና ምድር በመብረቅ ታርሶ ክርስቶስ በእልፍ አእላፋት መላእክት ታጅቦ የሚመጣ እየመሰላቸው ፤ የኋላ ኋላ ውሸቱን መሆኑ ታወቀ ።

* ዊሊያም ሚለር የተባለው የአድቬንቲስት እምነት መሥራች ክርስቶስ በ1844 ዓ.ም. ለፍርድ እንደሚመጣ ስለተነበየ ሰው ሁሉ የእምነቱ ተከታይ ሆኖ ነበር ። ኋላ ግን ጊዜው እንደዘበት ሲያልፍ ሐሰተኛ ነቢይ መሆኑ ተረጋገጠ ።

** ቻርልስ ራስል የተባለው የጂሆቫ እምነት መሥራችም እንዲሁ ስለ ጌታ መምጣት ተንብዮ ነበር ። ዳሩ ግን ይመጣል ባለበት ቀን ሳይመጣ ቀረ ። ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚነሱ ራሱ ጌታ አስቀድሞ የነገረን ስለሆነ ይሄ መሆኑ ሊያስደንቀን አይችልም ።

" አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል ፥ ሁሉን ቻይ አምላክ ጌታ ኢየሱስ ፥ እንደ ዮሐንስ እምነታቸውን ጠብቀው ልብሳቸውን አጽድተው ተጠናቀው ያሉት ደግሞ አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ፥ ቶሎ ና " ይላሉ ራዕይ 22 ፥ 21 ።

---

* Encyclopaedia Britannica, Page 497 ( Volume 15 )
** The Oxfoord Dictionary of the Christian Church Page 1189



# ምዕራፍ ፳

<u>ክብረ ድንግል</u>

በዚህ ንዑስ ርእስ ውስጥ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና ፥ ክብር እና አማላጅነት ተገልጾአል ።

1. <u>የስምዋ ትርጓሜ ፥ አባትና እናትዋ ስለምን ማርያም ብለው አወጡላት ቢሉ ፥</u>

— እነሆ በዚህ ዓለም ከሚመገቡት ሁሉ ምግብ ለአፍ የሚጥም ፥ ለልብ የሚመጥን ማር ነው ። በነትም በሕይወት የተዘጋጀ ጻድቃን ቅዱሳን ያም የሚባል ምግብ አላቸው ። ሁለቱን ስናገጥመው ማርያም የሚል እናገኛለን ። ስለዚህ ከዚህ ሁሉ የበለጥሽ የከበርሽ ነሽ ሲሉ ማርያም ብለው አወጡላት ይላሉ አባቶች

— ዳግመኛም ማርያም ማለት ፀጋ ወሀብት ማለት ነው ። ለጊዜው ለእናት አባትዋ ሐብትና ፀጋ ሆና ተሰጥታለች ። ፍጻሜው ግን ለምእመናን ሁሉ ጸጋና ሐብት ሆና ተሰጥታለች።

— አንድም ማርያም ማለት መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው ። ይህስ እንዴት ነው ቢሉ ፥ እነሆ ዛሬ በዚህ ዓለም ለዕውር መሪ በትር እንዲሰጡት ሁሉ እርሷም በፍቅሯ በጣዕመ ፍቅሯ የሰውን ሁሉ ኃጢአት ክፋት ፍታ ፥ ከልጅዋ አስታርቃ ፥ ከገሃነመ እሳት አውጥታ መንግሥተ ሰማያት የምታገባ ስለሆነች መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታገባ አሏት ።

— አንድም ማርያም ማለት ተላኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው ። እንዴት ነው ቢሉ መለኮት ከትስብእት ፥ ትስብእት ከመለኮት ተዋሀዶ በእመቤታችን በአግዝዕትነ ማርያም ማኅፀን አድሮ ነበርና ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የምትላላክ አሏት ።

- በሌላም በኩል ማርያም ማለት ፍጽምት ማለት ነው ። ለጊዜው መልከ ከዶም ግባት እሚልታ ይዛ ተገኝታለች ። ፍጻሜው ግን ንጽሐ ሥጋ ፣ ንጽሐ ነፍስ ፣ ንጽሐ ልቦና አንድ አድርጋ ይዛ ስለተገኘች ። እንዲሁም በሀሳብም በሥራም ንጽሕት ናትና ።
- እንድም ማርያም ማለት ልዕልት ማለት ነው ። አርያም ማለት ልዑል ማለት እንደሆነ እመቤታችንም መቅሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ይላታልና ( ከፈጣሪ በታች ፣ ከፍጡራን በላይ ) ናትና ።
- እንዲሁም በእብራይስጥ ማሪሃም ይሏታል ። ማሪ ማለት እመቤት ማለት ነው ፣ ሃም ማለት ብዙሃን ማለት ነው ። ስለዚህ ማሪሃም የብዙሃን እመቤት ማለት ነው ።

2. <u>ዘለዓለማዊ ድንግል ስለመሆንዋ</u>

ሴቶች ድንግልናን ከእናትነት ፣ እናትነትን ከድንግልና አስተባብረው መያዝ የማይቻላቸው ሲሆን ፣ እርስዋ ግን ድንግልና ከእናትነት፣ ተባብሮላት በክብረ ወሊድ ላይ ክብረ ድንግልና ተጨምሮላት የአምላክ እናት ዘለዓለም ድንግል መሆንዋን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ።

ስለዚህ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ድንግልና ልዩ ነው ። ሌሎች ደናግል ሴቶች በሥራ ድንግል ቢሆኑም በሃሳብ ግን ድንግል ሊሆኑ አይችሉምና ። እመበታችን ግን በሀሳብም በሥራም ድንግል ነች ።

<u>እመበታችን ለዮሴፍ ስለምን ታጨች ?</u>

ድንግል ማርያም ለዮሴፍ መታጨቷ በባልና በሚስት ግብር ለመገናኘት አይደለም ።እንኪያ ለምን በእጮኛ ስም ተሰጠች ? ቢባል በእጮኛ ስም መሰጠቷ ስለብዙ ምክንያት ነው ። የመጀመሪያው ምክንያት ከእርሷ የሚወለደው ክርስቶስ ከይሁዳ ከዳዊት ወገን እንደሆነ ትንቢት ተነግሯል ። ኢሣይያስ 11 ፣ 1 እና 10 ።

ነገር ግን ከእናት ብቻ ተወለደ እንጂ አባት ስለሌለው ፣ ዮሴፍ ከዳዊት ዘር ነውና ክርስቶስ በእናቱ እጮኛ በዮሴፍ የዳዊት ልጅ ተብሎ እንዲቆጠር ነው ። ምነው በእናቱ የዳዊት ልጅ አይባልም ? ቢባል አይሁድ ሴትን ከትውልድ ቁጥር አግብተው አይቆጥሩምና የናቱን ከትውልድ መቆጠር ስለማይቀበሉ ነው ። ስለዚህም ማለት በእናቱ እንዳይቆጥሩ አይሁድ ስለማይቀበሉአቸው ወንጌላውያን የክርስቶስን ትውልድ ሲቆጥሩ በዮሴፍ ቆጥረዋል ። ማቴ. 1 ፣ 16 ሉቃስ 2 ፣ 4 - 5



እኛ ግን ክርስቲያኖች ክርስቶስን የዳዊት ልጅ የምንለው በአንጻር በዮሴፍ ሳይሆን ከዳዊት ወገን በተወለደች በእውነተኛዋ እናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ነው ። እንዲሁም ዮሴፍና እመቤታችን ዝምድና ስለአላቸው ነው ። ዝምድናቸውም ቀጥሎ ተገልጾአል ።

አልአዛር

| | |
|---|---|
| ማታን | ቅስራ |
| ያዕቆብ | እያቄም |
| ዮሴፍ | ማርያም |

እንግዲህ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ወንጌላውያን የአልአዛር ልጆች ማታንና ቅስራ ሲሆኑና ትክክለኛውን የክርስቶስን ትውልድ ለመግለጽ በቅስራ በኩል አልፈው እመቤታችን ላይ አርፈው ጌታ ከእስዋ እንደተወለደ መጻፍ ሲኖርባቸው በማታን በኩል የቆጠሩት ዕብራውያን ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ሴትን ከትውልድ ቁጥር አግብተው ስለማይቆጥሩ ወንጌላውያንም ፣ አይሁዶች ምክንያት አግኝተው ወንጌልን ከመቀበል ወደ ኋላ እንዳይሉና የመዳንን መንገድ ከመከተል እንዳያዘነብሉ ሲሉ ነው። ስለዚህ በዘዴ የዮሴፍንና የእመቤታችንን ዝምድና አሳምረው ስለሚያውቁ በዮሴፍ ቆጠሩ ። ክርስቶስ ግን ከእመቤታችን የተወለደው ያለ ወንድ ዘር መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ ነው ። ለዮሴፍ እጮኛ የመባልዋ ምክንያት አንዱ ከላይ የተጠቀሰው ነው ።

ሁለተኛው ምክንያት ሴት ልጅ ናት ጠባቂ ያስፈልጋታልና በእጮኛ ስም እንዲጠብቃት ነው ። ሶስተኛው ክርስቶስ ያለወንድ ዘር መወለዱን አይተው እናቱ ማርያምን ከሰማይ የመጣች ኃይል ናት እንጂ የአዳም ዘር ሰው አይደለችም ። ክርስቶስም ከመልአክ የተገኘ መልአክ ነው የሚሉ መናፍቃን በኋላ እንደሚነሱ ስለሚያውቅ ከሰማይ የመጣች ኃይል ብትሆንማ ለዮሴፍ ትታጭ ነበርን? ብሎ ነገራቸውን ለማፍረስ እንዲመች ለምእመናን እውነተኛ የአዳም ዘር እንደሆነች ለማስረዳት በእጮኛ ስም ለዮሴፍ እንድትሰጥ ተደረገ ።

መታጨቷ ስለዚህ ምክንያት እንደሆነም አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ገልጾታል ። ገብርኤል መልአክም ወደ ድንግል ብቻ እንደተላከ አልተናገረም ። "ስሙ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ድንግል" አለ እንጂ ። የወንድ እጮኛ በማለቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእውነት ሴት እንደሆነች ያስረዳ ዘንድ ብሏልና ። ሃይማኖተ አበው አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ክፍል 17 ።

አራተኛው ምክንያት አገልጋይዋ ተላኪዋ እንዲሆን ነው ። ሄሮ
ድስ ልጅዋን ሊገድለው በአስፈለገው ጊዜ ስትሰደድ ዮሴፍ ተከታይ
ሆኖ እንዲረዳት እግዚአብሔር ለዮሴፍ እንድትታጭ አዘዘ ።

አምስተኛው ምክንያት ከመደብደብ ሊያድናት ፤ በኦሪት ዘኍልቍ
ምዕ. 5 ፥ 19 በተጠቀሰው መሠረት አንዲት ሴት ከባልዋ ሌላ ጸንሳ
ብትገኝ ማየ ዘለፋ ያጠጥዋት ነበር ። እንዲሁም አንዲት ሴት ባል ሳታ
ገባ ብትጸንስ በሙሴ ሕግ መሠረት ደብድበው ይገድሉአት ነበር ።
ስለዚህ እመቤታችን ለዮሴፍ ሳትታጭ ቀርታ ጸንሳ ቢሆን አይሁድ
ለድብደባ ባበቁአት ነበር ።

ድንግል ማርያም ለዮሴፍ መታጨቷ ስለዚህና ይህን ስለመ
ሰለ ምክንያት ነው እንጂ ለሚስትነት አይደለም ። ለዚህስ ቢሆን ኖሮ
ለዮሴፍ ትታጭ ሲል ተአምራት ባለሳየም ነበር ፤ ለዚህማ ቢሆን አን
ዲትን ሴት ለአንድ ወንድ ለማጋባት በትር እስከ ማለምለም በላስፈለገ
ነበር ። ቅን ልቡና ላለው ሰው ድንግል ማርያም ለዮሴፍ መታጨቷ
ለመገናኘት እንዳይደለ ተአምራቱ ያስረዳል ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋዋ ብቻ ሳይሆን
በህሊናዋም ድንግል ነበረች ፤ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ፤ መልአኩ
ገብርኤል ትጸንሺያለሽ ወንድ ልጅም ትወልጂያለሽ . . . ብሎ
ሲያበስራት ፤ እኔ ወንድ አላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል ? . . . ብላ መለ
ሰችለት። እንደ መናፍቃኑ አባባል ቢሆን ኖሮ በመጀመሪያውኑ ለዮሴ
ሴፍ ለሚስትነት ከታጨች አንድ ቀን አርግዛ እንደምትወልድ ስለም
ታውቅ ስለምን " ይህ እንዴት ይሆናል . . . " ብላ መልአኩን ትጠ
ይ ቅ ነበር ? ። ይህ እራሱ ዮሴፍ ለባልነት እንዳልታጨለትና እርሷም
ድንግል በክልዕ ( በሁለት ወገን ድንግል ) ማለትም በሥጋም በሕሊ
ናም ድንግል መሆንዋን ያረጋግጣል ።

የእግዚአብሔር ጥበብ ድንግል ማርያም በውጭ የዮሴፍ እጮኛ
እንድትባል ማድረጉ ከላይ ስለተዘረዘሩት ምክንያቶች ነው እንጂ ዘር
ለማስገኘት ሔዋን ለአዳም ረዳት ሁና እንደተሰጠችው ዮሴፍ ልጅ
ለማስገኘት ረዳት እንዲሆናት አይደለም ። እግዚአብሔር ድንግል
ማርያምን የፈጠራት 2ኛው አዳም ክርስቶስን ያለ ወንድ ዘር እንድ
ታስገኝ ስለሆነ ፤ ሴቶች ልጅ ለማስገኘት ከሚያሻቸው ግብር ሁሉ
በጥበቡ ጠብቋታል ።

ዮሴፍንም በባልነት ግብር እንዳያውቃት በጥበቡ ከልክሎታል
ስለዚህ ጻድቅ ዮሴፍ በውጭ (በግልጽ) ለድንግል ማርያም እጮኛዋ
ሲባል ፤ በውስጥ ማለትም በምሥጢር ጠባቂዋ ፤ አገልጋይዋ ፤ አሳዳ
ጊዋ ይባላል ።



ሐቁ ከላይ የተጠቀሰው ሆኖ ሳለ አንዳንድ ሰይጣን ያደረባቸው
የሰይጣን የግብር ልጆች የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 1 ቁጥር 25 በመጥቀስ
ዘለዓለማዊት ድንግል በሆነችው በእመቤታችን ላይ የማይገባ ጸያፍ
ነገር ይናገራሉ ። " የበኵር ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ አላወ
ቃትም " የሚለውን ይዘው ዮሴፍ ጌታን ከወለደች በኋላ እመቤታች
ንን በግብር አውቋታል የሚል የድፍረት ቃል ይናገራሉ ። በመሠረቱ
ይህን ጸያፍ ቃል የሚያናግራቸው ያ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ስለሆነ
እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው እያልን ለዚሁ ቃል አጠር መጠን ያለ
መልስ እንሰጣለን ።

እንደመናፍቃኑ አባባል " የበኵር " የሚለው ቃል ሌሎች ልጆ
ችም እንዳሉ ያመለክታል ሲሉ " እስከ " የሚለው ቃል ደግሞ ከዚያ
በኋላ የሚል ቃልን በውስጥ ያዘለ አድርገው " አላወቃትም." የሚለ
ውን ደግሞ " አዳም ሔዋንን ዐወቃት ፤ ከዚያም ቃየልን ወለደች "
በሚለው ወስደውት " በግብር ዐወቃት " የሚል ትርጉም ሰጥተውት
ይገኛሉ ። በመሠረቱ " የበኵር ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ ዐላወ
ቃትም " የሚለው ቃል በአጭሩ ሲተረጐም ፤ እመቤታችን ቅድስት
ድንግል ማርያምን በጊዜው የነበሩ ሰዎች በሚገባ እንዳላወቁአት ማለ
ትም ማን ወይም ምን መሆንዋን እንዳላወቁ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል
ከእግዚአብሔር መልአክ በሕልም የተማረዉ ዮሴፍ እንኳን የበኵር
ልጅዋን እስክትወልድ ስሙም ኢየሱስ ተብሎ እስኪጠራና ሌሎችንም
ምልክቶችን እስኪያይ ድረስ ቅድስት ድንግል ማርያም የአማኑኤል
እናት መሆንዋን አላወቀም ( አልተረዳም ) ነበር ። እርስዋ ግን ሁሉን
ነገር በእርጋታ ታስተውለው በልብዋም ታኖረው እንደነበር መጽሐፍ
ቅዱስ ይመሰክራል ፤ ሉቃስ 2 ፥ 19 እና 51 ።

## የበኵር ትርጉም

" የበኵር ልጅዋን ወለደች " የሚለው ቃል ብዙ ሰዎችን አሳስ
ቷል ። ይህም ሊሆን የቻለው በተለምዶ የበኵር ልጅ የሚባሉ የግድ
ተከታይ ያላቸው መሆን አለባቸው የሚል አስተሳሰብ በእያንዳንዱ
ህሊና ስለተቀረጸ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የበኵርን ትርጉም
ብዙሃኑ ከተረዳው ለየት ባለ አተረጓጐም ይተረጉመዋል ። እግዚአብ
ሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ " በእሥራኤል ልጆች ዘንድ
ከሰውም ከእንስሳም ማኅጸንን የሚከፍት በኵር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ
የእኔ ነው " ዘጸአት 13 ፥ 1—2

በመጽሐፍ ቅዱሱ እንደተገለጸው በኵር የሚባሉት ለመጀመሪያ
ጊዜ ከእናታቸው ማኅጸን የወጡ መሆናቸውን እንጂ የግዴታ ተከታይ
ሊኖራቸው እንደማይገባ ይገልጻል ። አንድ ብቻም ቢሆን የእናቱን

ማኅጸን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍቶ ከወጣ ተከታይ ባይኖረውም በኩር ነው ። የክርስቶስ በኩርና ግን በዚህ ብቻ የሚፈታ አይደለም ። ክርስቶስ በኩር መባሉ የእመቤታችን ብቸኛ ልጅ መሆኑን ለመግለጽ ብቻም አይደለም ። ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን የአብ የባሕርይ ልጅ መውለድዋን ለመግለጽ ወንጌላዊው ማቴዎስ " የበኩር ልጅዋን ወለደች " ብሏል ። በተጨማሪም ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ በኩር ተብሎ ተጠርቷል ። ጥቂቶቹን እንመልከት ፤

— <u>ቆላስይስ 1 ፥ 17</u> " . . . ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል ፥ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው " ፤ እዚህ ላይ በኩር የሚለው ቃል ተወዳዳሪ ላላቸው ነገሮች የሚጠቀስ ሆኖ ከቀረበ ጌታን ፍጡር አድርጎ ከፍጡራን ጋር አነጻጽሮ እርሱ ከፍጥረታት በፊት ቀድም ብሎ የተፈጠረ ፍጡር ነው እንደማለት ይሆናል ። ይህ ደግሞ የክርስትናን ትምህርት ሥረ መሠረት የሚያናጋ የተረፈ አርዮሳውያን ትምህርት ስለ ሆነ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነት ውጭ ነው ። አባባሉ የገ ባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጥረታት በፊት ያለ ፥ ፍጥረታ ትንም አሳልፎ የሚኖር ፤ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው መሆ ኑን ፈጣሪነቱን ለመግለጽ የተጠቀሰ ነው ።

— <u>ዕብራውያን 1 ፥ 6</u> " . . . በኩርን ወደ ዓለም ሲያገባ " እዚህም ላይ የክርስቶስ በኩር ተብሎ መጠራት አብ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጁን ወደ መሬት ሂድ ፥ ውረድ ተወለድ ፤ ሙት ፥ ተሰቀል ብሎ እንደላከው መግለጹ መሆኑ በክርስቶስ ክርስቲያን ተሰኝተናል የሚሉ ሁሉ የማይክዱት ነው ። እንግዲህ አብ በኩርን ወደ ዓለም ሲልክ . . . ስለአለ በኩር የሚለው ቃል ተጠቅሷልና አብ ከክርስቶስ ( ከወልድ ) ሌላ ልጅ አለው ማለቱ ነውን ? ይህማ እንዳይባል ፍቁረ እግዚ ዮሐንስ በምዕ. 1 ፥ 18 ላይ "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ባሕርይው ያየው አንድ ስንኳ የለም ፥ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ነገረን " ብሎ ወልድ ብቻ የአብ የባሕርይ ልጁ እንደ ሆነ አስረግጦናል ።

እንግዲህ " የበኩር ልጁዋን " መባሉ መጻሕፍት በኩር በኩር ብለው የተናገሩለት ፤ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረ ፤ ዓለ ምና በውስጥዋ ያሉ ት ፍጥረታትን የፈጠረ ፤ መጀመሪያና መጨ ረሻ የሌለውን አምላክ አዶናይ ፥ ልዑለ ባሕርይን ወለደች ለማለት ተፈልጎ ነው ።



በሌላ አንጻር " እስከ " ን ተገን አድርገው " እስከቀውልድ ድረስ አላወቃትም " የሚለውን እስከን ፍጻሜ ላለው ነገር አስገብተው ከዚያ በኋላ በግብር ዐወቃት የሚል ትርጓሜ ቢሰጡትም ፤ የተሣሣቱ መሆናቸውን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያጋልጣቸዋል ። " እስከ " ፍጻሜ ላለው ነገር እንደሚገባ ሁሉ ፍጻሜ ለሌለው ነገርም ይገባል ። የሚ ከተሉት ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ ሲሆኑ የ " እስከ ' ን አገባብ ግልጽ ያደረጉልናል ። በጽሞና እንመልከታቸው ።

1ኛ. " የሣኦል ልጅ ሜልኮል <u>እስከ</u> ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አል ወለደችም ይላል 2ኛ ሳሙ. 6 ፥ 23 ይህም ማለት እስከ መቼም ድረስ አልወለደችም ለማለት ነው እ'ንጂ ከሞተች በኋላ ወለደች ለማለት አለመሆኑ የታወቀ ነው ።

2ኛ. " ይህም ነገር በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ጆሮ ተሰማ ፥ እስከሞትሞቱ ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሰረይላችሁም " ይላል ። ከሞቱ በኋላ ይስተሰረይላቸዋል ማለት ነውን ? ኢሣይ ያስ 22 ፥ 14 ። የዚህ ትርጉሙ እስከ ዘለዓለም ለማለት ነው ።

3ኛ. <u>ሮሜ 5 ፥ 14</u> " ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ " ይላል ። ከሙሴ በኋላ ሞት ቀረ ማለቱ ነውን ? አይደለም ። "ሞት ሆይ መውጊያህ የታለ ? " የተባለው ክርስቶስ ሞትን ድል አድ ርጎ ከተነሣ በኋላ ነው ።

4ኛ. <u>በመዝሙር 110 ቁ.1</u> ላይ " እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መረጋገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲባል ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ በቀኝ መቀመጡ ቀረ ማለት አይ ደለም ። ወደ ቈላስይስ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው የጳው ሎስ መልዕክት ምዕ. 2 ፥ 14—15 ጌታችን በመስቀሉ ድል የነሣ መሆኑ የተነገረ ሲሆን ፥ በሐዋርያት ሥራ ምዕ. 7 ፥ 55 ላይ ደግሞ እስጢፋኖስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ጌታ ኢየሱስ በእግዚአ ብሔር አብ ቀኝ ሆኖ ያየው መሆኑን ተናግሮአል ። ይህም የሆ ነው ጌታ ጠላቶቹን ድል ከነሣ በኋላ በመሆኑ እዚህ ላይ የተጠ ቀሰው " እስከ " ፍጻሜ የሌለው " እስከ " ነው ።

5ኛ. <u>በማቴ. ምዕ. 28፥20</u> ላይ "እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ " ያለው ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ከእነርሱ ይለያል ለማለት አይደለም ። እስከ ዘለዓለም ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ለማለት እንጂ ።

6ኛ. ዘፍጥረት 8 ፥ 7 " ቁራውን ሰደደው እርሱም ወጣ ወጣው ከም ድር እስከሚደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይል ነበር " ሲል ከደ ረቀ በኋላስ ወዲያና ወዲህ ማለቱን ተወ ማለት ነው ?

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት በማቴ. ምዕ. 1 ፥ 25 የተ ጠቀሰው ፍጻሜ የሌለው "እስከ" መሆኑን ያስረዳናል ። ስለዚህም ዮሴፍ እመቤታችንን እስከ ፍጻሜው በግብር አላወቃትም የሚል ትርጉምን ይሰጠናል እንጂ እንደምናፍቃኑ ያለ ትርጉም አይሰጥም ።

መናፍቃን ለዚህ ጥቅማቸው አባሪ አድርገው የሚያቀርቡት የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ቁጥር 55 - 56 ያለውን ነው ። በዚህ ምዕራፍ ላይ ወንድሞቹና እህቶቹ የተባሉት ዮሴፍ ከሚስቱ ሚስቱ የወለዳቸው እንጂ የእመቤታችን ልጆች አይደሉም ። አይሁድ ግን ጌታን የዮሴፍ ልጅ ይሉት ስለነበረ ልጆቹንም የእመቤታችን ልጆች አድርገው ነበር የሚያዩአቸው ። በሌላም አባባል የወንድም ልጅ ፥ እንዲሁም የቅርብ ዘመድ ሁሉ ወንድምና እህት መባባሉ የእብራውያን ሥርዓት ነው ። ለዚሁም አብርሃምና ሎጥን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ። ዘፍጥረት 13 ፥ 8 ።

ስለ እመቤታችን ድንግልና በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ተጠ ቅሶ እናገኛለን። ለምሳሌ በኢሳይያስ 7 ፥ 14 ከዚያ በኋላ ባል ታገባለች አላለም ፥ ወይም ድንግል የሚለውን ስም አልነሳትም ። እንዲሁም ሕዝቅኤል በምዕ. 44 ፥ 1—2 ባለው ላይ የምሥራቅ በር ተዘግቶ ይኖ ራል ፥ ሰውም አይገባበትም ፥ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ብሎ የእመ ቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና ይነግረናል ፥ እመቤታችን ስለምን በም ሥራቅ ትመስላለች ቢሉ የፀሃይ መውጫ ምሥራቅ ነው ። እመቤታ ችንም የእማናዊ የፀሐየ ጽድቅ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ነችና ። በተ ጨማሪም ደግሞ በማቴዎስ ምዕ. 2 ፥ 16 ሰብአ ሰገል በመጡበት ጊዜ ጌታ ከተወለደ ሁለት ዓመት ሆናት ነበር ማለት ነው ። ዮሴፍን የም ታገባ ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል ዓመት ባልቆየች ነበር ። ከግብጽ በደች መልስም ያላገባች መሆንዋ በሚከተሉት ጥቅሶች ይታወቃል ።

ማቴ. ምዕ. 2 ፥ 13 " . . . ሕጻኑን ከእናቱ ጋር " አለው እንጂ ከሚስትህ ጋር አላለውም ። እንዲሁም በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 20 ዮሴፍን ከግብጽ ወደ እሥራኤል እንዲመለስ ሲነግረው " ሕጻኑን እናቱንም . . . " ነው ያለው ። እጮኛ የሚለው ስም እንኳ ጌታን ከወለደች በኋላ አልተጠራችበትም ። ይህ ሁሉ የሚያስረዳን ዮሴፍ እመቤታችንን እንዲጠብቅ እንጂ እንዲያገባት አለመሆኑን ነው ። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል 19 ፥ 26—27 እናቱን ለዮሐንስ አደራ መስጠቱ ሌላ ልጅ ከእሱ በስተቀር እንደሌላት የሚያስረዳ ነው ።



ሰሎሞንም በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 4 ፥ 12 " እህቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት የተዘጋ ምንጭ የታተመም ፈሳሽ ናት " ብሎ የእመ ቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና ይነግረናል ።

## ስለ እመቤታችን ክብርና አማላጅነት

— መዝሙር 44 ( 45 ) ፥ 9 - 17 " በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋ ንግ ሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች " ትርጉም ፥ እመቤታችን በሰጠሃት ክብር ፀንታ ትኖራለች ። " በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋ " ንጽሐ ሥጋ ፥ ንጽሐ ነፍስ ፥ ንጽሐ ልቡና አንድ አድርጋ ይዛ ማለት ነው ።

" ንጉሥ ውበትሽን ወዶአልና " ማለት ሥጋሽን ለመዋሃድ መርጧልና ፥

" የምድር ባለጠጐች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ " ማለት አማል ጅን ይላሉ ማለት ነው ። " በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለ ዱልሽ በነቢያት ፈንታ ሐዋርያት 318 ሊቃውንት ከዚያም በኋላ ያሉት ክርስቲያኖች ስለእመቤታችን ክብር የሚመሰክሩ ሁሉ የእመቤታችን ልጆች ናቸው "

መዝሙር 86 ( 87 ) ፥ 1 - 7

— " መሠረቶችዋ በተቀደሱ ተራሮች ላይ ነው " ማለት የእመቤ ታችን መገኛ ሥርወ ልደቷ ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት መሆኑን ያስረዳል ።

— " ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወ ዳቸዋል " ማለት ከሌሎች ደናግል ይልቅ የእመቤታችንን ሕዋ ሳት ለተዋሕዶ ይወደዋልና ።

— " የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ ፥ በአንቺ የተደረገው ምንኛ ድንቅ ነገር ነው " ማለት እመቤታችን ሆይ ስለአንቺ የተደረገ ነገር ድንቅ ነው ማለት ያለ ዘር ፥ ሩካቤ መጽነሷንና መውለዷን መና ገር ነው ።

— " ሰው እናታችን ጽዮን ይላል ፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ " ማለት እመቤታችን እናታችን እግዚአብሔር ወልድ አባታችን ይላሉ ። ጌታ ከእመቤታችን በሥጋ ተወለደ ።

— " እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት " ማለት እግዚአብሔር እመ ቤታችንን በንጽሕና አፅናት በእመቤታችን ያመኑ ሁሉ ደስ ብሎ አቸው እንዲኖሩ ይናገራቸዋል ።

መዝሙር 130 ( 131 ) ፥ 13 — 18

— በዚህ ምዕራፍ ላይ ጽዮን የሚላት በወርቁ እመቤታችንን ነው ። ይህም ይታወቅ ዘንድ " ይህቺ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት " ብሎ ለምድራዊትዋ ጽዮን (ለምድሪቱ) አለመሆኑን ያረጋግጥልናል ። ምክንያቱም " ሰማይና ምድር ያልፋሉ " ብሎ ራሱ ጌታ በማይታበል ቃሉ ተናግሯል ። ስለሆነም ምድሪቱ የዘለዓለም ማረፊያው ልትሆን አትችልም ። ለእመቤታችን ግን ይስማማል ። " ይህቺ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት " ሲል ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ ስትባል የምትኖር ስለሆነ በተጨማሪም ደግሞ ከእሷ የነሣው (የወሰደው) ሥጋ ለዘለዓለም መለኮትን ተዋሕዶ የሚኖር ስለሆነ " መርጫታለሁና አድሬባት እኖራለሁ " አለ ።

ትንቢተ ኢሣይያስ 60 ፥ 4

— " የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ ፥ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ ፥ የእግዚአብሔር ከተማ ( ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማህጸኗን ዓለም አድርጐ ተመስግኖበታልና ከተማ አለው ) የእሥራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል ። ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ለእመቤታችን መስገድ እንዳለብን ያሳስበናል ። ይህኮ ለማርያም ሣይሆን ለምድሪቷ እንድንሰግድ ነው የሚሉ አይጠፉ ይሆናል ። ለምድሪቱ እንድንሰግድ የምንገደደው እግዚአብሔር ሰላሳ ሶስት ዓመት በሥጋ ስለተመላለሰበት አይደለ ወይም ደግሞ መንፈሱ ስላደረባት አይደል ? እነሆ ከምድሪቱ ጽዮን የምትበልጥ ልዑለ ባሕርይን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንዋ የተሸከመች ታላቅዋ እመቤት አለች ። ይህችውም

የባሕሪያችን መመኪያ የሆነችው ንጽሕት ድንግል ማርያም ነች ። እመቤታችን ከሰው ፍጥረት ሁሉ የተለየች ነች የምትባልበት ብዙ ምክንያት አለ ። እግዚአብሔር በቅዱሳን ላይ ቢያድር በመንፈስ ነው ። በእመቤታችን ግን ከሥጋዋ ሥጋ ፥ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በአካል ( በከዊን ) ነው ያደረው ። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስገነዝብ " የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም ዕብራ. 2 ፥17 ብሎአል ። ሉቃስም በሐዋ. ሥራ 13 ፥22 — 23 " ከዳዊት ዘር እግዚአብሔር እንደተስፋው ቃል ለእሥራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ " በማለት አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ መንሳቱን ያረጋግጥልናል ። በዚህም የተነሣ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ትባላለች ።



እንግዲህ እመቤታችን ምን ያህል በአምላክ ዘንድ መመረጥዋንና መከበርዋን ልብ በሉ ። ታዲያ ቅዱሳን ለነበሩባት መንፈሱ ላይ ረባት ምድር ስግደት የሚገባ ከሆነ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማህፀንዋን ዓለም አድርጐ ለተመሰገነባት ለእመቤታችን በጸጋ የማይሰገድበት ምክንያቱ ምን ይሆን ? ክህደት ካልሆነ በቀር ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም ።

ሉቃስ 1 ፥ 39 — 55

ቅድስት ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ድምጽ በሰማች ጊዜ በማህፀንዋ ውስጥ ያለው ህጻን በደስታ ዘለለ ይለናል ። የጽንስ እንቅስቃሴ ነው እንዳንል እራስዋ ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ድምጽ ሰምቶ በደስታ መዝለሉን አረጋግጣልናለች ። ይህንንም ሐዋርያት " ሰገደ " ብለውታል ። ለአምላክ ማኅደር ለእመቤታችን የፀጋ ፥ በማህፀንዋ ውስጥ ላለው ለኢየሱስ ክርስቶስ የአምልኮት ስግደት ። እንግዲህበመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው እመቤታችንን ያከብራል ፥ እንደ ኤልሳቤትም ያመሰግናል ፥ እንደ ቅዱስ ገብርኤል " ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ " ይላል እንጂ እመቤታችንን አያቃልልም ። አንዳንዶች እመቤታችንን የአዳም ኃጢአት አለባት ፥ ስለዚህም በደሙ ከተዋጁት ወገን ነች ይላሉ ። ነገር ግን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአዳም ኃጢአት የሌለባት ፥ በሥጋም በነፍስም ንጽሕት መሆንዋን መንፈስ ቅዱስ ከእናትዋ ማህፀን ጀምሮ ያ በዘር የሚተላለፍ የመጀመሪያ ጥፋት ወደ እርስዋ እንዳይተላለፍ ጠብቆአታል ። ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነን የቅዱስ ገብርኤል ምስክርነት ነው ። " ጸጋ የሞላብሽ ሆይ" ማለቱ ከኃጢአት ከጥንተ አብሳ ( ከመጀመሪያው በደል ) ሁሉ የነጻች በሥጋም በነፍስም ንጽሕት መሆንዋን የሚያመለክት ነው ። ሰሎሞንም በማኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 4 ፥7 ላይ " ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ፥ ነውርም የለብሽም " ብሎ እመቤታችን ነጥብ የምታክል እድፍ ጉድፍ የሌለባት ንጽሕት መሆንዋን ይነግረናል ።

በተጨማሪም እራስዋ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመጀመሪያ የመልአኩ ፥ ቀጥሎም የኤልሳቤጥ ፥ ሶስተኛ በማኅፀን ያለውን የዮሐንስ ምስክርነት ይዛ አባትዋ ዳዊት በመዝ. 44 ፥ 16 ላይ ለልጅ ልጅ ስምሽን ያሳስባሉ ያለው ትንቢት እንደተፈጸመ ዐውቃ " ከእንግዲህ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል " በአንድ በመልአኩ ገብርኤልና በአንዲት ኤልሳቤጥ ብቻ ተመስግኜ አልቀርም ብላ ተናገረች ። በዚህም መሠረት እስከዛሬ ድረስ የክርስቶስ ወገኖች እመቤታችንን ያከብራሉ ያመሰግናሉ ።

መላእክት ሁሉ እመቤታችንን ያከብራሉ ፣ ያገናሉ ። ለእመቤታችንም ይሰግዳሉ ። በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንኳን ለዘካርያስ ልጅ እንደሚወልድ የምሥራች ቢነግረው ስለተጠራጠረ ቃሌን ስለአላመንክ ብሎ ወዲያው ድዳ እንዲሆን አድርጎታል ። ወደ እመቤታችን ሲቀርብ ግን ለየት ያለ አቀራረብ ይዞ ነው የቀረበው ። የምሥራቹን ከመንገሩ በፊት ልብዋን በደስታ ለመሙላት ነው የሞከረው ፣ ደስ ያለሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ፣ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ” ይህ የመልአኩ የምሥጋና ቃል ከእዚህ ቀደም ለማንም ያልቀረበ በመሆኑ እመቤታችን ወዲያውኑ እሺ በጄ ብላ አልተቀበለችውም።በዚህም ከእናትዋ ከሔዋን የተለየች መሆንዋ ይታወቃል መልአኩ ገብርኤል “ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ” ብላ በመለሰችለት ወቅት አሁንም በትሕትናና በአክብሮት “ ማርያም አትፍሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና ” “ ብሎ ይዞት የመጣውን የምሥራች ቃል ነገራት ። እመቤታችን ግን ብዙ ጥያቄ አቀረበችለት ። መልአኩም እስከተቻለው ድረስ መለሰላት ፣ በመጨረሻ ከባድ ጥያቄ በጠየቀችው ጊዜ “ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ”በሚለው አስደናቂ መልስ የቃል ልውውጣቸውን ፈጸሙ ።

እንግዲህ መልአኩ የዘካርያስን እንደበት በአንዲት የዘካርያስ የጥርጣሬ ንግግር ሲዘጋ ። እመቤታችን ግን ደግማ ደጋግማ ባቀረበችለት ጥያቄ እንኳን እንደ ዘካርያስ ተቆጥቶ አንደበትዋን ሲዘጋ ቀርቶ መልሱ እንኳን ፍጹም ትሕትና የተሞላበት ነበር ።

እንግዲህ ምን እንላለን በመላእክት ዘንድ እንኳን የከበረችውን እናት እኛ እናከብራትም ብንል ማን ይጐዳ ይሆን ? ጌታ ለሳውል እንዲህ አለው ። “ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል ” አዎን ? የዛሬ ፀረ ማርያሞችም እመቤታችንን ቢንቁ ለእነሱ ይብስባቸዋል እንጂ እሷንስ ኃያሉ ፈጣሪ አንድ ጊዜ አክብሯታልና ክብርዋን ሊነጥቅ የሚችል ሰው የለም ።

የዮሐንስ ራዕይ 12 ፣ 1 — 7

ክርስቲያን ወገኔ ሆይ ፣ የእመቤታችንን ክብር መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት አድርጐ እንደሚገልጽ ልብ በል ። ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃን ተጫምታ ፣ በራስዋም ላይ አሥራ ሁለት የከዋክብት አክሊል ሆኖላት ። ለማን ይሆን እንዲህ ዓይነት አገላለጽ ከዚህ በፊት የቀረበ? ከቶ ለማንም ተጽፎ አላነበብንም ። ይህ የተነገረው ለድንግል ማርያም አይደለም ብለው እንዳያብሉ ማስረጃው እዚያው ተጠቅሶላቸዋል ።



“ አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛውን ” ማለት ( በመለኮታዊ ሥልጣኑ ሕዝቡን የሚገዛውን ልጅ የወለደች ከሴቶች ወገን ከቶ ማን ትሆን ? ንጽሕት ስብሕት ቡርክት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነች ። መቼም ይኸን ቢክዱ እንኳን ሰው ሰይጣን ይታዘባቸዋል ። ለእመቤታችን የተነገረ መሆኑን ለማወቅ ሌላ ማስረጃ ካስፈለገ ” ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ሥፍራ ወደ በረሃ ሸሸች ”የሚለውን መመልከት ነው ። እመቤታችን ጌታን ይዛ መሰደድዋ በማቴ. 2 ፣ 13 — 18 ባለው ላይ ተጠቅሶአል ።

እንግዲህ ዲያብሎስ በእመቤታችን ተቆጥቶ “ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር የሆኑትን ከእመቤታችን ከዘርዋ የቀሩትን ማለት በአማላጅነትዋ የሚተማመኑትን ሊዋጋ ሄዶ በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ ማለት በመናፍቃን ልቡናና አንደበት ላይ ቆመ ፣ የእመቤታችንን ልጆች ሊቃወም ።

<u>በመጽሐፍ ቅዱስ የእመቤታችን ምሳሌዎች በጥቂቱ ፣</u>

1. <u>ገራህተ ስሉስ ( የማክሰኞ ዕለት እርሻ )</u> ዘፍጥረት 1 ፣ 9 - 13

የመጀመሪያይቱ ምድር ገበሬ ሳይግርባት ፣ ዘር ሳይዘራባት ውሃም ሳያስፈልጋት በቃለ እግዚአብሔር ብቻ ለፍጥረታት ምግብ የሚሆነውን ሁሉ ልታበቅል ችላለች ። እመቤታችንም ያለ ወንድ ዘር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች ። እርሱም በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ በእጸ መስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍስሶ እንኩ ሥጋዬን ብሉ ፣ ደሜን ጠጡ ብሎ ዘለዓለማዊ ምግበ ነፍስ ሆነልን ።

2. <u>የኖህ መርከብ ትባላለች ፣ ዘፍጥረት 7 ፣ 1 - 24</u>

— የኖህ መርከብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ተመስላ ብትገለጽም ፣ አባቶች የእመቤታችንም ምሣሌ እንደሆነች ይናገራሉ ። እግዚአብሔር በኖህ ጊዜ የነበሩትን ሰዎች በኃጢአታቸው ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው ሲያስብ ለኖህ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው ። ኖህም መርከብ ሠርቶ ገባ ። እግዚአብሔርም ምድርን ለአርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከላይ ከሰማይ ፣ ከታች ከምድር ውስጥ ውሃን በማዝነም በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች አንድ ሳይቀሩ ፈጃቸው ። ኖህን ግን መርከብዋን ምክንያት አድርጎ አዳነው ኖህ ሊድን የቻለው በሠራት መርከብ ጥንካሬና ብቃት አለመሆኑ ከማንኛውም

ክርስቲያን ያልተሰወረ ነው ። እግአብሔር ምክንያት ይሻልና መርከብዋን ምክንያት አድርጐ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደሆን የታወቀ ነው ። እንዲህስ ባይሆን ኖሮ ያን መአት እግዚአብሔር እንኳን የኖህ መርከብ ቀርቶ በአሁን ጊዜ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የተሠሩት ታላላቅ መርከቦችም ሊቋቋሙት አይችሉም ። እንደዚሁም ጌታ የአዳምን ልጆች ሊያድን ቢሻ እመቤታችንን ምክንያት አድርጐ ከእርስዋ ተወለደ ። ሁለተኛም የኖህ መርከብ በውስጥዋ ያሉትን ሰዎች ከመከራ ሥጋ እንዳዳነቻቸው ሁሉ እመቤታችንም በአማላጅነትዋ የሚያምኑትን ሰዎች ከሞተ ሥጋና ከሞተ ነፍስ ታድናቸዋለች ። ከመርከብዋ ውጭ ያሉት በንፍር ውሃ እንደጠፉ ፥ በእመቤታችን አማላጅነት የማያምኑትም በሥጋም በነፍስም ለዘለዓለም ይጠፋሉ ።

3, <u>በቀስተ ደመና ትመሰላለች ፤</u>

ከጥፋት ውሃ በኋላ እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውሃ እንዳያጠፋት ለኖህ ቃል ኪዳን ገባለት ። የቃል ኪዳኑ ምልክትም ቀስተ ደመና ነበር ። እግዚአብሔርም ለኖህ የገባለትን ቃል ማጽናቱን ሊገልጽ ከአማናዊትዋ ቀስተ ደመና ከእመቤታችን ተወለደ ። አስቀድሞ ነቢዩ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ “ ... እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን ፥ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር ” ኢሳ. 1 ፥ 9 ። ሲል የእናት አማላጅ እውነተኛ መድህን እንደሆነልን ነገረን ።

ስለሆነም እግዚአብሔር በኃጢአታችን ተቆጥቶ እንዳያጠፋን የባሕሪያችን መመኪያ የምትሆን እመቤታችንን ከጐኑ አደረገልን ።

4, <u>በእፀ ሳቤቅ ትመሰላለች ፤ ዘፍጥረት 22 ፥ 9 — 13</u>

ይስሐቅ የዚህ ዓለም ፥ በግ የጌታ ምሳሌ ነው ። በጉ ለይስሐቅ ቤዛ ሆኖ እንደተሰዋ ጌታም የዓለም ቤዛ ሆኖ ተሰውቷል ። በሌላ አገላለጽም ይስሐቅ የመለኮት ፥ በጉ የሥጋ ሰይፉ የሥልጣነ እግዚአብሔር ፥ ሰለቱ የሕማም ፥ የሞት ምሳሌ ነው እዚህ ላይ በጉ በእጸ ሳቤቅ ተይዞ ነበር ። ይህም የእመቤታችን ምሳሌ ነው ። እርሷ ዓለምን ሁሉ በክበረ ደሙ የሚያድነው መድኃኔዓለምን ተፈትሖ በሌለበት ማህፀኗ በድንግልና አሥራ ( ይዛ ) ተሸክማ ለቤዛነቱ ጊዜ አድርሳዋለችና ።



5, <u>ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ባያት መሰላል ትመስላለች</u> ፥ ዘፍ. 28 ፥ 10 — 12

እመቤታችን ያዕቆብ ሎዛ በተባለችው ሥፍራ በራእይ ያያትን መሰላል ትመስላለች ። መላዕክት ይወጡባትና ይወርዱባት ነበረ ። ጌታችን ከእመቤታችን ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ለተልእኮ አይወጡም አይወርዱም ነበር ። ጌታ ከእመቤታችን ሰው ከሆነ በኋላ ግን ለተልእኮ የሚወጡ የሚወርዱ ሆነዋል ።

ሁለተኛም እርሷ ለቃል መውረድ ፥ ሥጋ ዕርገት ምክንያት ሆናለችና አንድም እረገ መባሉ ከእርሷ የነሳው ሥጋ ነውና ፥ አንድም ቅዱሳን ማረጋቸው ከእርሷ የነሳውን ሥጋ በኩር አድርገው ነውና

እንዲሁም ከምድር እስከ ሰማይ እግዚአብሔር መንበር የምትደርስ በላይዋም መላዕክት ሲወጡባት እንደነበር ፥ እንዲሁ ደግሞ በቅድስት ድንግል እመቤታችን የአማላጅነት መሰላልነት የሰው ሁሉ ልመና ወደ ባሕርይ አምላክ ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል ። ያለ እመቤታችን አማላጅነት የማንም ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ አይችልም ።

6. <u>እፀ ጳጦስ ዘሲና ዘጸአት 3 ፥ 2 - 3</u>

ሙሴ በሲና ያያት በእሳት የተከበበችው ቁጥቋጦ በእመቤታችን ትመሰላለች ። ሐመልማሉ ከነበልባሉ ፥ ነበልባሉ ከሃመልማሉ ጋር አንዱ አንዱን ሳያጠፋ ተዋሕደው መታየታቸው ጊዜያዊና ፍጻሜያዊ ምሳሌ አለው ።

ለዚያን ጊዜ የነበረው ምሳሌ ሐመልማሉ የእሥራኤል ፥ ነበልባሉ የሚደርስባቸው መከራ ሐመልማሉ ነበልባሉን ማያቃጥለው ማየቱ በመከራቸው አዝነው ንስሐ ገብተው ነጻ ለመውጣት የተዘጋጁ አለመሆናቸውንና በመከራ ውስጥ የሚኖሩ መሆኑን ፥ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥላት ማየቱ መከራው የሚፀናባቸው ቢሆንም ጨርሶ የማያጠፋቸው መሆኑን ያመለክታል ። ፍጻሜው ግን ነበልባሏ የመለኮት ፥ ሐመልማሉ የእመቤታችን ምሳሌ ነው ። ቅዱስ ኤፍሬም እንደመሰለው ነበልባሉ በአካባቢው የነበሩትን ቁጥቋጦዎች ሲያቃጥል አንዲቱን ብቻ ያላቃጠለ መሆኑ መለኮትን በማህጸኗ ለመሸከም የተመረጠች ቅድስት ድንግል ማርያም መሆኗን አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ከሥጋዋ ሥጋን ፥ ከነፍሷ ነፍስን በነሣ ጊዜ የመለኮት ባሕርይ አላቃጠላትምና ባሕርየ መለኮት ያልለወጣት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ፥ እርሷን ሳያቃጥል ሌሎችን ቁጥ

ቋጠሮች ማቃጠሉ ግን የመለኮትን ባሕርይ ለመሸከም ሌሎች የማይችሉ መሆናቸውንና የመለኮት ባሕርይ የሚያቃጥላቸው መሆኑን ያስረዳል ።

7. <u>የጌድዮን ጸምር መጽ.መሳ. 6 ፥ 36 - 40</u>

— ለወቅቱ ፥ ጸምር የእሥራኤል ፥ ጠል የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው ። ጠሉ በጸምሩ ላይ መውረዱ እግዚአብሔር እሥራኤል በረድኤት የመርዳቱ ፤ በዳርና በዳር ባለው መሬት ላይ አለመውረዱ ረድኤተ እግዚአብሔር አህዛብን የማይጠብቅና ከእነርሱ የራቀ መሆኑ ምሳሌ ነው ። በሌላ በኩልም ጸምር የእሥራኤል ፤ ጠል የመቅሰፍቱ ምሣሌ ነው ። ጠሉ ከጸምሩ ላይ አለመውረዱ እሥራኤል እግዚአብሔር ከመቅሰፍት ይጠብቃቸው የነበረ ለመሆኑ ፥ በዳር ባለው ምድር ላይ መውረዱ እግዚአብሔር አሕዛብን በየጊዜው በመቅሰፍት ያጠፋ የነበረ ለመሆኑ ምሣሌ ነው ።

— <u>ፍጻሜው</u> ፥ ጸምር የእመቤታችን ፥ ጠል የጌታ ምሣሌ ሲሆን

ጠል በጸምሩ ላይ መውረዱ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ለመንሣቱ ፥ በእርሷ የማደሩ ምሣሌ ነው ። ጠል በጸምሩ ዳርና ዳር ባለው ምድር ላይ አለመውረዱ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በሌሎች ሴቶች ያለማደሩ ምሣሌ ነው ። ጠሉ በጸምሩ ላይ አለመውረዱ እመቤታችን ያለ ወንድ ዘር በድንግልና ጸንሣ በድንግልና የመውለድዋ ሲሆን በዳርና በዳር ባለው ምድር ላይ መውረዱ ሌሎች ሴቶች በዘርዐ ብእሲ በሩካቤ የመውለዳቸው ምሣሌ ነው ። እንግዲህ እመቤታችን ከአንስት ዓለም ተለይታ ያለወንድ ዘር ፥ ያለ ሩካቤ ጸንሳ በመውለድዋ በጌድዮን ጸምር ተመስላለች ።

## <u>ማጠቃለያ</u>

1ኛ/ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችን ስለእመቤታችን ያላት እምነት በአጭሩ ሲገለጽ ፥ " ጸጋ የተመላሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ ፥ ከሰዎች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ ፥ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ የተባረክሽ ነሽና ደስ ይበልሽ " ሉቃስ 1፥ 28 በሚለው በመመሥረት እመቤታችን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ፥ ከእናትዋ ማህጸን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ከአዳም ኃጢአት የጠበቃት ነች ።



2ኛ/ እናትና ድንግል ፥ ዘላለማዊት ድንግል ፥ በሀሣብ በሥራ ድንግል ነች ።

3ኛ/ በአማላጅነትዋ ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አገናኝታ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ ታስጠናለች ።

4ኛ/ " ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቀማለች " መዝሙር 44 ፥ 9 የሚለውን መሠረት በማድረግ ዛሬ በመንግሥተ ሰማያት እንዳለች ፥ ሞታ ያልቀረች በልጅዋ ኃይል የተነሣች መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ፥ ታስተምራለችም። መዝ. 131 (132)፥8 መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 2 ፥ 10—14

ከንጹሐን ይልቅ ንጽሕት የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ሆይ ፥ ካንቺ ተጸንሶ የተወለደውን የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ከደን በስሕተት ጉዳና እንዳንንጉድ ጠብቂን ፥ የልጅሽን ሥጋና ደምም ለመቀበል እንበቃ ዘንድ እያዘንሽ አማልጅን ፥ የእኛ ሳንነጻ መቀበል ክቡር ልጅሽን ማዋረድ መናቅ እንዳይሆን ፥ እርሱን ልጅሽን በምትቀበይበት ጊዜ የተደረገን ያንቺን ንጽሕና ስለ እኛ ፈንታ እንድታቀርቢልን እንለምናለን ።

ከአንስተ ዓለም መርጦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የሰጠን አምላክ ይክበር ይመስገን አሜን ! !

# ምዕራፍ ፱

## የቅዱሳን አማላጅነት

ጽድቅን የሚሰሩ ሰዎች በኦሪትና በሐዲስ እንደሚያማልዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል ።

ሀ/ አብርሃም ሚስቱን ሣራን ይዞ ወደ አቤሜሌክ ንጉሥ ጌራራ በተሰደደ ጊዜ መልከ መልካም ስለነበረች የዚህ ሀገር ሰዎች አንቺን ቢሉ እንዳይገድሉኝ ወንድሜ ነው በይ ፣ እኔም እህቴ ናት እላለሁ አላት ፣ እሺ አለች ። ከዚያ ሲደርሱ እሱም እህቴ ናት አለ፣ እሷም ወንድሜ ነው አለች ።

አቤሜሌክ ከእልፍኙ አግብቶ አደርሰበታለሁ ሲል እግዚአብብሔር በሕልም መጥቶ ፣ ይህች ሴት ባለ ባል ናትና እሷን በመቀማትህ ሞት የተፈረደብህ ነህ አለው ። አቤሜሌክም እውቄ አላደረግሁምና ያለኃጢአቴ እንደምን ታጠፋኛለህ ? አለው ። እግዚአብሔርም መልሶ እኔም ባለማወቅ መሥራትህን በውቄ ከመድረስ ከለከልሁህ ፣ አሁንም ሴቲቱን ወደባልዋ መልስ ፣ እሱም ነቢይ ነውና ስለአንተ ይጸልይልህ ትድናለህ ፣ ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ያንተ የሆነውም ሁሉ እንዲጠፋ እወቅ አለው ። እዚህ ላይ አቤሜሌክ መጸለይ ሲችል ሳለ እግዚአብሔር አብርሃም ስላንተ ይጸልይልህ ማለቱ ከአቤሜሌክ ጸሎት ይልቅ የአብርሃምን ጸሎት እንደሚቀበል መግለጹ አይደለም? ከዚህ በኋላ አብርሃም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ፣ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ከደዌው ፈወሰው ይላል ዘፍጥረት 20 ፣ 1—18 ።

ለ/ ኢዮብ ልዩ ልዩ ፈተና ደርሶበት በሕማም ሲሰቃይ በነበረበት ጊዜ ኤልፋዝ በልዳድ ሶፎር የሚባሉ ወዳጆቹ ሊጠይቁት መጥተው በማረጋጋት ፋንታ የሚያሳዝነው ነገር ተናግረው ስለ አሳዘኑት ፣ ኋላ ከደዌው በፈወሰው ጊዜ እግዚአብሔር ኤልፋዝን አንተና ሁለቱ ባልንጀሮችህ ስለእኔ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንነት አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ትነዳለች ። አሁንም ሰባት ወይፈንና ሰባት ዳንግሌ ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱና ስለናንተ የሚያቃጠል

መሥዋዕት አሳርጉ ። ኢዮብም ስለእናንተ ይጸልይላችሁ ፤ እኔም
ጸሎቱን እቀበላለሁ ” ። ከእዚህ እንደምንረዳው ስለኃጢያታ
ችሁ እግዘእብሔር ወደ እኔ ጸልዩ ከማለት ኢዮብ ስለ እናንተ
ይጸልይ ነው ያለው ። ይህም የኢዮብን አማላጅነት ያሳያል ።
“ እግዚአብሔርም የኢዮብን ጸሎት ተቀበለ ፤ እግዚአብሔርም
ኢዮብ ስለወዳጆቹ በጸለየ ጊዜ ምርኮውን መለሰለት ይላል ።
ኢዮ. 42 ፥ 7 — 11

ሐ/ እሥራኤል አሮንን ፊት ፊታችን እየሄዱ ጠላት የሚያጠፉልን
ጣኦታት ሥራልን ብለው ጣኦት አሠርተው በሰገዱ ጊዜ ፤ ጌታ
ተቆጥቶ ሙሴን ተወኝ እኒህን ሰዎች ላጥፋቸውና አንተን በሌላ
ሕዝብ ላይ እሾምሃለሁ ቢለው ፤ አቤቱ ብዙ ተአምራት
አድርገህ ባሕር ከፍለህ ጠላት አሥጥመህ ባወጣኸው ሕዝ
ብሕ ላይ ጽኑ ፍርድ ለምን ትፈርድብታለህ ፤ ይህማ ከሆነ ግብ
ጻውያን ለካስ ከኛ ዘንድ ያወጣቸው በምድረ በዳ ሊያጠፋቸው
ኖሯልና ይሉህ የለምን ? አቤቱ ከመአት ወደ ምሕረት ፤ ከቁጣ
ወደ ትዕግሥት ተመልሰህ ወገኖችህን ይቅር በላቸው ፤ ልጆቻ
ችሁን እንደ ሰማይ ኮከብ አበዛላችኋለሁ ፤ ይህችን ምድር ለዘ
ለዓለም ይወርሷት ዘንድ ለልጆቻችሁ እሰጣለሁ ብለህ የማልክ
ላቸው ባሮችህ አብርሃምን ፤ ይስሐቅን ፤ ያዕቆብን አስብ ብሎ
ቢጸልይላቸው ፤ እግዚአብሔር ከመአት ወደ ምሕረት ፤ ከቁጣ
ወደ ትዕግሥት ተመልሶ ይቅር አላቸው ። ያደርግባቸው ዘንድ
የተናገረውን ጥፋት አላደረገባቸውም “ ዘፀአት 32 ፥ 1—15 ፥ ዘዳ
ግም 9 ፥ 12 — 20 እና 25 ። “ ተወኝ ላጥፋቸው ” ብሎ ማማከሩ
ባለሟልነቱን ፤ አማላጅነቱን ለመግለጽ አይደለም ? ልብ አም
ላክ ዳዊት እንኳን የሙሴን አማላጅነት ሲጠቅስ “ እንዳያጠፋ
ቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት
ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ ” መዝሙር
105 ( 106 ) ፥ 23 ። በፊቱ ባይቆም ኖሮ ሲል ባያማልዳቸው ኖሮ
ለማለት መሆኑ ግልጽ ነው ።

መ/ እግዚአብሔር እሥራኤልን ከግብጽ በሚያወጣበት ወራት በፈ
ርኦን እንቢተኛነት ጓጉንቸር ባወረደባቸው ጊዜ ፈርኦን ሙሴንና
አሮንን ጠርቶ ጓጉንቸሩ ይርቅልኝ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸል
ዩልኝ ፤ እኔም ሕዝቡን ልልቀቅ አላቸው ። ሙሴም እሥራኤልን
እስከመቼ ትለቀዋለህ ንገረኝና ልጸልይልህ ቢለው ጓጉንቸሩ ይል
ቀቀኝ እንጅ ነገ ይሂዱ አለው ። ሙሴና አሮንም ከዚያ ወጥተው
ጓጉንቸሩ ይጠፉ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ ። እግዚ
አብሔርም ልመናቸውን ሰምቶ ጓጉንቸሩን ከቤትም ከደጅም ከሜ



ዳም አጠፋላቸው ይላል ዘፀአት 8 ፥ 6 - 15 ። ፈርኦን እንኳን
በነአሮን አማላጅነት አምኖ ጸልዩልኝ ብሏቸዋል ።

ሠ/ ዳታን አቤሮን በሙሴ ደቂቀ ቆሬ በአሮን ላይ በምቀኝነት በተነ
ሱባቸው ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሁሉንም ባንዲት ጊዜ አጠ
ፋቸው ዘንድ ከጉባኤያቸው ፈቀቅ በሉ ቢላቸው ሙሴና አሮን በግ
ንባራቸው ተደፍተው ወድቀው አቤቱ አምላክ ሆይ አንተ የሰው
ነፍስ አምላክ አይደለህምን ? አንድ ሰው ኃጢአት ሠራ
ብለህ በማኅበሩ ሁሉ ላይ ለምን ትቆጣለህ ብለው ለምነው ጥፋ
ተኞች ዳታን አቢሮን ደቂቀ ቆሬ ተለይተው ሲጠፉ ሕዝቡን አዳ
ነዋቸዋል ” ዘኁልቅ 16 ፥ 20 — 36 ። በነጋውም የእሥራኤል
ልጆች ሁሉ በሙሴና በአሮን ላይ ሕዝቡን አስገደላችሁ ብለው
በድንጋይ ሊደበድቡአቸው ተነሱ ። ሙሴና አሮንም ወደ ደብ
ተራ አሪት ሸሹ ። ዓምደ ብርሃን ጋርዶ አዳናቸው ። እግዚአብ
ሔርም ሙሴን ከዚህ ከእሥራኤል ፊት ፈቀቅ በሉ ፤ እኔ አሁን
በቅጽበት አጠፋቸዋለሁ ። ብሎ ወዲያው መቅሰፍት አምጥቶ
ይፈጃቸው ጀመር ፤ ወዲያው በአንድ አፍታ 14 ሺህ ከ700 ሰዎች
ሞቱ ። በዚህ ጊዜ ሙሴና አሮን በግንባራቸው ወድቀው ይጸልዩ
ጀመር ሙሴም አሮንን ልብሰ ተክሕኖ ለብሰህ ማዕጠንተ ወርቅ
ይዘህ ጸልይላቸዋል ፤ ኃጢአታቸውን አስተሰርይላቸው አለው።
አሮንም ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ በሙ
ታንና በሕያዋኑ መካከል እየተመላለሰ ቢጸልይላቸው መቅሰ
ፍቱ ፀጥ ብሎላቸዋል ፤ ሞት ተከልክሎላቸዋል ። ” ዘኁልቅ 16፥
41 — 50 ።

ሰ/ እሥራኤል ተሰብስበው ሄደው ኤርምያስን ጸሎታችን በፊትህ
ይድረስ ፤ ለእኛም ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን ፤
አይንህ እንደሚያየን ከብዙ ጥቂት ቀርተናልና ቢሉት እሺ ወደ
አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልይላችኋለሁ ፤ እግዚአብሔ
ርም የሚሰጣችሁን መልስ አልደብቃችሁም እነግራችኋለሁ
ብሏቸው እስከ 10 ቀን ከጸለየላቸው በኋላ የእግዚአብሔር
ነገር ወደ ኤርምያስ መጣ ፤ ከአሥር ቀን በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ
ጸሎታችሁን በፊቱ አቀርብ ዘንድ ወደርሱ የላካችሁኝ እግዚአ
ብሔር የእሥራኤል አምላክ በዚች ምድር ብትቀመጡ እሠራ
ችኋለሁ ፤ አላፈርሳችሁም ፤ እተክላችኋለሁ አልነቅላችሁም ።
እናንተ በሠራችሁት ኃጢአት ከደነገጣችሁበት እኔም ባደረግ
ሁባችሁ ክፉት እጸጸታለሁና ከባቢሎን ንጉሥ ፊት አትፉሩ አላ
ችሁ እግዚአብሔር ብሎ ነግሯቸዋል ። ኤር. 42 ፥ 2 —13

እንግዲህ እራሳቸው ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እየቻሉ ለምን ኤርምያስን ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን አሉት ? እግዚአብሔር የኤርምያስ አምላክ ብቻ ነው ? “ እኔ መንገድና እውነት ፥ ሕይወትም ነኝ ፥ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ” ዮሐ. 14 ፥ 6 የሚለውን በመጥቀስ ጌታን አማላጅ አድርገው የሚያቀርቡና ቅዱሳንን ደግሞ እንደማንኛውም ተራ ሰው አድርገው የሚያቀርቡ ብዙ ሰዎች አሉ ። በእርግጥ እነኝህ ሰዎች እጅግ በጣም ተሳስተዋል ። እኔ በቀጥታ ወደ ጌታ ፊት ለመቅረብ ብቁ ነኝ የሚል የትዕቢት አስተሳሰብም ያላቸው አሉ ። እነዚህ ሰዎች የዲያብሎስ ገንዘብ የሆነችውን ትዕቢት በመያዛቸው በእግዚአብሔር ፊት የከበሩትን ቅዱሳን ያቃልላሉ ። ነገር ግን እኔ በቀጥታ ወደ ጌታ ፊት ለመቅረብ ብቁ አይደለሁም በኃጢአት ባሕር የምዋኝ ነኝ ብሎ እግዚአብሔር ባከበራቸው መላእክትና ቅዱሳን አማካይነት መጸለይ ትሕትናን ወንድማዊ ፍቅርን ያመለክታል ። እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በትክክለኛ መንገድ መፈጸምን ያሣያል እንጂ አያስነቅፍም ።

ከላይ የተጠቀሱት የአማላጅነት ጥቅሶች ከብሉይ ኪዳን ብቻ ናቸው ። ግን በሐዲስ ኪዳን ስለምልጃ የተጠቀሰ የለም እንዳይባል በሐዲስ ኪዳንም የምልጃ ትምህርት ስለተጠቀሰ እንመልከታለን ።

“ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ” ማለት . . . እኔን ( በእኔ የባህርይ አምላክነት ) ያላመነ አብን ሊያምን አይችልም አብም ሊቀበለው አይችልም ማለት ነው እንጂ ቅዱሳን ሊያማልዱ አይችሉም ማለት አይደለም ።

በመሠረቱ ጌታ በአማናዊ ቃሉ እንደተናገረው “ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይመስላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም ” ማቴ. 5 ፥ 17 ። እንግዲህ ባለቤቱ ራሱ በአሪት ያሉት ሁሉም ሕጎች እንዳልተሻሩ እየገለጠዑን አንዳንድ አማኞች የሚሉት ቢያጡ ምልጃ በብሉይ ጊዜ ነበር ፥ በሐዲስ ግን የምልጃን ሥራ የሚሠራው ጌታ ብቻ ነው እያሉ የባሕርይ አምላክ በሆነውና ተማላጅ በሆነው አምላክ ላይ የማይገባ ነገር ይናገራሉ ። እኛ ግን አማላጅነት የፍጡር ሥራ እንጂ የፈጣሪ ሥራ አለመሆኑን እየገለጽን ፥ እንዲሁም በሐዲስ ኪዳንም ከተጠቀሱት የቅዱሳንን አማላጅነት አጠር መጠን ባለ ሁኔታ እንገልጻለን ።

ሀ/ “ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ፥ ነቢይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ይወስዳል ፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንድ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያ



ጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ” ማቴዎስ 10 ፥ 40—42 ።

ለ/ የያዕቆብ መልእክት ምዕ. 5 ቁ. 14—19 የቅዱሳን ጸሎት በሥራዋ እጅግ ታላቅ ኃይል እንደምታደርግ ይገልጻል ። እንዲሁም የካህናት ፀሎት ( አማላጅነት ) ከሥጋ ደዌና ከኃጢአት ደዌ እንደሚፈውስ ይገልጻል ።

ሐ/ የማቴዎስ ወንጌል 15 ፥ 21 —28 ባለው ላይ የሐዋርያትን አማላጅነት ያሣያል ። ጌታ ከነናዊት የሆነችው ሴት “ ጌታ ሆይ ማረኝ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞታል ” ብላ ስትጮህ ምንም መልስ አልመለሰላትም ነበር ። ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው “ በኋላችን ትጮሃለችና አሰናብታት” እያሉ ሲለምኑት “ ከእርስዋ ጋር የቃል ምልልስ ሊያደርግ ተገዶአል ። የሴትየዋ እምነት ብቻ አይደለም ልጅዋን ከደዌው ሊያስፈወስላት የቻለው ፥ የሐዋርያትም አማላጅነት እንጂ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ቃል ኪዳን እንደገባ የሚገልጽ አለ ፥ ለምሳሌ መዝሙር 88 (89) ፥ 3 “ ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ ” በሌላ በኩል በመጽሐፈ ነህምያ 1 ፥ 4 —7 “ . . . አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ ለሚወዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ . . . ” እያለ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የገባውን ቃል ኪዳን እንደማያጥፍ ያስረዳናል ።

እንዲያውም ባይገርማችሁ ቅዱሳን የፀጋ አማልክት ይባላሉ ። ይህም ማለት እግዚአብሔር እርሱ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እነሱ እንዲሠሩ አድርጐ ሾሙዋቸዋል ። እግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንደሚያደርግ ሁሉ እነሱም ድንቅ ሥራ እንዲሠሩ አድርጐአቸዋል ። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት አስደግፈን ማቅረብ እንችላለን ።

— <u>ዘፀአት 7 ፥ 1</u> “ እግዚአብሔር ሙሴን አለው ፥ እይ እኔ ለፈርኦን አምላክ አድርጌ ሃለሁ ፥ ወንድምህም አሮን ነብይ ይሆንልሃል ” ይህ ማለት እግዚአብሔር ሙሴ ታላላቅ ድንቅ ተአምራትን ያደርግ ዘንድ ከአማላጅነት አልፎ የአምላክነትን ሚና ይጫወት ዘንድ የጸጋ አምላክ ሆኖ መሾሙን የሚያስገነዝበን ነው ።

— <u>መዝሙር 81 (82) ፥ 1 - 8</u> “ እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ ፥ በአማልክትም መካከል ይፈርዳል ፥ . . . እኔ ግን አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ ነገር ግን እንደ ሰው

ትምታላችሁ፤ ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ አልሁ ።" እንግዲህ እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ብሎ የአምላክነትን ሥልጣን የሰጠው ለነማን ነው? ለቅዱሳን አይደለምን? ። ይህንን ልናብል እንችልም፤ ቃሉም ሊሻር እንደማይችል "እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን ? መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው . . ." ዮሐንስ ወንጌል 10፤34 ብሎ የቅዱሳንን ዘለዓለማዊ አማላጅነት ያረጋግጥልናል ። እንግዲህ በዚያን ጊዜ ሁሉም በእግረ ኢጋንንት እየተጠቀጠቀ ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ሆነ ይሉ በነበረበት ወቅት የፀጋ አምላክነት ከተሰጣቸው፤ ዛሬ በክርስቶስ ካሳ ከማኅበረ መላእክት ከተጨመሩ በኋላ "እኛ በክርስቶስ ፈንታ ክርስቶስን መስለን እንደ ክርስቶስ እንለምናለን" 2ኛ ቆሮ. 5፤20 ለማለት የበቁት የሐዲስ ኪዳን ጻድቃንማ ምን ያህል አይከብሩ ? እነሱም የፀጋ አማልክት ይባላሉ። ለማማለድም የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም" እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል ዮሐ. ወን. 14፤12 እንግዲህ የቅዱሳን አማላጅነት ብርቅ ድንቅ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልሰፈረ ነው ተብሎ የሚነገረው ለምንድን ነው? እራሱ ጌታ እኔ ካደረግኩት የበለጠ ያደርጋሉ ብሎ እየመሰከረ ። እሱ የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛርን እነሣ፤ እነቅዱስ ጊዮርጊስ ደግሞ ከሞቱ ዘለግ ያለ ጊዜ የሆናቸውን ሙታን በክርስቶስ ስም አስነሱ ። አይችሉም እንዳንል ራሱ ባለቤቱ ከእኔ የበለጠ ያደርጋሉ ብሎ አስረድቶናል ።

እንዲያውም ይድነቃቸውና ቅዱሳን እንኳን ማማለድ ይፈርዳሉ። ሁሉንም ነገር ለማድረግ ይችላሉ፤ የሚሳናቸው ነገር የለም "የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል የሚሳናችሁም ነገር የለም" ማቴ. 17፤19 አያማልዱም፤ የእኛን ጉዳይ ሊያስፈጽሙ አይችሉም ከተባሉ የጌታ ቃል ተፈጻሚነቱ ምኑ ላይ ነው ? ጌታ ደግሞ የእውነት አምላክ ነው ። ውሸቱን ሁሉንም እፈጽምላችኋለሁ ብሎ ኋላ አልፈጽምም አይልም ። ጌታ በማቴ. 5፤14 "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ብሏል ። በዮሐንስ ወንጌል 9፤12 ላይ ደግሞ ሐዋርያት "የዓለም ብርሃን ናችሁ ተብለዋል፤ አማልደው ከጌታ ጋር ካላገናኙን የዓለም ብርሃንነታቸው ምኑ ላይ ነው ?

እንኳን ለክርስቶስ ወንጌል የታመኑት እስከ ፍጻሜ ሕይወታቸው ለቃሉ ምስክር የሆኑት ሰማዕታት፤ ሐዋርያት፤ ጻድቃን ቀርተው፤ ጌታ በዚህች ምድር ላይ በሥጋ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሰዎች



ሌሎችን አማልደው ድህነተ ሥጋ አሰጥተዋቸዋል ። አባት ለልጁ በመለመን፤ እናት ለልጅዋ በመለመን ዘመድ ለዘመዱ በማማለድ፤ ብዙዎች ከጌታ ዘንድ ለወገኖቻቸው ፈውስ አሰጥተዋል ። መጽሐፍ ቅዱስ አሁንም ይህን ለመመስከር ዝግጁ ነው ።

ወደ ቅፍርናሆም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ "ጌታ ሆይ ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሰቃየ በቤት ተኝቶብኛል" ብሎ ለመነው ። ኢየሱስም "እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው፤ የመቶ አለቃውም መልሶ፤ ጌታ ሆይ በቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም፤ ነገር ግን በቃልህ እዛዝ እንጂ፤ ብላቴናዬም ይፈወሳል ። ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ፤ "እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም" ማቴዎስ 8፤10 ።

— እነሆም በአልጋ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አመጡ፤ ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን "አንተ ልጅ አይዞህ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ" አለው ።. . . ተነሳ አልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው፤ ማቴዎስ 9፤26 ።

— ይህንንም ሲነግራቸው አንድ መኮንን መጥቶ፤ ልጄ አሁን ሞተች ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት በሕይወትም ትኖራለች" እያለ ሰገደለት ማቴዎስ 9፤18 ።

— ወደ ሕዝቡም ሲደርሱ አንድ ሰው ቀረበና ተንበርክኮ "ጌታ ሆይ ልጄን ማርልኝ በጨረቃ እየተነሳበት ክፉኛ ይሰቃያልና ብዙ ጊዜ በእሣት ብዙ ጊዜም በውሃ ይወድቃልና ወደ ደቀመዛሙርትህም አመጣሁት፤ ሊፈውሱትም አቃታቸው አለው፤ ማቴ 17 ። 14 ።

— እነሆም ከነናዊት ሴት ከዚያ አገር ወጥታ ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ማረኝ፤ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል፤ ብላ ጮኸች ። እርሱ ግን አንዳችም አልመለሰላትም፤ ደቀመዛሙርቱም ቀርበው "በኋላችን ትጮሃለችና አሰናብታት" እያሉ ለመኑት፤ እርሱም መልሶ "ከእሥራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም" አለ ። እርሷ ግን ወጥታ "ጌታ ሆይ እርዳኝ" እያለች ሰገደችለት፤ እርሱ ግን መልሶ "የልጆችን ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም" አለ፤ እርስዋም "አዎን ጌታ ሆይ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ" አለች ። በዚህን ጊዜ ኢየሱስ "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ" አላት ። ልጅዋም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነች ማቴዎስ 15፤22 — 29

— አራት ሰዎችም የተሸከሙትን ሽባ አመጡለት ፤ ስለሕዝቡም ብዛት ወደእርሱ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሱ ፤ ቀጥለውም ሽባው የተኛበትን አልጋ አወረዱ ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን “ አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ” አለው ማርቆስ 2 ፥ 3 ።

— ኢየሱስም ደግሞ ወደ ማዶ ከተሻገረ በኋላ . . . ኢያኤሮስ የተባለ ከምኩራብ አለቆች አንዱ መጣ ፤ ባየውም ጊዜ በእግሩ ላይ ወደቀና “ ታናሽቱ ልጄ ልትሞት ቀርባለችና እንድትድንና በሕይወት እንድትኖር እጅህን ጫንባት ” ብሎ አጥብቆ ለመነው ፤ ማር. 5 ፥ 22

— ታናሺቱ ልጅዋ ርኩስ መንፈስ ያደረባት አንዲት ሴት ስለእርሱ ሰምታ መጣችና በእግሩ ላይ ተደፋች ፤ . . . ከልጅዋም ጋኔን ያወጣለት ዘንድ ለመነችው . . . ስለዚህ ቃልሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል ። አላት ። ወደቤቷም ሄዳ ጋኔኑ ወጥቶ ልጅዋም በአልጋ ላይ ተኝታ አገኘች ማርቆስ 7 ፥ 25 — 29

— ወደ ቤተ ሳይዳም መጡ ። ዕውርም አመጡለት ፤ እንዲዳስሰውም ለመኑት ፤ ዕውሩንም እጁን ይዞ ከመንደር ውጭ አወጣው ፤ በዓይኑም ተፍቶበት እጁንም ጭኖበት አንዳች ታያለህን ? ብሎ ጠየቀው ፤ አሻቅቦም ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ አለ ። ማር. 8 ፥ 22 — 23 ።

— ከሕዝቡ አንዱ መልሶ መምህር ሆይ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼአለሁ ፤ በያዘውም ስፍራ ሁሉ ይጥለዋል ። አረፋም ይደፍቃል ፤ ጥርሱንም ያፋጫል ፤ ያደርቃልም ፤ እንዲያወጡለትም ለደቀመዛሙርትህ ነገርኳቸው ፤ አልቻሉም አለው ፤ ማር . 7 ። 17 ።

— እነሆም አንድ ሽባ በአልጋ ተሸክመው አመጡ ፤ አግብተውም በፊቱ ሊያኖሩት ይሹ ነበር ፤ ስለሕዝቡም ብዛት እንዴት አድርገው እንዲያገቡት ሲያቅታቸው ወደሰገነቱ ወጡ ፤ የጣራውንም ጡብ አሳልፈው በመካከል በኢየሱስ ፊት ከአልጋው አወረዱት እምነታቸውንም አይቶ “ አንተ ሰው ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ” አለው ፤ ሉቃስ 5፥18 — 20 ።

— እነሆም ከሕዝቡ አንድ ሰው እንዲህ እያለ ጮኸ “ መምህር ሆይ ለእኔ ያለኝ አንድ ልጅ ነውና ልጄን እንድታድንልኝ እለምንሃለሁ ” ሉቃስ 5 ፥ 18 ።



— አንድ የመቶ አለቃም ነበረ ፤ የሚወደው ባሪያው ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር ። ስለኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን ለመነው ሉቃስ 7 ፥ 2 ።

— እርሱም ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እንደመጣ ሰምቶ ልጁ ሊሞት ስላለው ወደ እርሱ ሄዶ ፤ ወርዶም እንዲፈውስለት ለመነው ፤ ዮሐ. 4 ፥ 46 ።

— ማርታ ኢየሱስ እንደመጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው መጣች ፤ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር ። ማርታም ኢየሱስን “ ጌታ ሆይ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተ ነበር ፤ አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ ” አለችው ። ኢየሱስም “ ወንድምሽ ይነሳል አላት ፤ ዮሐ. 11 ፥ 21—24 ።

— በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች ፤ ትርጓሜው ዶርቃ ማለት ነው ። እርስዋም መልካም ነገር የሞላበት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች ። በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች ፤ አጥበውም በሰገነት አኖሩአት ። ልዳ ለኢዮጴ ቅርብ ናትና ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስ በዚያ እንዳለ ሰምተው ወደ እነርሱ ከመምጣት እንዳይዘገይ እየለመኑ ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ ላኩ ። “ . . . ጣቢታ ሆይ ተነሺ ” አላት ፤ እርስዋም አይኖችዋን ከፈተች ። ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች ፤ የሐዋ. ሥራ 9 ፥ 36—40 ።

አሳሳቾች ማወናበድ ልማዳቸው ነውና ቀደም ተብሎ የተጠቀሰውን የሚመስል ብዙ ማስረጃዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲገኝባቸው ከህይታቸውን ቀየር አድርገው ቅዱሳን በምድር ላይ በሕይወተ ሥጋ እያሉ ያማልዱ ነበር ። ከሞቱ በኋላ ግን አያማልዱም ይላሉ ። ግን ምልጃ በአጸደ ነፍስ ማለተ ቅዱሳን ከዚህች ዓለም ወደ እዚያችኛዋ በሞት ከተላለፉም ። በኋላ ማማለድ እንደሚችሉ አሁንም በቅዱስ መጽሐፍ የተረጋገጠ ነው ።

በመሠረቱ ይህንን ለማወቅ አስቀድሞ የሰውን ተፈጥሮ መርምሮ ማወቅ ያስፈልጋል ። ከአራቱ ባሕርያት ለተፈጠረ ሥጋ የሚያንቀሳቅሱት ደማዊት ነፍስና ነባቢት ነፍስ አሉት ። በአጸደ ሥጋ ሣለ ደማዊት ነፍስ የምትሰለጥንበት ስለሆነ በሥራው ሁሉ እንስሳትን መስሎ እንዲኖር በአጸደ ነፍስም ዓለሙ ዓለመ መላእክት ስለሆነ በአካለ ነፍስ መላእክትን መስሎ ይኖራል ። ይህንንም ጌታ ሲገልጽ “ በሰማይ

እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ መላእክት ይሆናሉ ” ብሎአል ፤ ማቴዎስ 22 ፤ 27 — 30 ።

ከትንሣኤ አስቀድሞ ያለውም ዘመን በዓለም ሥጋም ቢሆን በዓለመ ነፍስም ቢሆን የሥራ ዘመን ነው እንጂ የዕረፍት ጊዜ አይደለም ። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ “ መላእክት ሁሉ ረቂቃን ሲሆኑ የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለተልእኮ ይላካሉ ” ብሏል ፤ ዕብራውያን 1 ፤ 14 ።

ስለዚህ ጊዜው የሥራ ጊዜ ስለሆነ ዓለሙም ሥራ የሚሠራበት ዓለም ስለሆነ መላእክትና ጻድቃን አንድነት ሆነው በዓለመ ነፍስ በአጸደ ሥጋ ላሉት ለበጐዎቹ ይጸልዩላቸዋል ። ( ያማልዱላቸዋል ) በክፉዎች ይጸልዩባቸዋል ።

ማስረጃ ፤ የዮሐንስ ራዕይ 6 ፤ 9 - 11 “ አምስተኛውን ቁልፍ በከፈተ ጊዜ ከመሰዊያው በታች ሕጉን ስለጠበቁ ስለ እግዚአብሔር ቃል የሞቱትን ሰዎች ነፍስ አየሁ ፤ እነሱም እውነተኛ የባሕርይ አምላክ አቤቱ ደማችንን በግፍ ያፈሰሱትን ሰዎች በምድር ከሚኖሩ ሰዎች ለይተህ አትበቀላቸውምን አትፈርድባቸውምን ? እስከመቼ ድረስ ትታገሳቸዋለህ ? እያሉ በታላቅ ድምጽ ጮሁ ፤ ለእያንዳንዳቸውም ብሩህ ብሩህ ልብስ ሰጥተው እንደ እነርሱ በሰማዕትነት ይሞቱ ዘንድ ያላቸው ወንድሞቻቸው ምዕመናን በሰማዕትነት እስኪፈጸሙ ድረስ ይታገሱ ዘንድ ትንሽ ቆዩ አሏቸው ። ”

ይህ የሚያሳየን ከሞት በኋላ መጸለይ እንደሚቻል አይደለምን ? በክፉዎቹ ላይ ከጸለዩባቸው ለበጐዎቹ ደግሞ እንደሚጸልዩላቸው የታመነ ነው ። መናገር አይችሉም የሚሆነውን አያውቁምና ፤ ከሞቱ በኋላ አያማልዱም ማለት ግን “ እኔ የሕያዋን የእነአብርሃም የነይስሐቅ አምላክ ነኝ እንጂ የሙውታን አምላክ አይደለሁም ” ማርቆስ 12 ፤ 26 ፤ ያለውን አለማስታወስ ነው ። አብርሃምና ይስሃቅ ከሞቱ በኋላ አይደል እንዴ ስለአብርሃም ፤ ስለ ይስሃቅ ብለህ እያሉ እነሙሴ ይለምኑት የነበረው የሞቱትን ባለማሎቹን ቃል ኪዳን በሕይወተ ሥጋ እያሉ ብቻ ነው የምጠብቀው መቼ አላቸው ? እንዲያውም በሥሩት የጽድቅ ሥራ ሕያዋን እንጂ ምውታን አለመሆናቸውን ገለጸ እንጂ ።

በአጸደ ነፍስ መተዋወቅ መነጋገር መጸለይ እንደሚቻል አሁንም ባለቤቱ ራሱ በሉቃስ 16 ፤ 19—31 ባለው ላይ ግልጽ አድርጐ አስታውቆናል ። ሀብታሙ ሰው አብርሃምን ማረኝ ማለቱ ምንን ያመለክተናል ? የአብርሃምን የአማላጅነት ሥልጣን መቀበል አይደል ? አብርሃምስ ሀብታሙን ሰውዬ አላነጋገረውም ? በአብርሃም አማላጅነትስ የሚያምኑትን ሰዎች መላእክት በአብርሃም እቅፍ እንደሚያኖሩአቸው ይገልጽ የለም ? ።



በ2ኛ ነገሥት 13 ፤ 20 ላይ ኤልሳ ከሞተ በኋላ ነፍስ የተለየው አጥንቱ የአንድ ምውት ሬሣ እንዳስነሳ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ። ቅዱሳን እንኳን በነፍስ በሥጋቸው ፤ እንኳን አማልደው ፤ ሙትን ያስነሳሉ ። እንግዲያው የኤልሣ አጥንቱ ሙት ካስነሳ በአማላጅ ነቱ ተማምነን ከኃጢአት ሞት እግዚአብሔር እንዲያድነን ጸልይልን ፤ ቅማልደን ብንለው ይህን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ አያስደርግልን ይሆን ? እንመን ያለምንም ጥርጥር እንድናለን ። ይህ ጸጋ ለኤልሣ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ኤልሳዕን ለመሰሉ ቅዱሳን ሁሉ የተሰጠ ጸጋ ነው ።

ቅዱሳን እንኳን መለመንና ማስያረግ ቀርቶ በዓለሙ ላይ ሁሉ እንዲፈርዱ ጌታ እንዲህ ሲል ይናገራል ፤ “ እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገድ ልትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ ” ማቴዎስ 19 ፤ 28 — 29 ።

እንግዲህ ምን እንላለን ፤ ባለቤቱ ራሱ ፈራጅ ሲያደርጋቸው ፤ እኛ አይሆንም ፍጡራን ናቸው ስለሆነም በፍጡር ላይ ሊፈርዱ አይችሉም ልንል መብት አለን ? አንችልም ። እግዚአብሔር ያከበረውን ማንም ሊያዋርድ አይችልም ።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን የጌታ አማናዊ ቃል መሠረቱ በማድረግ “ ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን ” ይለናል ፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 6 ፤ 2 ። ጌታ መፍረድ ሰጥቶአቸው ከፍርድ ያነሰውን ማማለድ ከለከላቸውን ? አይደለም ። እነሆ ዛሬ ቅዱሳን በእግዚአብሔር አገር በደስታ አሉ ። በምድር ላይ እንደወርቅ በእሳት ተፈትነው አልፈዋልና እነሆ ቅዱሳን ዛሬ ስለእኛ ወደ አምላካቸውና አምላካችን ሌት ተቀን ይጮሃሉ ። የጽድቅ ሥራቸው የመጨረሻ ውጤት አፈር ትቢያ ሆኖ መቅረት እንዳልሆነ እናምናለንና አማልዱን ፤ አርዱን ፤ ተራዱን ፤ ባላጋራችን ዲያብሎስ እንደ ተራበ አንበሳ አፉን ከፍቶ ሊውጠን እየተንቆራጠጠ ነው ። ዲያብሎስ ብዙ ሠራዊቶቹን አሰማርቶ ከአንዲቱ ሃይማኖት ሊያስወጣን ነው ፤ ከጐናችን ሆናችሁ አስተምሩን ፤ ምሩን እንላችዋለን ። በክብሩ ዙፋን ዙሪያ የቆማችሁ ቅዱሳን ስለእኛ ወደ ሃያሉ ፈጣሪያችን አማልዱ አሜን ! ! !

# ምዕራፍ ፤

## ታቦት ፣ ጽላት

የሰው ልጆች ተጨባጭ የሆነ ፣ ሕሊናቸው የሚያርፍበት ቁሳዊ ነገር መፈለግ እግዚአብሔር መገለጡንና ክብሩን በሚታዩና በሚጨበጡ ነገሮች ላይ እንዲገልጽ አድርጎታል ። እግዚአብሔርን በማምለክ ከሙላው ዓለም ቀደምትነት ያላቸው እስራኤላውያኖች እግዚአብሔር ቃል በቃል እያነጋገራቸው ታላላቅ ተዓምራት እየሠራ መኖሩን ቢገልጽላቸውም እነሱ ግን ሌሎች ባእዳን አማልክትን ከማምለክ ወደ ኋላ አላሉም ነበር ። ከእብሪታቸው የተነሣ በቃል ብቻ የሚያነጋግረን አምላክ አንሻም የምናያቸው በመካከላችን የሚመላለሱ አማልክትን ስሩልን እያሉ መሪዎቻቸውን ያስቸግሩ እንደነበርና ጣኦታትም ሠርተው ከግብጽ ባርነት ያወጣቸውን በአማልክት መካከል እንዳንተ ማን አለ ? ብለው የመሰከሩለት አምላካቸውን በጣኦት ለውጠው የሠሩላቸውን ጣኦታት አምላኮቻችን ናችሁ አሉ ።

በዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ከምድረ ግብፅ ወጥተው ማርና ወተት ታፈሳለች ወደምትባለው ተስፋይቱ ምድር ከነዓን ለመግባት በጉዞ ላይ እያሉ በሙሴ አማካይነት የቃል ኪዳኑና የመታዘዝ ምልክት የሚሆኑ አሥር ሕግጋትና ትእዛዛት የተጻፈባቸው ሁለት ጽላቶች ሰጠው ። ለጽላቱም ማስቀመጫ የሚሆን ታቦት ከግራር እንጨት እንዲሰራ በእግዚአብሔር ታዘዘ ይህንንም አደረገ ። ለታቦቱም ማደሪያ ቤተመቅደስን ሰሎሞን ሠራ ይህን ሁሉ በተራ እንመለከታለን ።

— ጽላት ከእግዚአብሔር ስለመሰጠቱ

ሀ. ኦሪት ዘጸአት 24 ፡ 12 " እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ በዚያም ሁን እነርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍሁት ትእዛዝ ከከበረ ድንጊያ የተሠራ ጽላት እሰጥሃለሁ አለው እንግዲህ ጽላት ጣኦት ነው ከተባለ ጣኦትን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረጸው እግዚአብሔር ነው ማለታቸው አይደለምን ? ታዲያ ከዚህ የበለጠ ክህደት ከየት ይገኛል ።

ለ. <u>ዘጸአት 31 ፥ 18</u> “ እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸው ከክበረ ድንጊያ የተሰሩ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው ። ” እግዚአብሔር እሰጥሃለሁ ብሎም አልቀረ ለሙሴ ሰጠው ።

ሐ. <u>ዘጸአት 32 ፥ 15 — 17</u> “ ሙሴም ተመለሰ ሁለቱንም የምሥክር ጽላቶች በእጅ ይዞ ከተራራው ወረደ ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ ፤ ጽሕፈቱም በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር ” ። ጽላት የእግዚአብሔር እንጂ የሰይጣን ገንዘብ አለመሆኑን ሲያስረዳን ጽላቶችም የእግዚአብሔር ሥራዎች ነበሩ ይለናል ። ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ጽላት ይዞ ወደ እስራኤል ዘንድ ሲወርድ እስራኤል የጥጃ ምሥል አቁመው ለእሱ ሲሰግዱ ተመለከታቸው ። ከንዴቱ የተነሣ በእጁ የያዘውን የእንቁ ጽላት በጥጃው ሥእል ላይ ወረወረበት ጣአቱም ደቀቀ ጽላቱም ተሰበረ ። ይህንን በመጥቀስ ለሙሴ የተሰጠው ጽላት ተሰብሯል እና ሌላ ጽላት አልሰጠውምና ከዚያ በኋላ ቀርቷል የሚሉ አሉ ይህ ግን የእነሱ ክህደት እንጂ እግዚአብሔር እንደፊተኞቹ ያሉ ጽላት እንዲሰራ አዞታል ። ከታች የምንጠቅማቸው ጥቅሶች ማስረጃዎች ናቸው ።

መ. <u>ዘጸአት 34 ፥ 1</u> “ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው ሁለት ጽላቶች እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ በሰበርካቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን እጽፍባቸዋለሁ ”

ሠ. <u>ዘዳግም 10 ፥ 1 — 5</u> “ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እንደፊተኞቹ ያሉትን ሁለት የእብነበረድ ጽላቶች ጠርበህ ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ ” አለ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች የሰጠሁህን ጽላት ሰብረሃልና ከእንግዲህ ጽላት አያስፈልግህም የሚል ሃሣብ የያዙ ሆነው ተገኝተዋል? አያችሁ በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንትን ትምህርት አታዳምጡ ያለው ጳውሎስ ለዚህ ነው ።

ታቦት ማለት ትርጓሜው ማደሪያ ሲሆን ነገር ግን ለማደሪያነት ብቻ ማይሆን መታያም መግለጫም ነበር ። ንጉሥ በዙፋን እንዲገኝ ፤ እንዲገለጥ ታቦት የእስራኤል አምላክ መገለጫ ነው። ባጠቃላይ ታቦት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለምሕረት ለሕዝቡ በሚገለጥበት ጊዜ ዙፋኑ ነው ።



<u>ታቦት የጽላት ማደሪያነቱ</u>

ሀ. <u>ዘዳግም ፥ 10 ፥ 1—5</u> “ . . . ለአንተም የእንጨት ታቦት ሥራ ከግራር እንጨትም ታቦትን . . . ሠራ ጽላቶችንም በሠራሁት ታቦት ውስጥ አደረግኋቸው እግዚአብሔርም እንዳዘዘ በዚያ ኖሩ” ታዲያ ታቦትን የሰይጣን መመለኪያ ጣኦት አድርገው የሚያዩ ሰዎች ምን ያህል እንደተሣሣቱ ተረድተውት ይሆን ? በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተሰራውን ታቦት ማንቋሸሽ እግዚአብሔርን መናቅ ማዋረድ ነው ። እነዚህን ጥቅሶች ልብ ብለህ ተመልከታቸው ። ዘጸ 25 ፥ 10 — 40 ፥ ዘጸአት 37 ፥ 1 — 29 ዘጸ 26 31 — 37

አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ሲሳለሙ የቤተክርስቲያንን ደጅ በእጃቸው እያሻሹ ፊታቸውን ሰውነታቸውን ሲተባበሱ ሲያዩ ፤ ይሣለቁባቸዋል ። ከመጽሐፍ ቅዱስም የወጡናቸው እያሉ ይተቻሉ ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ያላነበቡና ያላወቁ እነሱ ሆነው እናገኛቸዋለን ዘጸአት 30 ፥ 22—38 ያለውን ስንመለከት እግዚአብሔር ለሙሴ ከተለያዩ ጥሩ ሽታና መዓዛ ካላቸው ነገሮች ቅዱስ ቅባት እንዲሰራ አዘዘው በዚያም ከመገናኛው ድንኳን ጀምሮ በውስጡ የሚገኙትን ነዋየ ቅዱሳት እንዲቀባና እንዲቀድስ ነገረው ፤ እነሱንም የነካ ቅዱስ እንዲሆን እግዚአብሔር በማይታበል ቃሉ ተናገረ ይህም ስርዓት ለትውልድ እንዲተላለፍና እንደማይቋረጥ ተናገረ ።

እንግዲህ በቅብአ ሜሮን የተቀደሰውን ቤተክርስቲያን ማሻሸት መሣም የሚቀድስ መሆኑን አውቀን አደረግነው እንጂ ባለማወቅ አላደረግነውም ።

<u>ስለ ቤተመቅደስ</u>

ለጽላቱ ማደሪያ የሚሆን ታቦት እንደተሰራ ሁሉ ቤተ መቅደስ ደግሞ ለታቦቱ ማደሪያ ይሆን ዘንድ ተሰራ ። በመጀመሪያ የመገናኛ ድንኳን ነበረ ይኸውም ፦

በአሪት ዘፀአት 33 ፥ 9 -- 11 ባለው የተጠቀሰው ነው ። ቀጥሎም ሰለሞን ታላቁን ቤተ መቅደስ ሠራ 1ኛ ነገሥት 8 ፥ 1 — 66 ቤተ መቅደስ ሠርቶ እንደጨረሰ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እግዚአብሔር ለዘላለም የሚኖርበት ማደሪያ ቤት መስራቱን ተናገረ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ እንዲህም አለ ። በፍጹም ልባቸው በፊትህ ለሚሄዱ ባሪያዎችህ ቃል ኪዳንንና ምህረት የምትጠብቅ ብሎ

ቃል ኪዳን ጠባቂነቱን ተናገረ ። እንዲሁም የእግዚአብሔር ዓይኖች በቤተመቅደስ እንደሆን ስሙም በቤተመቅደስ እንዲመሰገን ። ሕዝቡ ሁሉ በዚህ ቤተመቅደስ የሚጸልዩትን ጸሎት እንዲቀበል በቤተ መቅደስ መጥተው ስለሃገር ስለግል ሕይወታቸው የሚያቀርቡትን ጸሎት እንዲሰማቸው ቃል አስገባው ። እግዚአብሔርም በ1ኛ ነገሥት 9 ፥ 1 —9 ባለው ላይ ሰለሞን ለጠየቀው ሁሉ የእሽታ መልስ መስጠቱን እናነባለን ።

## ለታቦት ሊደረግ የሚገባ ክብር

ታቦት የእግዚአብሔር የክብሩ መግለጫ ዙፋን እንደሆኑ ሁሉ ይከበር ዘንድ ግድ ነው ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት እናያለን ።

— መጽሐፈ ሣሙኤል ቀዳማዊ 4 ፥ 5 " የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ እስራኤል ሁሉ ታላቅ እልልታ አደረጉ " ምዕመናን ታቦት በሚወጣ ጊዜ እልልታ የሚያቀርቡት የሚያጨበጭቡት ይህን መሰረት አድርገው ነው ።

— መጽ ሣሙኤል ከልዕ 6 ፥ 16 — 23 ዳዊት ለታቦተ ጽዮን የሚገባውን ክብር ሲያቀርብ ሜልኮል እንደናቀችው ( እንደ ዛሬዎቹ መናፍቃን ) እግዚአብሔር በሜልኮል ትዕቢት ተቆጥቶ ሜልኮልን መካን እንዳደረጋት ይገልጻል ።

— ዘጸአት 3 ፥ 5 " ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ " ምዕመናን ቤተመቅደስ የተቀደሰች ስፍራ መሆንዋን ያምናሉና ወደ ተቀደሰችው ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጫማቸውን አውልቀው ነው ለሙሴ የተሰጠው ትዕዛዝ ምዕመናንን ሁሉ ይመለከታልና ።

— መጽ ኢያሱ 5 ፥ 15 " አንተ የቆምክባት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ " ሥጋውና ደሙ ከሚሠዋበት ፤ ስሙ ከሚጠራባት ከቤተ ክርስቲያን የበለጠ ቅዱስ ስፍራ በምድር ላይ የት ይገኝ ይሆን ? ስለዚህ ክርስቲያኖች ለኢያሱ የተሰጠው ትእዛዝ እነሱንም እንደሚጠቀልል ያውቃሉና ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጫማቸውን ያወልቃሉ ። በዚህም ትዕዛዝ እግዚአብሔርን ፈጻሚዎች መሆናቸውን ይመሰክራሉ ።



— መጽ. ኢያሱ 3 ፥ 3 " ሕዝቡን የአምላካችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ከስፍራችሁ ተነሥታችሁ ተከተሉት በእናንተና በታቦቱ ያለው ርቀት በስፍር ሁለት ሺህ ክንድ ያህል ይሁን በዚህ መንገድ በፊት አልሄዳችሁበትምና የምትሄዱበትን መንገድ እንድታውቁ ወደ ታቦቱ አትቅረቡ ብለው አዘዙ "

ይህ ሁሉ ሥርዓት ዛሬም በጥንታዊት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል ።

— ዘሌዋውያን 16 ፥ 2 " እኔ በስርየት መክደኛው ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ስርየቱ መክደኛው ወደ ተቀደሰው ስፍራ ሁል ጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው " የእግዚአብሔርን ቤት እንደማንኛውም ቤት ያለምንም ዓላማ የምንወጣበት የምንገባበት የምንጨፍርበት አይደለምና ደግሞም ከጸሎት በስተቀር ዓለማዊ ድርጊቶች በፍጹም አይደረጉበትም ።

— ዘሌዋውያን 26 ፥ 1 " እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ለእናንተ ጣኦት አታድርጉ የተቀረጸም ምስል ወይም ሐውልት አታቁሙ ትሰግዱለትም ዘንድ በምድራችሁ ላይ የተቀረጸ ድንጊያ አታኑሩ ። ሰንበታቴን ጠብቁ መቅደሴንም ፍሩ "

የተቀረጸ ምስል የተባለው ሁሉ ታቦትን እንደማይመለከት ከላይ ያረጋገጥነው ነው ። መቅደሴንም ፍሩ ብሎ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ እንኳን በመራድ በመንቀጥቀጥ መሆን እንዳለበት ገለጸልን ።

ደግሞም ታቦትን ሊነኩ የሚገባቸው ካህናት ብቻ እንደሆኑ እግዚአብሔር በዖዛ ትምህርት ሰጥቶናል ። ዖዛ ባይገባው የእግዚአብሔርን ታቦት ስለነካ እግዚአብሔር ቀሰፈው 1ኛ ሣሙኤል 6 ፥ 6 —7 ተመልከት ። እኛም በድፍረት ሳይገባን የጌታን ታቦት ከነካን እንቀሰፋለን ።

ይህ ሁሉ በብሉይ ኪዳን የነበረ ስርዓትና አምልኮት ነው ። በሐዲስ ኪዳን ግን ቀርቷል የሚሉ አሉ ። ይህም ለማስመሰል ሰውን ለማማለት እንጂ በሐዲስ ኪዳንም ከላይ የጠቀስናቸው ሥርዓታት ክርስቲያናዊ ሕግና ሥርዓት ሆነው እናገኛቸዋለን ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ክርስቲያን አገሮች በተለየ ሁኔታ የብሉይ ኪዳን ሥርዓትና ሕግን ወደ ክርስትና ሕግና ስርዓት ለውጣ ትጠቀምበታለች ። ይህም ሊሆን

የቻለው ከቤተ ይሁዳ ቀጥላ እግዚአብሔርን በመቀበል ( በአምልኮተ እግዚአብሔር ውስጥ በመግባት ) ከሌሎች ሀገሮች ቀደምትነት ያላት ስለሆነ ነው ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ሕግና ስርዓት አልፋለች ። ከብሉይ ኪዳን ሕግና ስርዓቶች ብዙዎችን የወሰደች ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ነው ።

አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሰራበት ጊዜ ከፅድ ወይም ከእብነበረድ ተቀርጾ በላዩ የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ስም ( ሕቡዕ ስም ) አልፋና ኦሜጋ ተጽፎ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሠየማል ። በቅዳሴም ጊዜ ሕብስቱና ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ፥ ወይኑን ደም መለኮት ወደ መሆን የሚለውጠው በዚሁ በታቦቱ ላይ ነው ። ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ታቦት የሐዲስ ኪዳን ታቦት ለየት ያለ ነው ። ያ ምሣሌያዊ ሲሆን ይህ ግን አማናዊ ነው ።

የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእስራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን ነበር የሐዲስ ኪዳን ታቦት ግን የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትበት ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ፥ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ እያለ ያመኑትን ሁሉ የሚጠራበት የምሕረት መሰዊያ ነው ። ክብርና ስግደትም የሚደረግለት ስለዚህ ነው ።

<u>እግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ባርኮ በሐዲስ ኪዳን እንደሰጠ የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ፥</u>

— <u>ማቴ. 5 ፥17</u> " እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ " ባለው አምላካዊ ምስክርነት የኦሪት ሕጋትና ስርዓት ሁሉም አለመሻራቸውን ልንጠቅስ እንወዳለን ። የሻራቸውን ሰዋዊ ስርዓቶች ራሱ በቅዱስ ወንጌል ገልጾልናል ። ታቦት ግን ሕገ እግዚአብሔር እንጂ ሰው በፈቃዱ የመሰረተው ሕግ ስላልሆነ አልተሻረም ምሣሌነቱ አማናዊ ሆነ እንጂ ።

ቅዱስ ጳውሎስ እንኳን አይሁድን ላለማደናገር ሥርዓተ ኦሪትን ሲፈጽም ይታይ ነበር ለምሣሌ በታናሽ እስያ ሲያስተምር በነበረበት ጊዜ ጢሞቴዎስ የተባለውን ወጣት ሊያስከትል ሲጠራው በዙሪያው ብዙ አይሁድ ስለነበሩ እነሱን ለማስደሰት ገዝሮ አስከትሎታል። የሐዋ. ሥራ 16 ፥ 3 እሱም ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ



በሕገ ኦሪት የተጻፈውን የብፅአት ሥርዓት ያደርስ ነበር። ለምሣሌ በክንክራኦስ ስለቱን ለማድረስ ራሱን መላጨቱ የሚታወስ ነው ። የሐዋርያት ሥራ 18 ፡ 18 ይህም የኦሪት ስርዓት መሆኑን ለማወቅ ብንሻ ዘኁ. 6 ፥ 9 መመልከት ይቻላል ።

ጌታ ራሱ ቤተ መቅደስን አድሶ ባርኮ እንደሰጠን ሊያስረዳን በመቅደስ የሚገበያዩትን ሁሉ አስወጥቶ " ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት" ማቴ. 21 ፥ 12 — 13 ብሏል የቤተ መቅደስ ማለፍ የተገለጸው ጌታ በመስቀል ላይ ሁሉ ነገር ተፈጸመ ብሎ በተናገረ ጊዜ ነው ያን ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መቀደዱ ከእንግዲህ ወዲህ ቤተመቅደስና በውስጡ ያለው ስርዓት አያስፈልግም ማለቱ ነው ሲሉም ይሰማሉ ።

በመሰረቱ ጌታ ተፈጸመ ያለው ነብያት ይወርዳል ይወለዳል ስለኃጢያታችንም ተላልፎ ይሰጣል እኛን ከሰይጣን ባርነት ነጻ ለማውጣት እንደ ወንበዴ ተቆጥሮ ይሰቀላል ተብሎ የተነገረው የነቢያት ትንቢት ተፈጸመ ማለቱ ሲሆን የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መከፈሉም ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ከታዩት ሰባት ተአምራት አንዱ ነው እንጂ አሁንም የቤተ መቅደስን ስርዓት ማለፍ የሚጠቁም አይደለም ። እንዲህማ ቢሆንኖሮ ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ኦሪት ስርዓት ሊጸልዩ ባልሄዱ ነበር ፥ የሐዋርያት ሥራ 3 ፥1 ። ጳውሎስም በ2ኛ ቆሮ. 6 ፥ 16 " ታቦትን በጣኦት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው " ብሎ ተቆርቋሪነቱን ለእግዚአብሔር ታቦት ባላሣየ ነበር ።

- <u>1ኛ ጢሞ. 3 ፥15</u> " . . . በግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ ቤቱም የእውነት አምድና መሰረት የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው " ።

እውን ጳውሎስ በቤተክርስቲያን እንኖር ዘንድ በጢሞቴዎስ ውክልና አሣወቀን ቤተመቅደስ በሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተብሏል ። ደግሞስ ሰሎሞን በ1ኛ ነገሥት 18 ፥ 13 ላይ እኔም ለዘላለም የምትኖርበት ማደሪያ ቤት በእውነት ሠራሁልህ እያለ እንዴት ተሸሯል ይባላል ። እግዚአብሔርም የሰሎሞንን ልመና ሲያጸድቅለት " በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ ለዘለዓለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ

ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ " ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ " ። 1ኛ ነገሥት 7 ፥ 3 ብሎ የለምን? ይህን ቃል ኪዳኑን ሽር በሐዲስ ኪዳን ሕገ ኦሪት እንዳለ ተሽሯል እንዴት ይባላል ? ። ይኸ እግዚአብሔርን ማስዋሸት አይሆንም ? ። እርሱስ ክብርና ምስጋና ይግባውና የተናገረውን ቃሉን አያጥፍም ። ዛሬም ቃሉን አክብር በቃሉ አለ ። ቀድሶ የሰጠን ቤቱን ዛሬም እርሱ ይገኝበታል ።

— <u>ዕብ. 7 ፥ 1—14</u> የፊተኛይቱ ሥርዓት ከአሁኑ ሥርዓት ለየት ያለመሆኑ የብሉይ ኪዳኑ ሥርዓት ለአዲስ ኪዳኑ ስርዓት እንደ ምሳሌ እንደነበር ። አሁን ግን በአማናዊ ሥርዓት ውስጥ መሆናችንን ይገልጻል ። እንጂ የፊተኛው ሥርዓት ጭራሽ ተፍቋል አላለም ።

— <u>ራእይ 11 ፥ 1 — 17</u> " እንኳን በምድር በሰማይም የኪዳኑ ታቦት እንዳለ ይነግረናል ።



## ምዕራፍ ፲፭

### <u>መስቀል</u>

ከጌታ በፊት መስቀል የመቅጫ መሣሪያ ነበር ። ሰውን በመስቀል ላይ መስቀል የተጀመረው በፋርስ ነው ። በፋርስ ሰዎች አምልኮት የመሬት አምላክ ( አርሙዝድ ) ይባላል ። ወንጀለኛ በሀገራቸው ሲገኝ ቅጣቱን በመሬት የተቀበለ እንደሆነ አምላካቸው እንዳይረክስ ወንጀለኛውን ሁሉ በመስቀል ይሰቅሉት ነበር ። ይህ አድራጎት እንደ ልማድ ሆና በሮማ ግዛት ሁሉ የተለመደ ሕግ ሆነ ። በኦሪትም ሥርዓት በመስቀል በስቅላት የሚቀጡ ርጉማንና ውጉዛን ነበሩ ። ከጌታ በኋላ ግን የነጻነታችን አዋጅ የተነገረበት ሰላማዊ ዙፋን ስለሆነ ፥ ለክርስቲያኖች ሁሉ የነጻነትና የድል ምልክት ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን ፥ እኩልነትን በመስቀሉ አድርጓልና ። ይህ የመስቀል አማናዊና ምሥጢራዊ ኃይል ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ላመኑት ነው እንጂ ላላመኑ አልደረሳቸውም ። እንዲያውም መስቀልን ኃይለ እግዚአብሔር ነው ማለቱ ዋዛ ይመስላቸዋል ። መስቀልን በመቅጫነቱ የሚመለከቱት ብዙ ናቸው እርግጥ መስቀል ለሞትና ለኢጋንንት መቅጫ ሆኗል ።

### <u>ጌታ የተሰቀለው በተመሳቀለ እንጨት (በመስቀል ) ላይ እንጂ ቀጥ ባለ እንጨት ላይ እንዳልሆነ</u>

ጌታ ቀጥ ባለ እንጨት ላይ ነው የተሰቀለው የሚሉ ክፍሎች ለማስረጃነት ከሚያቀርቡ አቸው ጥቅሶች መካከል የሐዋ. ሥራ 5 ፥ 30 እና 10 ፥ 39 ያለውን ነው ። በነዚህ ቦታዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በእንጨት መስቀል መሰቀሉን ይገልጻሉ እንጂ ቀጥ ባለ እንጨት ተሰቀለ አይሉም ። በእንጨት መስቀል መሰቀሉን እኛም እናምናለን ። በብረት መስቀል ተሰቀለ ያለ የለም ። ነገር ግን ጌታ በመስቀል ላይ መሰቀሉን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ሲሉ ያስረዱናል ።

— <u>ቆላ. 1 ፥ 20</u> " . . . በመስቀል ባፈሰሰው ደሙም ሰላምን አደረገ " ይላል ። ቀጥ ያለ እንጨት ከወፈረ ግንዲላ ወይም ግንድ ከቀጠነም በትር ወይም ዱላ ይባላል እንጂ መስቀል አይባልም ።

— ማቴ. 27 ፥ 32 " ስምዖንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደ ዱት " መስቀያውን ቢል ኖሮ ቀጥ ያለ እንጨት ሊሆንም ይችል ነበር ፤ ግን ለይቶ ቅርጹን ሲናገር መስቀሉን አለ ።

— ማርቆስ 15 ፥ 29 — 30 " ከመስቀል ወርደህ ራስህን አድን አሉ " ከተሰቀልክበት እንጨት ላይ አላሉትም ። አይሁድ የሰቀሉት በተ መሳቀለ እንጨት ላይ ስለነበር ከመስቀል ወርደህ አሉት።

— ዮሐ. ወን. 19 ፥ 17—19 " መስቀሉንም ተሸክሞ . . . " መስቀያውንም እንጨት ሳይሆን ያለው ፤ ለይቶ መስቀሉን ማለቱን ልብ እንበል ።

— ዕብራ. 12 ፥ 1 — 2 " . . . እርሱ ነውርን ንቆ . . . በመስቀል ታግሶ . . . " በመስቀያው እንጨት ሳይሆን ያለው ፤ በመስቀል ነው ።

— ኤፌ. 2 ፥ 14 — 17 " በመስቀል ላይ በሞትም . . . "

— ፊልጵ. 2 ፥ 8 " . . . ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ " የተሰቀ ቀለው ቀጥ ባለ እንጨት ላይ ሳይሆን በመስቀል ላይ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል ።

— ገላ. 6 ፥ 14 " እኔ ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም " ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ መመኪያ የለኝም ማለቱ የክርስቲያኖች መመኪያ መስቀል መሆኑን መግለጹ አይደለምን ? ታዲያ ፀረ—መስቀሎች አባትህ ወይም አጎትህ የተገደለበትን ሽጉጥ ትወዳዋለህ ታከ ብረዋለህ ወይ ? እያሉ የማይሆን ምሳሌ የሚመስሉት ለምን ይሆን የየዋሃንን ልቡና ለመስለብ ይሆን ? ጳውሎስ እንዲህ ይለናል "ክር ስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ የሚለው ቃል ለሚጠፉት ሰዎች እንደሞኝነት ይቆጠራል ። ለዳንነው ለእኛ ግን የእግዚአ ብሔር ኃይል ነው " 1ኛ ቆሮ. 1 ፥ 18 ። ጌታም ራሱ መስቀሉን ጥሉ ሳይሆን ያለው " ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ " ማርቆስ 8 ፥ 34 ።

የጥፋት ልጆች ግን ክርስቶስ ለማን እንደሞተና ይልቁንም ማን ም ሳያስገድደው በገዛ ፈቃዱ እንደተሰቀለ መረዳቱ እንደ ሰማይ ርቆ ባቸው ፤ የማይሆን ምሳሌ ሲመስሉ ይገኛሉ ። ጌታ አይሁድ ሊሰቅ



ሉት ስለፈለጉና እርሱም ማምለጥ ስላልቻለ ለመስቀል የበቃ አድ ርገው ማቅረባቸው ከክርስትና እምነት የወጡና ተረፈ አይሁድ መሆ ናቸውን ይመሰክርባቸዋል ። እኛስ የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክር ስቶስ አዳምንና የአዳምን ልጆች ከግብርናተ ዲያብሎስ (ከዲያቢሎስ ባርነት) ነጻ ሊያወጣ በገዛ ፈቃዱ ንጽሕት ቅድስት ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን እንደተወለደና በመስቀልም በፈቃዱ ተሰቅሎ አዳምን ከነልጆቹ ነፃ እንዳወጣ እናምናለን ። ስለሆነም ራሱ ፈቅዶ ባደረገው ሞቱ እንመካለን ፤ ድህነትንም አግኝተንበታል እንጂ ፤ እንደ አባታ ታችን ወይም እንደ ሌላ ዘመዳችን ሞት ሳይወድ በግዱ የተቀበለው አይደለም ። ደግሞስ የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት መስቀል ቀርቶ እግሩ የረገጠው መሬት እንኳን ምን ያህል እንደከበረና ቅዱስ እንደ ተባለ አላነበቡ ይሆን ? 2ኛ ጴጥ. 1 ፥ 18 " . . . በቅዱስ ተራራ " ምሳሌያ ቸውም የማይመስል ስለሆነ በአላዋቂነታቸው ታዝበናቸው ከማለፍ ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን ፤ መቼም አላዋቂን ለማግኘት እሩቅ መ ሄድ አያስፈልግም ተብሏል ፤ በቅርቡ አውቃለሁ ብሎ ሲቀባጥር ይገ ኛልና ።

የመስቀል ጠላቶች ፥

1ኛ ፊልጲ. 3 ፥ 17 — 21 " . . . ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ ብዙ ጊዜ ስለእነርሱ እፈሯችሁ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላችኋለሁ "

ለመስቀል መስገድ እንዲገባን

መዝሙር 131 (132) ፥ 7 " . . . እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን ። ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን እግሮቹ በመስቀል ላይ ተቸንክረው ውለዋል ።

ማጠቃለያ

በቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ የመስቀል አይነቶች አሉ የወርቅ የብረት ፤ የእንጨት

የእንጨቱ መስቀል የተሰቀለበት ስለሆነ ነው ። የብረት መስ ቀል አባቶቻችን የሚይዙበት ምክንያት በብረት መስቀል ተሰቀለ ማለት ሳይሆን እጁና እግሩን የተቸነከረበትን ጎኑ የተወጋበትን የብ ረት ችንካር ለማመልከት ነው ። የወርቅ መስቀል የሚይዙበት ደግሞ ወርቅ ንጹህ እንደሆነ ሁሉ በመስቀል ላይ የተሰቀለው አምላካችንም ንጹሐ ባህርይ አምላክ እንደሆነ ለመግለጽ ( ለማስረዳት ) ነው ።

# ምዕራፍ ፲፱

## ስግደት

ስግደት በሁለት ይከፈላል እነዚህም የባሕርይና የፀጋ ተብለው ይከፈላሉ ። የባሕርይ ወይም የአምልኮት ፣ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ ሲሆን ፣ ፈጥረኸናል ፣ ትገዛናለህ ለወደፊቱም ተስፋ መንግሥተ ሰማይን ታወርሰናለህ ብለን የምንሰግድለት ነው ።

የፀጋ ወይም የአክብሮት ፣ ለእመቤታችን ለቅዱሳን ፣ ለጻድቃን ፣ ለመላእክት ሁሉ እግዚአብሔር መርጦአችኋል ፣ አክብሮአችሁማል ፣ እኛም እናከብራችኋለን ብለን የምናቀርበው ነው ።

### ለመላዕክት የፀጋ ስግደት እንደሚገባ

— ዘፍ. 19 ፥ 1-2 " ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ ። ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር ፤ ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ ፣ ፊቱን ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ "ለመላእክት መስገድ ባይገባ ኖሮ ሎጥ ባልሰገደ ነበር ። ሰው መስለውት ነው የሰገደው የሚሉ ካሉ ፣ ለሰው ከተሰገደ ለመላእክት ለምን አይሰገድም ? ደግሞስ ለወጣ ለገባ ሰው ሁሉ ይሰገዳል እንዴ ? ያም ሆነ ይህ እኛም የሎጥን ፈለግ በመከተል ለመላእክት እንሰግዳለን ።

— ዘኍልቊ 22 ፥ 31 " እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ፣ የእግዚአብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ ፣ ሰገደም በግንባሩም ተደፋ " ወደድንም ጠላንም የመላእክት ተፈጥሮአቸው ማለትም ክብራቸው በፊታቸው ቻለን እንድንቆም አያደርገንም ። ወደን ባንሰግድም እንደ በልዓም ከክብራቸው ጽናት የተነሣ በአፍ ጢማችን ተደፍተን እንሰግዳለን ። በግዴታ ከመስገድ በውዴታ ክብራቸውን በማወቅ መስገዱ ከእግዚአብሔርም ዋጋ ያሰጠናል ፣ በእነርሱም ዘንድ ባለሟልነትን እናገኛለን ፣ በመከራችንም ጊዜ ይረዱናል ።

— መጽሐፈ ኢያሱ 5 ፥ 13 " . . . እርሱም አይደለሁም እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ አለ ፣ ኢያሱም

ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው አለው ፤" "የምታመልኩትን ከአሁን ምረጡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን "ያለው ኢያሱ ለመላእክት መስገድ ተገቢ ባይሆን ኖሮ ለመልአኩ ባልሰገደ ነበር ተገቢ መሆኑን ስለሚያውቅ ሰገደ ። እንግዲህ ከኢያሱ የሚበልጥ በአሁን ዘመን ይኖር ይሆን ?

— <u>መጽ ዜና መዋ. ቀዳማዊ 21 ፥ 16</u> " ዳዊትም ዓይኖቹን አንሳ

የእግዚአብሔርም መልአክ በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ አየ ፤ ዳዊትም ሽማግሌዎቹም ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ተደፉ "በግንባር መደፋት መስገድ አይደለም ! እንግዲህ " እንደ ልቤ የሚሆነኝ ዳዊትን አገኘሁ" ብሎ እግዚአብሔር እንኳን ለዳዊት መስክሮለታል ፤ ለመላእክት መስገድ ተገቢ አለመሆኑን ቢያውቅ ኖሮ ለመለአኩ ባልሰገደ ነበር ። ዳሩ ግን ትሁት ነውና ለእግዚአብሔር መልአክ መስገድ ተገቢ መሆኑን አውቆ ሰገደ ። በዚህም እግዚአብሔር አልተቆጣውም ።

— <u>ትንቢተ ዳንኤል 8 ፥ 15</u> " . . . ዳንኤል ለቅዱስ ገብርኤል በኡ

ባል ወንዝ መካከል ሰግዷል። ደንግጦ እንጂ ወዶ አይደለም ሊሉ ይችላሉ ። ዳሩ ግን በመደንገጥ የማይገባውን ነገር ቢያደርገው ኖሮ በሁለተኛ ጊዜ ባናገረው ወቅት ተረጋግቶ ስለነበር ባልሰገደለትም ነበር ። ዳሩ ግን ዳንኤል በመፍራት ሳይሆን በአክብሮት ነው ለቅዱስ ገብርኤል የሰገደለት ። ለመላእክት መስገድ የማይገባ ከሃይማኖት ውጭ ቢሆን ኖሮ ዳንኤልም ቀደም ብለን የጠቀስናቸው ሁሉ ባልሰገዱ ነበር ። ዳንኤልም በአምልኮተ እግዚአብሔር ብቻ የተወሰነ መሆኑ የታወቀ ነው ። በፍርሃት እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ነገር አልሠራም ። ዳርዮስን ፈርቶ ለጣኦት አልሰገደምና ። ለተራቡ አንበሶች እስኪጣል ድረስ በአምልኮተ እግዚአብሔር የተጠመደ መሆኑ ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም ከአክብሮት አንጻር ነው ።

— <u>መጽሐፍ መሳፍንት 13 ፥ 20</u> ማኑሄና ሚስቱ ለመልአኩ ሰግደዋል

— <u>የዮሐንስ ራዕይ 19 ፥ 10</u> " በመልአኩ እግር ፊት ሰገድኩለት እሱ

ግን አትስገድልኝ ሁለታችንም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነንና ለእግዚአብሔር ስገድ አለው "
ይህን በመጥቀስ ለመላእክት መስገድ ተገቢ አይደለም የሚሉ



ክፍሎች አሉ ። ዳሩ ግን የመልአኩን አባባል ካለመረዳት እንጂ ለመላእክት መስገድ ከሃይማኖት ውጭ ሆኖ ዮሐንስ ባለማወቅ የሰገደለት ሆኖ አይደለም ይህንንማ እንዳንል የሰጋጁ የዮሐንስ ማንነት ያግደናል።ዮሐንስ ድንግላዊና የጌታ ሐዋርያ ከመሆኑም ሌላ ጌታ የሚወደው ፤ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ፤ ወንጌልን መልእክታትን የጻፈ ፤ እንዲሁም የዓለምን ፍጻሜ በራእይ ያየ ነው ። ይህን ያህል የጌታ ባለሟል የሆነ ቅዱስን ሰው ስለትንሽዋ ነገር ለመላእክት መስገድ ተገቢ አለመሆን አጥቶት በስሕተት ሰገደ ማለት የጻፋቸው ወንጌሎችም መልእክታትም ስሕተት አላቸው ማለት ነው ። ይህ ማለት ግን ሰው እንደ እግዚአብሔር ፍጹም ነው ማለት አይደለም ። እሱ በፍጹም እምነት ውስጥ ሳይሆን ፤ እሱ ማን መመለክ እንዳለበት ሳያውቅ ለእኛ ማሳወቅ አይችልምና ፤ ስለዚህ በስሕተት ሰገደ ማለት ከፍተኛ ስሕተት ነው። ዮሐንስ ለመልአኩ የአክብሮት ስግደት ያቀረበው ለመላዕክት መስገድ ተገቢ መሆኑን ስላወቀ ነው ። መልአኩም ደግሞ አትስገድልኝ ማለቱ የዮሐንስን ክብርና ማዕረግ መግለጡ ነው። ዮሐንስ በክብሩ ከመልአኩ እኩል ሆኖ ነበርና ። ስግደት ደግሞ የበላይና የበታች መግለጫ ስለሆነ አንተ'ኮ በክብር ከእኔ እኩል ነህ ፤ ስለዚህ ለእኔ ልትሰግድ አይገባም ቢለውም ዮሐንስ ግን ከመስገድ ወደ ኋላ አላለም ትሁት ነውና። ይህንንም ለማረጋገጥ ከፈለግን ራእይ 22 ፥ 8 — 7 እንመልከት ። እንግዲህ ዮሐንስ ተሳስቶ ሰገደ ቢባል እንኳን ሁለት ጊዜ ይሳሳታል ? የመጀመሪያው እንስ ? እንግዲህ አባባሉ የትሕትና አባባል መሆኑ ግልጽ ነው ።

<u>ለቅዱሳን መስገድ ተገቢ ስለ መሆን</u>

— <u>መጽ. ሳሙኤል ቀዳማዊ 28 ፥ 14</u> " ሳኦልም ሳሙኤል እንደሆነ

አወቀ ፤ በፊትም ተጐንበሰ ፤ በምድርም ላይ እጅ ነሣ " ሳኦል ሳሙኤልን በማክበር መስገዱን ልብ እንበል ፤ ሳሙኤል ደግሞ ለምን ትሰግድልኛለህ ተገቢ አይደለም አላለውም ።

— <u>መጽሐ. ነገ. ካልዕ 2 ፥ 15</u> " ከኢያሪኮም መጥተው በአንጻሩ የነ

በሩት የነቢያት ልጆች ባዩት ጊዜ የኤልያስ መንፈስ በኤልሣዕ ላይ አርፎአል አሉ ፤ ሊገናኙትም መጥተው በፊቱ ወደ ምድር ተደፉ " እያችሁ መንፈስ ቅዱስ ሳደረባቸው በእግዚአብሔር ለተመረጡ ቅዱሳን አባቶች መስገድ ተገቢ መሆኑን የነቢያቶቹ ልጆች አውቀው እንደሰገዱ ?

— መጽ. ነገ. ቀዳ 19 ፥ 7 “ አብድዩም በመንገድ ሲሄድ እነሆ ኤልያስ ተገናኘው ፤ አብድዩም አወቀው ፤ በግንባሩም ተደፍቶ ጌታዬ ሆይ ፥ ኢልያስ አንተ ነህን ? አለው ። ኤልያስና ኤልያስን የመሰሉ ቅዱሳን በእግዚአብሔር የተመረጡ ስለሆነ ያያቸው ሁሉ ይወዳቸው ያከብራቸው ዘንድ ይገደዳል ። መንፈሳዊ የሆነው ሰው አብድዩም የኤልያስን ቅድስና ያውቅ ነበርና በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደለት ። መስገዱ ስሕተት ቢሆን ኖሮ ኤልያስ በዝምታ ባላለፈው ነበር ። ተሣስተሀል ባለው ነበር ። ግን አላለውም ፤ በተጨማሪም በሐዋ. ሥራ. 14 ፥ 8—17 ላይ እንደተጠቀሰው ቅዱስ ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራንና ደርቤን በተባሉት የሊቃኦንያ ከተማዎችና አካባቢያቸው ወዳለው አገር ወንጌልን ሲሰብኩ ቅዱስ ጳውሎስ በአካባቢው አንድ እግሩ የሰለለና ከእናቱም ማኅጸን ጀምሮ አንካሳ የሆነን በሽተኛ ሲፈውሰው ሕዝቡ ጳውሎስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ አማልክት አድርገዋቸው ካህናቱ ጭምር ኮርማዎችን አምጥተው መስዋዕት ሊያቀርቡላቸው እንደተዘጋጁ በሰሙ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስና በርናባስ ልብሳቸውን ቀድደው እየጮሁ ወደ ሕዝብ መካከል እንደሮጡ ይነግረናል ፤ እዚህ ላይ ታዲያ ጻድቃን ሰማእታትና ሐዋርያት ለእግዚአብሔር ብቻ መደረግ የሚገባውን የአምልኮ ክብር ሕዝቡ እንዲያቀርቡላቸው እንዳልፈለጉና እንዳልተቀበሉ እንረዳለን ። ሆኖም የፀጋ ስግደት ወይም የአክብሮት ስግደት ሲደረግላቸው ተቃውሞ አላቀረቡም ። ከዚህ የምንረዳው መከባበር ተገቢ መሆኑን ነው ።

— ትን. ዳንኤል 2 ፥ 46 “ የዚያን ጊዜ ናቡከደነጾር በግንባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት ” ንጉሡ ናቡከደነፆር እንኳን ለወጣቱ ለዳንኤል መስገዱ የእግዚአብሔር ኃይል በዳንኤል ላይ መኖሩን በማወቁ አይደለምን ?

— መጽ. ሳሙኤል ካልዕ 1 ፥ 1 - 2 “ በሶስተኛው ቀን እነሆ ከሳኦል ሠፈር አንድ ሰው ልብሱን ቀድዶ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ ወጣ ፤ ወደ ዳዊትም በመጣ ጊዜ በግንባሩ ተደፍቶ እጅ ነሣ ”

— ዘፍጥ. 33 ፥ 1 - 8 ታናሹ ለታላቁ መስገድ እንዲገባ ታናሹ ደግሞ ታላቁን ማክበር የሚገባው ስለሆነ ያዕቆብ ከሶርያ ሚስቶቹንና ልጆቹን ይዞ ተመልሶ ከወንድሙ ከኤሳው ጋር በተገናኘ ጊዜ እስከ ሰባት ጊዜ መላልሶ ከምድር እየወደቀ ለኤሣው ሰገደለት ፤ ከእርሱም በኋላ ልያና ልጆችዋ ባሮቹም ሁሉ ለኤሳው ሰገዱለት



— የሐዋ. ሥራ 10 ፥ 25 “ ጴጥሮስ በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት ፤ ጴጥሮስ ግን ተነሣ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ” ብሎ አስነሳው ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን አክብሮ በሰገደለት ጊዜ ጴጥሮስ ግን በትሕትና ተው ተነስ ብሎ እንዳስነሳው እናያለን ። ይህም ማለት መስገድህ ስሕተት ነው ማለቱ ሳይሆን አይገባኝም ብሎ ራሱን ዝቅ ማድረጉ ነው ።

— ዮሐንስ ራዕይ ፥ 3 ፥ 9 “ . . . እነሆ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ . . . ” እራሱ እግዚአብሔር ለመረጣቸው ቃሉን ለጠበቁትና ሰማዕት ሆነው ላለፉት ወዳጆቹ እንሰግድ ዘንድ ፈቃዱ ነው ።

— መጽ. ነገሥት ካልዕ 4 ፥ 8 “ ገብታም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ፤ በምድርም ላይ ተደፋች ፤ ልጅዋንም አንስታ ወጣች ” በሕይወት ሥጋ እያሉ እንደተሰገደላቸው ሁሉ በአጸደ ነፍስ መላእክት መስለው በሚኖሩበት ሥፍራም ይሰገድላቸዋል ። ለዚሁም ቅዱሳን ሕያዋን እንጂ ምውታን አለመሆናቸውና ከሞቱ በኋላም እንደሚያማልዱ የቅዱሳን አማላጅነት በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር የተጠቀሰውን ይመልከቱ ።

— ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለታቦት መስገድ ተገቢ ስለመሆኑ

ታቦት የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያድርበትና ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት ስለሆነ ሊከበርና ሊሰገድለትም ይገባል ። ፊልጵስዩስ 2 ፥ 10 “ጉልበት ሁሉ ለክርስቶስ ስም ይንበረከክ” ብሏልና ።

— ኦሪት ዘፀአት 33 ፥ 10 “ ሕዝቡም ሁሉ የዳመናው ዓምድ በድንኳንም ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር ። ሕዝቡም ሁሉ ተነስቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር።በድንኳኑ ውስጥ የእግዚአብሔር ታቦት ነበረች ፤ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ከመውደዳቸው ማደሪያውንም ከማክበራቸው የተነሣ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግዱ ነበር ። ይህንን በማድረጋቸው ተመስገኑበት እንጂ አልተነቀፉበትም ።

— መጽ. ኢያሱ 7 ፥ 6 “ ኢያሱም ልብሱን ቀደደ ፤ እርሱና የእሥራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግንባራቸው ተደፉ ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ ”

ፀሐይን ያቆመ ታላቁ የእግዚአብሔር ባለሟል ኢያሱ በእግዚ
አብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ በግንባሩ ተደፍቶ መዋሉ
ለጣኦት መስገዱ ይሆን ?

— <u>መጽ. ሳሙኤል ካልዕ 12 ፥ 20</u> " ዳዊትም ከምድር ተነስቶ
ታጠበ ፥ ተቀባም ፥ ልብሱንም ለወጠ ፥ ወደ እግዚአብሔርም ቤት
ገብቶ ሰገደ " ለቤተክርስቲያን መስገዳችን ዳዊትን አብነት አድ
ርገን መሆናችን መሆኑን ተቃዋሚዎች ይገነዘቡልን ።

— <u>መዝሙር 5 ፥ 7</u> " እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገ
ባለሁ፥አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ "ክር
ቲያኖች እንደ ዳዊት እግዚአብሔርን በመፍራት ለቤቱ እንሰግ
ዳለን እንጂ ጣኦት አምልኮ ልቦናችን ነዶ አይደለም ። ጣኦ
ትም ምን እንደሆነ የምናውቅና እንኳን ልንሰግድለት ቀርቶ ቀና
ብለን በዓይናችን ልናየው የምንጸየፈው ነው ።

— <u>መዝሙር 95 (96) ፥ 9</u> " በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር
ስገዱ " የቅድስናው ሥፍራ ስሙ የሚጠራበት አምልኮቱ የሚ
ፈጸምባት ፥ ክቡር ሥጋው ፥ ቅዱስ ደሙ የሚፈተትባት ቅድ
ስት ቤት ክርስቲያን አይደለችምን !

— <u>መዝሙር 131 (132) ፥ 7</u> " ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን ፥ እግ
ሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን " የእግዚአብሔር ማደ
ሪያው ቤተ ክርስቲያን አይደለችምን ? ታቦት ማለት ራሱ ማደ
ሪያ ማለት አይደለም ወይ ?

— <u>መዝሙር 137 (138) ፥ 2</u> " በመላእክት ፊት እዘምራለሁ ፥
ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ " መላእክት በቅጥረ ቤተ ክርስ
ቲያን ዘወትር አይጠፉም ። ቤተ ክርስቲያንም የተቀደሰች የእ
ግዚአብሔር መቅደስ ነች ። ስለዚህ የዳዊትን ፈለግ ተከትለን
ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያን እንሰግዳለን ፥ በቤተ ክርስቲያ
ንም እግዚአብሔርን በመላእክት ዝማሬ (በያሬዳዊ ዜማ) እና
መሰግለናን ።

— <u>መዝሙር 28 (29) ፥ 2</u> " የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ
በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ " በሚሰለስባት ፥በሚ
ቀደስባት በቤተ ክርስቲያን እንሰግድ ዘንድ ክርስቲያናዊ ግዴታ
ነው ።



— <u>ትን. ሕዝ. 46 ፥ 1 — 2</u> " አለቃውም በስተውጭ ባለው በር
በደጇ ስላሙ መንገድ ገብቶ በበሩ መቃን አጠገብ ይቁም ፥ ካህ
ናቱም የእርሱን የሚቃጠለውን መስዋዕትና የደኅንነቱን መስ
ዋእት ያቅርቡ ፥ እርሱም በበሩ መድረክ ላይ ይስገድ " ለቤተ
ክርስቲያን መስገድ አስፈላጊም ፥ ክርስቲያናዊ ግዴታም ነው
ይህን በትእቢት መንፈስ ያበጠ ልቦናችንን በትሕትና መዶሻ
ሰብረን ለእግዚአብሔር በቅድስናው ሥፍራ ልንሰግድለት ይገ
ባናል ። ለታቦት መስገድ ለእንጨት መስገድ ሳይሆን በላዩ
ላይ ስለሰፈረው ስመ እግዚአብሔርና በውስጡ ስለሚያድረው
መንፈስ እግዚአብሔር ነው ። ለቤተክርስቲያንም መስገዳችን
ለግንቡ ወይም ለቤቱ መስገዳችን አይደለም ፤ በውስጡ ለሚመ
ለክ እግዚአብሔርና በውስጡ ስላሉት ቅዱሳን እንጂ ።

# ምዕራፍ ፲፫

<u>ቅዱሳን ሥዕላት</u>

ሥዕል አምልኮተ እግዚአብሔርን በሚያውቁት በጥንት እሥራኤላውያን ዘንድና ድንጋይ ጠርበው እንጨት አለዝበው ጣእታትን በመሥራት በሚያመልኩ አሕዛብ ዘንድ የአምልኮት መግለጫ እንደነበረ ታሪክ የዘገበው እውነታ ነው ። ይሁን እንጂ የአሕዛብ ቅርጸ ቅርጽ በእግዚአብሔር ዘንድ የተነቀፉ ቢሆንም በእሥራኤል ዘንድ የነበሩት ቅርጸ ቅርጾች ግን ከራሱ ከእግዚአብሔር የተፈቀዱ በመሆናቸው እንደ አሕዛብ ጣእታት የማይነቀፉ የእግዚአብሔር የአምልኮቱ መግለጫዎች ናቸው። ይህንንም በማስረጃ ለማስደገፍ ዘፀ. 25 ፥ 19-20 መጽሐፍ ነገሥት ቀዳማዊ 6 ፥ 23—28 ሕዝቅኤል 9 ፥ 3 መመልከት እንችላለን ።

በዚህ ( ከላይ በተጠቀሱት ) ምዕራፍና ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ ለሙሴ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሰራ እንዳዘዘው እናነባለን ። ይህንንም መሠረት በማድረግ ዛሬም ሥዕለ ኪሩብ በታቦተ ሕጉ ላይ ይሳላል ።

ስለ ሌሎች ቅዱሳት ስዕላት ግን በቤተ ክርስቲያን የተጀመረበት ለየት ያለ ምክንያት አለው ። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት ዋሻ ፈልፍለው ፣ ጉድጓድ ቆፍረው በዋሻ በፉርክታ ውስጥ ነው ። በዚህ ዋሻ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በስዕላዊ መግለጫ እያስደገፉ ያስተምሩ ነበር። በተጨማሪም ስለ ሃይማኖታቸው ሲሉ በአላውያን ነገሥታት ሰይፍ የወደቁትን ሰማዕታት እስከነአማሟታቸው በሥዕል ለመታሰቢያነት ይቀርጹ ነበር ። በዚህ አኳኋን ክርስቲያኖች እምነታቸውን የሚገልጹባቸውን ቅዱሳት ስዕላትን በአክብሮት በመያዝ እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከቆዩ በኋላ በሥዕል ምክንያት በሮምና በባዛንታይ ግዛት በሚኖሩ ክርስቲያኖች ዘንድ አለመግባባት ተፈጠረ ። ለዚሁም አለመግባባት ዋናው ምክንያት አንዳንድ ክርስቲያኖች ሥዕል ከመውደዳቸው የተነሣ ሥዕሎችን አማልክት ናቸው እስከ ማለት ሲደርሱ ( ኢኮኖላትሪያ ) ፣ ሌሎች ደግሞ ጸረ ስዕል አቋም በመያዝ እንዲያውም

ስዕላት መጥፋት አለባቸው በማለት ተነሱ ( ኢኮኖማኪያ ) ። በሁለቱ መካከል አለመግባባት ከመኖሩ የተነሣ ፀባቸው እየተካረረ መጣ ። በመጨረሻ የሁለቱንም ክፍሎች ሃሣብ በሚጣጣም መልኩ ያቀረበ አንድ ጉባኤ በ784 ዓ. ም. ተደረገና ለሥዕል ክብርና ስግደት እንደ ሚገባ ቀኖና ሠራ ።

ልብ ልንለውና ልናስተውለው የሚገባን አንድ እውነታ ቢኖር በሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ ከባለ ሥዕሉ ረድኤት በረከትና ምልጃ ለማግኘት ነው እንጂ ወረቀቱን ማክበራችን ወይም መለመናችን አይ ደለም። ለምሣሌ በጌታ ስዕል ፊት መጸለያችን ለባለ ስዕሉ ለጌታ መጸ ለያችን ነው እንጂ ለወረቀቱ አይደለም ። ለሥዕል መስገድ ፣ መሳም ለጣኦት መስገድና ጣኦትን እንደ መሳም አይቆጠርብንም ። በሥዕሉ አማካይነት ለሥዕሉ ባለቤት ክብርና ፍቅርን መግለጻችን ነው ። ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ጥንታዊ ትውፊት ነው ። በእምነት በፍቅር የሆነ ደግሞ ሕግም ባይሆን እንኳን ያጸድቃል እንጂ አያስኮንንም ።

" የተቀረጸ ምስል ለአንተ አታድርግ " ዘጸ. 20 ፣ 4 የሚለውን በመጥቀስ ብዙዎች አነስተኛ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታቸውን በመጠቀም ይሄ ታቦታትን ቅዱሳት ስዕላትን ፣ የጌታን መስቀል እንደ ሚመለከት አድርገው ሲያቀርቡ ይሰማል ።

ይህ ግን የእነሱን መጽሐፍ ቅዱስ አለማወቅ የሚያሳየን እንጂ እነሱ እንደጠቀሱት ታቦት ፣ ስዕላት ፣ መስቀል ፣ ጣኦታት ሆነው ለእ ነሱ አትስገዱ ፣ አታክብሯቸው ፣ አምልኮታችሁንም በእነሱ አትግ ለጹ የሚል አይደለም ።

በመሠረቱ ይህ ትዕዛዝ ታቦትን የማይመለከት ለመሆኑ የራሱ የእግዚአብሔር ቃል ምስክር ነው። "ታቦትን ከግራር እንጨት ሥራ" ብሎ ሙሴን ያዘዘው እራሱ ነውና ። ዘዳግም 10 ፣1 — 5 እንግዲህ እግዚአብሔር የተቀረጸ ምስል አታድርግ ካለ በኋላ ታቦትን እንዲሰራ ማዘዙ ጣኦትን አምልክ ማለቱ ይሆን ? የራሱን ቃል በራሱ ቃል እንደ ሰው ያፈርስ ይሆን ? " ሎቱ ስብሐት " ለአምላካችን ክብር ምሥጋና ይግባውና የእኛስ ፈጣሪ ቃሉን የማያጥፍ ቃል ኪዳኑ እንኳ ለልጅ ልጅ የሚወርድ ነው ።

ዳሩ ግን ታቦት የተቀረጸ ምስል ቢሆንም ራሱ እግዚአብሔር የሚ መለከበት የክብሩ መግለጫ ዙፋኑ ስለሆነ ጣኦት በሚለው ስም ፈጽሞ ሊጠራ አይችልም ። ታቦትን ጣኦት ካልን እግዚአብሔርንም " በማ



መሳሰል እግዚአብሔር ይቅር ይበለንና " ሰይጣን ማድረጋችን ነው ። ምክንያቱም በጣኦት ላይ የሚገለጽ ሰይጣን ነውና ።

መስቀልም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን ለሰው ልጆች ለማደል የተሰቀለበት ፣ ክቡር ደሙ የፈሰሰበት ፣ ቅዱስ ሥጋው የተቆረ ሰበት ፣ እግሮቹ የተቸነከሩበት ፣ በክቡር ደሙ የከበረ የጌታ ዙፋኑ ነው ። መስቀልንም እንደ ጣኦት መውሰድ ከላይ የጠቀስነውን አመለ ካከት የያዘን ያስመስልብናል ።

ታዲያ የተቀረጹ ምስል የተባሉት እነማን ናቸው ? ቢባል "የአ ሕዛብ ጣኦታት ፣ የብርና የወርቅ የሰው እጅ ሥራ ናቸው ። አፍ አላ ቸው አይናገሩም ፣ ዓይን አላቸው አያዩም ፣ ጆሮ አላቸው አይሰሙም ፣ እስትንፋስም በአፋቸው የለም ፣ የሚሠሩአቸው ሁሉ የሚታመኑባቸ ውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ " መዝ. 134 ( 135 ) ፣ 15 — 18 ።

ጣኦት የሚባሉት ቅዱስ ዳዊት የገለጻቸው አሕዛብ ይሠሩአ ቸው የነበሩት እነ ዳጎን ፣ በአል ፣ የመሳሰሉት ናቸው እንጂ እሥራኤ ላውያን አምልኮታቸውን ሲገልጹበት የነበረው ዳዊት እራሱ ሲያከ ብረው እርቃኑን እስኪቀር ድረስ ሲዘምርለት የነበረውን ታቦት አለ መሆኑን ልብ በሉ ።

" አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታ መልኩ እንደሆን የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ ። እኔና ቤቴ ግን እግ ዚአብሔርን እናመልካለን ፣ ኢያሱ 24 ፣ 14 — 15 ።

ኢያሱ ጣኦትን ፈጽሞ የሚጠላ ለእሥራኤላውያንም ይህን አቋሙን በግልጽ ያሳወቀ አምልኮቱም በእግዚአብሔር ላይ የተመሰ ረተ ሆኖ ሳለ ዳሩ ግን እሱ ራሱ ከዶብተራ ኦሪት ፊት ( ከታቦት ) እስከ ሠርክ በግንባሩ ወድቆ በጾም በጸሎት መዋሉ ተዘግቧል ። መጽሐፈ ኢ.ያሱ 7 ፣ 6 — 9 ። ይህም የሚያሳየን ታቦት የእግዚአብሔር የክብሩ ዙፋን እንጂ ጣኦት አለመሆኑን ነው ። በተጨማሪም የጣኦታትን ምን ነት ለማወቅ ከፈለግ ዘዳግም 30 ፣17—18 ትን. ኢሳይያስ 44 ፣ 9-20 መመልከት ይቻላል ። ቅዱሳን ስዕላት ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳት ሁሉ እግዚአብሔር የሚመለከባቸው ስለሆኑ በጣኦት ስም ሊጠሩ ፍጹም አይገባም ።

እሥራኤልን ከምድረ ግብጽ እየመራ ያወጣ ታላቁ ነቢይ ሙሴ እሥራኤል በበደላቸው ምክንያት ከመጣባቸው መቅሰፍት እግዚአብ ሔር እንዲምራቸው ጠይቅልን ባሉት ጊዜና ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ የምሕረት መልስ ባገኘ ጊዜ ምን ነበር ያደረገው ? የነሐስ እባብ ሰርቶ

በምድረ በዳ ላይ ሰቀለው ። በሽታው ብዙ ያልጐዳቸው ከየቦታቸው እየ ወጡ ያን የተሰቀለ እባብ እያዩ እንዲድኑ ፣ የባሰባቸውና የአልጋ ቁራኛ ሆነው መነሳት የተሣናቸው እርሱ በበትር ሲመታው ድምጹን ሰም ተው እንዲድኑ ይህን እግዚአብሔር ነግሮት ስለነበረ ፣ እንደ ታዘዘው አደረገ ። እንደተባለው የቻሉት የተሰቀለውን እባብ አይተው ዳኑ ፣ ያልቻሉት የደወሉን ድምጽ ሰምተው ዳኑ ፣ ዘኁልቅ 21 ፣ 8 ።

እንግዲህ ስለዚህ ምን እንላለን ? እግዚአብሔር በቃሉ ማዳን ሲቻ ለው የነሐስ እባብ ሙሴ ሰርቶ ያንን እንዲያዩና እንዲፈውሱ ማድረጉ ምሥጢሩ ምን ይሆን ? የተቀረጸ ምስል ለእናንተ አታድርጉ ካላቸው በኋላ ያ ሁሉ መቅሰፍትም ሊመጣባቸው የቻለው ከአምልኮተ እግዚ አብሔር ወጥተው ወደ አምልኮተ ጣኦት በማዘንበላቸው ሆኖ ሳለ የእ ባብ ምስል ሠርተው እንዲድኑ ማድረጉ በእውነት ይደንቃል ።

ታዲያ ሙሴ በበረሃ ላይ የሰቀለው ያ እባብ ለብዙዎች መድኃኒት ሥጋ ከሆናቸው ስለብዙዎቻችን ኃጢአት ተላልፎ በመስቀል ላይ የተ ሰቀለው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስነ ስቅለቱማ ምን ያህል አያድነን ? ሙሴ የሰቀለው የእባብ ምስል ከደዌ ሥጋ እንጂ ከደዌ ነፍስ አላዳናቸውም ፣ የእኛ አምላክ ክርስቶስ ግን ሞተ - ነፍስን ያጠፋልን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ያወጣን እውነተኛ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው ። በስነ ስቅለቱ ብናምን ብርቱ ድንቁ ምኑ ላይ ነው ? በጣኦት አመለ ካችሁስ ያስብላል ወይ ? በፍጹም ! እኛስ አልተሳሳትንም እነሱ ግን ፍጹም ስተዋልና ይመለሱ እንላለን ።

ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው የእባብ ምሥል የክርስቶስ ምሣሌ መሆኑን ራሱ ጌታ በዮሐንስ ወንጌል 3 ፣ 12 ገልጾታል ። ብርሃን ዓለም ጳውሎስ “ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎላችሁ ነበረ ? ለእው ነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው ” ገላ. 3 ፣ 1 - 2 በማለት ስዕላት ምን ያህል የአምላኪውን አእምሮ ለአምልኮት ዝግጁ እንደሚያደርጉት ገልጾልናል ።

በሐዋርያትና በጻድቃን ስዕል ፊት ቆመን ምልጃ ጸሎት ማቅረ ባችን ብዙዎችን ሲያስገርማቸው ይታያል ። ዳሩ ግን ከሐዋርያት ሕይ ወት የተለየ ለየት ያለ ሥርዓት አለመሆኑ በብዙ ማስረጃዎች ማሳየት እንችላለን ። ሐዋርያት በዘመናቸው ብዙ ሕሙማንን በጥላቸው ይፈ ውሱ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ ተጽፎ እናነባለን ። “ ጴጥሮስ ሲያ ልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋረድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በወሰካ ያኖሩአቸው ነበር ፣ ሁሉም ይፈ ወሱ ነበር ” ሐዋርያት ሥራ 5 ፣ 15 ።



በመሠረቱ እግዚአብሔር የሚገኘው በፍጹም ትሕትናና እም ነት እንጂ በመራቀቅና በዕውቀት ብዛት አይደለም ። እግዚአብሔር የዓለም ጠቢባንን ሳይሆን በሰው ዘንድ ተንቀው እንደ ምናምንቴ ይቆ ጠሩ የነበሩትን ሰዎች መረጠ እንጂ ። አሁንም የእግዚአብሔር መን ግሥት በፍጹም የዋህነት የምትወረስ መሆንዋን ራሱ ጌታ በማይታ በል ቃሉ ተናግሯል ።

ተመልከቱ የእነዚህን ሰዎች እምነት ፣ ከእምነታቸው ጽናት የተነሣ በጴጥሮስ ጥላ ብቻ ፈውስ እንደሚደረግ አምነው ድውያንን ጥላው በሚያርፍበት መንገድ ላይ ማስቀመጣቸው ታዲያ የእምነታ ቸው መልስ ምን ሆነ ? ፈውስን አላሰጣቸውም ? እንግዲህ እነሱ በጴ ጥሮስ ጥላ ከተፈወሱ እኛማ በጴጥሮስ ስዕል ፊት ቆመን ብንለምን የም ንሻው አይደረግልንም ብላችሁ ትጠራጠራላችሁ ? አዎን አቀራረባ ችን በጥርጥር ከሆነ አይደረግልንም ። ለሚጠራጠር ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች አይደረግለትም ተብሎ ተጽፏልና ። በፍጹም እምነት በሥ ዕሉ ፊት ለሚማጸን ግን ይሆንለታል ፣ ያሻውም ይፈጸምለታል ። ከጥላ ይልቅ ሥዕል ግልጽ አድርጐ የዚያን ሰው ማንነት ይገልጸልና ፤ በይበ ልጥም በእውነታነት ላይ የተመረኮዘ ነው ።

የእምነት ውጤቱ መች ይህ ብቻ ሆነና፣ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ ወደ ቤቱ የሚገባው እራቁቱን ነበር ። ይህም ሊሆን የቻለው በፍጹም እምነት ውስጥ የነበሩ ምዕመናን ከአካሉ ጨርቅ እየቀረጡ በመውሰድ በድ ውያን ላይ በመጣል ብዙዎች ከደዌያቸው ይፈወሱ ስለነበር ነው ።ተጠ ራጣሪዎች እስቲ ለተወሰነች ደቂቃ ያህል አይኑ ልቦናቸውን ከፈት አድርገው በሰቂለ ሕሊና ይህን ምሥጢር ያጢኑት ። በጨርቅ መፈ ወስ ከተቻለ በሥዕል መፈወስ ምን ያህል ይከብዳል ? እነዚህ ሰዎች በእምነት ብቻ ይህን አድርገው ድህነተ ሥጋ ካገኙ እኛማ የመጻሕፍት ማስረጃነት እያለን በሥዕላት ፊት እግዚአብሔርን ብንማጸን ከጌታ ዘንድ የፈለግነው ይደረግልናል ። ከላይ የተጠቀሰው ማስረጃ የሐዋ. ሥራ 19 ፣ 11 — 12 ያለውን ተመልከት ።

አንዳንዶች የጌታና የእመቤታችን ሥዕል እውነተኛ የእነሱ ስዕል ነው ወይ ? በማለት በጥርጥር ማዕበል ሲዋዥቁ ይስተዋላሉ ። ለእነ ዚህ ተጠራጣሪዎችና ለሌሎችም የጌታችንና የእመቤታችን ስዕል ከየት እንደተገኘ ታሪካዊ ማስረጃ ቀርቧልና ያንን እኔም እዚህ ላይ እጠቅሰ ዋለሁ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ሥዕል የሳለው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው ። ከ14 — 37 ዓ.ም. ሮምን ይገዛ የነበረው ጢባርዮስ ቄሣር ነው ። ጌታም የተሰቀለው በእሱ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው ። ጢባርዮስ የሚወ

ደው አንድ ልጅ ነበረው ። እሱም ሞተበት ። በልጁ ሞት በጣም አዝና ሬሳውን ሳያስቀብር ሰነበተ ፤ ከጥቂት ቀን በኋላ ጌታ በኢየሩሳሌም ያደ ርገው የነበረውን ታምራት ያውቅ ስለነበር “ ከጢባርዮስ ቄሣር ምድ ራዊ ንጉሥ የተላከች መልእክት ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ትድረስ ” ብሎ ልጁን እንዲያስነሣለት የምልጃ የልመና ጽ ሑፍ ጽፎ መልእክቱን የያዘቸውን ደብዳቤና የልጁን ሬሣ ወስደው ጐልጐታ (የጌታ መቃብር) ላይ እንዲያኖሩለት ባለሟሎቹን ላከ ። እነ ሱም ሄደው ደብዳቤይቱንና ሬሣውን በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ሬሳው አፈፍ ብሎ ተነስቷል ። ጢባርዮስም ከደስታው ብዛት የተነሣ የጌታን ውለታ ለመክፈል የዚህንስ ሰው እናቱን አምጡልኝ ፤ እኔ ቋሚ ለንግሚ ፤ ሚስቴ ገረድ ደንገጡር ሆኜ አገለግላታለሁ ብሎ እን ደገና ሰው ቢልክ የድንግል ማርያም ክብር ስማያዊ እንጂ ምድራዊ ስላ ልሆነ ተሰውራባቸው አላገኟትም ።

ጢባርዮስ ግን ተስፋ እንዳይቆርጥ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ እንዳየው አድርጐ ከለሜዳ አስታጥቆ ጌታን ስሎለታል ዮሐንስ ሥዕሉን ስሎ እንደጨረሰ “ አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደ ሰቀሉኝ አንተ ደግሞ ሁለተኛ ሰቀልከኝ ? ” የሚል ድምጽ ከስዕሉ ወጥቶአል ፤ ይህም የስዕሉን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ነው ።

ሌላው የጌታ ሥዕል ምንጭ ጲላጦስ ለጢባርዮስ ቄሣር ስለጌ ታና ስለእናቱ እመቤታችን የላከው ሥዓላዊ መግለጫ ነው ። ጲላ ጦስ ወደ ጢባርዮስ ቄሣር የላከው መልዕክት እንደሚከተለው ነው ። “ ለጢባርዮስ ቄሣር ሰላም ላንተ ይሁን ፤ ኢየሱስ ስለሚባለው ሰው ግርማዊነትህ ለማወቅ የጠየቅኸውን ለማሟላት ከዚህ የሚከተለውን እጽፍልሃለሁ ።።

በዚህ እኔን እንደራሴህ አድርገህ በሾምኸኝ በፍልስጥኤም ምድር እጅግ በጣም የተለየ መልክና ሥልጣን ያለው አንድ ሰው ተነስቷል ። ታላቅ መምህርና ነቢይም ነው ይሉታል ። ደቀ መዛሙርቱ ግን የእግ ዚአብሔር ልጅ ነው ይላሉ ። ስሙ ኢየሱስ ይባላል እንደ እውነቱ ከ ሆነ ቄሣር ሆይ ይህ ኢየሱስ የተባለ ክርስቶስ በየጊዜው ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያደርጋል ። ሙታንን ያስነሣል ፤ ድውያንን ከማናቸውም ደዌና ሕመም ይፈውሳል ፤ ከዚህም ጋር ጥልቅና መንፈሣዊ በሆነ ትም ህርቱ መላዋን ኢየሩሣሌም አስደንቋታል ፤ አቋሙ አካሉ ግርማ ያለውና መልኩም አንጸባራቂ ጸጋ የተሞላበት በመሆኑ ማናቸውም የሚያየው ሁሉ ይወደዋል ፤ ይፈራዋልም ። አንዳንድ ጊዜ ቀላ ያለው መልኩና መሐል ለመሐል ተከፍሎ የሚታየው ጽሕሙ የሚሰጠው ውበት ፍጹም ግምት የሌለው ነው ። የፊቱ ቅርጽ መልአካውያን ፤ አይኖቹና የጥቁር





የኢየሱስ ፤ እውነተኛ ፤ መልክ ፤ ሥዕል ።

ይህ ፤ ሥዕል ፤ የተሣለው ፤ ጢባርዮስ ፤ ንጉሠ ፤ ነገሥት ፤ በከበረ ፤ ድንጋይ ፤ ላይ ፤ « ኤሜራልድ » ፤ ካስቀረጸው ፤ ምስል ፤ ላይ ፤ ነው ። ይህም ፤ ቅርጽ ፤ የምስጥንጥንያ ፤ ቤተ ፤ መንግሥት ፤ ሀብት ፤ ሆኖ ፤ ከቈየ ፤ በኋላ ፤ እ ፤ ኤ ፤ አ ፤ በ፲፬፻፶፫ ፤ ዓ ፤ ም ፤ በቱ ርኮች ፤ እጅ ፤ ወድቆ ፤ ስለነበረ ፤ ዳግማዊ ፤ ባገርዜድ ፤ የተባለው ፤ ሡልጣን ፤ በክርስቲያን ጦርነት ፤ ጊዜ ፤ ርዲ ፤ ላይ ፤ ወንድሙ ፤ ተማርኮ ፤ ታስሮ ፤ ስለነበረ ፤ እሱን ፤ ለማስለቀቅ ፤ ለፓፓ ፤ ኢኖቼንሶ ፤ ስምንተኛው ፤ ይህንን ፤ ቅርጽና ፤ እንዲሁም ፤ የክርስቶስ ፤ ጐን ፤ የተ ወጋበትን ፤ ቅዱስ ፤ ጦር ፤ ጋራ ፤ አብሮ ፤ የተሰጠ ፤ ነው ። በኢኮኖግራፍ ፤ ሲተነሣው ፤ ለዚሁ ፤ እጅግ ፤ ጣዕም ፤ ላለው ፤ ሥዕል ፤ በአይሁድ ፤ አገር ፤ ተጠባባቂ ፤ ገዥ ፤ የነበረው ፤ ፒ. ሌንቱሎ ፤ ለዚሁ ፤ ለጢባርዮስ ፤ ንጉሠ ፤ ነገሥት ፤ በጻፈው ፤ የታወቀው ፤ ታሪካዊ ፤ መልእክቱ ፤ የሰ ጠው ፤ ጽሑፋዊ ፤ አገላለጽ ፤ ዐይነተኛ ፤ ምስክር ፤ ነው ።

ይህ ፤ ቃል ፤ ከሥዕሉ ፤ ግርጌ ፤ ተጽፎ ፤ የሚገኘው ፤ የጣልያንኛው ፤ ትርጉም ፤ ነው ።

ወርቃማ ጠጉርቹም አወራረድ በሚሰጡት የተንጸባረቀ ውበት ማንም ሰው ቢሆን ለረጅም ጊዜ አተኩሮ ሊመለከተው አይችልም ። የሚ መስለው እናቱን ነው ፤ እሷም ደግሞ በዚህ ክፍለ ሀገር በማንም ላይ ያልታየ ውበትና የትሕትና መልክ ያላት ናት ። ቀራጥ ከባድና የሚያ ከራክሩ ንግግሮቹም በውስጣቸው የሚገኘው ፍጹም የሆነ የመንፈስ ልዕልናና የዕውቀት መጠናቸው ከታላላቅ አዋቂዎች ተብለው ከሚ ገመቱት ሰዎች እጅግ አድርጐ የራቀ የጠለቀ ምሥጢር አላቸው ፤ በተግሣጽና በእዝናት ጊዜም በጣም ኃይለኛ ነው ። በማስተማርና በማ በረታታት ጊዜ ደግሞ ትሑት ፣ ተወዳጅና ልብ የሚመስጥ ነው። ራሱን ሳይከናነብና መጫሚያ ሳይጫማ በእግሩ ይሄዳል ። በሩቅ የሚያ ዩት አንዳንዶቹ ይስቁበታል ። ነገር ግን ወደፊቱ ሲቆሙና ሲቀርቡ በመንቀጥቀጥ ያደንቁታል ። ማንም ቢሆን ሲስቅ አየሁት የሚል የለም። ነገር ግን ብዙዎች ሲያለቅስ አይተውታል ። የቀረቡት ሁሉ ብዙ ሥራና ፈውስ ማግኘታቸውን ይናገራሉ ። ነገር ግን ገዥና ተገዢ ሁሉም (ባባቴ ፊት) በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው ፣ ምንም ልዩነት የላቸውም ብሎ ስለሚያስተምር የግርማዊነትህ አጥፊ ሳይሆን አይቀርም በማለት ብዙ ሰዎች እየመጡ ይነግሩኛል ። ስለዚህ ጉዳይ ብታዝዘኝ ወዲያውኑ ትዕዛዝህ የሚፈጸም ይሆናል ። ጤና ሁን ፔ· ሉንቱሉ ”

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ እንዲህ የሚል ታሪክ ጽፏል ። “ አብጋር ዑካማ የተባለው የዑር ንጉሥ በማይድ በሽታ ተይዞ ስለነበር ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት ጽፎ ላከ መል እክቱን ይዞ የሄደው ሰው በአብጋር ቤተ መንግሥት የታወቀ ሰአሊ ሲሆን ፣ ደብዳቤው እንዲህ የሚል ነበር ፤ ” ስለአንተና ስለምታደርገ ውም ተአምራት እሰማለሁ ፣ ያንተ ማዳን እንደሌሎች ሥር ምስህ ቅጠል በጥሰህ አይደለም ። አንተ ያዳንኸው ተረፈ ደዌ የለበትም ፣ እንደ ሰማሁት ዕውራን እንዲያዩ ታደርጋለህ በሽተኞች ጉልበታቸው ቀን ቶላቸው እንዲራመዱ ታደርጋለህ ፣ ለሙጻንን ታነጻለህ ፣ ርኩሳን መናፍስትን ታሳድዳለህ ፣ በማይድን በሽታ የተያዙትንም በምሕረትህ ትፈውሳቸዋለህ ፣ ሙታንን ታነሣለህ ። ስለዚህ ወደኔ እንድትመጣና ከዚህ ከሚያሰቃየኝ ደዌዬ እንድትገላግለኝ ለእኔም ምሕረት እንዲደር ሰኝ ይህችን የልመና ደብዳቤ ጻፍሁልህ። አይሁድ በአንተ ላይ ክፉ ነገር እንዳሰቡና ክፉ ሊያደርጉብህም እንደከጀሉ እሰማለሁ ። ከተማዬ በጣም ትንሽ ናት ትነስ እንጂ በጣም ውብ ናት ። ለሁለታችን ትበቃናለች ፣ እባክህ ና ” የሚል ደብዳቤ ጽፎ ለጌታ ላከለት ፤ ጌታም የሚከተለ ውን መለሰለት ፣ “ አብጋር ሆይ ፣ ሳታየኝ ስላመንህብኝ ብጹዕ ክቡ ር ነህ ፣ ስለእኔ ተጽፎአልና የሚያዩኝ እንዲንቁኝ ፣ የማያዩኝ ግን እንዲ ያምኑብኝ ። በኔ ያመኑ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ ። እኔም አስቀድሜ የመ

ሠ ሁበትን ሥራ መፈጸም አለብኝ፣ ከፈጸምሁም በኋላ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ ። ከሄድሁ በኋላ ከደዌህ እንዲፈውስህና ላንተና ለቤተ ሰዎችህም የሕይወትን ቃል እንዲያስተምሯቸው ከደቀ መዛሙርቴ አንዱን እልክልሃለሁ፣ ከተማህም የተባረከች ትሆናለች፣ ጠላቶች አይገዟትም ” ብሎ መልስ ላከለት ።

ጌታ ካረገ በኋላ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ ዕጣው በእስያ ስለነበር ከሰብአርድአት አንዱን ታዴዎስን ወደ ዑር ላከው ታዴዎስም እዚያ እንደ ደረሰ ለጊዜው ያረፈው ጥንት በፍልስጥኤም በሚያውቀው በአንድ አይሁዳዊ ቤት ነበር ። ከዚያ ሆኖ በማስተማርና ተአምራት በማድረግ ጥቂት እንደቆየ በቤተ መንግሥትም ዜናው ተሰማ ። ወዲያውም ተጠርቶ ወደ ቤተ መንግሥት ሄደ ። ንጉሡና ታዴዎስ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ታዴዎስ “ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጅን እጭንብሃለሁ ” ብሎ እጁን ጫነበት ። በዚህ ጊዜ አብጋር ከነበረበት ደዌ ሁሉ ተፈወሰ ።

አብጋር ወደ ጌታ የላከው ሰው ሠዓሊ ስለነበር ወዲያው ጌታን ሲያይ ልቡ ስለተመሰጠ ሥዕሉን በንድፍ ለማስቀረት ፈለገ ። ጌታን በሚያነጋግርበት ጊዜ ዓይኑን ጣል እያደረገ የጌታን ገጽ በወረቀት ነድፎት ነበር ። ወደ ሀገሩ ሲመለስ ያንን ለአብጋር አሳየው ። እሱም ባየው ጊዜ በፍጹም እምነት ከመሬት ወድቆ ሰገደ፣ ያን ጊዜም ከደዌው ተፈወሰ የሚሉ ሌሎች የታሪክ ጸሐፍትም አሉ ።

አውሳቢዮስ ዘቂሣርያ ለጌታ ሥዕል ሌላ ምንጭ ያመለክተናል፣ እሱ እንደሚለው “ በወንጌል የታወቀችው 12 ዓመት ሙሉ ደም ሲፈሳት የነበረችውና በኋላም በጌታ ዘንድ ፈውስ ያገኘችው ሴት ለዚህ ውለታው ለጌታ የቅርጽ ሐውልት አሠርታለት ነበር ” ።

የቢሮኒኪም ታሪክ ለጌታ ስዕል ጥሩ መነሻ ነው ። ጌታ በዕለተ ዓርብ ደሙን እያንጠፈጠፈ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጐልጐታ በሚወጣበት ጊዜ መስቀሉ ከብዶት ደሙ ዓይኑን ጋርዶት በላብ ተጠምቆ አይታ ልቧ በሐዘን ስለተነካ ከተከተሉት ሴቶች አንድዋ ቢሮኒኪ ሻሽዋን አውልቃ ፊቱን እንዲጠርግበት ወረወረችለት፣ እርሱም ተቀብሎ በሻሽዋ ፊቱን አብሶ ሲመልስላት ገጹ ከሻሿ ላይ ታትሞበት ቀረ ።

ሌላው ጌታ ተገንዞበት የነበረው ከፈን( ሰበን )እና መጠምጠሚያ ነው ። ዮሐንስ ወንጌላዊና ጴጥሮስ በባዶው መቃብር ውስጥ ገብተው ያዩት ጌታ ተገንዞበት የነበረው ሰበንና መጠምጠሚያ ላይ የጌታ አካል ታትሞበት ነበር ። ይህንንም በኋላ ጊዜ የተነሱት ምድራውያን ጠበብት ( ሳይንቲስቶች ) ልዩ የሆነ ምርመራ አድርገው በመጨረሻ ሰው ሰራሽ



ቀለም፣ እንዲሁም የሰዓሊ ቡርሽ ያላረፈበት መሆኑንና በተአምር ተስሎ የተገኘ መሆኑን የቃል እማኝነታቸውን ሰጥተዋል ። በአሁን ጊዜ ይህ የመግነዝ ጨርቅ በሮም ይገኛል ።

ይህንንም ኒውስ ዊክ የተሰኘው መጽሔት ባንድ ወቅት የዘገበው ዘገባ ትንሣኤ መጽሔት ላይ ወጥቶ ነበር ። ይህንንም ለግንዛቤ ያህል ቀንጭቤ አቅርቤዋለሁ ።

“ በመግነዙ ላይ ይታያል የሚባለው ምስል የተራቀቀ የሥዕል ችሎታ የነበራቸው ክርስቲያኖች አስመስለው ሌላውን ለማሳመን የሳሉት ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ በሳይንቲስቶችና በታዛቢዎች ዶ ቦና ሲጉላላ ቆይቶአል ። አሁን ግን በተደረገው ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር መሠረት ምንም የሰዓሊ እጅ ወይም የሰዓሊዎች ቀለም እንደ አላረፈበት ተረጋግጦአል ። በተጨማሪ ይህን ዓይነት ሥዕል ለመሳል በዚያን ጊዜ የአናቶሚና የፓቶሎጂ ምሥጢርን ጠንቅቆ ያወቀና የፎቶግራፍ ጥበብም አጠናቅቆ ያጠና ሰው መኖር ነበረበት ። ግን እንዲህ ዓይነት ሰው ጌታ በተሰቀለበት ጊዜ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም ። ምክንያቱም የፎቶ ግራፍ ጥበብ የታወቀው ከስቅለት በኋላ 500 ዓመታት ቆይቶ ነው ። ስለዚህ የፎቶግራፍን ሕግና ጥበብ ያወቀ ሰው ካሜራ ከመሠራቱ ከ500 ዓመታት በፊት ነበር ብሎ ማሰብ ፌዝ ሆኖ ይቀራል ።

ከዚህም ሌላ ከአሜሪካ የጠፈር ምርምር ድርጅት በተገኘው የሥእል መመርመሪያ መሣሪያ ምስሉ ተመርምሮ እንዲህ ዓይነት ከ3 አቅጣጫ ሊታይ የሚችል ሥዕል ወይም ምስል በቀለም ወይም ሁል ጊዜ በምንጠቀምበት ካሜራ መሳል እንደማይቻል ተረጋግጦአል ። የታወቁት አሜሪካዊ ሳይንቲስት ስቲቨንስን ሲናገሩ “ ባደረግነው ምርመራ መሠረት እንዲህ ዓይነት ምስል በፎቶግራፍ ጥበብ ወይም በእጅ ለመሳል ለዚያን ጊዜ ሰው እንደማይቻል አረጋግጠናል ” ይላሉ ።

ከአሁን በፊት የተካሄዱት ምርመራዎች በአንድ አንድ ሳይንቲስቶች አእምሮ የነበረውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ችሎአል ። የመግነዙ መርማሪ ቡድን መሪ የሆኑት አሜሪካዊው የሳይንስ ሊቅ ኬኔት ስቲቨንስን እስከአሁን ያደረጉአቸውን ሳይንሳዊ ምርመራዎች መሠረት በማድረግ ሲናገሩ “ ከቡድኑ መካከል አብዛኞቻችን መግነዙ ትክክል የጌታ መግነዝ መሆኑን እናምንበታለን ” ብለዋል፣

በአሁን ጊዜ በኢጣሊያ ውስጥ ቱሪን ከተማ ላይ በሚገኘው ካቴድራል ውስጥ በሚገኘው በዚህ መገግነዝ ላይ ያለው ምስል ቁመቱ 5

ጫማ ከ11 ኢንች የሆነ ያረፈ ወይም ያንቀሳፈ የሚመስል እጆቹ በወገቡ አጥንት ላይ ዘና ብለው ተዘርግተው ሁለቱ እግሮቹም በቁርጭምጭሚቱ ላይ ተደራርበው እንዳለ የሚያሳይ ምስል ይዘው ይገኛሉ ።

ይህ ሰው ረዥምና ጽህም እንደነበረው ይታያል ። በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጠው የዕብራውያን ልማድ መሠረትም በምስሉ ላይ ፀጉሩ ተጐንጉኖ ይታያል ። የዚህ ምስል ሁኔታ ለሐኪሞችና ለሰው አካል አጥኝዎች አስደናቂ ሆኖ ተገኝቷል ። በወንጌሉ ውስጥ በተገለጠው ሁኔታ በመገረፉና በመቸንከሩ ምክንያት ቁስልና ሰንበር በፊቱና በሌላው አካል ክፍሉ ይታይበታል ። ይህም በወንጌል ውስጥ ከተጠቀሰው የመገረፍ የመደብደብና የመቸንከር ሁኔታ ጋር በትክክል ይመሳሰላል ።

ሁለቱ ትከሻዎቹ ከባድ መስቀል እንደተሸከመባቸው የሚያሳዩ ምልክቶች ይታይባቸዋል ። እጆቹና እግሮቹም እንደተቸነከሩ የሚያሳይ ምልክት ይገኝባቸዋል ። በ5ኛውና በ6ኛው የጐን አጥንቱ መካከል ያለው ቦታም በጦር ተወግቶ እንደቆሰለ ያሳያል ። ይህ በመግነዙ የሚታየው ምልክት ይህ ሁሉ ሥቃይ ፣ መወጋትና ግርፋት የደረሰበት መሆኑን ያስረዳል ። በራሱ ላይ በተደፋለት የእሾህ አክሊል ምክንያት የፈሰሰው ደም በራሱ ፀጉር ተረጭቶና በግንባሩ ላይ ወርዶ መገኘቱ ነው

በቅርቡ በመግነዙ ላይ የተካሄዱት ሳይንሳውያን ምርመራዎች ጌታ በነበረበት ጊዜ በእሥራኤል ይሰራ እንደነበረው የልብስ ዓይነት መሆኑን አረጋግጠዋል ። በተለይም የስዊዙ የወንጀል ጉዳይ ምርመራ ሊቅ የሆኑት ማክስ ፍራይ ከመግነዙ ደቃቅ ብናኞች በመውሰድ ለ9 ዓመታት ጥናትና ምርመራ ካካሄዱ በኋላ ጌታ በነበረበት ዘመን በሙት ባህር አካባቢ ይገኝ ከነበረው የጨርቅ ዓይነት ጋር አንድ መሆኑን ገልጠዋል ። በበኩሌ ይላሉ ማክስ ፍራይ " የጌታ መግነዝ መሆኑን ለማመን ችያለሁ ። በምርመራው መሠረት መግነዙ 2,000 ዓመታት ያህል ሆኖታል ።

ምንጭ ፤— ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 431 መጋቢት 1972 ዓ. ም.

የእመቤታችንን ስዕል የሣለው ወንጌላዊው ሉቃስ ነው ። የእመቤታችን ሆነ የጌታ እንደዚሁም የተለያዩ የቅዱሳን ሥዕል ታላላቅ ድንቅ ተአምራት ማድረጋቸው በተለያዩ መንፈሳዊ መጻሕፍት የሰፈሩ ስለሆነ ያንን ማንበቡና መረዳቱን ለአንባብያን ትቻለሁ ። መንፈሳዊ ሥዕላት ድንቅ ሥራዎችን ሊያደርጉ የሚችሉት በላያቸው ላይ የእግዚአብሔር ኃይል ስላለ መሆኑ ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም ።



<u>ማጠቃለያ</u> — በአሁኑ ጊዜ የክርስቶስን የመልክ ጠባይ በዝርዝር የሚገልጹ ሁለት የጽሕፈት ንድፎች ይገኛሉ ። እነሱም አንደኛው በቫቲካን ገዳም በሚገኘው በጥንታውያን ዕቃዎች መኖሪያ ( ሙዚየም ) ውስጥ ሁለተኛው ደግሞ በጀኔቫ ከተማ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር ሥፍራ ተቀምጠዋል ። ሁለቱም ንድፎች የወንጌላዊ የቅዱስ ሉቃስ ሥራዎች እንደሆኑ ይታመናል ።

# ምዕራፍ ፲፫

## ጾም

### የጾም ትርጉም ፤

ለተወሰነ ጊዜ እህል ከመብላትና ውሃ ከመጠጣት መታቀብ ወይም ለተወሰነ ወራት ከጥሉላት ፣ ከሥጋ ፣ ከቅቤ ፣ ከወተት ፣ ከእንቁላል ፣ በአጠቃላይ ከእንስሳት ውጤት መከልከል ነው ። ይህ ብቻ ጾምን ፍ ጹም ስለማያደርግ ቅዱስ ያሬድ ሕዋሳት ሁሉ በየሬማቸው ክፉ ከመ ሥራት መጠበቅ አለባቸው ብሎአል ። ይኸውም ዓይን ክፉ ከማየት ጆሮ ክፉ ከመስማት ፣ ምላስ ክፉ ከመናገር ይከልከሉ ። በተጨማሪም አእምሮን ጉድተው ለውን አስከረው የማይገባ ከሚያሠሩና ከሚያሳ ስቡ የአልኮል መጠጦችም መጠበቅ እንዳለብን ማወቅ ይገባናል ።

### የጾም ጥቅሙ ፤

የሥጋን ምኞት የምታጠፋ ( የኃጢአት ምኞት ማለት ነው ) የነፍስን ቁስል የምታደርቅ ለጉልማሶችም ጸጥታንና ርጋታን የምታ ስተምር ፣ ከእንስሳዊ ግብርና ጠባይ የምትከለክልና ሰው መላእክትን መስሎ የሚኖርባት ደገኛ ሥርዓት ነች ።

በብሉይ ኪዳን ብዙዎች በጾም ተጠቅመዋል ። እግዚአብሔር የጾምን ሥርዓት የደነገገው ገና ከጠዋቱ አዳምን በፈጠረበት ወቅት ነው ። "እጸ በለስን አትብላ" ማለት ትዕዛዝ ቢሆንም ትዕዛዙ የጾም ትዕዛዝ መሆኑ ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም ። አዳምና ሔዋን ይህን የጾም ሥርዓት በመሻር እጸ በለስን በልተው በመገኘታቸው ምን እንደደረሰባቸው ማንኛችንም በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የምናነበው ነው

በጾም የተጠቀሙ ቅዱሳን አበው ጾምን የጸሎት እናት የእንባ ምንጭ ፣ የጽድቅ መሠረት በማለት ደገኛዋን ሥርዓት በተዋቡ ቃላ ቶች ከሸኑው ሲያቀርቡአት ፣ ዲያቢሎሳዊ ትምህርት ያደረባቸው ደግሞ " ወደ ሆድ የገባ አያረክስም ከአፍ የሚወጣ ስድብ ምንዝርነት ግን ያረ ክሳል " ነው ያለው መጽሐፉ እና ጾምን አልጾምን ለመንፈሳዊ ሕይ ወታችን የሚሰጠው ረብ የለም ሲሉ ይስተዋላሉ ።

በመሠረቱ ይህን ቃል ጌታ የተናገረው ለጾም አለመሆኑን ማቴ. 15 ፣ 1 — 20 ብቻ ማንበቡ በቂ ቢሆንም ለእነዚህ ሃሰተኞች ማሳፈሪ ይሆን ዘንድ ሌሎች ጥቅሶችንም አክለን እናቀርብላቸዋለን ። በዚያን ጊዜ የነበሩ አይሁድ ጌታ ይህን ቃል ሲናገር በሰሙ ጊዜ እንደ አሁኖቹ የጾም ጠላቶች ሁሉ ልባቸው ጠማማ ነውና እጣመው ተርጉመውት ሲያጉረመርሙ ሐዋርያት በመስማት " በዚህ ቃል እንደተሰናከሉ " አወቅህን ? ቢሉት ጌታ ግን የተናገረው ቃል የሚያሰናክል ስላልነበረ "ተውአቸው አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል ፣ እውርን እውር ቢመራው ተያይዘው ገደል ነው " ብሏል የዛሬዎቹም ዓይነ ልቦናቸው የታወረ ሆነው ሳለ ሌሎችንም እንምራ በማለት ወደ ገደል ይዘዋቸው ሲገቡ ይታያሉ ።

ጌታ ግን ደቀመዛሙርቱ የዚህን ምሳሌ ትርጉም ንገረን ባሉት ጊዜ " እጅን ታጥቦ መብላትና አለመብላት ሰውን ከሃይማኖት አያወጣውም ወይም አያረክሰውም ፣ ክፉ መሥራትና መናገር እንጂ " ብሎ እጅን ታጥቦ ስለመብላትና ስለአለመብላት መናገሩን ግልጽ አድርጐ አስቀምጦታል ። እነሆድ አምላኩቹ ቃሉን በጥሞና ያስተውሉት ዘንድ ። እንመክራቸዋለን ።

ጾም በብሉይ ኪዳን ፣

ጾም በሕዝብ ላይ የተቃጣውን መከራ ለማቅለል ይረዳል ። ለዚሁም በማስረጃነት የሚጠቀሱ አያሌ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍረው እናገኛለን ።

ኢያሱ እሥራኤላውያንን እየመራ ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚገቡበት ጊዜ ኢያሪኮን በቁጥጥር ሥር ካደረጉ በኋላ ጋይ የተባለችውን ከተማ ለመያዝ በሚነሳሳበት ወቅት ከዚያ በፊት በእሥራኤል ሰልፈኞች ዘንድ ያልታየ የመሸሽ የመፍራት ስሜት ተንጸባረቀ ። ከሰልፈኞቹም 36 ሰዎች በጠላት ተመተው ወደቁ ። ኢያሱም ስለደነገጠ በታቦተ ሕጉ ፊት እስከ ሠርክ በግንባሩ ወድቆ በጾም ዋለ ። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል በደል የፈጸሙ እንዳሉ ነግሮት እጥፊዎችን ቀጥቶ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቋል ። መጽሐፈ ኢያሱ 7 ፣ 6 — 9 ።

በአንድ ዘመን የጊብዓም ሰዎች በአንድ ሌዋዊ ሰው ሚስት ላይ እንደ ውሻ በመፈራረቅ የማይገባ አስጸያፊ ድርጊት ሲፈጽሙባት ስላደሩ ቤት ላይ ሞታ ያገኛታል ። እርሱም ይህን በደሉን ለወገኖች ለመግለጥ የሚሰቱን አካላት ቆራርጦ ወደ እሥራኤል ርስት አገር ሁሉ ፍረቆኛ ብሎ ሰደደ ። የእሥራኤል ልጆች በዚህ ተቆጥተው አራስ ነብር



ሆነው ወደ ብንያም ልጆች ይህን እኩይ ምግባር ያደረጉትን የጊብዓም ሰዎች አሳልፈው እንዲሰጡአቸው መልዕክት ይልካሉ ። የብንያም ልጆች ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ ። በዚህ የተነሣ በእሥራኤል ልጆችና በብንያም ልጆች መካከል ጦርነት ተከፈተ ። የእሥራኤል ልጆች አራት መቶ ሺህ ጦር አሰለፉ ፣ የብንያም ልጆች 26 ሺህ ሰባት መቶ ጦር አሰለፉ ። ይሁን እንጂ የእሥራኤል ልጆች በቁጥር እጅግ ከፍተኛ ቢሆኑም ሁለት ጊዜ በብንያም ልጆች ድል ተደረጉ ። ከመካከላቸውም ብዙ ወገኖቻቸውን አጡ ። ለሶስተኛው በጾም ወደ እግዚአብሔር ሮሁ እግዚአብሔርም ረዳቸው ፣ የድል ግዳይ ለእነሱ ሆነ ።

እኛም ዛሬ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ ከብዙ ሠራዊተ አጋንንት ጋር በዚህች ምድር ላይ ጦርነት ገጥመናል ፣ ሠራዊተ አጋንንት ቢያሸንፉንም እኛ ግን በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ከሙሀን የማታ ማታ ድል የክርስቲያኖች መሆኑን ባለመጠራጠር በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መውደቅ አለብን ።

ከሕንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በ127 አገሮች ላይ የነገሠ አርጤክስስ የሚባል ንጉሥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር ። በሚገዛቸው በ127 አገሮችም ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጐ የሾመው ሐማ መርዶኪዮስ የተባለ አይሁዳዊ ለምን አልሰገደልኝም በሚል ቂም ተነስቶ በአጠቃላይ በ127 አገሮች ያሉ አይሁዳውያን እንዲፈጁ ትዕዛዝ አስተላለፈ ። መርዶኪዮስ ግን የንግሥቲቱ የአስቴር አጐት ነበርና ወደ እሷ ዘንድ ይህ በወገኖችሽ ላይ የተቃጣውን የሐማን ሰይፍ ወደ ንጉሡ ዘንድ ገብተሽ በመንገር ልታስቆሚ ይገባል ይላታል ። አስቴርም ነገደ ይሁዳ ሁሉ በጾም በጸሎት ያስቡኝ ዘንድ መልእክት አስተላልፉ ፤ በንጉሡ ዘንድ ባለሟልነት አገኘ ዘንድና የሐማን ነገር አፈርስ ዘንድ ስላለች ፣ በአጠቃላይ በ127 አገር ተበትነው ያሉ አይሁዳውያን ለሶስት ቀንና ሌሊት ጾምና ጸሎት ያዙ ። በመጨረሻም ሐማ በቆፈረበት ጉድጓድ ገባ ። አይሁዳውያን ግን ከተቃጣባቸው ሰይፍ በጾም ምክንያት ዳኑ ። ይህንን ከእኛ ሕይወት ጋር እናገናዝበው ፤ መጽሐፈ አስቴርን በሙሉ ይመልከቱ ፣ በተለይ ም.4 ፣ 16 ።

እግዚአብሔር በነነዌ ከተማ ላይ ፈርዶ በእሳት ሊያጠፋት ካሰበ በኋላ የነነዌ አገር ሰዎች ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተራው ሰው ሶስት ቀን፣ ሶስት ሌሊት በጾም ቢለምኑት ምሯቸዋል ። ትንቢተ ዮናስን በሙሉ ይመልከቱ ።

ዳዊት ኦርዮንን በማስገደሉ በደል ስላደረገ በነቢዩ ናታን ግሳጼ ሰባት ቀን በጾም በጸሎት ውሏል ፤ መጽ. ሳሙኤል ካልዕ 12 ፣ 17 ። ነቢዩ ሙሴ አንድ ጊዜ ሕግ ለመቀበል ፣ ሁለት ጊዜ እሥራኤልን በበደ

ላቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ለማስታረቅ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከምግብ በመለየት ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቷል ፣ኦሪት ዘዳግም 9 ፣ 9—18 እና ምዕራፍ 10 ፣ 10 ።

ነቢዩ ኤልያስም ከኤልዛቤል ተጣልቶ ወደ ኮሬብ በሸሸ ጊዜ በመንገድ ደክሞት ከክትክታ ዛፍ ጥላ ሥር ዓረፈ ? ወዲያው እንቅልፍ እንቀላፋ ። የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ ቀስቅሰው ሲነቃም ከራስጌው መብል መጠጥ አገኘ ፣ በልቶ ጠጥቶ ጉዞውን ጀመረ ። ከዚያም በኋላ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት እስከ እግዚአብሔር ተራራ ድረስ ያለ ምንም ምግብ ተጓዘ ፣ 1ኛ ነገሥት 19 ፣ 6 — 10 ።

— ትንቢተ ኢዮኤል 2 ፣ 14 " በጽዮን መለከት ንፉ ፣ ጾምን ቀድሱ"

ታዲያ ነቢዩ ጾምን ቀድሱ እያለ ሲነግረን የዛሬዎቹ እነሆድ አምላኮቹ ጾም አያስፈልግም የሚሉት ከየት አምጥተው ይሆን ?

— መዝ. 34(35) ፣ 13 "ነፍሴን በጾም አደከምኋት" ዳዊት የጾምን

አስፈላጊነት ሲገልጽ አየኸውን ?

— ትን.ዳን. 10 ፣ 2 " በዚያም ወራት እኔ ዳንኤል ሶስት ሳምንት

ሙሉ ሳዝን ነበርሁ ፣ ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም ፣ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም " በጾማችን ወቅት ሥጋ መብላት ፣ ጠጅ መጠጣት እንደማይገባን ዳንኤል ነግሮናል ።

— መዝ.108 ፣ 24 " ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ ፣ ሥጋዬም ቅቤ በማ

ጣት ከሳ " ከቅቤ መጾም እንዳለብን ዳዊት ነገረን ።

አንዳንድ ሰዎች የጾም ጊዜ ለምን ይወሰናል ፣ ሥጋ ቅቤ የመሳሰሉትስ ለምን ጾም ሆኑ ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ቀን ጹሙ ፣ ከእንዚህ ከእነኚህ ጹሙ የሚል የለም ይላሉ መጾም አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ሕግና ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን አውጥታ በዚህ ቀን ጹሙ ብትለን የሚያስነቅፋት አይደለም ? ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ሙሉ ስልጣን ሰጥቶአቸዋልና ። " እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል " ማቴዎስ 10 ፣ 40 " እናንተ በምድር ላይ ያሰራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል ። እናንተ በምድር ላይ የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል " ማቴ. 18 ፣ 18 ብሎ ይህን አማናዊ ቃሉን የተናገረው ለሐዋርያትና እነሱን መስለው እስከ እለተ ምጽአት ቤተ ክርስቲያንን ለሚመሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ነው ። መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርገው በሚደነግጉት ድንጋጌ ባንመራ አመጸኞች ነን ። ክርስቶስም " ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይ



ደለም ፣ ትዕዛዜን የሚያከብር እንጂ " ብሎ አስቀድሞ የተናገራትን ሁሉ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን አስጠንቅቆናል ፣ በትዕቢታችን እነሱም ሰው ፣ እኛም ሰው እነሱ ባወጡት ሕግ እንመራም የሚሉ ከሆነ ፣ " በዚያን ጊዜ ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን ? በስምህስ ብዙ ድንቅ ሥራዎችን አላደረግንምን ? ይሉኛል ፣ እኔ ግን እናንተ አመፀኞች ከእኔ ሂዱ ብዬ እፈርድባችዋለሁ " ሲል ማቴዎስ 7 22—23 ላይ ተገልጿል ። ስለዚህ አመጸኝነት አያዋጣም ። " በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ " የሐዋ. ሥራ 20 ፣ 28 ። ይህን የመሰለ ሃላፊነት የተሰጣቸውን የአባቶችን ትዕዛዝ መናቅና አለመቀበልን የመሰለ አመጽ ከዬት ይገኛል ?

ጾም በሐዲስ ኪዳን ፣

የሐዲስ ኪዳን ጾም ከብሉይ ኪዳን ጾም የተለየ ነው ። በብሉይ ኪዳን ያለው ጾም ሥጋዊ ችግርን የሚመለከት ሲሆን ፣ በሐዲስ ኪዳን ግን የሚጾመው ለጽድቅ ነው። ይኸውም ለእግዚአብሔር ተብሎ ነው ማለት ነው ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥራው መጀመሪያ ያደረገው ጾምን ስለሆነ መሥራቹም ራሱ ክርስቶስ ነው ። የሚከተሉት ጥቅሶች በሐዲስ ኪዳን ጾም እንዲታዘዘ የሚያመለክቱ ናቸው ።

— ማርቆስ 9 ፣ 29 " በጸሎትና በጾም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይ

ችልም " አጋንንትን ለማስወጣት ከእግዚአብሔር ኃይል ለማግኘት ጾም አስፈላጊ መሆኑን ጌታ ራሱ ተናግሯል ፣

— ማርቆስ 2 ፣ 20 " ሙሽራው ከእነሱ የሚወሰድበት ወራት ይመ

ጣል ፣ በዚያ ወራት ይጾማሉ ፣ እስ እንጂ እኔ ጾሜላችዋለሁና መጾም አያስፈልጋቸውም አላለም ። ስለዚህ ጌታ ጾሞልናል መጾም አያስፈልገንም የሚሉ ክፍሎች ምን ያህል የተሳሳቱ መሆናቸው በዚህ ይታወቃል ። እንደዚህማ ቢሆን ኖሮ ክርስቶስ ስለ እኛ ጸልይዋል እኛም መጸለይ አያስፈልገንም ነበር ።

— ማቴ. 6 ፣ 16 " ስትጦሙም እንደግብዞች አትጠውልጉ " ማለቱ

መጾም መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑን መግለጹ አይደለምን ? ጾም ለክርስቲያኖች ሕግ ባይሆን ኖሮ ስትጦሙ እንዲህ ሁኑ ብሎ ትዕዛዝ ባልሰጠ ነበረ ።

— <u>ሉቃስ 6 ፥ 21</u> “ እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁአን ናችሁ ትጠግ ባላችሁና” ብሎ ዛሬ ወደው ፈቅደው ስለ እግዚአብሔር መንግ ግሥት ብለው የሚራቡ የሚጠሙ ኋላ በመንግሥት ሰማያት በተ ድላ ደስታ እንደሚኖሩ ራሱ ጌታ ተናግራል ።

— <u>የሐዋ. ሥራ 13 ፥ 3</u> “ ከጾሙ ከጸለዩ በኃላ . . . ” ሲል ሐዋርያት ጌታ ጾሞልናል ብለው ከመጾም እንዳልተከለከሉና ይልቁንም እነሱም ለሥራቸው ሁሉ ጾምን መሠረት ያደርጉ እንደነበር ነው የምናየው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለጾም ሥርዓትና ደንብ አውጥታለች በዓመት ውስጥ ሰባት የአዋጅ አጽዋማት እንዳሉና ማንኛውም ክርስቲያን እነኝህን አጽዋማት እንዲጾም ታዛለች ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ <u>ዓቢይ ጾም</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ የጾመው ጾም ሲሆን፣ ለእኛም አር አያ የሆነበት ነው ። ይህም በማቴ. 4 ፥ 1 – 11 የተገለጸ ነው ። ጌታ የጾመው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሲሆን እኛ ግን አሁን የምንጾመው 55 ቀናት ነው። ይህም በብዙዎች ዘንድ ሲተች ይሰማል ። በመሠረቱ እንኳን 55 ቀን ዓመቱም ብንጾም እግዚአብሔር በጸጋ ላይ ጸጋ ይጨምርልናል እንጂ አያስኮንነንም ። ዳሩ ግን ተጨማሪዎቹ አሥራ አምስት ቀናት የተጨመሩበት ምክንያት አለው ።

— አንደኛው ምክንያት በአብይ ጾም ውስጥ ስምንት ሳምንታት ይኖራሉ ። ከነዚህም ቀኖች ውስጥ ሰባት ቅዳሜ ። ስምንት እሑድ ይገኛሉ ። እነዚህም አሥራ አምስት ቀናት ሲሆኑ ከጥሉላት እንጂ ከእህል ውሃ ስለማይጦሙ እነዚህ ቀናት ሲቀነሱ አርባ ቀን ይመጣል ፣ ስለዚህ ተጨማሪዎቹ አሥራ አምስት ቀናት በዓብይ ጾም ውስጥ ላሉት ቅዳሜና እሁድ ምትክ የሚሆኑ ናቸው ።

ዓቢይ ጾም የተባለበት ምክንያት የጌታ ጾም ስለሆነና ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች ድል የተነሱበት ፣ ዛሬም ክርስቲያኖች የጌታን አርአያ ተከትለው ሰይጣንን ድል የሚነሱበት ጾም ስለሆነ ነው ። በሕዝቡ ዘንድ ሁዳዴ ይባላል ፤ ሁዳድ ማለት የመንግሥት መሬት ፣ የመንግሥት ርስት ማለት ነው ። የመንግሥት ሁዳድ በሚታረስበት ጊዜ አዝመራው በሚሰበሰብበት ጊዜ ልጅ አዋቂ ሳይባል የመንግ



ሥቱ ዜጋ ሁሉ ለሥራ ታጥቆ እንደሚነሳ ይህንንም የጌታ ጾም የጌታ ሁዳድ የክርስቶስ ዜጐች የሆኑ ምዕመናን ሁሉ ይጾሙታልና የሁዳዴ ጾም ተባለ ።

2ኛ/ <u>ጾመ ሐዋርያት ፣</u>

ይህ ጾም ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የወንጌልን መልዕክት ለማዳረስ ወደ ዓለም ከመሰራጨታቸው በፊት አምላካቸውን አብነት በማድረግ የሥራቸው መጀመሪያ ያደረጉት ጾም ነው ። መነሻው ከዕለተ ጰራቅሊጦስ ማግስት ሆኖ ፣ መጨረሻው ወይም መፈቻው ሐምሌ 5 ቀን ነው።

3ኛ/ <u>ጾመ ስብከት ፣</u>

የክርስቶስን መምጣት የሚጠባበቁ አበው እነ ኢሳይያስና እነ ዳንኤልን የመሳሰሉት የጾሙት ሲሆን ፣ ይኸውም ጾመ ነብያት ተብሎ ይታወቃል ። የጾሙ መጀመሪያ መንፈቀ ኅዳር ማለት የኅዳር እኩሌታ ሲሆን መጨረሻው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታኅሣሥ 29 ቀን ነው ።

4ኛ/ <u>ጾመ ፍልሰታ</u>

ይህን ጾም ለመጀመሪያ ጊዜ የጾሙት ቅዱሳን ሐዋርያት ሲሆኑ ፣ በአሁን ጊዜ ግን ከሕጻን እንስቶ እስከ ሽማግሌ ድረስ የሚጾሙት ጾም ነው ። የሚጀምረው ነሐሴ 1 ቀን ሲሆን ፣ የሚያበቃው ወይም መፈቻው ነሐሴ 16 ቀን የእመቤታችን የትንሣኤና የዕርገቷ መታሰቢያ በዓል ላይ ነው።

5ኛ/ <u>ጾመ ድኅነት</u>

የረቡዕና የአርብ ጾም ነው ። ከሌሎቹ ዕለታት ተለይተው ረቡዕና ዓርብ የሚጾሙባቸው ምክንያት ፣

— <u>ረቡዕ ፣</u> የጌታ ምክረ ሞቱ ማለትም በአንድ ሰው ምክንያት የተነሣ ሕዝቡ ከሚታመስ አንድ ሰው ቢሞት አይጐዳምና ይሙት በቃ ብለው ተማክረው ሞቱን የፈረዱበት ዕለት ስለ ሆነ ፣

— <u>ዓርብ ፣</u> ረቡዕ ያጸደቁትን ይሙት በቃ ፍርድ በዕለተ ዓርብ ተግባራዊ አድርገውታል ። እኛም በነዚህ ቀናት በጾም በስግደት ስለ እኛ ሲል የሞተውን አምላካችንን እናስባለን ። በዚህ ምክንያት ጾመ ድኅነት ይባላል ።

6ኛ/ የነነዌ ጾም ፣

መሠረቱ የነነዌ ሰዎች የጾሙት ጾም ነው ። ዛሬም እኛ እንደ እነሱ በኃጢአታችን እንዳንጠፋ ጌታ ምሕረቱን ይሰጠን ዘንድ የምንለምንበት ጾም ነው ።

7ኛ/ ጾመ ገሃድ ፣

ገሃድ የቃሉ ትርጉም መገለጥ መታየት ነው ። በጥምቀት መገለጥ መባሉ ሰው የሆነው አምላክ በዓለም ሲኖር እስከ 30 ዓመት ዕድሜው ድረስ ሰዎችን ለማዳን የመጣ መሲሕ ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እሱ መሆኑን ሳያውቁ ከኖሩ በኋላ በ30 ዓመት ዕድሜው በባሕረ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ አብ በደመና ሆኖ "የምወደው ልጄ ይህ ነው" በማለቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ሲያርፍ በመታየቱ ነቢያት ይወርዳል ፣ ይወለዳል ፣ ይሰቀላል ፣ ይሞታል ፣ ይነሣል ብለው የተናገሩለት መሲህ እርሱ መሆኑ ተገልጦአልና ፣ እንዲሁም ሶስቱ አካላት በአንድ ጊዜ ታይተዋልና ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠበት በመሆኑ ገሃድ ይባላል ። የገሃድ ጾም ጥር 10 ቀን ለ11 አጥቢያ ነው ።



# ምዕራፍ ፲፩

## ስለ ሰው ነፍስ ሕይወት

የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ሕያው ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቅዱሳን መጻሕፍቶችህን ለንመለከት አስተዋዮች እንሆን ዘንድ ዐይነ ልቡናችንን ግለጽልን ፣ ዐይነ ነፍሳችንን አብራልን አሜን ! ይሁንልን ይደረግልን ።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የነፍስን አለመሞት የገነትና የሲኦልን መኖር እንመለከታለን ። ነፍስ ትሞታለች ፣ ገነትና ሲኦል የለም የሚሉ መናፍቃን እንደ አሸን ፈልተዋልና ።

ይህን ከደካማ አስተሳሰብ የመነጨ ትምህርታቸውን ሰናስ ተውለው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በሕይወታቸው ላይ እንደነገሠና እንዳሸው እንደሚነዳቸው እንረዳለን ። ገናና ክቡር ሆኖ የተፈጠረውን ሰው ተስፋ ከሌላቸውና ለሰው ከተፈጠሩት ከእንስሳት ጋር አስተካክለው " ሰው ከእንስሳ ምንም ብልጫ የለውም " ማለታቸው ፣ ከክርስትና እምነት ወጥተው በሙት ፍልስፍና መጓዛቸውን ይመሰክርባቸዋል ። መጽሐፍ ቅዱስንም በስም እንጂ በንባብና በትርጉም እንደማያውቁት ያረጋግጣሉ ።

በእርግጥ ወልድ ፍጡር የሚሉ ተረፈ አርዮስ በለሆኑ እግ ፊንታቸውና ጽዋ ተርታቸው እንደ አባታቸው እንደ አርዮስ ስለሆነ የክብር ትንሣኤ ሳይሆን የእሣር ትንሣኤ እንደሚጠብቃቸው አውቀውት ፈርስን በስብሰን እንቀራለን ማለታቸው ፣ እርግጥ ! ክቡር ፍጡር ሆነው ተፈጥረው በአስተሳሰባቸው እንስሳትን ስለመሰሉ በአራት እግራቸው ከሄዱት እንስሳት ጋር አንድ ነን ማለታቸው የማይታበል ሃቅ ነው ፣ አራዊት ናቸውና እውነቱን ተናግረዋል ። እኛ ግን ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚመሰክረው " በሥላሴ አርአያ የተፈጠርን የማትሞት የማትፈርስ ሕያዊት ነፍስ ያለን ሰዎች ነን ። ጳውሎስ እንዳለ " እኛ የሕያው የእግዚአብሔር ቤት መቅደስ ነን "2ኛ ቆሮ.6፥16 ። እነሱ ግን አሁንም ጳውሎስ እንደተናገረው " እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስለአለከበሩትና ስለአላመሰገኑት

በአስቦቻቸው ከንቱ ሆኑ ፤ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ ፤ ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ ” ሮሜ 1 ፥ 21 ። ሰውን እንደ እንስሳ አድርጎ ከማመን የበለጠ ድንቁርናና ከየት ይገኛል ? ።

እኛ ግን በወንጌል አናፍርምና ይህን የክህደት ትምህርታቸውን በአማናዊውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ትምህርታቸውን የሙት ትምህርት መሆኑን እንገልጻለን ።

<u>በቅድሚያ ስለሰው ተፈጥሮ ፥</u>

ሰው በስድስተኛው ቀን “ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ” ዘፍጥ. 1 ፥ 26 በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ከአራቱ ባሕርያትና ከደማዊት ነፍስ የተፈጠረ ሲሆን ፤ ከአራቱ ባሕርያትና ከደማዊት ነፍስ በመፈጠሩ በማናቸውም ነገር ከእንስሳት ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው ነገር ግን ከእንስሳት የሚበልጥበት እግዚአብሔርን የሚመስልባት እንደ መላዕክት ፍጹም የማትሞት ፥ የማትፈርስ ፥ የማትበሰብስ የምታስብና የምትናገር ፥ ዘወትር ሕያው ሆና የምትኖር ነባቢት ነፍስ አለችው ዘፍጥረት 2 ፥ 7 ።

እንግዲህ ሰው እንስሳትን የሚመስልበትና መላእክትን የሚመስልበት ሁለት ጠባያት አሉት። እነዚህም ደማዊት ነፍስ ፥ ነባቢት ነፍስ ናቸው ። እነዚህ ሁለቱ በፈቃድ የማይገናኙ የሚለያዩ ናቸው ። የማይስማሙ የተለያዩ ስለሆኑ ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሥጋን ለመማረክ እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ ፥ ሮሜ 7 ፥ 22

ደማዊት ነፍስ በምታይልበት ጊዜ ሰው እንስሳትን መስሎ ይኖራል ፥ ይህም ማለት ሕግ እንዳልተሠራላቸው እንደ እንስሳት ጊዜ ሳይወስኑ መብላት ፥ መጠጣት ፥ መተኛት ፥ መነካት ፥ በልዩ ልዩ ዓይነት ሥጋን ደስ የሚያሰኛትን ሥራ ብቻ ሲሰሩ መኖር ነው ፥ መዝሙር 49 ፥ 12 — 20

ነባቢት ነፍስ ስታይል ሰው መላእክትን መስሎ ይኖራል ። ይህም ማለት በጾም ፥ በጸሎት ፥ በስግድ በቁመት በልዩ ልዩ የትሩፋት ሥራ ተወስና ሰማያዊ ነገርን እያሰቡ መኖር ነው ።

<u>የሰው ሞትና የእንስሳት ሞት አንድ ነውን ?</u>

አይደለም ። እንስሳት ሕያዊት ነፍስ ስለሌላቸው አንድ ጊዜ ከሞቱ ከፈረሱ ከበሰበሱ በኋላ ትንሣኤ የላቸውም ። እድል ፈንታቸው ጽዋ ተርታቸው ወደ አፈርነት ተለውጠው ለዘለዓለም መጥፋት ነው ። መክብብ 3 ፥ 21 ይመልከቱ ። “ የሰው ልጆች ነፍስ ግን ወደ ላይ ትወጣለች ” ይላል ። ከዚህም የምንረዳው የሰው ሞት የሥጋና የነፍስ መለያየት መሆኑን ነው ። በዚህ ጊዜ ሰው ከአራቱ ባሕርያትና ከደማዊት ነፍስ በመፈጠሩ ከሌሎች ፍጥረታት የሚሻለው መሻል ስለሌለው የማይንቀሳቀስ ሬሳ ሆኖ ይወድቃል ። ንቃሀ መዋቲ የሚለው የትንሣኤ አዋጅ እስኪሰማ ድረስ ሥጋው በመቃብር ፈርሶ በስብሶ ዐፈር ትቢያ ሆኖ ይኖራል ነፍሱ ግን በባሕርይዋ መፍረስ መበስበስ የለባትምና በደማዊት ነፍስ ኃይል ተሸንፋ እንስሳትን መስላ ኖራ እንደሆነ ከአጋንንት ጋር በመከራ ቦታ ( በሲኦል ) በሥቃይ ትኖራለች ። ደማዊት ነፍስን አሸንፋ መላእክትን መስላ ኖራ እንደሆነ በዕረፍት ቦታ ከመላእክት ጋር እየተደሰተች ትኖራለች ። ሉቃ 16 ፥ 22 — 26

እንግዲህ ሰው እንደ እንስሳ በሥጋው የሚሞት እንደ መላእክት በነፍሱ ሕያው ሆኖ የሚኖር ስለሆነ ፥ መጻሕፍት ሰውን በሥጋ መደብ አቁመው ሲናገሩ “ ደመና ተበትኖ እንዲሄድ እንዲሁ ወደ ሙታን ሥፍራ የሚወርድ አይወጣም ወደ ቤት ደግሞ አይመለስም ሥፍራውንም አያውቀውም ። እንዲሁም ሰው ከተኛ በኋላ አይቆምም ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ ( ምጽአት እስኪሆን ) በሥጋው ከእንቅልፉ አይነቃምም አይሰማም ፥ ልጆቹ ቢከብሩ ወይም ቢዋረዱ አያውቅም አያስተውልም ” እያሉ ይናገራሉ ፥ ኢዮብ 7 ፥ 9—10 እና ኢዮብ 14 ፥ 12—24

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ሰው በሥጋው በመቃብር ውስጥ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እንደ እንስሳት ፈርሶ በስብሶ እንደሚቆይና ጌታ በክብር በሚመጣበት ቀን ግን የሰው ሁሉ ሥጋ ከመቃብር እንደሚነሣ የሚገልጽ ነው እንጂ ፥ ሰው እንደ እንስሳ በሥጋም በነፍስም ይሞታል ማለት አይደለም። ኢሳይያስ ስለሞቱ ሰዎች መነሣት እንዲህ ይላል “ ሙታንም ሕያዋን ይሆናሉ ( ነፍስ ከሥጋ ጋር ትዋሃዳለች ማለት ነው ) ሬሳዎችም ይነሳሉ ፥ በምድር የምትኖር ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ ” ኢሣይያስ 26 ፥ 19 ።

የሰው ሥጋ እንደ እንስሳት ሥጋ ፈርሶና በስብሶ እንደማይቀርም ዳንኤል በምዕ. 12 ፥ 2 “በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ ፥ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረት ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ” ብሎ ይመሰክራል ። እንግዲህ ከላይ በጠቀስናቸው ማስረጃዎች መሠረት ፥ የሰውና የእንስሳት እድል ፈንታ አንድ እንዳልሆነ ልብ በሉ ። እንግዲያው መክብብ 3 ፥ 19 እንዴት ነው የምንረዳው ? ሰሎሞን በዚህ ቦታ ላይ የሰውን ከንቱነት እንስሳት እንደሚሞቱት ሁሉ እሱም በሥጋ ሟች ፈራሽ መሆኑን ሊያስረዳን ፈልጎ ነው ።

ደግሞ መጻሕፍት ሰውን በነፍስ መያብ አቁመው ሲናገሩ አብርሃም ፥ ይስሐቅና ያዕቆብ ከሞቱ በኋላ ፥ እኔ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ይላል፡፡ ዘፀ. 3 ፥ 15 እና የሐዋ. ሥራ 7 ፥ 32 ። እንዲህ ሲል የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አለመሆኑን ይገልጻል ። ሁሉም በእርሱ ዘንድ ሕያዋን ናቸውና “ የሕያዋን አምላክ ነኝ እንጂ የምውታን አምላክ አይደለሁም ብሎ ጌታ በወንጌል ተርጉሞታል ” ሉቃስ 20 ፥ 38 እና ማቴ. 22 ፥ 32 ።

ቅዱስ ጳውሎስም “ እኔ በሕይወተ ሥጋ ብኖርም ክርስቶስን ለማገልገል ነው ። ብሞትም ዋጋዬ ይቆየኛልና በሕይወትም ቢሆን በሞቱም ቢሆን የክርስቶስ ክብሩ በኔ ላይ አለ። እሳቸውን ከሚያሻን ከኒህ ከሁለቱ በአካለ ሥጋ በዚህ ዓለም ከመኖርና በአካለ ነፍስ ከክርስቶስ ጋር ከመኖር ለሰውነቴ የምመርጠው ቸገረኝ ፥ መውደዱንስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቼ ከክርስቶስ ጋራ ልኖር እወዳለሁ ፥ ይልቁንም በሞት መለየቱ ይሻላል ” ብሎ በነፍስ ሕያው መሆኑን አስረድቶናል ፊልጲ. 1 ፥ 22 — 23 ።

የነፍስን ሕያውነት የሚያስረዱ ተጨማሪ ጥቅሶች ፥

— መዝ. 30 (31) ፥ 5 “ በእጅህ ነፍሴን አስጣለሁ . . . ” ይህ ጥቅስ የሚያስረዳን የነፍስን ሕያውነትና ሰው በሞተ ጊዜ ነፍሱ በእግዚአብሔር ወይም በሰይጣን እጅ እንደምትወድቅ ነው ። ክፉ ከሰራን የሰይጣን እንሆናለን ። ሃይማኖታችንን ጠብቀን ከተገኘን ነፍሳችን በእግዚአብሔር እጅ ትሆናለች ፥ በአብርሃምም ጉያ እንሆናለን ።

— መክ. 12 ፥ 7 “ . . . ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ባይ መለስ ” በሞታችን ጊዜ ነፍሳችን ሕያው ስለሆነች ለፍርድ ወደ እግዚአብሔር እንደምትሄድ ይነግረናል ።

— ማቴ.10 ፥ 28 “ ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ፥ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ ” አንድ ሰው ሞተ የሚባለው በሥጋ መሆኑን ነገር ግን ነፍስን ለመግደል ማንም ሰው እንደማይችል ይነግረናል ። ምክንያቱም ሕያዊት አድርጎ ነው የፈጠራትና ። ስለዚህ የነፍስ ሞት በገሃነም መጣል ብቻ ነው ።



— ሉቃስ 23 ፥ 46 “ . . . አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ እደራ እሰጣለሁ ” ጌታ ከእመቤታችን የነሣው ሥጋን ብቻ ሳይሆን ነፍስንም ስለሆነ ሞት ማለት ደግሞ የሥጋና የነፍስ መለያየት መሆኑን ግልጽ ያደርግልናል ።

— ዮሐ. ወን. 10 ፥ 18 “ ነፍሴን በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም ” ማለቱ እኛ ነፍሳችን በፈቃዳችን ሳይሆን የምንሰጠው በግዴታ ነው ፥ እሱ ግን በፍላጎቱ ነው ።

— የሐ. ሥራ 7 ፥ 59 “ . . . ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል . . . ” ቅዱስ እስጢፋኖስ ለጌታ ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱ ወዳንተ ልመጣ ነው ተቀበለኝ ማለቱ አይደለምን ? ታዲያ ነፍስ ሟች ፈራሽ በስባሽ ከሆነች እንዴት ነፍሱን እንዲቀበለው ተጣራ ? ።

— 1ኛ ጴጥ. 3፥19 “በሥጋ ሞተ በመንፈስ (በመለኮት) ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወህኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው ” ጌታ ቀደም ብለው የሞቱትን በአካለ ነፍስ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል ላሉት ነፍሳት ነጻነትን ማወጁን የሚናገር አይደለምን ? ታዲያ ሰው የምትሞት ፈራሽ በስባሽ ነፍስ ያለው ከሆነ ጌታ ወደ መቃብር ወርዶ ለፈረሰው ሥጋ ነው ነጻነትን የሰበከው ? ወህኒ የተባለውም የነፍሳት መኖሪያ ሲኦል ነው ።

— የሐ. ራዕይ 6 ፥ 9 “ አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሰዊያው በታች አየሁ ። . . . ” በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ መሥዋዕትነትን ከፍለው በእጸደ ነፍስ በክብር ቦታ በሕያዊት ነፍስ መኖራቸውን መናገሩ መሆኑ አይካድም ። ሰው በሥጋ ቢሞትም በነፍስ ግን ሕያው መሆኑን ያስገነዝበናል። ለምን አትፈርድልንም የሚሉትስ ሞተው አፈር ትቢያ የሆኑት ነፍሳት መሆናቸው ይሆን ! ነፍስ ሟች ፈራሽ በስባሽ ከሆነች መናገር አይቻላትም። እንግዲህ ሰው በነፍሱ ሕያው መሆኑን ሲነግረን ነው ።

ተቃዋሚዎች ትንቢተ ሕዝቅኤል 18 ፥ 4 በመጥቀስ ነፍስ ትሞታለች ይላሉ ። ቃሉን ግን አበክረን ብንመለከተው ለእነሱ ለራሳቸው ሃሰታዊ ትምህርት መልስ የሚሆናቸው ነው ። “ ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች ” ይህን ብቻ ብሎ አላቆመም ። በመቀጠል “ ፍርድንና ቅን ነገርን የምታደርግ የጻድቅ ነፍስ በሕይወት እንደምትኖር ተናግሯል ፤ ከቁጥር 5 - 9 ይመልከቱ ።

" ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች " ሲል ትፈር ሳለች ትበሰብሳለች ፤ ሕያዊት አይደለችም ማለት ሳይሆን ፤ በሲኦል ወይም በገሃነም ስትሰቃይ መኖርዋን መግለጹን ነው ። የነፍስ ሞት ሲኦል ወይም ገሃነም መግባት ነው እንጂ እንደ ሥጋ መቃብር መግ ባት መፍረስ መበስበስ አይደለም ።

ነፍስና ሥጋ የተለያዩ መሆናቸው በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍ ልም በብዛት ተጠቅሷል ፤ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት ።

— <u>ኦሪት ዘፍጥረት 35፥16—19</u> " . . . እርስዋም ስትሞት ነፍ ስዋ በምትወጣበት ጊዜ ስሙን ቤንኦን ብላ ጠራችው ። ራሔል በምጥ መሞትዋን ሙሴ ሲገልጽ ነፍስዋ ስትወጣ ብሎ ነፍስ ከሥጋ የተለየች ፤ ሞትም የነፍስና የሥጋ መለያየት መሆኑን አስረዳ።እንግዲህ ራሔል ራስዋ ነፍስ የምትባል ከሆነ ነፍስዋ ስትወጣ ብሎ እንዴት ሊናገር ቻለ ? ወጥታስ ወዴት ሄደች ?

— <u>መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፥19—23</u> " . . . ኤልያስ ይመ ገብባት የነበረችው መበለት ልጅዋ በሞተባት ጊዜ ኤልያስን እንዲያስነሳላት ለመነችው ፤ እሱም ልጅዋን እንድትሰጠው ጠይቆ በአልጋው ላይ አጋደሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጸለየ " አቤቱ አምላኬ ሆይ ልጅዋን በመግደልህ ይህችን ትቀ ልበኝ የነበረችውን ባልቴት እንዲሁ ደግሞ አስጨነቅሃትን ? " ብሎ ጮኸ ፤ በብላቴናውም ላይ ሶስት ጊዜ ተዘረጋበት ፤ ወደ እግ ዚአብሔርም"አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ " ብሎ ጮኸ ። እግዚአብሔርም የኤ ልያስን ቃል ሰማ ፤ የብላቴናው ነፍስ ወደእርሱ ተመለሰች ።

ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ከየት ይገኛል ? ። ነፍስና ሥጋ የተለያዩ ባይ ሆኑ ሞትም የሥጋና የነፍስ መለያየት ካልሆነ ኤልያስ የልጁን ነፍስ መልስ ብሎ እግዚአብሔርን እንዴት ሊጠይቅ ቻለ ? ነፍሱ ብትሆን ኖሮ የሞተችው ፤ የሞተችውን ነፍሱን አንግት ነበር ሊል የሚገባው የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች ማለት ተለይታው ወደ ነበረው ሥጋ መጥታ መዋሐድዋን የሚያረጋግጥ አይደለምን ? ።

— <u>መዝሙር 103 ( 104 ) ፥29</u> " ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ ፤ <u>ነፍሳቸውን ታወጣለህ</u> ይሞታሉም ። ወደ አፈራቸውም ይመለ ሳሉ " ሞት ማለት የነፍስ መውጣት ወይም ከሥጋ መለየት መሆኑን ዳዊት ግልጽ አድርጐ አስፍሮታል ። ነፍስ በምትወጣ ጊዜ ሥጋ በድን ይሆናል ፤ ወደ አፈርነቱም ይመለሳል። እስከ ጊዜ



ምጽአት ድረስም ፈርሶ በስብሶ ይቆያል ። በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ ሰው ለማለት ነፍስ በማለትም ይጠራል ለዚህም ማስረጃ ብንፈልግ የሐዋ. ሥራ 14፥7 ያዕቆብ ሰባ አምስት ነፍስ ሆኖ ወደ ግብጽ መውረዱን ይናገራል ። እዚህ ላይ ሥጋን በነፍስ ስም ሲጠራ ነው እንጂ ሥጋቸው በከነዓን ቀርቶ ነፍሳ ቸው ተለይታ ግብጽ ወረደች ለማለት አይደለም ።

<u>የጻድቃን ነፍስ ጊዜያዊ መኖሪያ ስለሆነችው ስለገነት</u>

መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ አንብበው ያልተረዱ ሰዎች ሰው ራሱ ነፍስ ስለሆነ በሞተ ጊዜ ነፍሱ ትሞታለች እና የሰው ሁሉ መኖሪያ ከሞተ በኋላ መቃብር ነው እንጂ ገነትና ሲኦል የሉም ይላሉ ። ይህ ግን ፍጹም ሐሰት የሆነ ትምህርት ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው ሕያ ዊት ነፍስ እንዳለች በተረዳ ነገር አውቀናል ። እና የሕያዊት ነፍስ መኖሪያ የት ነው ? ነፍስ ሕያው ከሆነች ከሞት በኋላ መኖሪያ ይኖ ራታል ። ሲኦልና ገነት የኃጥአንና የጻድቃን ነፍስ መኖሪያ ናቸው ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገነት መኖር እንዲህ ሲል ያስረዳናል ። ዘፍ. 2፥8—15 " የገነትን መዘጋጀት ይነግረናል ።

— <u>ኢሳይያስ 51፥3</u> " ምድረ በዳውን እንደ ኤደን እንደ እግዚአብ ሔር ገነት . . . " እዚህ ላይ ገነት የምትባል እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጃት መኖርዋን መግለጹ ነው ። ይህቺ የምንኖርባት ምድ ርም አለመሆንዋ ግልጽ ነው ።

— <u>ትን. ሕዝ. 36፥35</u> " ባድማ የነበረች ይህቺ ምድር እንደ ኤደን ገነት ሆናለች " ብሎ ይህቺ ዝሙት ምንዝርነት የበዛባት ምድር ሳትሆን ገነት የንጹሃን መኖሪያ ደስ የምታሰኝ ቦታ መሆንዋን ይገልጽልናል ።

የገነትን መኖር የሚክዱ ክፍሎች " ገነት ከጥፋት ውሃ በፊት ነበ ረች ፤ ኋላ ግን ምድር በውሃ በጠፋች ጊዜ እርሷም ጠፍታለች " ይላሉ ። ይህን ዓይን ያወጣ ውሸታቸውን ከየት እንዳገኙት ባላ ውቅም ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን እንዳልሰፈረ እርግጠኛ ኝ ። እስቲ እነዚህን ወተቱን አጥቁረው ፤ ማሩን አምርረው ለተ ኖሩ መሰሐቲዎች አንድ ጥያቄ ላቅርብ ላቸው ፤ በጥፋት ውሃ ጊ ለመሆኑ ይህቺ አሁን ያለንባት ምድርስ ጠፍታ ነበር ወይ ? ምድር በንፍር ውሃ ጠፋች ሲባል ምድሪቱ ሳትሆን በውስጥዋ ያሉ ሰዎችና እንስሳት መሆናቸውን ቢረዱ ኖሮ እንዲህ ዓይ ነት ቅሌት ውስጥ ባልገቡ ነበር ። እንደ እነሱ አባባል ቢሆንማ

ይህችም ምድር ጠፍታ ለሁለተኛ ጊዜ ነው የተፈጠረችው ማለት ነው ። ምክንያቱም በኖህ ዘመን መላ ዓለም ጠፋች ብለው ያምናሉና ። ዓለም ሲባል በምድር ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችዋ መሆናቸውን ግን በነገረልን ። እኛ ግን ይህን ከጥርስ ተርፎ ዓይን የሚያስቀውን ቀልዳቸውን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሳችን አፈር ትቢያ እናለብሰዋለን ።

— ሉቃስ 23 ፥ 43 " ጌታ ኢየሱስም እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው'' ቀርጦ ቀጥሎች ይሄን ቃል ምን ይሉት ይሆን ? ገነት በኖህ ዘመን የጠፋች ከሆነ ጌታ በገነት ዛሬ ከእኔ ጋር ትኖራለህ ማለቱ ገነትን ደግሞ አበጅቶ ይሆን ? ደግሞስ ይህቺ የምንኖርባት ምድር ገነት ተብላ ትጠራለች የሚሉ ከሆነ ምን ሊያተርፍለት ነው ባለበት ቦታ ከእኔ ጋር ትኖራለህ የሚለው? የሌለባትን ከዚህ ከኖረባት ምድር ለየት ያለች ፍጹም የተድላ ደስታ ቦታ ስለሆነች ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትኖራለህ አለው እንጂ ። ሲኦልንስ በመቃብር መስለዋታል ፤ ገነትንስ በምን ይመስሉአት ይሆን ? ።

— 2ኛ ቆሮ. 12 ፥ 4 " . . . ወደ ገነት ተነጠቀ ሰውም ሊናገር የማይገባውን ቃል ሰማ " ወደ ገነት ተነጠቀ ማለቱ ከዚህች ካለንበት ዓለም ለየት ወዳለች ቦታ ተወሰደ ማለት አይደለም ? ሰውስ ሊናገረው የማይገባ ቃል በዚህች ምድር ላይ ይኖር ይሆን ? በገነት ግን ብዙ የሚያስደንቁ ነገሮች አሉና እነኛን ሁሉ ማየቱን ነገረን ።

— ራዕይ 2 ፥ 7 " ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ " ገነት ይህቺ የምኖርባት ምድር ከሆነች በውስጥዋ የሚገኙት ፍራፍሬዎች ያለምንም መጠቀጠብነት በገንዘባችን ገዝተን እንበላቸዋለን ። መታገልና ድል መንሳት አያስፈልግም ። ደግሞም በዚህች በምንኖርባት ምድር ላይ ሕይወትን የምትሰጥ የሕይወት ዛፍ የለችም ። እንግዲህ አድቃን በዚህች ምድር ላይ ከዲያብሎስ ጋር ተዋግተው ድል ሲነሱ በገነት ይኖራሉ ።

ስለሲኦል ፤

ጻድቃን ሲሞቱ ነፍሳቸው በገነት እንደምታርፍ ፤ በአንጻሩ ደግሞ የኃጥአን ነፍስ መኖሪያ ሲኦል ነው። እስከ ዕለተ ምጽአት ነፍሳት በሁለቱም ሥፍራ ይኖራሉና ። ሲኦል ማለት ጉድጓድ ወይም



መቃብር ማለት ነው ጉድጓዳውን ቦታ ሁሉ ሲኦል ይለዋል በሲኦል ይመስለዋልና ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ፤

— መዝ. 15 (16) ፥9 —10 " ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና " ይህ አነጋገር የሥጋና የነፍስን መኖሪያ የተለያየ መሆኑን ያመለክተናል ። ልበ አምላክ ዳዊት ከክርስቶስ መወለድ ፲ ዓመት ቀደም ብሎ የነበረ ሰው ነው ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩ ጽድቅ ሥራ የሠሩም ሆኑ የኃጢአት ሥራ ፥ የሁሉም ነፍስ የተሰፋው ቀን እስኪፈጸም ወደ ሲኦል ነበር የምትወርደው ። ዳዊትም ጌታ በአካል ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነጻነትን ሰብኮ ከሲኦል እንደሚያወጣው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ሲናገር " ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች ፤ በመጨረሻው ዘመን ነፍሴን ተዋሕዳ ስለምትነሣ " ብሎ ሥጋው ሞቶ ፈርሶና በስብሶ እንደ ደማይቀር ጭምር ተናገረ ።

— መዝሙር 9 ፥ 17 " ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይወርዳሉ " ይህን አባባል ተቃዋሚዎች ወደ መቃብር ነው የሚወርዱ ካሉ ኃጢአተኞች ብቻ ሳይሆኑ ጻድቃንም ጭምር ናቸው ። ሙሴ እራሱ በመቃብር ተቀብሯል ። እረ ሌሎቹን ቅዱሳን ትተን የእውነት ንጉሥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እራሱ ሶስት መዓልትና ሶስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሯል ። እንግዲህ ሲኦል ማለት መቃብር ማለት ከሆነ ጌታንም ኃጢአተኛ ነው ሊሉት ነው ?

— ምሣሌ 15 ፥ 24 " በታች ካለው ከሲኦል መንገድ ያመልጥ ዘንድ የሕይወት መንገድ አስተዋዩን ሰው ወደ ላይ ይወስደዋል " የሲኦል መንገድ የተባለው ኃጢአት ሲሆን ፤ የሕይወት መንገድ የተባለው የጽድቅ ሥራ መሆኑ ግልጽ ነው ። እንግዲህ ሰው ሁሉ በሚሠራው ኃጢአት ወደ ሲኦል ፤ በሚሠራው የጽድቅ ሥራ ወደ ገነት እንደሚገባ እንወቅ እናስተውል ።

— ሉቃስ 16 ፥ 22 - 31 " እዚህ ላይ የኃጢአተኞች ነፍስ በሲኦል በሥቃይ እንደምትኖር ጌታ ራሱ በማይታበል ቃሉ ገልጾልናል ምሳሌ ነው ቢሉ በሌለ ነገር መስሎ አልተናገረም ። በሌለ ነገር እንኳን ጌታ ሰውም አይመስልም ። ደግሞ የሌለን ነገር እንደ

ሙሽታም ሰው ያለ አስመስሎ አወራ ማለት ፍጹም ኃጢአት ነው። እሱ የእውነት አባት መሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጿልና።

— ራዕይ 20 ፥ 13 የሲኦልን መኖር ይገልጽልናል ።

## ማጠቃለያ

1ኛ ምቹ የአትክልት ቦታ ሁሉ ገነት እየተባለ ይጠራል ይህም በገነት ምሳሌ መጥራት ነው እንጂ ከመንግሥት ሰማይ በታች ከምድር በላይ መካከል ያለች ገነት የምትባል የጻድቃን ነፍስ መኖሪያ የለችም ማለት አይደለም ። አዳምና ሔዋን ሳይሳሳቱ ይኖሩባት የነበረ ገነት ከምድር በላይ ከሰማይ በታች እንደነበረ እና ምናለን ። ጌታ በከበበ ትስብዕት በግርግ መንግሥት በሚመጣበት በዕለት ምጽአት "እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ" ብሎ ጻድቃንን የሚጠራቸው ከገነት "ሒዱ ብሎ" ኃጥአንን ወደ ገሃነም የሚያሰናብታቸው ከሲኦል ነው ምክንያቱም ገነትና ሲኦል የነፍሳት ጊዜያዊ መቆያዎች ናቸው ።

2ኛ ሲኦል ማለት ጉድጓድ ወይም መቃብር ማለት ቢሆንም ነገር ግን የኃጥአን ነፍስ መኖሪያ የሆነው ሲኦል የለም ማለት አይደለም ሲኦል የስቃይ ስፍራ ስለሆነ ማናቸውንም የስቃይ ስፍራዎች በተለምዶ ሲኦል እያልን እንጠራቸዋለን ። ደስ የሚያሰኘን አትክልት ያለበትን ቦታ ገነት ነው እንደምንል ሁሉ የሥቃይንና የመከራ ቦታ የሆነውንም ደግሞ ሲኦል ነው እንላለን ።

ውስብሐት ለእግዚአብሔር



## ለጽሁፌ ረዳት የሆኑ መጻሕፍት

1/ መጽሐፍ ቅዱስ ( በአማርኛ በእንግሊዝኛ ) ቋንቋዎች

2/ አባ ጎርጎርዮስ ( ሊቀ ጳጳስ ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አዲስ አበባ 1974 ዓ. ም.

2/ አድማሱ ጀንበሬ ( መልአከ ብርሃን ) ኩሉሐ ሃይማኖት አዲስ አበባ 1949 ዓ. ም.

4/ አባ ጉርጉዮስ ( ሊቀ ጳጳስ ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ አዲስ አበባ 1978 ዓ. ም.

5/ አያሌው ታምሩ ( አለቃ ) ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ አዲስ አበባ 1979 ዓ. ም.

6/ አያሌው ታምሩ ( አለቃ ) የጽድቅ በር አዲስ አበባ 1979 ዓ.ም.

7/ መሐሪ ትርፌ ( ሊቀ ሊቃውንት ) የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባብ ከነትርጓሜው አዲስ አበባ 1948 ዓ. ም.

8/ ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜው ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1959 ዓ. ም.

9/ ዓሥራት ገብረ ማርያም ፥ ትምህርተ መለኮት አዲስ አበባ 1983 ዓ. ም.

10/ ዮሐንስ ሳንድኼድ የቤተክርስቲያን ታሪክ በመካከኛው ዘመን በአማርኛ ) አዲስ አበባ 1974 ዓ. ም.

11/ ምሥጢረ ሥላሴ ፥— መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል አዲስ አበባ 1960 ዓ. ም.

12/ ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ( ሊቀ መዘምራን ) ፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት አሥመራ 1969 ዓ. ም

13/ ኃይለ መስቀል ገ/መድህን ( ሊቀ ሊቃውንት ) ሥርወ ሃይማኖት አዲስ አበባ 1960 ዓ. ም

14/ መዝሙረ ዳዊት - ንባቡ ከነትርጓሜው ትዲስ አበባ 1973 ዓ. ም